# አልበያን

## ጀምዒያ፣ ሱሪና የተብዲዐ ህግጋት

ዝግጅት፡-

ሙሐመድ አሕመድ ሙነወር

**<u>ነሐሴ 2008</u>**

ማውጫ

መግቢያ......................................................................3

**ምዕራፍ አንድ፡ ጀምዒያ (ማህበር)........................................... 4**

**ማህበር ምንድን ነው? ..........................................................4**

**በማህበር ላይ የዑለማእ አስተያየት ..............................................10**

ሀ/ ማህበርን የፈቀዱ ዑለማዎች ...............................................10

ለ/ ማህበርን የከለከሉ ዑለማዎች...............................................68

ዑለማዎችም “ጀምዒዮች” ናቸው?!.............................................80

የሚነቅፉም የሚፈቅዱም መኖራቸው ምን ያሳያል? ..........................81

አንድም ዐሊም የሌለበት አቋም ውስጥ ነህ!!...................................83

ፈቃጅ ፈትዋዎችን ዋጋ ለማሳጣት የሚደረጉ ብልጠቶችና ብዥታዎች .....84

**ምዕራፍ ሁለት፡ ሱሪ.........................................................136**

**ሲርዋል እና ሱሪ ይለያያልን?...................................................139**

**በሱሪ ላይ የዑለማዎች አቋም....................................................160**

[ሀ] ከልካዮች ...........................................................160

[ለ] ፈቃጆች.............................................................163

**ሱሪን ለመከልከል የሚነሱ ምክንያቶች ሲቃኙ.....................................167**

**ሶላት በሱሪ ...................................................................176**

**ለከት ይኑርህ! ..................................................................181**

**ምዕራፍ ሶስት፡ የተብዲዕ ቅድመ-ሁኔታ........................................182**

**ጠቃሚ መርሆዎችና ጥንቃቄዎች .................................................183**

ማጠቃለያ.................................................................218

بسم الله الرحمن الرحيم

## <u>መግቢያ</u>

የማህበር ጉዳይ ከፊል ወንድሞች ዘንድ ማነታረክ ከጀመረ ሰነባብቷል። አስተዋይ ለሆነ አካል በንፁህ መንፈስ ርእሰ-ጉዳዩን ከመፈተሽ ይልቅ ፍፁም ፅንፈኝነት የነገሰባቸው ፍረጃዎችን መመልከት ልብ የሚያደማ ነገር ነው። እራሱን መካሪ የሆነ ሰው ይጠቀምበታል በሚል እሳቤ በዚህ ረገድ ዑለማዎች የተጓዙበትን አቋም ለማስፈር ሞክሬያለሁ።

የዚህ ፅሑፍ መነሻ ከ 7 ወራት በፊት የሞነጫጨርኳት ማስታወሻ ነች። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ እንደ አዲስ ጉዳዩ ጠንከር ብሎ ሲነሳ ቀድሜ ያላሰብኳቸው ብዥታዎችና አንዳንድ ነጥቦችን ሳክልባት ይዘቷ ከመነሻዋ ከእጥፍ በላይ አድጓል። በተጓዳኝ የሚነሳውን የወንዶች ሱሪ ጉዳይም በመጠኑ ያካተትኩ ሲሆን በመጨረሻም አንገብጋቢ ነው ብዬ ስላሰብኩ ከተብዲዕ ጋር የሚያያዙ ጥቂት መርሆዎችንና ጥንቃቄዎችን በስሱ አካትቻለሁ። ሚዛናዊ ሆኖ በማንበብ ሀሳቡን ለሚያካፍለኝ ሁሉ ከወዲሁ ላመሰግን እወዳለሁ።

**<u>ማስታወሻ</u>፡-** በመፅሐፉ ውስጥ የዑለማእ ፈትዋዎችና ንግግሮችን ሳካትት ከሞላ ጎደል ከቃል በቃል ትርጉም ይልቅ የነፃ ትርጉም አካሄድን መርጫለሁ።

# ምዕራፍ አንድ፡ ጀምዒያ (ማህበር)

## ማህበር ምንድን ነው? [1]

ጀምዒያ ወይም ማህበር (NGO) ማለት ባጭሩ መንግስታዊ ያልሆነ፣ በመርህ ደረጃ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ የተለያዩ ህዝባዊ ተልእኮዎችን ይዞ በበጎ ፈቃደኞች የሚመሰረት ተቋም ነው። እንዲህ አይነቱ ማህበር ሲመሰረት በመንግስት ይሁንታ የሚቋቋም በመሆኑ እንቅስቃሴዎቹ ከሞላ ጎደል ህጋዊ እውቅና ያላቸው፣ የገቢ ምንጩ፣ አሰባሰቡ፣ መጠኑ፣ አፈፃፀሙና የገንዘብ ዝውውሩ ግልፅ እንዲሆን የሚገደድ፤ በየተወሰነ የጊዜ ገደብ ገንዘቦች ለታቀደው አላማ መዋላቸው የሚገመገም፣ በሙቶኛ ተወስኖ ዝቅተኛና ከፍተኛ አስተዳደራዊና ተግባሮታዊ ወጪዎቹ ገደብ የተበጀባቸው፣ ያለበትን ሀገር ህግና ደንብ እንዲያከብር የሚገደድ ተቋም ነው። እንደ ሃገራቱ ስርኣት እነዚህ ነገሮች ሊጠብቁና ሊላሉ ይችላሉ። አላማው ደካሞችን መርዳት፣ ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር፣ የጤና ወይም የደህንነት ጠንቆችን መጋፈጥ፣ ጥናትና ምርምሮችን ማበረታታት፣ በህዝብ ውስጥ ስለሆነ ጉዳይ ንቃተ-ህሊናን መጨመር፣ እምነትን ማስፋፋት፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል።

በሀገራችን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ብናይ ሰፊ ህዝባዊ ግልጋሎቶች ያሏቸው ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትን፣ የቲሞችን፣ አረጋውያንን፣

---

[1] ስለማህበር ምንነት ጥቂት ማለት የፈለግኩት "ጀምዒያ" "ጀምዒይ" የሚሉ ጨኸቶች እጅግ በመጦዛቸው የተነሳ አንዳንዶች ዘንድ ልክ እንደ ጀህሚያ፣ ቀደሪያ፣ ኸዋሪጅ፣ ሺዐ … ያለ የሆነ አዲስ አደገኛ የሆነ ዐቂዳ ይዞ የመጣ አንጃ እስከሚመስል ስለደረሰ አጭር ጥቆማ ለመስጠት ያክል ነው፡፡

አቅመ-ደካሞችን፣ ጋለሞታዎችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ወዘተ <u>**በሰፊ፣ በተደራጀና በተቀናጀ**</u> መልኩ ለመርዳት <u>**የግድ**</u> ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ፈቃድ መውሰድ ይጠይቃል።

በሌላ በኩል <u>**ሰፋ ባለ መልኩ**</u> መስጂዶችን ለመገንባት፣ ኡዱሒያና ዘካተል ፊጥር ለማከፋፈል፣ ሀይማኖታዊ ትምህርት የሚሰጡ መርከዞችን ለማቋቋም፣… የግድ ከፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ፈቃድ መውሰድ ያስፈልጋል። በርግጥ ያለምንም ፈቃድ ቀላል የማይባሉ ስራዎችን መስራት እንደሚቻል ለማንም አይዘነጋም። ነገር ግን አንድ ሙስሊም የሆነ ከተማ ሄዶ ያለምንም ፈቃድ አይታሞችን ሰብስቦ መዝግቦ ሲረዳ ቢገኝ ያለጥርጥር ከርቸሌ ይወረወራል። የግለሰብ ዳዕዋዎች ሳይቀሩ ከህጋዊ ማህበራት ፈቃድ ከሌላቸው እንቅፋት የሚበዛባቸው ሁኔታ ሰፊ እንደሆነ የሃገራችንን ነባራዊ ሁኔታ የሚያውቅ አይዘነጋውም። እንዲያውም በፌደራል ጉዳዮች ስር ያለው የሃይማኖትና እምነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል አንዱ ተግባርና ኃላፊነት የሃይማኖት ተቋማት ሰባኪያን ፈቃድና አገልግሎቱም ስርአት እንዲኖረው ከሃይማኖት ተቋማት ጋር በመመካከር መመሪያና ደንብ ማዘጋጀት ነው። ይሄ በሂደት ምን አይነት አንድምታ እንዳለው አስተዋይ የሆነ ሰው ኣያጣውም።

የማህበራት የገንዘብ ምንጭ በአብዛሀኛው አላማቸውን የሚደግፍ ህዝብና የአባላት መዋጮ ሲሆን ከዚህም ባለፈ ግን የመንግስት ተቋማት፣ ሌሎች ማህበራት፣ አለም አቀፍ ድርጅቶች የሚረዷቸው ማህበራትም ብዙ ናቸው። ጥቂቶች ደግሞ እንደ ሃገራቱ ህግና ደንብ አትራፊ የንግድ ተቋማትን በጎን በማቋቋም ስራቸውን የሚያግዙ አሉ።

በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ማህበራት <u>**በአሁኑ ሰዐት**</u>፡-

- ገቢያቸው መጠኑ ከመንግስት ዘንድ እንዲታወቅ ይገደዳሉ።
- ያለ በቂ ምክንያት ስባሪ ሳንቲማቸውን ማንቀሳቀስ አይችሉም።
- የገንዘብ ፍሰታቸው ጤናማነቱ በራሳቸው ሳይሆን ከመንግስት ዘንድ ተጠያቂ በሆነ የውጭ ኦዲተር ይፈተሻል።
- በሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት የቅርብ ክትትል ይደረግባቸዋል።
- ስራቸው በግልፅ ይታወቅ ዘንድ የሚገለገሉበት መኪና፣ የሚይዙት ቢሮ ለመንግስት አካላት ቀርቶ ለአላፊ አግዳሚ ሳይቀር በሚታወቅ መልኩ ስማቸውንና አርማቸውን በይፋ እንዲለጥፉ ይገደዳሉ።

ከዚህ አንፃር ምንም እንኳን ረቂቅ በሆነ መልኩ ደባ የሚፈፅሙ ባይጠፉም ከብዙዎች አእምሮ ውስጥ እንዳለው ያለተጠያቂነት ገንዘብ የሚዛቅበት ሂደት ያን ያክል አይደለም። የደዕዋ ስራ ላይ የሚሰማሩ ማህበራት ግን በአብዛሀኛው ሰፊ ገንዘብም አያንቀሳቅሱም።

## የዚህ ፅሁፍ አላማ

የዚህ ፅሁፍ አላማ ስለ ማህበር ወይም ማህበራት አመጣጥ ታሪክ ወይም ዛሬ ስላሉበት ነባራዊ እውነታ ወይም በውስጣቸው ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ሴራዎች ወይም ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ ስለሚያበረክቱት የማይካድ ግዙፍ አስተዋፅኦ ሰፊ ትንታኔ ወይም ጥናት ማድረግ አይደለም። ይህን ለማድረግ አቅሙም፣ ጊዜውም፣ ፍላጎቱም የለኝም። አላማዬ ከየትኛውም

ማህበር መከላከል ወይም በየትኛውም ላይ መዝመትም አይደለም። [2] ይልቁንም የዑለማዎችን ፈትዋዎች በማቅረብ አንባቢ ሚዛናዊ የሆነ እይታ እንዲኖረው ማገዝ ነው።

የማህበር ጉዳይ የኢጅቲሃድ ርእስ ነው። በኢጅቲሃድ ነጥብ ያልተጋራቸውን ከሱና የሚያስወጡ ሰዎች ይሄ አካሄዳቸው ሱንይነታቸውን ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ጤናማነትም ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ህሊናው በቡድናዊ ስሜት ላልተሸፈነበት ሁሉ ግልፅ ስለሆነ ብልሹነቱን ለማስረዳት ማስረጃ እንኳን መጠየቅ የማይሻ የቢድዐ ሰዎች አካሄድ ነው። አልኢማም ኢብኑ አቢል ዒዝ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *“የቢድዐ ሰዎች ንግግሮች ውድቅነታቸው፡ ማስረጃ መጥቀስ ከሚያስፈልገው በላይ የጎላ ነው።”* [ሸርሑ አጥጦሐውያህ: 387]

በዚህ ነጥብ ላይ የተለያየ ሀሳብ የሰነዘሩ የሱና ዑለማዎች ዛሬ አንዳንዶች እንደሚያደርጉት *“እንዴት የተለየ ሀሳብ ታንፀባርቃለህ?”* በሚል እርስ በርሳቸው በቢድዐ ሊወራረፉ ቀርቶ በክፉ እንኳን አንዱ ሌላውን አላነሳም። የተለያየ ሀሳብ የተሰነዘረባቸው የኢጅቲሃድ ጉዳዮች ብዙ በመሆናቸው ሁሉም እየተነሳ “ይህን ካልተከተላችሁ እንዲህ ናችሁ” የሚል ከሆነ መቋጫ የሌለው ንትርክና ብጥብጥ ነው የሚከተለው። ለያገኘም እንጂ እንዲህ አይነቱ ስሌት ዋጋ ቢያገኝ የሱና ሰዎች እራሳቸው እጅግ ከብዙ ቦታ እንዲከፋፈሉ በር ይከፍት ነበር። በነገራችን ላይ በኢጅቲሃዳዊ ጉዳዮች የሆነን

---

[2] ይህን ስል ጅምላ ፈራጅ ውንጀላዎችን ወይም ውሃ የማያነሱ ብዥታዎችን እያየሁ አልፋለሁ ማለቴ አይደለም፡፡ በተቻለኝ ግን በሱና ዑለማዎች ንግግርና አካሄድ ለማገናዘብ እሞክራለሁ፡፡

ዐሊም አቋም "ካልተቀበላችሁ" የሚል አጉል አካሄድ እራሱን የቻለ የቢድዐ ሰዎች መገለጫ ነው። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*"ከነብዩ ﷺ በስተቀር ማንንም ሰው ቢሆን ወደሱ መንገድ የሚጠራበት፣ በዚያም ላይ ወዳጅ ጠላት የሚያደርግበት የሆነ አንድን ሰው ሊመድብ ማንም ቢሆን አይገባውም።* ***ልክ እንዲሁ ከአላህ፣ ከመልእክተኛውና ኡማው ወጥ አቋም ካያዘበት ንግግር በስተቀር ከሱ አንፃር የሚወዳጅበት ወይም ጠላት የሚያደርግበት ንግግርን (አቋምን) ሊመድብ አይገባውም። እንዲያውም ይሄ የቢድዐ ሰዎች ከሚፈፅሙት ድርጊት ውስጥ ነው!! የነዚያ በዚያ ንግግር ወይም በዚያ ማስጠጋት ሳቢያ ወዳጅነትና ጠላትነትን በመመስረት ህዝብን የሚለያዩበት ከሆኑ (ድርጊቶች) ነው።"*** [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 20/164]

## <u>በማህበራት አማካኝነት ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞች</u>

- በግለሰቦች የማይሞከሩ እጅግ ብዙ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ የጤና ተቋማት፣ የሙያ ማሰልጠኛዎች፣ የውሃ ጉድጓዶች ወዘተ ይገነባሉ።
- እልፍ አእላፍ የቲሞች፣ አረጋውያን፣ ጋለሞታዎች፣ በጎርፍ፣ በጦርነት፣ በእሳተ-ገሞራ፣ በድርቅና በመሰል ከባባድ አደጋዎች የተጠቁ ወገኖች የማይናቅ ማገገሚያ ያገኛሉ።
- በርካታ መስጂዶች፣ የዲን መርከዞች፣ መድረሳዎች፣ ተቋማት፣ የሒፍዝ ማዕከላት፣ ... ይገነባሉ።
- በታላላቅ ዑለማዎች የተዘጋጁ ኪታቦችን በየሃገራቱ ቋንቋዎች በመተርጎም በተለይም የዐቂዳ ትምህርቶች ለህዝብ እንዲደርሱ ትልቅ ስራ ሰርተዋልም የሚሰሩም አሉ።

- ዱዓቶችን በመደገፍ፣ የደዕዋ መድረክ በማመቻቸት፣ ኪታቦችን በማስተማር ላይ ይሰማራሉ። ወይም የተሰማሩትን ያግዛሉ።
- በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ድሃው መድረስ ለማይችሉ በተለይም በመካከለኛው ምስራቅ፣ አውሮፓና አሜሪካ የሚገኙ ትልልቅ ሀብታም ለጋሾችን ገንዘባቸውን በአፍሪካና በኤሲያ ለሚገኙ ችግረኞች በማድረስ እንደ ድልድይ ያገለግላሉ።
- ሰፋፊ ስራዎች ያሏቸው ደግሞ በስራቸው ብዙ ሰራተኞችን በመቅጠር የስራ እድል ይፈጥራሉ።

## <u>በከፊል ማህበራት ላይ የሚያጋጥሙ ግድፈቶች</u>

- ሃይማኖታዊ ከሆነ ወይም ፖለቲካዊ ዝንባሌ ካለው ማህበሩን ያማከለ ማቅረብና ማራቅ ሊኖር፣ ለልዩነትም ሊያጋልጥ ይችላል።
- ባለ ማህበራቱ በዲን ላይ ደካማ ከሆኑ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመመሳጠር የሰው ሐቅ ያላግባብ የሚበላበት አጋጣሚ ይኖራል።
- በሐራም ነገሮች ላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች (ዶሩራት) ከሚጠይቁት የዘለለ ግዴለሽነት የሰፈነበት መዘናጋት ያጋጥማል።
- በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለቢድዐ አንጃዎች እንቅስቃሴ ድጋፍ በማድረግ እንዲጎለብቱ የሚያደርጉበት አጋጣሚ አለ።
- ሸሪዐዊ ሑክሞችን በቅጡ በማይለዩ ወይም ደንታ-ቢስ በሆኑ የማህበር መሪዎች ሳቢያ አደራዎች በአግባቡ የማይፈፀሙበት ብዙ አጋጣሚ አለ። ለምሳሌ የዘካን ገንዘብ ለማይገባው ሰው የሚሰጡ፣ እንዲሁም ዘካን ከሌሎች ሰደቃዎች ጋር በመቀላቀል ከማይገናኙ ፕሮጀክቶች ላይ በማዋል ጥፋት የሚፈፅሙ ይኖራሉ።
- ሃይማኖትንና ሰብኣዊ ግልጋሎቶችን እንደ ሽፋን በመጠቀም ፖለቲካዊ አላማ የሚያራምዱ ማህበራትም ያጋጥማሉ።

<u>ማሳሰቢያ፡-</u>

በማህበራት ውስጥ ያለጥርጥር እዚህ ላይ ከቀረቡት የሚልቁ ጥቅሞችም ጉዳቶችም ይኖራሉ። የቀረቡት ምሳሌዎች ነቃፊም ይሁን ደጋፊ የሆነ ሰው ማጠልሸት ላይ ወይም ማንቆለጳጰስ ላይ ብቻ እያነጣጠረ ወሰን እንዳያልፍ ለመጠቆም ያክል ነው።

## <u>በማህበር ላይ የዑለማእ አስተያየት</u>

### <u>ሀ/ ማህበርን የፈቀዱ ዑለማዎች</u>

ከሱናህ ዑለማዎች ውስጥ በርካታ ማህበርን የፈቀዱ ወይም ማህበር የመሰረቱ ወይም የማህበር መሪ የሆኑ ወይም ደግሞ በማህበር ዝግጅቶች ላይ የተካፈሉ፣ ያስተማሩና ማህበራትን ያወደሱ ታላላቅ መሻይኾች አሉ። ለምሳሌ የህንድ፣ የግብፅ፣ የፓኪስታን፣ የሳዑዲ፣ የሻም፣ የአልጀሪያ፣ … ዑለማዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከፊሎቹን እንመልከት፡-

1. **የህንድ ዑለማዎች**

“ጀምዒየቱ አህሊል ሐዲሥ” በህንድ ክፍለ-አህጉር በታላላቅ የሱና ዑለማዎች እ.ኤ.አ. በ 1906 የተቋቋመ ማህበር ነው። ማህበሩ በርካታ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎችን ከፍቷል። ለምሳሌ ታዋቂው የበናሪስ የሰለፊያ ዩኒቨርሲቲ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው። የረሕማኒያ ዩኒቨርሲቲ፣ የአሕመዲያ ሰለፊያ ዩኒቨርሲቲ፣ የኬረላ ሰለፊያ ዩኒቨርሲቲ፣ ኢብኑ ተይሚያ ዩኒቨርሲቲ፣ አልኢማም አልቡኻሪ ዩኒቨርሲቲና ሌሎችም በዚህ ማህበር የተከፈቱ የእውቀት ተቋሞች ናቸው።

ከዩኒቨርሲቲዎቹ በተጨማሪ በርካታ ኢስላማዊ ተቋማት በዚህ ማህበር ተቋቁመዋል። ማህበሩ የተመሰረተውና ሲንቀሳቀስም የነበረው በታላላቅ የሱና ዑለማዎችና ሙሐዲሦች ነው። የዐውኑል መዕቡድ ኪታብ አዘጋጅ የሆኑት ሸይኽ ሸምሱል ሐቅ አልዐዚም አባዲ እና የ "ቱሕፊቱል አሕወዚ ቢሸርሒ ጃሚዒ ቲርሚዚ" ኪታብ አዘጋጅ የሆኑት ሸይኽ ሙሐመድ ዐብዱረሕማን አልሙባረክፉሪ ከዚህ ማህበር ዑለማዎች ውስጥ ናቸው።

## 2. የፓኪስታን ዑለማዎች

ይሄኛው "ጀምዒየቱ አህሊል ሐዲሥ" ህንድና ፓኪስታን ከተለያዩ በኋላ የተመሰረተ ነው። ማህበሩ የተመሰረተው እንደ ሸይኽ ሙሐመድ ዳውድ አልገዝነዊና ሙሐመድ ኢስማዒል አሰለፊ ባሉ ታላላቅ የሐዲሥ ምሁራን ነው። በዚህ ማህበር ስርም ልክ እንደ ህንዱ የተለያዩ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎች ተከፍተዋል። በፈይሰል አባድ ከተማ የተከፈተው የሰለፊያ ዩኒቨርሲቲ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ነው። የመዲና ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ ሲከፈት የፓኪስታኑ የአህሉል ሐዲሥ ማህበር መሪ የነበሩት ሸይኽ ሙሐመድ ዳውድ አልገዝነዊ የመማክርት ጉባኤው ቀዳሚ አባል ሆነው ተመርጠዋል። ከዚህ ማህበር አባላት ውስጥ ስማቸው ከገነኑት አንዱ የሱናው አንበሳ ኢሕሳን ኢለሂ ዞሂር ናቸው። [3]

---

[3] ሸይኽ ኢሕሳን ረሒመሁላህ በመዲና ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ በሸይኹል አልባኒ ረሒመሁላህ ከተማሩ ተማሪዎች አንዱ ናቸው፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች አጠቃላይ አንደኛ ወጥተው ነው ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት፡፡ በሀገራቸው ትምህርታቸውን ቀጥለው ስድስት የተለያዩ ሸሃዳዎችን ይዘዋል፡፡ የሺዐዎችን ጠማማ አስተሳሰብ በማጋለጥ በርካታ የከበሩ ኪታቦች ፅፈዋል፡፡ ሸይኽ ኢሕሳንን ኢብኑ ባዝ አወድሰዋቸዋል፡፡ የሳቸውን የደዕዋ ጥረት የሚዘክር "አሸይኽ ኢሕሳን ኢለሂ ዞሂር ወጁሁዱሁ ፊ ተቅሪሪል ዐቂደቲ ሰለፊያ ወረድ ዐለል ፊረቂል ሙኻሊፋ" የተሰኘ የዶክትሬት ማሟያ ጥናት ተሰርቷል፡፡ በዚህ ኪታብ መግቢያ ላይ ሸይኽ ረቢዕ ሰውየውን በሚደንቅ መልኩ አወድሰዋቸዋል፡፡ በፓኪስታን ላሆር ከተማ ደዕዋ እያደረጉ ባሉበት በሺዐዎች በተጠመደ ቦምብ ጥቃት ደርሶባቸው በኢብኑ ባዝ ጥቆማ የሳዑዲ መንግስት

እዚህም ላይ የነዚህን ዑለማዎች ደረጃ በቅጡ ስላላወቅን ወደ መዳፈር እንዳንገባ ላስታውስ እወዳለሁ።

እነዚህ ማህበራት ዛሬ ያሉበት ሁኔታ ጥሩ የሚባል እንዳልሆነ አንዳንድ ዐሊሞች ይጠቅሳሉ። ስለወቅታዊ ሁኔታ መረጃ የለኝም። የሆነ ሆኖ ማህበራቱን የመሰረቱትና ለዘመናት ሲያስኬዷቸው የነበሩት ታላላቅ የሱና ሊቃውንት ስለሆኑ የቀደመውን ታሪክ በዛሬ ክፍተቶች ለማጠልሸት መዳፈር ሚዛናዊ አካሄድ አይደለም።

## 3. የአልጀሪያ ዑለማዎች

የአልጀሪያ ሙስሊም ዑለማዎች ማህበርን ከመሰረቱት ውስጥ እንደ ሸይኽ ዐብዱል ሐሚድ ኢብኒ ባዲስ ያሉ ታላላቅ የሰለፊያ ዑለማዎች ነበሩበት።

ከነዚህ በተጨማሪ በግብፅ የአንሷሩ ሱና ማህበርን የመሰረቱና በአባልነት ታቅፈው ተውሒድና ሱናን ካሰራጩት ውስጥ በሱናው አለም ስመ-ገናና የሆኑትን ብቻ ልጥቀስ።

## 4. ሸይኽ ሙሐመድ ሓሚድ አልፈቂ ረሒመሁላህ

የአንሷሩ ሱና ማህበር **መስራችና የመጀመሪያ ሊቀመንበር** ናቸው። ሸይኹ በሱናው አለም በሰፊው የሚታወቁ ታላቅ ዐሊም ናቸው።

## 5. ሸይኽ ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ ረሒመሁላህ

---

ልዩ ሄሊኮፕተር አዝዞ ለህክምና ወደ ሪያድ ቢወሱም ሊተርፉ አልቻሉም፡፡ አላህ ከሰፊው ጀነቱ ውስጥ ያኑራቸው፡፡

<u>ከአንሷሩ ሱና ማህበር መስራቾች ውስጥ አንዱ ሲሆኑ ሁለተኛው የማህበሩ መሪ ነበሩ።</u> ኋላ በሳዑዲ የታላላቅ ዑለማዎች ምክር ቤት ውስጥ አባል ሆነው አገልግለዋል። የነ ሸይኽ ሷሊሕ አሉሐይዳን፣ ሸይኽ ዐብደላህ አልቀዑድ፣ የአሁኑ የሳዑዲ ሙፍቲ ዐብዱል ዐዚዝ ኣሊ ሸይኽ፣ የሸይኽ ዐብደላህ ጉደያን፣ የሸይኽ ሷሊሕ አልፈውዛን እና የሌሎችም ታላላቅ ዑለማዎች ሸይኽ ናቸው።

### 6. ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ አብዲል ወህሃብ አልበና ረሒመሁላህ

ከአንሷሩ ሱና ማህበር <u>መስራቾች</u> ውስጥ አንዱ ነበሩ።

### 7. ሸይኽ ዐብዱዟሂር አቡ ሰምሕ ረሒመሁላህ

የሐረም አልመኪ ኢማምና በመካ የዳሩል ሐዲስ ትምህርት ቤት መስራች ሲሆኑ ከአንሷሩ ሱና ማህበር ዑለማዎች ውስጥ አንዱ ናቸው።

### 8. ሸይኽ ዐብዱረሕማን አልወኪል ረሒመሁላህ

የተውሒዱ አንበሳ ዐብዱረሕማን አልወኪል የአንሷሩ ሱና <u>ማህበር አባል፣ ወኪል፣ ምክትል ሊቀመንበር አልፎም ዋና ሊቀመንበር</u> ሆነው አገልግለዋል።

### 9. ሸይኽ ሙሐመድ ኸሊል ሀራስ ረሒመሁላህ

እንደ ሸይኽ ሙሐመድ አማን አልጃሚና ሸይኽ ዐሊይ ኢብኑ ናሲር አልፈቂሂ ያሉ የታላላቅ የሱና ዑለማዎች ሸይኽ ሲሆኑ የዐቂደቱል ዋሲጢያ

ሸርሓቸው በሰፊው ትታወቃለች። <u>የአንሷሩ ሱና  ማህበር አባልና ምክትል ሊቀመንበር ሆነው አገልግለዋል።</u>

### 10. ሸይኽ አሕመድ ሙሐመድ ሻኪር ረሒመሁላህ

ስማቸው ማስተዋወቅ የማይሻ ታላቅ የሱና አንበሳ ሲሆኑ ከአንሷሩ ሱና  ማህበር ታላላቅ ዑለማዎች ውስጥ አንዱ ነበሩ።

ሌሎችም በርካቶችን መዘርዘር ይቻላል። እነዚህ ከምስረታ እስከ አባልነት በአንሷረ ሱና ማህበር (ማህበር) ውስጥ ያለፉ ማስተዋወቅ የማያስፈልጋቸው የሱና ከዋክብት ናቸው። በነዚህ ላይ የተገደብኩት እነዚህ ዑለማዎች ሺርክንና ቢድዐን በመዋጋት፣ ተውሒድንና ሱናን በማሰራጨት ያላቸው ዝና ከፍ ያለ በመሆኑ፣ ከሌሎች ታዋቂ የሱና ዑለማዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ፣ እንዲሁም ወደ ሸሪዐዊ እውቀት ቀረብ የሚለው አህለ ሱናው ክፍል አይዘነጋቸውም ብየ ስለገመትኩ ነው።

### 11. የሰዑዲያህ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ፡-

ከማህበራት ጋር የተያያዙ እጅግ በርካታ ጥያቄዎች ሲቀርቡለት የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ከመመለስ ባለፈ ዛሬ አንዳንዶች እንደሚያራግቡት *“ማህበራት ሐራም ናቸው፣ ቢድዐ ናቸው፣ ሒዝቢያ ናቸው”* የሚል ሂስ አልሰነዘሩም። ምናልባት የማህበር አደጋ ከነሱ ይልቅ ለኛ ስለገባን ይሆን?! ወይስ ይሄ ሁሉ ተያያዥ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ጥያቄዎቹን ከመመለስ ባለፈ ማህበራቱን ዝም ማለታቸው ለዲኑ ተቆርቋሪነት ስለማይሰማቸው ይሆን?!

ለማህበራት ዘካ ወይም ሌላ ገንዘብ መስጠት ይቻል ከሆነ ሲጠየቁ ከመስረቱ ማህበራትን ወይም ማህበራትን ሳይቃወሙ፣ ሳያብጠለጥሉ እንደሚፈቀድ ደጋግመው ገልፀዋል። አንድ ምሳሌ እንውሰድ፡-

**ጥያቄ፡-**

**هل يجوز جمع الأموال للمشاريع الخيرية وبيع الكتب الإسلامية في المساجد بفرنسا؟**

**جواب: يجوز جمع التبرعات المالية في المسجد للجمعيات الخيرية؛ لما في ذلك من التعاون على البر والخير، وقد قال الله تعالى: (وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى).**

*"በፈረንሳይ ለሚገኙ የበጎ አድራጎት ፕሮጀክቶችና ለመስጂዶች የሚውሉ ኪታቦችን ለመግዛት ገንዘብ መሰብሰብ ይቻላልን?"*

**መልስ፡-**

***<u>"ለበጎ አድራጎት ማህበራት የሚውሉ ልገሳዎችን ከመስጂዶች ውስጥ መሰብሰብ ይቻላል። በዚህ ውስጥ በበጎና በመልካም ነገር ላይ መተጋገዝ አለውና።</u>*** *የላቀው አላህ በርግጥም እንዲህ ብሏል፡- 'በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተጋገዙ።'"* [ፈትዋ ቁጥር 3664፣ ተራ ቁ. 4] (ፈትዋውን የሰጡት፡ **<u>ኢብኑ ባዝ፣ ዐብዱላህ ኢብኑ ቀዑድ፣ ዐብዱላህ ኢብኑ ጉደያን፣ ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ</u>** ናቸው።)

በተጨማሪ በነዚህ ቁጥሮች እየገቡ በቋሚ የፈትዋ ኮሚቴው የተሰጡ ተቀራራቢ ይዘት ያላቸው ፈትዋዎቻችን መመልከት ይቻላል፡- (ቁ. 105፡ 9/440-441፣ ቁ. 265፡ 9/442-444፣ ቁ. 1083፡ 9/445-446፣ ቁ. 5162፡ 9/449-451፣ ቁ. 5586፡ 9/451-453፣ ቁ. 6986፡ 9/455-456፣...)

## 12. የሰዑዲያህ እውቀታዊ ጥናት፣ የፈትዋ፣ የደዕዋና የኢርሻድ አስተዳደር ጠቅላይ ጉባኤ

የዚህን የታላላቅ ዑለማእ ስብስብ የጥናት ማእከል አቋም ሲናገሩ ሸይኽ ኢብኑ ባዝ ረሒመሁላህ እንዲህ ይገልፃሉ፡-

**وبهذه المناسبة نحب أن نشير إلى أن للرئاسة العامة لإدارات البحوث العلمية والإفتاء والدعوة والإرشاد بحمد الله جهودا في مختلف البلاد الإسلامية والبلاد التي فيها أقليات...**

**فقد قامت الرئاسة بمواصلة نشر رسالة الإسلام ... من خلال المساجد والمدارس والجمعيات والمؤسسات الإسلامية التي تدعمها وتساهم في تأسيسها وبنائها بواسطة دعاتها .. وبحث ما فيه مصلحة لدعم الجمعيات الإسلامية المعروفة بسلامة الاتجاه**

*"ለእውቀታዊ የጥናት፣ የፈትዋ፣ የደዕዋና የኢርሻድ አስተዳደር ጠቅላይ ባለስልጣን - ምስጋና ለአላህ ይሁንና - በተለያዩ ኢስላማዊ ሃገራትና ሙስሊሞች ዝቅተኛ ቁጥር በሚይዙባቸው ሃገራት ብዙ ጥረቶች እንዳሉት በዚህ አጋጣሚ ልጠቁም እወዳለሁ። ... እናም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በመስጂዶች፣ በመድረሳዎች፣* ***በማህበራት፣*** *በዱዓቶቹ አማካኝነት በሚረዳቸው፣ በሚመሰርታቸውና በሚገነባቸው ኢስላማዊ*

*ተቋማት አማካኝነት የኢስላም ተልእኮን በማሰራጨት ላይ ተሰማርቷል። ... <u>አካሄዳቸው ጤናማ መሆናቸው የታወቁ ኢስላማዊ ማህበራትን ለማገዝ ጠቃሚ የሆኑ ጥናቶችንም ያካሂዳል።</u>...”*
[መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኑ ባዝ፡ 2/374-376]

**13. ሸይኽ ሙሐመድ ናሲሩዲን አልአልባኒ ረሒመሁላህ፡-**

**أيُّ جمعيةٍ تُقام على أساسٍ من الإسلامِ الصحيحِ، المستنبطةِ أحكامُها من كتاب الله، ومن سنة رسول الله، ومما كان عليه سلفنا الصالح؛ <u>فأيُّ جمعيةٍ تَقوم على هذا الأساس فلا مجال لإنكارها واتّهامها بالحزبية؛</u> لأن ذلك كلَّه يدخل في عموم قوله تعالى: ﴿وَتَعَاوَنُوا۟ عَلَى ٱلۡبِرِّ وَٱلتَّقۡوَىٰ﴾ والتعاونُ أمرٌ مقصود شرعاً، وقد تختلف وسائلُه من زمن إلى زمن، ومن مكان إلى مكان، ومن بلدةٍ إلى أخرى؛ ولذلك <u>فاتهامُ جمعيةٍ تقوم على هذا الأساسِ بالحزبيةِ أو بالبدعية فهذا لا مجال إلى القول به؛ لأنه يخالف ما هو مقرر عند العلماء من التفريق بين البدعة الموصوفة –بعامةٍ– بالضلالة، وبين السنةِ الحسنة؛</u> السنةُ الحسنة: هي الطريقة تُحدَثُ وتوجَد لتوصِل المسلمين إلى أمر مقصودٍ ومشروعٍ نصّاً، فهذه الجمعيات في هذا الزمن لا تختلف من حيث وسائلها عن الوسائل التي جدّت في هذا العصر لتسهِّل للمسلمين الوصول إلى غايات مشروعة؛ فما نحن الآن في هذه الجلسة من استعمال المسجلات –على أشكالها وألوانها– إلا من هذا القبيل، إنها وسائل أُحدثت، فإذا استعملت فيما يحقق هدفاً وغرضاً شرعياً؛ فهي وسيلة مشروعة، وإلا فلا، كذلك وسائل الركوب الكثيرة والمختلفة اليوم، من السيارات والطيارات**

**ونحو ذلك؛ هي أيضاً وسائل، فإذا استُعملت في تحقيق مقاصد شرعية؛ فهي شرعية، وإلا فلا..**

***"የትኛውም በትክክለኛው የኢስላም መሰረት ላይ የሚቋቋም፣ ከአላህ ኪታብና ከአላህ መልእክተኛ ሱና እንዲሁም መልካም ቀደምቶቻችን ከነበሩበት አካሄድ ብያኔዎቹ የተወሰደ ማህበር፣ የትኛውም በዚህ መሰረት ላይ የሚቆም ማህበር ሊቃወሙትና በቡድንተኝነት ሊወነጅሉት ዘንድ ቦታ የለም።*** *ምክንያቱም ይሄ ሁሉ 'በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ' ከሚለው የላቀው ጌታ ንግግር ጥቅል መልእክት ውስጥ የሚገባ ነውና። መተባበር ከሸሪዐህ አንፃር የሚፈለግ ነው። መዳረሻዎቹ ደግሞ ከዘመን ዘመን፣ ከቦታ ቦታ፣ ከሀገር ሀገር ሊለያዩ ይችላሉ። ስለዚህም* ***በዚህ መሰረት ላይ የሚቋቋምን ማህበር በቡድንተኝነት (ሒዝቢያህ) እና በመጤ ፈሊጥ (ቢድዐ) መወንጀል ይሄ ይጓዙበት ዘንድ ቦታ የሚሰጠው አቋም አይደለም።*** *ምክንያቱም ይሄ (በዚህ መልኩ የተቋቋመን ማህበር በቡድናዊነት በቢድዐ መወንጀል) በጥቅሉ በጥመት በተገለፀችው ቢድዐና በመልካም ሱና መካከል መለያየት እንዳለ በዑለማእ የፀናውን የሚፃረር ነውና። መልካም ሱና ማለት በግልፅ ማስረጃ የተደነገገን ተፈላጊ ግብ ሙስሊሞችን ለማድረስ የሚገኝ መንገድ ነው። እነዚህ በዚህ ዘመን ያሉ ማህበራትም ከመዳረሻነት አንፃር ወደ ሸሪዐዊ ግቦች በቀላሉ ለመድረስ በዘመናችን ከተገኙ ሌሎች መዳረሻዎች የሚለዩ አይደሉም። አሁን በዚህ ጉባኤያችን ላይ የምንጠቀማቸው የተለያዩ ቅርፅና ቀለማት ያላቸው የድምፅ መቅረጫዎች ከዚህ ምድብ ስር የሚካተቱ እንጂ ሌላ አይደሉም። እነዚህ አዲስ የመጡ መዳረሻዎች ናቸው። ሸሪዐዊ የሆኑ*

*ግብና አላማዎችን ለማሳካት ጥቅም ላይ ከዋሉ ሸሪዐዊ መዳረሻዎች ናቸው። ካልሆነ ግን (ሸሪዐዊ) አይሆኑም። እንደ መኪናዎች፣ አውሮፕላኖችና ይህን የመሰሉ ዛሬ አይነታቸው የበዛ መጓጓዣዎችም እንዲሁ መዳረሻዎች ናቸው። እናም ሸሪዐዊ ግቦችን ለማሳካት ጥቅም ላይ ከዋሉ ሸሪዐዊ ፍቃድ ያላቸው ሲሆኑ ካልሆነ ግን አይፈቀዱም።…"*
[ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ ካሴት ቁ. 590]

ድሆችንና ችግረኞችን ለመርዳትና መልካም ስራዎችን በመስራት ላይ ስለተሰማሩ የበጎ አድራጎት ማህበራት አስመልክቶ ብይኑን ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡-

**«إذا كانت الجمعية –الخيرية كما تقول وهذا يعود بنا إلى أن نقول :أن القضية واحدة في كل بلاد إسلامية، فإذا كان عندكم جمعية خيرية، وعندنا أيضاً –يمكن– أكثر من جمعية خيرية، في سوريا أيضاً وهكذا، والجواب يشمل كل هذه الجمعيات في كل بلاد الدنيا، وبخاصة الذين يعيشون في بلاد الكفر، في أوروبا في أمريكا إلى أخره، إذا كانت هذه الجمعيات قائمة على الأحكام الشرعية فهي جائزة، وهي داخلة في عموم قوله تعالى: ﴿أَرَءَيْتَ ٱلَّذِى يُكَذِّبُ بِٱلدِّينِ ﴿١﴾﴾ وفيها بعدُ: ﴿وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلْمِسْكِينِ ﴿٣﴾﴾ وهذه الآية دائماً نقرأها؛ إذن الحضّ على طعام المسكين هذا أمر مشروع..**

*"የበጎ አድራጎት ማህበሩ እንደምትለው ከሆነ ጉዳዩ በሁሉም ኢስላማዊ ሃገራት አንድ ነው እንድንል ያስችለናል ማለት ነው። እናንተም ጋር የበጎ አድራጎት ማህበር ካለ እኛም ጋር ብዙ የበጎ አድራጎት ማህበር ይኖራል። ሶሪያም ውስጥ እንዲሁ። ስለዚህ መልሱ በሁሉም የአለም*

*ሃገራት ያሉ ማህበራትን ያጠቃልላል ማለት ነው። በተለይ ደግሞ እንደ አውሮፓ፣ አሜሪካና ሌሎችም የክህደት ሃገራት የሚኖሩትን!! እናም እነዚህ ማህበራት ሸሪዐዊ ህግጋት ላይ የሚቆሙ ከሆነ የተፈቀዱ ናቸው። ‘ያንን በምርመራው የሚያስተባብለውን አየህን?’ ከሚለው የላቀው ጌታ ንግግር ጥቅል መልእክት ውስጥ የሚገቡ ናቸው። በሷ (በዚች ምዕራፍ) ውስጥ ‘ምስኪኖችን በማብላት ላይም የማያነሳሳ ሰው ነው’ የሚል አለ። ይቺ አንቀፅ ዘወትር እናነባታለን። እናም ምስኪኖችን በማብላት ላይ ማነሳሳት ሸሪዐው ያዘዘው ነገር ነው።…”* [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ ካሴት ቁ. 358] [4]

---

[4] ሸይኹ *“በሙስሊሞች መካከል በተለይም በሰለፍዮች መካከል ያለው ልዩነት ኢስላማዊ ማህበራትን ከመመስረት የመነጨ ነውን? ነው ወይስ ሸሪዐዊ ማስረጃዎችን ካለመረዳት ነው?”* የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡-

*“አይ መመስረቱ ከዚህ ጉዳይ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ልዩነቱ ስር የሰደደ የዐቂዳ ልዩነት ነው፡፡ ከዚያም ይሄ ልዩነት ተግባራዊ ልዩነት ይከተለዋል፡፡ ማህበራትን በተመለከተ አሁን እንደሚመስለኝ የምንስማማበት ነገር ቢኖር የበጎ አድራጎት ማህበራት የግድ ሸሪዐዊ ህግጋቶች ላይ የተገነቡ መሆን አለባቸው፡፡ ታዲያ እኛ እንጠይቃለን፡፡ መልሱ ግልፅ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በሙስሊሙ ዐለም የሚገኙ ማህበራት በሙሉ በሸሪዐዊ ህግጋቶች ላይ የተገነቡ ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁን?”*

ጠያቂ፡- *“ከፊሉ በሸሪዐዊ ህግጋቶች ላይ የተገነቡ ሲሆኑ ከፊሎቹ ግን አይደሉም፡፡”*

ሸይኹል አልባኒ፡- *“ጥሩ፡፡ ስለዚህ መልሱ እጅግ የቀለለ ነው ማለት ነው፡፡ **እናም ‘ሁሉም አይደሉም’ በል፡፡ ነገሩ ያልቃል፡፡ ሁሉም አይደሉም፡፡ ይልቁንም ከፊሉ በሸሪዐዊ ህግጋት ላይ የተገነቡ ሲሆኑ ከፊሉ ግን አይደሉም፡፡”*** [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 790]

ውይይቱ ረጅም ነው፡፡ በውስጡም ማህበራቱ የሸሪዐ ህግጋት የሚጠብቁ ሊሆኑ እንደሚገባ አስምረው ሁለት መስፈርቶችን አውስተዋል፡፡ አንዱ **መሪዎቹ ዑለማእ ሊሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ገንዘባቸውን በባንክ ላያስቀምጡ ነው፡፡** በሌላ ፈትዋቸውም ላይ *“ስለ ማህበር ምን ይላሉ?”* ሲባሉ *“ገንዘባቸውን የት ነው የሚያስቀምጡት?”* ብለው ጠየቁ፡፡ *“በባንክ”* ሲሏቸው ***“ውድቅ ነገር ላይ የተገነባ ውድቅ ነው”*** አሉ፡፡ [አስኢለቱ ሰያራ፡ ካሴት]

ሌላ የሙሐመድ ናሲሩዲን አልአልባኒ ረሒመሁላህ ፈትዋ፡-

...إذا أرادوا أن يشتغلوا بغير الدعوة: كأن يكونوا في جمعية خيرية تجمع الأموال، وتساعد الفقراء والمساكين، فهذه الجمعيةُ الخيريةُ خيرٌ؛ لأنها من معاني قول الله تبارك وتعالى: ﴿ولا تحاضُّون على طعام المسكين﴾، فهذا الحض أمرُ خير، محضوض عليه في القرآن الكريم، ...

*"ከደዕዋ ውጭ ባለ ዘርፍ መሰማራት ከፈለጉ፣ ለምሳሌ ገንዘብ የሚሰበስብና ድሆችንና ምስኪኖችን የሚረዳ ማህበር (ማህበር) ውስጥ መሆን ቢፈልጉ* ***<u>ይሄ የበጎ አድራጎት ማህበር መልካም ነው።</u>*** *ምክንያቱም ይሄ* ***'ምስኪኖችን በማብላት ላይ አታነሳሱም'*** *ከሚለው የአላህ ተባረከ ወተዓላ ንግግር መልእክት ውስጥ የሚካተት ነውና። ይሄ ማነሳሳት መልካም ነገር ነው።*

---

እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ማህበራትን ማገኘት ከባድ ነው፡፡ *"እውነታው እንዲያ ከሆነ ሸይኹን ማህበርን ከሚፈቅዱ ዑለማዎች ጋር ለምን ቆጠርካቸው?"* ሊባል ይችላል፡፡ ምክንያቱ፡-

1. ሸይኹ እራሳቸው ማህበራት እንደሚፈቀዱ ደጋግመው በግልፅ ስለተናገሩ፡፡
2. ማህበር መመስረት **<u>ቢድዐ እንዳልሆነ</u>** በግልፅ ስለተናገሩ፡፡ ይሄ "በሸርጥ ነው የፈቀዱት" የሚሉ ሰዎች የሚዘነጉት ሐቅ ነው፡፡ እንዲሁም፡-
3. ያስቀመጧቸው ሸርጦች ከሌሎች ዐሊሞች ዘንድ እንደ ሸርጥ ስላልተቆጠሩ ነው፡፡

በነገራችን ላይ በማህበር ምክንያት ሰዎችን ከሱና የሚያስወጡ ወንድሞች ቢያስተውሉ ኖሮ የአልባኒ ጥብቅ መስፈርቶችን ለአቋማቸው ማጠናከሪያ ከማቅረብ ይቆጠቡ ነበር፡፡ ምክንያቱም አልባኒ ***<u>"መስፈርቶቹን ያላሟላ ከሱና ይወጣል"</u>*** አላሉምና፡፡

**ለጥቆማ ያክል፡-** ሸይኹል አልባኒ በህንድ የሚገኘው የበናሪስ የሰለፊያ ዩኒቨርሲቲ የሐዲሥ ክፍሉን እንዲመሩ ጠይቋቸው ነበር፡፡ በጊዜው በህንድና በፓኪስታን መካከል በነበረው ግጭት ምክንያት ቤተሰባቸውን ለመውሰድ አስቸጋሪ እንደሆነ በመግለፅ ነው የቀሩት፡፡ ዩኒቨርሲቲው በአህሉል ሐዲሥ **<u>ማህበር</u>** ስር መሆኑን አሳልፌያለሁ፡፡

*በተከበረው ቁርኣንም ውስጥ የተበረታታ ነው። …”* [አልአስኢለቱ ሻሚያ፡ 27-28]

በሌላም ቦታ ለበጎ አድራጎት ማህበራት ዘካተል ፊጥርን ስለ መሰብሰብ ሲጠየቁ ስለ አካባቢው ድሃዎች ከባለገንዘቡ የተሻለ መረጃው ካላቸውና ወቅቱን ጠብቀው የሚሰጡ ከሆነ ለማህበራቱ ገንዘቡን መስጠቱ ችግር እንደሌለው ተናግረዋል። ባለ ማህበራቱ ዘካተል ፊጥር የሚሰጥበትን የጊዜ ገደብ የማይጠብቁ ከሆኑ በሚል ስጋታቸውን ከመግለፃቸው ውጭ ማህበራቱን በጅምላ አልኮነኑም። [ዱሩሱን ሊሸይኺል አልባኒ፡ 26/10]

### 14. ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ኢብኑ ባዝ ረሒመሁላህ:-

**سماحة الوالد الشيخ العلامة\ عبد العزيز بن عبد الله بن باز حفظه الله**
**السلام عليكم ورحمة الله وبركاته**
**متعكم الله بالصحة والعافية ، وزادكم إيمانا وتقوى، أما بعد:**
**س: فنحن مجموعة من الدعاة وطلبة العلم الشرعي بالسودان بحمد الله من الله تعالى علينا بعقيدة ومنهج السلف الصالح في توحيد العبادة والأسماء والصفات وغير ذلك، وهدفنا هو طلب العلم الشرعي ونشره بين الناس والدعوة إلى الله تعالى على طريقة السلف في مراكز مختلفة في أنحاء البلاد، وتعليم الناس أمور دينهم في التوحيد وأركان الإسلام وغير ذلك، ومحاربة الشرك والبدع، والدعوة إلى التمسك بالكتاب والسنة على فهم السلف الصالح، وغرس الفضيلة ومحاربة الرذيلة، وتربية الناس على مكارم الأخلاق والنأي بهم عن أراذلها. ونتعاون مع كافة من يعمل في حقل الدعوة إلى الله تعالى فيما وافق فيه الحق والصواب،**

تعاونا شرعيا؛ لقوله تعالى: {وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى} الآية، بعيدا عن التكتلات الحزبية والتعصب للرجال أو التنظيمات وعقد الولاء والبراء على ذلك، وإنما نحب في الله ونبغض في الله، ونوالي في الله ونعادي في الله على منهج السلف الصالح، ونعمل على إنشاء المراكز التعليمية وبناء المساجد والمعاهد الشرعية ودور تحفيظ القرآن والمكتبات العامة ونشر الكتب والرسائل العلمية النافعة، والأشرطة العلمية المفيدة، والحجاب الشرعي، وربط الأمة بالعلماء الربانيين .

ولهذا أنشأنا هيئة سلفية علمية تضم مجموعة من خريجي الجامعات الإسلامية بالمملكة العربية السعودية، وممن تتلمذوا على كبار مشايخ الدعوة السلفية في العالم الإسلامي تحت اسم جمعية الكتاب والسنة الخيرية التي مقرها الخرطوم، فهل هنالك محذور شرعي في العمل على تحقيق هذه الأهداف المذكورة من خلال الجمعية آنفة الذكر دون الالتزام بتنظيم جماعة معينة بالسودان؛ لما لدينا عليها من ملاحظات هامة مع الاحتفاظ بأخوة الإسلام والتعاون معهم على الحق؟ أفتونا مأجورين.

*"ገራገሩ አባታችን ታላቁ ዐሊም ሸይኽ ዐብዱል ዐዚዝ ኢብኒ ዐብዷላህ ኢብኒ ባዝ አላህ ይጠብቅዎትና አሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ። አላህ በጤናና በደህንነት ያጣቅምዎት፤ ኢማንና ተቅዋም ይጨምርዎት። በመቀጠል፡*

***ጥያቄ፡-*** *እኛ በሱዳን የምንገኝ ዱዓቶችና የሸሪዐ እውቀት ተማሪዎች ነን። የላቀው አላህ በአምልኮት፣ በአስማእ ወሲፋትና በሌላም ተውሒድ በመልካም ቀደምቶች ዐቂዳና ጎዳና መሆንን ስለዋለልን*

*እናመሰግነዋለን። አላማችን በሃገሪቱ የተለያዩ አቅጣጫዎች በሚገኙ መርከዞች በሰለፎች መንገድ ላይ ሸሪዐዊ እውቀትን መፈለግ፣ ለሰዎች ማሰራጨት፣ ወደላቀው አላህ መጣራት፣ በተውሒድ፣ የኢስላም ማዕዘናትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ሰዎችን መጣራት ነው። እንዲሁም ሺርክንና ቢድዐን መዋጋት፣ በሰለፎች ግንዛቤ ላይ ሆኖ ቁርኣንና ሱናን አጥብቆ ወደ መያዝ መጣራት፣ ጥሩ ስነ-ምግባርን መትከል፣ ርካሽ ስነ-ምግባርን መዋጋት፣ ሰዎችን በመልካም ስነ ምግባር ላይ መኮትኮት፣ ከዝቃጭ ባህሪዎች ማራቅ ነው። ሐቅንና እውነትን እስከገጠመ ድረስ ወደላቀው አላህ በመጣራት ዘርፍ ከተሰማራው ሁሉ ሸሪዐዊ መረዳዳትን እንረዳዳለን። የላቀው ጌታ (አላህ) እንዲህ ስላለ፡ 'በመልካም ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ።' ከቡድናዊ መሰባሰቦችና ለሰዎች ወይም ለድርጅቶች ጭፍን ተከታይ ከመሆን፣ እንዲሁም በዚህም ላይ መወዳጀትና መጠላላትን ከመመስረት በመራቅ ነው። ይልቁንም የምንወደውም የምንጠላውም ለአላህ ነው። ውዴታንና ጥላቻን የምንመሰርተውም በመልካም ቀደምቶች ጎዳና መሰረት ለአላህ ስንል ነው። የማስተማሪያ ማዕከላትን በመመስረት ላይ፣ መስጂዶችን፣ የሸሪዐ ተቋማትን፣ የቁርኣን ተሕፊዝ ማዕከላትን፣ አጠቃላይ ቤተ-መፃሕፍትን እንሰራለን። ጠቃሚ የሆኑ እውቀታዊ ኪታቦችና አነስተኛ መፃህፍቶችን፣ ጠቃሚ የሆኑ እውቀታዊ ካሴቶችን፣ ሸሪዐዊ ሒጃቦችን በማሰራጨት ላይ፣ ህዝበ-ሙስሊሙን ከዑለማእ ጋር በማስተሳሰር ላይ (እንሰራለን።)*

*ለዚህም ሲባል በሳዑዲ ዐረቢያ ከሚገኙ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎች የወጡ ምሩቃንንና በኢስላማዊው አለም ከሚገኙ ታላላቅ የሰለፊያ ደዕዋ መሻይኾች ላይ የተማሩ ሰዎችን ያቀፈ*

*'ጀምዒየቱል ኪታብ ወሱና አል'ኺይሪያ' በሚል ስያሜ እውቀታዊ የሰለፊያ መድረክ መስርተናል። ዋና ቢሮው ካርቱም ነው። ሱዳን ውስጥ ከሚገኙ የየትኛውም ቡድን መዋቅር ስር ሳይገደቡ - በነሱ ላይ የጎሉ የምናስተውላቸው ነገሮች ስላሉን ነው- አሁን በተጠቀሰው ማህበር አማካኝነት ያወሳናቸውን ግቦች ለማሳካት መስራት ሸሪዐዊ ነቀፌታ ይኖረዋልን? ባይሆን ኢስላማዊ ወንድማማችንና በሐቅ ላይ ከነሱ ጋር መተባበርን ከመጠበቅ ጋር ነው (ይህን የምንለው።) ፈትዋ ይስጡን (አላህ) ይመንዳዎትና።"*

**الجواب: بسم الله، والحمد لله، والصلاة والسلام على رسول الله، وآله وصحبه، أما بعد:**

**فهذا المنهج الذي ذكرتم أعلاه في الدعوة إلى الله تعالى، وتوجيه الناس إلى الخير على هدي الكتاب والسنة وطريق سلف الأمة منهج صالح نوصيكم بالتزامه والاستقامة عليه، والتعاون مع إخوانكم الدعاة إلى الله في السودان وغيرها فيما يوافق الكتاب والسنة، وما درج عليه سلف الأمة في بيان توحيد الله وأدلته والتحذير من الشرك ووسائله، والتحذير من البدع وأنواع المعاصي بالأدلة الشرعية والأسلوب الحسن؛ عملا بقوله تعالى: {وَمَنْ أَحْسَنُ قَوْلًا مِمَّنْ دَعَا إِلَى اللَّهِ وَعَمِلَ صَالِحًا} الآية، وقوله سبحانه: {قُلْ هَذِهِ سَبِيلِي أَدْعُو إِلَى اللَّهِ عَلَى بَصِيرَةٍ أَنَا وَمَنِ اتَّبَعَنِي} الآية، وقوله سبحانه: {ادْعُ إِلَى سَبِيلِ رَبِّكَ بِالْحِكْمَةِ وَالْمَوْعِظَةِ الْحَسَنَةِ وَجَادِلْهُمْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ} وقول النبي ﷺ: «من دل على خير فله مثل أجر فاعله»، خرجه مسلم في صحيحه، «وقول النبي ﷺ لعلي رضي الله عنه لما بعثه إلى خيبر لدعوة اليهود: ادعهم إلى الإسلام، وأخبرهم بما يجب عليهم من**

**حق الله تعالى فيه، فوالله لأن يهدي الله بك رجلا واحدا خير لك من حمر النعم»، متفق على صحته. والآيات والأحاديث في هذا المعنى كثيرة.**
**والله المسئول أن يمنحكم التوفيق والإعانة على كل خير، وأن يجعلنا وإياكم من الهداة المهتدين، إنه جواد كريم، وصلى الله وسلم على نبينا محمد ، وعلى آله وصحبه أجمعين.**

**መልስ፡-** *"ቢስሚላህ። ምስጋና ለአላህ ይሁን። ሶላትና ሰላም በአላህ መልእክተኛ፣ በቤተሰባቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን። በመቀጠል፡- ይሄ ወደላቀው አላህ ለመጣራት፣ እንዲሁም ሰዎችን በቁርኣን፣ በሱናና በመልካም ቀደምቶች ጎዳና መሰረት ወደኸይር ለማዞር* ***ከላይ የጠቀሳችሁት መንገድ ጥሩ የሆነ መንገድ ነው። አጥብቃችሁ እንድትይዙትና እንድትፀኑበት፣ እንዲሁም በሱዳንም ይሁን በሌሎች (ሃገራት) ካሉ ዱዓት ወንድሞቻችሁ ጋር ቁርአን፣ ሱናንና ሰለፎች የተጓዙበትን በሚገጥም መልኩ ተውሒድንና መረጃዎቹን ግልፅ በማድረግ፣ ከሺርክና መዳረሻዎቹ በማስጠንቀቅ፣ ከቢድዐና ከተለያዩ የወንጀል አይነቶች በሸሪዐዊ ማስረጃዎችና በመልካም ብልሃት በማስጠንቀቅ እንድትተባበሩ አደራ እንላችኋለን።*** *ይህም 'ወደ አላህ ከጠራ፣ መልካምንም ከሰራና እኔ ከሙስሊሞች ነኝ ካለም ሰው ይበልጥ ቃሉ ያማረ ማን ነው?' በሚለው የላቀው ጌታ ንግግር፤ 'ይህቺ መንገዴ ናት። ወደ አላህ እጠራለሁ። እኔም የተከተለኝም ሰው በግልፅ ማስረጃ ላይ ነን' በሚለውም የላቀው ጌታ ንግግር፤ 'ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳፄ ጥራ። በዚያችም እርሷ መልካም በሆነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው' በሚለው የላቀው ጌታ ንግግር፤ እንዲሁም 'በበጎ ላይ ያመላከተ ለሱ የሰሪው*

*አምሳያ ምንዳ አለው’ በሚለው የነብዩ ﷺ ንግግር በመስራት ነው። ሙስሊም በሶሒሐቸው ዘግበውታል። ነብዩም ﷺ ለዐልይ ወደ ኸይበር የሁዶችን ለመጥራት በላኩት ጊዜ እንዲህ ብለውታል፡- ‘ወደ ኢስላም ጥራቸው። በነሱ ላይ ግዴታ የሚሆንባቸውን የላቀውን አላህ ሐቅም ንገራቸው። በአላህ ይሁንብኝ! በአንተ አማካኝነት አላህ አንድን ሰው ቢያቀናልህ ላንተ ከቀያይ ግመሎች የበለጠ ነው።’ በሶሒሕነቱ ላይ ተስማምተውበታል። ይህን መልእክት የሚደግፉ አንቀፆችና ሐዲሦች ብዙ ናቸው። መታደልንና በሁሉም ኸይር ላይ መታገዝን እንዲሰጣችሁ፣ እኛንም እናንተንም ከአቅኚዎችና ከተቀኚዎች እንዲያደርገን የሚጠየቀው አላህ ብቻ ነው። እሱ ለጋስና ቸር ነው። በነብያችን በሙሐመድ፣ በቤተሰባቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ አላህ ሶላትና ሰላሙን ያውርድ።”* [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኑ ባዝ፡ 8/432-435]

እንዲህም ብለዋል፡-

**..والجمعيات إذا كثرت في أي بلد إسلامي من أجل الخير والمساعدات والتعاون على البر والتقوى بين المسلمين دون أن تختلف أهواء أصحابها فهي خير وبركة، وفوائدها عظيمة أما إن كانت كلٌّ واحدة تضلل الأخرى وتنقد أعمالها فإن الضرر بها حينئذ عظيم والعواقب وخيمة**

*“**ማህበራት** በየትኛውም ኢስላማዊ ሃገራት ባለቤቶቹ ስሜታቸው ሳይለያይ ለበጎ ነገር፣ ለእርዳታዎች፣ በመልካምና አላህን በመፍራት ላይ ለመተባበር **ቢበዙ ይሄ በረካ ያለው በጎ ነገር ነው።** ጥቅሞቻቸውም የላቀ ነው። አንዱ ሌላውን የሚያጠም፣ ስራዎቹንም የሚተች ከሆነ ግን*

*ያኔ ጉዳቱ ከባድ ነው፣ ውጤቱም ጎጂ ነው።"* [*መጅሙዑ ፈታዋ* ኢብኑ ባዝ፡ 4/136፣ 5/203]

ልብ በሉ! ጤናማ መሰረት ያላቸው ሰዎች የሚከፍቷቸው ማህበራት መብዛታቸው ኸይርና በረካ ያለው እንደሆነ ነው የገለፁት። ይሄ "ይፈቀዳል" ከማለትም አልፎ ማበረታታት ነው።

የአሁኑ የሳዑዲያህ ንጉስ ሰልማን የሪያድ አካባቢ ገዢ በነበረበት ወቅት "አልቢር" ለሚባል ማህበር ዋና ሀላፊ ነበር። እናም ከአሚር ሰልማን ለኢብኑ ባዝ ስለማህበሩ አንዳንድ ስራዎች አስመልክቶ ሲጠየቁ የቀረበውን ጥያቄ ከመመለስ ባለፈ ማህበሩንና ሀላፊዎቹን አላወገዙም። እንዲያውም *"ሁላችሁንም አላህ እሱ ለሚወደው እንዲያድላችሁ፣ የክቡርነትዎንና የሌሌቹንም* ***<u>የማህበሩን ተጠሪዎች ጥረታችሁን እንዲባርክላችሁ እለምነዋለሁ።</u>*** *እሱ ምን ያማረ ተለማኝ ነውና"* ብለው ነው የመለሱት። [*መጅሙዑ ፈታዋ* ኢብኑ ባዝ፡ 14/250]

ኢብኑ ባዝ ሌሎች ቦታዎችም ላይ ማህበርን የፈቀዱባቸው ወይም በማህበር በተዘጋጁ የደዕዋ ዝግጅት ላይ ቀርበው ያስተማሩባቸው ወይም ማህበራቱን ወይም ባለማህበራቱን ያወደሱባቸው፣ ከባለማህበራቱ ጋር የተፃፃፉባቸው ፈትዋዎችና ንግግሮች አሏቸው። ለምሳሌ፡ [*መጅሙዑ ፈታዋ* ኢብኑ ባዝ፡ 4/105፣ 14/276-277፣ 20/64፣ 21/51]

## 15. ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ሷሊሕ አልዑሠይሚን

ሸይኹ በ 1405 በዑነይዛህ ከተማ የተመሰረተውን "ጀምዒየቱ ተሕፊዚል ቁርኣኒል ከሪም አልኸይሪያህ" ማህበር እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ

መሪ ሆነው አገልግለዋል። ይሄ አስተዋይ ለሆነ ሰው "ይፈቀዳል" ከማለት በላይ መልእክት አለው።

በተጨማሪም ለሸይኹ እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር:-

**بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ فضيلة شيخنا الفاضل مُحَمَّد بن صالح بن عثيمين –حفظه الله ورعاه، وأمتع المسلمين بحياته–**

**السلام عليكم ورحمة الله وبركاته أما بعد:**

**س: فإن خلافاً يدور بين الشباب في بلدنا حول جواز إقامة جمعيات خيرية تقوم برعاية المساكين والأيتام، وتنشئة الشباب على القرآن بتوفير الجو المناسب لهم للقيام بحفظ القرآن الكريم والسنة النبوية؛ فبعض الشباب يرى أن ذلك بدعة لا تجوز؛ لأنها لم تكن موجودة في عهد النبي –ﷺ–، ولا في عهد الصحابة الكرام –رضي الله عنهم–! ويصل الخلاف إلى حد الشتائم والسباب والتوتّر، الذي يظهر لمن عنده أدنى بصيرة أنه يخالف روح الإسلام، الذي ينهى عن الاختلاف والتدابر والتنابز بالألقاب. فنرجو يا فضيلة الشيخ أن توجه نصيحة لهؤلاء الشباب مصحوبةً بالفتوى الشرعية؛ فإنه ظهر لي أن الجميع يحبونكم، ويثقون بعلمكم، جزاكم الله خيراً ورعاكم.**

**ج: بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ، وعليكم السلام ورحمة الله وبركاته، لا بأس بتكوين لجنة لقبول الصدقات والزكوات وغيرها من النفقات الشرعية؛ لأن ذلك من الوسائل إلى ضبط هذه الأمور تحصيلاً وتوزيعاً، وهذا مقصود شرعي لا يقصد به إلا ضبط هذه الأشياء، وما كان وسيلة لمقصود شرعي فلا بأس به ما لم يقصد التعبد بنفس الوسيلة. كتبه مُحَمَّد الصالح العثيمين في 1417/7/11 هـ**

*“እጅግ ርህሩህና አዛኝ በሆነው አላህ ስም። የተከበሩ ክቡር ሸይኻችን ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አልዑሠይሚን አላህ ይጠብቅዎት፣ ይንከባከብዎት! በህይወትዎም ሙስሊሞችን ያስጠቅማቸው። አሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ። በመቀጠል፡-*

*በሀገራችን ድሆችንና የቲሞችን ለመርዳት፣ የሚስማማቸው ሁኔታ እንዲኖር በማድረግ ወጣቶችን የተከበረውን ቁርኣንና ነብያዊ ሱናን እንዲሐፍዙ በቁርኣን ለመኮትኮት በማለም የበጎ አድራጎት ማህበራት ማቋቋም ስለመፈቀዱ በወጣቶች መካከል ውዝግብ ተነስቷል።* [5] *አንዳንዱ ወጣት ይሄ የማይፈቀድ ቢድዐ እንደሆነ ያምናል። ምክንያቱም በነብዩ ﷺ እና በተከበሩ ሶሐቦች ረዲየላሁ ዐንሁም ዘመን አልነበረምና። ውዝግቡ የኢስላምን መንፈስ የሚፃረር እንደሆነ ትንሽ ግንዛቤ ላለው እንኳን የጎላ የሆነ እስከመሰዳደብ፣ መወራረፍና ውጥረት ማንገስ ጥግ ይደርሳል። ያ (ኢስላም) ከመወዛገብ፣ ጀርባ ከመሰጣጠት፣ ቅፅል ስም ከመለጣጠፍ የሚከለክል ሆኖ ሳለ። እናም የተከበሩ ሸይኽ ሆይ! ከሸሪዐዊ ፈትዋ ጋር የተቆራኘ ምክር እንድትለግሱ እንከጅላለን። እንደሚታየኝ ሁሉም ይወድዎታል። በእውቀትዎም ይተማመናሉ። አላህ በመልካም ይመንዳችሁ፣ ይንከባከባችሁም።”*

ወንድሜ ሆይ! እህቴ ሆይ! ወደ መልሳቸው ከመግባታችን በፊት ይህን ጥያቄ በደንብ እናስተውል! ከራሳችን ነባራዊ ሁኔታ ጋርም እናገናዝበው።

---

[5] አስተውሉ! “ማህበር ይፈቀዳል” ወይስ “አይፈቀድም” የሚለው ውዝግብ ያኔም ነበር፡፡ የሰጡትን መልስ ግን ተመልከቱ፡፡ ይሄ “ያኔ ችግሩ ስላልነበር ነው የፈቀዱት” ለሚሉ ሰዎች በቂ መልስ አለው፡፡

**<u>እሳቸው የሰጡትን መልስ አንድ ሰው ቢሰጠው ወይም የሳቸውን ፈትዋ ጭብጥ ተቀብሎ ቢያስተጋባ ዛሬ ምን አይነት ቅፅል ስም እንደሚወጣለት ይገመታል።</u>** ወደ መልሳቸው እናምራ።

*"እጅግ ርህሩህና አዛኝ በሆነው አላህ ስም። ወዐለይኩም አሰላም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ። ሶደቃዎችን፣ ዘካዎችና ሌሎችንም ሸሪዐዊ ልገሳዎችን ለመቀበል ኮሚቴ ማዋቀር* ***<u>ችግር የለውም።</u>*** *ምክንያቱም ይሄ እነዚህን ነገሮች በስርኣት ለማገኘትና ለማሰራጨት* ***<u>ከመዳረሻዎች</u>*** *ነውና። እነዚህን ነገሮች ስርኣት ለማስያዝ የሚታለም እንጂ ሌላ አላማ የለውም።* ***<u>ለሸሪዐዊ ግብ መዳረሻ የሆነ ደግሞ በራሱ በመዳረሻው አምልኮት ካልታሰበበት በስተቀር ችግር የለበትም።</u>*** *ሙሐመድ አሷሊሕ አልዑሠይሚን በ11/7/1417 ፃፈው።"* [መጅሙዑ ፈታዋ ወረሳኢል ፈዲለቱ አሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አልዑሠይሚን፡ 18/465-466]

በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፡-

**فلا يخفى ما في جمعيات البر الخيرية التي نشأت في زماننا هذا من عون للناس على صرف أموالهم في طرق الخير النافعة للمجتمع، فهي خيرٌ للآخذ والمعطي جميعاً، وخير للقائمين عليها بمساعدة إخوانهم، تلقياً من الأغنياء، وصرفاً إلى المستحقين. وفيها راحة تامة لكون القائمين عليها، يبذلون جهداً كبيراً في التحري عن المستحقين، ليقع الصرف موقعه، فهي من نعم الله علينا في هذا الزمن الذي قصرت فيه الهمم عن التحري، وكثر الآخذون ما ليس لهم بحق، فالحمد لله على نعمه**

*“በዘመናችን በተቋቋሙት በበጎና በመልካም <u>ማህበራት</u> ውስጥ ያለው ሰዎችን ገንዘባቸውን ለህብረተሰብ ጠቃሚ በሆኑ መንገዶች ላይ* ***እንዲለግሱ ያላቸው እገዛ አይሰወርም። እነዚህ (ማህበራት) <u>ለተቀባይም ለሰጭም ለሁሉም በጎ ናቸው።</u> ወንድሞቻቸውን ለመርዳት በማሰብ ከሀብታሞቹ በመቀበል፣ ወደሚገባቸው በማድረስ በነሱ (በማህበራቱ) ላይ ለሚሰሩትም በጎ ናት።*** *በሷ ላይ ለሚሰሩትም የተሟላ (የሀሲና) እረፍት አለው። ምክንያቱም የሚገባቸውን በመለየት ላይ፣ ገንዘቡ ከቦታው ላይ እንዲያርፍ ትልቅ ጥረት ያደርጋሉና። እናም እነዚህ (ማህበራት) በዚህ ለጥንቃቄ ምራሎች በደከሙበት፣ ሐቃቸው ያልሆነን የሚወስዱ በበዙበት ዘመን* ***<u>አላህ በኛ ላይ ከዋላቸው ፀጋዎች ውስጥ ናቸው።</u>*** *አላህ በፀጋው ላይ ምስጋና ይድረሰው። ....”* [መጅሙዑ ፈታዋ: 18/439]

እዚህም ላይ ማህበር “ይፈቀዳል” ከማለትም አልፈው ብዙ ኸይር እንዳለው በመዘርዘር አላህን ልናመሰግንበት የሚገባ የሱ ፀጋ እንደሆነ ነው የገለፁት።

በተጨማሪም በአንድ ደብዳቤ ላይ እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል፡-

**بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ 1397/9/12 هـ**

**من مُحَمَّد الصالح العثيمين إلى الأخ المكرم... السلام عليكم ورحمة الله وبركاته، وبعد:**

**كتابكم الكريم المؤرخ 27 من الشهر الماضي وصلني قبل أمس، أي: يوم الأربعاء 10 من الشهر الحالي، سرنا صحتكم، الحمد لله على ذلك، ونسأل أن يديم علينا وعليكم نعمته، ويرزقنا شكرها. كما سرنا كثيراً تكوين جمعية إسلامية من الطلبة**

**والعمال المسلمين في المدينة التي أنتم فيها في...، تهتم هذه الجمعية بأمر الإسلام والمسلمين، فنسأل الله أن يثبتهم على ذلك، وأن يرزقهم البصيرة في دين الله، والحكمة في الدعوة إليه...**

*“ከሙሐመድ አሷሊሕ አልዑሠይሚን ወደ ተከበረው ወንድም ...*

*አሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ። በመቀጠል፡-*

*ባለፈው ወር በቀን 27 የተፃፈ የተከበረ ደብዳቤያችሁ ከትላንት በስቲያ ደርሶኛል። እሮብ እለት ማለት ነው በዚህ ወር፣ በ10። ጤንነታችሁ አስደስቶናል። ስለዚህም አላህን እናመሰግነዋለን። በኛም ላይ በናንተም ላይ ፀጋውን እንዲያዘወትርልን ምስጋናውንም እንዲያድለን እንለምነዋለን። ልክ እንዲሁ ባላችሁባት ከተማ ውስጥ በኢስላማዊና በሙስሊሞች ጉዳዮች* ***<u>ላይ የሚያተኩር ተማሪዎችንና ሙስሊም ሰራተኞችን ያማከለ ኢስላማዊ ማህበር መመስረታችሁ አስደስቶናል።</u>*** *በዚህ ላይ አላህ እንዲያፀናቸው፣ በአላህ ዲን ላይ እውቀትን፣ እንዲሁም ወደሱ በመጣራትም ላይ ጥበብን እንዲያድላቸው እንለምነዋለን።”* [መጅሙዑ ፈታዋ፡ 16/225]

ሌላም ሐዲሥ አጣቅሰው የማህበር ስራ ኢስላማዊ መሰረት እንዳለው የተናገሩበት ቦታ አለ። ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- *“የአሽዐሪ ጎሳዎች በዘመቻ ላይ ስንቃቸው ሲያልቅ ወይም ሊያልቅ ሲቃረብ ወይም ደግሞ መዲና ውስጥ የቤተሰቦቻቸው ምግብ ሲቀል ያላቸውን በአንድ ልብስ ላይ ይሰበስቡና ከዚያም በአንድ እቃ እኩል አድርገው በመካከላቸው ይካፈሉታል። እነሱ ከኔ ናቸው። እኔም ከነሱ ነኝ።”* [ቡኻሪ፡ 2486፣ ሙስሊም፡ 2500]

ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን ከዚህ ሐዲሥ ስር እንዲህ ይላሉ፡-

***"ይሄ ሐዲስ ዛሬ አንዳንድ ሰው የሚሰራውን የትብብር ማህበራት ስራን በተመለከተ መሰረት ነው።*** *አንድ ጎሳ ተሰብስቦ የተገራላቸውን ገንዘብ በሱ ውስጥ ለመሰብሰብ ሳጥን ያስቀምጣሉ። መዋጮውም በመቶኛ (በፐርሰንት) ወይም ሁሉም የጥረቱን ወይም ደግሞ በጥቆማ ይሆናል። ለምሳሌ እያንዳንዱ ከደሞዙ ወይም ከሚሰራው ወዘተ ሁለት ፐርሰንት ሊሰጥ ይስማማሉ። ከዚያም ይሄ ሳጥን በአንዳቸው ላይ ለሚደርስ ችግርና መከራ የተዘጋጀ ይሆናል።"* [ሸርሑ ሪያድ አሷሊሒን፡ 2/215-216]

ሌላም እንዲህ የሚል ፈትዋ አላቸው፡-

**من مُحَمَّد الصالح العثيمين إلى الأخ المكرم– .......حفظه الله–**

**السلام عليكم ورحمة الله وبركاته.**

**كتابكم الكريم المؤرخ 32 رمضان1397 هـ وصل، سرني صحتكم الحمد لله على ذلك، وأسأله أن يتم نعمته على الجميع ويرزقنا شكرها، كما سرني نبأ وصول جوابي على كتاب الأخ .... حول تأخير صلاة العيد، وأشكر جمعيتكم على عنايتها بذلك، وأسأل الله أن يرزقنا جميعاً البصيرة في دينه والثبات عليه.**

**كما أفيدكم بأني أحب مواصلة الكتابة والتعرف على أحوال الجمعية لأن هذا يهم الجميع. وقد تضمن كتابكم المذكور أربع مسائل بل خمساً: المسألة الأولى : تأسيس مركز إسلامي في مدينة ....وأنا أؤيد فكرة تأسيسه للأسباب التي ذكرها مؤيدو الفكرة، ولما فيه من ظهور شأن الإسلام، وبيان اعتزاز أهله به وعنايتهم بشؤونه، ثم إنه لابد أن يلفت نظر أهل المدينة**

**فيجتمع إليه من يمكن دعوته إلى الإسلام فيسلم إذا خلصت نية الداعي، وسلك طريق الحكمة في دعوته، ففكرة تأسيسه فكرة جيدة نبيلة نافعة للإسلام والمسلمين إن شاء الله. والأسباب التي ذكرها المعارضون مدفوعة بكون بعضها غير وارد إطلاقاً وبعضها غير مؤثر**

*ከሙሐመድ ኢብኑ አሷሊሕ አልዑሠይሚን ለተከበረው ወንድም... አላህ ይጠብቀውና። አሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ።*

*በረመዳን 32/1397 ሂ. የተፃፈው ደብዳቤያችሁ ደርሷል። ጤና መሆናችሁ አስደስቶኛል፣ በዚህ ላይ አላህ ይመስገን። በሁሉም ላይ ፀጋውን እንዲሞላ፣ እንዲሁም ማመስገኑን እንዲቸረን እለምነዋለሁ። የዒድ ሶላትን ስለማዘግየት በተመለከተ በወንድም... ደብዳቤ ላይ የሰጠሁት መልስ መድረሱም እንዲሁ አስደስቶኛል።* ***<u>ማህበራችሁ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ስለሰጠም አመሰግናለሁ። ሁላችንንም በዲኑ ላይ እውቀትንና ፅናቱን እንዲቸረን አላህን እለምነዋለሁ። የማህበሩን ሁኔታዎች ለማወቅ መፃፃፋችን መቀጠሉን እንደምወድ ልጠቁማችሁ እወዳለሁ። ምክንያቱም ይሄ ሁሉንም ይመለከታልና።</u>*** *ደብዳቤያችሁ አራት ኸረ እንዲያውም አምስት ጥያቄዎችን አካቷል።*

*የመጀመሪያው ጥያቄ፡- በ..... ከተማ ኢስላማዊ ማዕከል ስለማቋቋም ነው። እኔ የሀሳቡ ደጋፊዎች ያነሷቸውን በመመርኮዝ፣ የኢስላምን ጉዳይ ማንፀባረቅ ስላለበት፣ ባለቤቶቹ በሱ ላይ ያላቸውን ኩራትና በጉዳዮቹ ላይ ያላቸውን ትኩረት የሚገልፅ ስለሆነ* ***<u>የማቋቋሙን ሀሳብ እደግፋለሁ።</u>*** *ደግሞም የከተማዋን ነዋሪዎች የግድ ትኩረት ይስባልና ወደ ኢስላም ሊጥጠራ የሚችል ሰው ሊሰባሰብ ይችላል። በዚህም*

*የተጣሪው ኒያ ከጠራና በደዕዋው ላይ ጥበብን ከተጠቀመ ሊሰልም ይችላል። ስለሆነም የመመስረቱ ሀሳብ ጥሩና ግሩም የሆነ አላህ ከፈቀደ ኢስላምንና ሙስሊሞችን የሚጠቅም ሀሳብ ነው። ተቃዋሚዎቹ ያነሷቸው ምክንያቶች ከፊሎቹ ጭራሽ የሚከሰቱ አይደሉም። ከፊሎቹ ደግሞ ተፅእኖ የሚያሳድሩ አይደሉም።"* [መጅሙዑ ፈታዋ፡ 16/21]

ሌሎችም የማህበር ስራን ያወደሱበት፣ ለማህበራት ሶደቃዎች እንዲሰጡ የቀሰቀሱበት፣ ከማህበራት ጋር የተላላኩበት፣ ጥያቄ ተጠይቀው የመለሱበት፣... ብዙ ቦታዎች አሉ። [አሊ.ቃኡ ሸህሪይ፡ 11/20፣ 21/14]፣ [ሊ.ቃኡል ባቢል *መፍቱሕ*፡ 2/46፣ 43/12፣ 141/13]፣ [*መጅሙዑ ፈታዋ*፡ 18/280-283፣ 18/295-296]

እዚህ ማስታወሻ ላይ ከሰፈሩት በተጨማሪ "ሑክሙል ዐመሊል ጀማዒይ ፊል ኢስላም" የሚል ኪታብ ላይ **<u>የአልባኒን፣ የኢብኑ ባዝንና የኢብኑል ዑሠይሚንን ተጨማሪ ፈትዋዎች</u>** ማግኘት ይቻላል። ለኪታቡ መቅዲም የፃፉት ሸይኽ ፈውዛን ናቸው።

### 16. ሸይኽ ዐብዱል ሙሕሲን አልዐባድ፡-[6]

**السؤال: هل يجوز تأسيس جمعية هدفها الدعوة إلى الكتاب والسنة على فهم السلف الصالح ، هذه الجمعية لها رئيس وأعضاء مع العلم بأنه لا يسمح لأهل السنة إقامة الدروس والمحاضرات في المساجد إلا لمن يوافق أهواءهم**

[6] ዐብዱል ሙሕሲን ሸይኽ ሙቅቢልን ጨምሮ ለብዙ ታላላቅ ዑለማዎች ሸይኽ ናቸው፡፡

**الجواب :**

**إذا كان بلد فيه جمعيات مخالفة للسنة وأراد أهل السنة أن يكونوا جمعية يعني يقومون بسببها بالنفوذ إلى الناس وأنهم يقومون بالدعوة إلى الله عز وجل فإن هذا شيء مطلوب لا بأس هذا شيء طيب، يعني يترك المجال للبعيدين عن السنة يعني يسرحون ويمرحون ويضرون الناس يعني أهل السنة كونهم يكونون لهم جماعة مادام البلد فيه جماعات يعني غير سليمة وفيها القريب من الحق والبعيد عنه وأولئك يريدون أن يكونوا جمعية للدعوة إلى الكتاب والسنة والسير على ماكان عليه سلف الامة هذا أمر مطلوب**

**ጥያቄ፡-**

*"በመልካም ቀደምቶች ግንዛቤ መሰረት ወደ ቁርአንና ሱና ለመጣራት ማህበር መመስረት ይቻላልን? ይሄ ማህበር መሪና አባላት አሉት። ከግንዛቤ እንዲገባ የምንፈልገው ለአህሉ ሱና ትምህርቶችን (ደርሶችን) እና ጉባኤዎችን (ሙሓዶራዎችን) በመስጂዶች ውስጥ መስጠት አይቻልም፣ ስሜቶቻቸውን ለሚጋራቸው ካልሆነ በስተቀር።"*

**መልስ፡-**

*"ሀገሩ ለሱና ተፃራሪ የሆኑ ማህበራት ያሉበት ከሆነና የሱና ሰዎች ማህበር ማቋቋም ከፈለጉ፣ ማለትም በሱ አማካኝነት ወደ ሰዎች መድረስ፣ ወደ አላህ ዐዘ ወጀል ለመጣራት ከተነሱ ይሄ የሚፈለግ ነገር ነው። ችግር የለበትም ይሄ ጥሩ ነገር ነው። ታዲያ ሜዳውን ከሱና የራቁ ሰዎች እንዳሻቸው እንዲንፈላሰሱ ሰዎችን ሲጎዱ ሊተዋቸው ነውን? እናም በሀገሩ ውስጥ ከፊሉ በአንፃሩ ለሐቅ የቀረቡ ሌሎች*

***ደግሞ ከሱ የራቁ ጤናማ ያልሆኑ የተለያዩ ቡድኖች ካሉ እነዚያ ሰዎች ማለትም የሱና ሰዎች ወደ ቁርኣንና ወደ ሱና እንዲሁም መልካም ቀደምቶቻችን ወደነበሩበት ለመጣራት ማህበር ቢያቋቋሙ ይሄ የሚፈለግ ነገር ነው።”*** [ሸርሑ ኪታቢል ሐጅ ሚን ኪታቢ ቡሉጊል መራም፣ ዙልቂዕደህ፡ 23/1432]

ወንድም እህቶች! ይህን ፈትዋ ከኛ ሃገር ነባራዊ ሁኔታ ጋር አዛምዱና አስተውሉት።

- በሃገራችን ከሱና የወጡ ማህበራት አሉ ወይስ የሉም? ግልፅ ነው።
- እንዲህ አይነቱን አደጋ ለመጋፈጥ ደግሞ የሱና ሰዎች ማህበር ማቋቋማቸው ተፈላጊ እንደሆነ ነው ሸይኹ እየጠቆሙ ያሉት። እንዲያውም ፈር ለለቀቁ አንጃዎች መድረኩን መተው እንደማይገባ ነው የጠቆሙት።

ሌላም ሸይኹ ከማህበር ጋር በተያያዘ የተናገሩትን በነዚህ ምንጮች ገብቶ መመልከት ይቻላል። [ሸርሑ ሱነን አቢ ዳውድ፡ 1/2]፣ [ሪፍቀን አህለ ሱና ቢአህሊ ሱና፡ 19]

### 17. ሸይኽ ሙቅቢል ቢን ሃዲ አልዋዲዒ ረሒመሁላህ፡-

**..ثم نسمعهم بعد ذلك يقولون: أنتم تطعنون في الجمعيات! فمن قال لك: إننا نطعن في الجمعيات؟ نعم، إننا نطعن في بعض الجمعيات التي اشتملت على حزبيات وعلى ولاء ضيّق، وعلى لصوصية واختلاس الأموال، فهذه هي التي نطعن فيها وننفر عنها.**

*"ከዚያም ከዚህ በኋላ 'ማህበራትን ታነውራላችሁ' ሲሉ እንሰማቸዋለን! ማነው እኛ ማህበራትን እንደምናነውር የነገረህ? [7] አዎ! እነዚያን ቡድንተኝነት፣ (ማህበሩን ያማከለ) ጠባብ መወዳጀት፣ ሴብነትና ገንዘብ መሞጭለፍን የያዙትን **<u>አንዳንድ</u>** ማህበራትን እናነውራለን። **<u>እነዚህ ናቸው የምናነውራቸውና ሰዎችን ከነሱ የምናስጠነቅቃቸው የሆኑት።"</u>***

[ቱሕፈቱል ሙጂብ፡ 190]

የሸይኹን ንግግር በደንብ ያጢኑት። የሚተቹት ምን አይነት ማህበራትን እንደሆነ ይጠቁማል። እንዲህ አይነት ግልፅ መልእክት ያላቸውን ፈትዋዎች ገሸሽ በማድረግ የሚተቹበትን ብቻ እየመረጡ ማቅረብ እራስን መሸወድ ነው። እንዳልኩት ሸይኽ ሙቅቢል ማህበራትን የሚተቹባቸው ብዙ ንግግሮች አሏቸው። ለምሳሌ እንዲህ ይላሉ፡-

*"እነዚህ ማህበራት በማህበራዊ ጉዳዮች (መስሪያ ቤት) ቁጥጥር ስር ሆነው በተወሰኑ መስፈርቶች፣ (ለምሳሌ) ምርጫዎች ሊኖራቸው፣ ገንዘቦቻቸው ወለድ ባለባቸው ባንኮች ሊያስቀምጡ ሆነው እንጂ ፈቃድ የማይሰጥባቸው ናቸው። ከዚያ ግን ባለቤቶቹ 'መስጂዶችን መገንባት፣ የውሃ ጉድጓዶችን መቆፈር፣ የቲሞችን መርዳት ሐራም ነውን?' እያሉ ሰዎችን ያምታታሉ። እናም ለነሱ እንዲህ ይባላቸዋል፡ 'እናንተ አምታቾች ሆይ! ማን እነዚህን ነገሮች ሐራም ናቸው አለ?! **<u>ሐራም የሆነው ቡድንተኝነት ነው! ሙስሊሞችን መለያየት! ጊዜያችሁን በልመና</u>***

---

[7] በስማቸው የምታወራ ወንድም ሆይ! አደጋ ላይ ነው ያለኸው ተመከር፡፡ የሚያወግዙበትን ፈትዋ እያጣቀስክ እራስህን አትሸውድ፡፡ የሚቃወሙት ምን አይነት ማህበራትን እንደሆነ በዚህም በሌሎቹም ፈትዋዎቻቸው ደግመው ደጋግመው ገልፀዋል፡፡

*ማጥፋት!!’ በረመዳን የሚደረገው ዑምራ በርግጥም ወደ ልመና* ***ተቀይሯል።*** *…”* [ዘምሙል መስአላህ፡ 218]

የሚከለክሉትን ነገር በጥሞና ያስተውሉት። ስለዚህ በጅምላ እንደማይከለክሉ የተናገሩባቸውን ከሚተቹባቸው ፈትዋዎቻቸው ጋር ስናገናዝብ የሚከለክሉት እንዲህ አይነት ችግሮች ያሉባቸውን ማህበራት ብቻ እንደሆነ እንረዳለን።

ሌላ ጊዜ ደግሞ *“የሆነ ሰው ‘የደዕዋ ማህበራት በነብዩ ﷺ ዘመን ቢያስፈልጉ እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ምክንያት ነበር። ከነሱ የሚያግድ ምክንያት አልነበረም። ስለዚህ ከነብዩ ﷺ በኋላ በነሱ መስራቱ ከመጤ ፈሊጦች ነው’ ቢል ይህ ንግግር ምን ያክል ትክክል ነው?”* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ነበር የመለሱት፡-

> *“… ያቀረበው ጥያቄ ጥሩ ጥያቄ ነው። ለዚህም ሲባል ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እኛ ‘ማህበራትን መተው ከመኖራቸው* ***<u>የተሻለ</u>*** *ነው’ እንላለን። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ እና ሶሐቦቻቸው ከኛ በበለጠ ገንዘብ ያስፈልጋቸው ነበር። እንዲያውም ከኛ እጅግ በበለጠ የሚያስፈልጋቸው ነበሩ። ይህ ከመሆኑ ጋር ግን ማህበር አልመሰረቱም። ከዚህም በመነሳት እነሱን (ማህበራትን) መተው ከመኖራቸው* ***<u>የተሻለ</u>*** *ነው። ከመመሪያ ሁሉ በላጩ የሙሐመድ ﷺ መመሪያ ነው። ማህበራት የቡድንተኝነት መንስኤ መሆናቸውን ስታስብማ ተወው። ‘ከኛ ጋር የሆነን እንረዳዋለን። ከኛ ጋር ያልሆነን ግን አንረዳውም።’ … እነዚህ ማህበራት የሙስሊሞችን ህበረት ለያይተዋል።… እነዚህ ማህበራት*

*የግድ ለማህበራዊ ጉዳዮች (መስሪያ ቤት) ተገዥ ይሆናሉ። ለሃገሪቱ ህጎች ተገዥ ናቸው። ከመንግስት ጋር የሚያያዘው ስራ በረከቱ የቀለለ ነው፣ ምናልባት በረካ ቢስ ካልሆነ።"* [አልጋረቱ ሽዲዳህ ዐላ ጀምዒየቲል ጀዲዳ፡ ካሴት]

ልብ ብለን ካስተዋልነው በዚህ ፈትዋቸውም ውስጥ ማህበርን እንደማይከለክሉ ጥቆማ አለ። እሱም *"ማህበራትን መተው ከመኖራቸው **<u>የተሻለ</u>** ነው"* ማለታቸው ነው። በሚገባ ያጢኑት።

በብዛት ከመተቸታቸውም ጋር ሸይኽ ሙቅቢል ድፍን አድርገው ማህበርን እንደማይከለክሉ ቀደም ብለን እንዳየነው በማያወላዳ መልኩ ይናገራሉ። ይህንንም ይበልጥ ግልፅ የሚያደርግልን *"ቡድንተኛ በሆኑ ባለ ማህበራት ላይ ሰላምታ ማድረስ ብይኑ ምንድን ነው?"* ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ ነው። እንዲህ ነበር ያሉት፡-

*"አዎ። **<u>በቡድንተኝነት መገደቡ ጥሩ ነው። እኛ ማህበራቱን እራሳቸውን እንደምንቃወም ያወራሉ። እውን ማህበራትን እራሳቸውን እንቃወማለን? ምን ማለት ነው ወንድሞቻችን ሆይ?! አዎ ምን ማለት ነው?!</u>** ወንድሞች ሆይ! **<u>እኛ ማህበራትን አንቃወምም!! ይሄ በአህሉ ሱና ላይ የሚፈፀም ቅጥፈት ነው።</u>** [8] አህሉ ሱና 'መስጂዶች አይገንቡ፣ የውሃ ጉድጓዶች አይቆፈሩ፣ የቲሞች አይረዱ' ይላሉ? ወንድሞች ሆይ! አህሉ ሱና ይህን አይሉም። <u>አህሉ ሱና 'እነዚህ ያቋቋማችኋቸው</u>*

---

[8] ማነው ዛሬ በሳቸው ስም እየቀጠፈ ያለው?! ትችታቸውን ብቻ እየገነጠሉ በማቅረብ *"የሙቅቢል አቋም ይሄ ነው"* በሚሉ ሰዎች የተሸወድክ ሁሉ ረጋ ብለህ አስተውል፡፡

*<u>ማህበራት ምንድን ናቸው ነው?’ የሚሉት። ቡድንተኞች ናቸው። ለዚህም በብዙ ማስረጃዎች ነው፣ ኢንሻአላህ (እነዚህን ማስረጃዎች) እናሰራጫቸዋለን</u>። …”* [ሐዚሂ ሱኑሪያ ፈሕዘሩሃ፣ ካሴት]

**<u>ለግንዛቤ</u>**

ሙቅቢል ማህበርን በጅምላ እንደሚከለክሉ የሚያወሩ ሰዎች በአህሉ ሱና ላይ የሚቀጥፉ እንደሆኑ እራሳቸው ሙቅቢል መናገራቸውን አሳልፈን። ዛሬ ደግሞ ጭራሽ *“ሸይኽ ሙቅቢል ማህበርን ከሚፈቅዱበት ፈትዋቸው ተመልሰዋል”* እያሉ የሚዋሹ መጥተውብናል። አላሁል ሙስተዓን!! ወንድሞቼ! ዲን በውሸት ይታገዛል እንዴ?! ብቻ፡-

**አንደኛ፡-** ያለ ግልፅ ማስረጃ በዚህ መልኩ ማውራት በቅጥፈት ላይ ቅጥፈት መጨመር ነው።

**ሁለተኛ፡-** ሸይኹ እራሳቸው በጅምላ እንደማይከለክሉ ይልቁንም ችግር ያለባቸውን ብቻ እንደሚቃወሙ ገልፀዋል።

**ሶስተኛ፡-** እንዲያውም *“ከባለ ማህበራት ጋር የሚለያያችሁ እራሱ የማህበር ጉዳይ ነው ወይስ ሌላ ምክንያት አለ”* ተብለው ሲጠየቁ *“በኛና በነሱ መካከል ያለው ልዩነት ማህበርን በማቋቋም ላይ አይደለም”* ይላሉ። ነብዩ ﷺ እና ሶሐቦቻቸው ከኛ ይበልጥ ገንዘብ የሚያስፈልጋቸው ሆነው ሳለ ነገር ግን ማህበር አላቋቋሙም። ስለሆነም መተው የተሻለ ነው ይላሉ። ግና እየተቃወሙ እንዳይመስልህ። **<u>ምክንያቱም ቀጥለው ሐራምነት ይቅርና መጠላት (ከራህነት) እንኳን እንደማይደርስ ነው በግልፅ የተናገሩት።</u>**

http://www.muqbel.net/fatwa.php?fatwa_id=1852

ሌሎችም ከባለማህበራት ጋር የሚለያቸው በውስጣቸው ያለው ችግር እንጂ ማህበር ማቋቋማቸው እንዳልሆነ የተናገሩባቸው ቦታዎች አሉ። ለምሳሌ *"አልሒክማ ማህበርን የምትተቹበት ሰበቡ ምንድን ነው? ማህበር ስላቋቋሙ ነው ወይስ በውስጡ ባሉ ነገሮች ነው?"* ተብለው ተጠይቀው ነበር። *"ጀምዒየተል ሒክማን የምንተችበት ምክንያቱ ቡድናዊነትን ስላካተተ ነው። እንጂ የውሃ ጉድጓዶችን መቆፈር፣ መስጂዶችን መገንባት፣ አይታሞችን መደጎምና ሌላም መሰል ስራዎች ይሄ እንከን የማይወጣለት ስራ ነው"* እያሉ ነው የመለሱት። http://www.muqbel.net/fatwa.php?fatwa_id=1365

## 18. ሸይኽ ዘይድ ቢን ሙሐመድ አልመድኸሊ ረሒመሁላህ

ጥያቄ፡- *"ማህበራትን ማቋቋም ከሰለፎቻችን መንገድ ነውን?"*

መልስ፡-

**الجمعيات في الدّولة المسلمة يجوز تأسيسها للمصالح الدينية والدنيوية؛ ولكن يجب أن تكون منضبطة بشروطٍ يُقرّها الإسلام، ولا يكون الغرض من الجمعيات أهدافًا سيئة؛ فتصبح ضررً على الإسلام والمسلمين؛ كمثل ما فعله الخوارج: جعلوا جمعيات، وجمعوا الأموال، واستعانوا بها على قتال المسلمين والمسلمات، وتخريب المنشئات، وشقِّ عصا الطاعة، فالجمعيات تصح؛ ولكن ينظر إلى أهدافها: فإن كانت أهدافها صالحةً ومَن قاموا بها كذلك صالحين –لهم نوايا حسنة– فهذا عمل مبرور وعمل صحيح، وإن كانت الأهداف سيئة ومَن قاموا عليها مِن أهل الشغَب، ومِن أهل المخالفة لعقيدة الإسلام والمسلمين فلا خير فيها ولا خير فيهم.**

*“**ማህበራት፣ በሙስሊም ሀገር ውስጥ ለሃይማኖታዊም ለአለማዊም ጥቅሞች ሲባል መመስረት ይፈቀዳል።** ነገር ግን ኢስላም በሚያፀድቃቸው መስፈርቶች የተገደቡ ሊሆኑ ይገባል። **እንጂ የሚመሰረቱበት አላማ መጥፎ አላማዎችን ያነገበ መሆን የለበትም።** ያለበለዚያ በኢስላምም በሙስሊሞችም ላይ ጉዳትን ያስከትላል። ልክ ኸዋሪጆች እንዳደረጉት ማለት ነው። ማህበራትን አቋቋሙ። ገንዘቦችን ሰበሰቡና ሙስሊሞችን ለመዋጋት፣ ተቋማትን ለማፍረስ፣ ለመሪዎች ታዛዥነትን ለመሰንጠቅ ታገዙባቸው።*

***ስለዚህ ማህበራት ይፈቀዳሉ።** ነገር ግን **አላማቸው ሊታይ ይገባል። አላማቸው በጎ ከሆነና አንቀሳቃሾቹም በጎ እሳቤ ያላቸው ደጎች ከሆኑ ይሄ በጎ ስራ ነው፣ መልካም ተግባር።** አላማዎቹ መጥፎ፣ ሀላፊዎቹም በጥባጮችና የኢስላምን እና የሙስሊሞችን ዐቂዳ የሚፃረሩ ከሆኑ ግን (ማህበሩም) ኸይር የለውም። እነሱም ኸይር የላቸውም።”*
https://www.youtube.com/watch?v=Fqht66VxNrk

ማህበር መመስረት እንደሚቋቋምበት አላማ ሊወሰን እንደሚችልና በጎ ነገር ከታሰበበት የሚበረታታ እንደሆነ ንግግራቸው ያስረዳል። ኢስላም በሚያፀድቃቸው መስፈርቶች የተገደቡ ሊሆኑ እንደሚገባ ቢገልፁም *“የሚመሰረቱበት አላማ መጥፎ ግቦችን ያነገበ መሆን የለበትም”* ከማለታቸው ውጭ የጠቀሱት መስፈርት የለም።

### 19. ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ዐብዲላህ አሱበዪል፡-

ሸይኹ የሰዑዲያህ ታላላቅ ዑለማዎች ምክር ቤት አባል፣ የመስጂደል ሐራም ኢማምና ኸጢብ ነበሩ፣ ረሒመሁላህ።

<u>**ሸይኹ የአንድ ማህበር ሊቀ-መንበር ነበሩ**</u>!!! “ጀምዒቱል ኸይሪያህ ሊሙሳዐደቲ ሸባብ ዐለዘዋጅ ቢመከተል ሙከረማህ” የተሰኘ ማህበር። (“በተከበረችው መካህ ወጣቶችን በትዳር ላይ የሚያግዝ የበጎ አድራጎት ማህበር።”) እንዲያውም የዚህ ማህበር አዲስ የጠቅላላ ጉባኤ <u>**ምርጫ**</u> ሲካሄድ ነው ሸይኹ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆነው የተመረጡት።

## 20. ሸይኽ ሷሊሕ አሉሐይዳን

*“ሸሪዐዊ ተቋማትና ሌሎችንም የሚያቅፍ የበጎ አድራጎት ማህበራት መመስረትን በተመለከተ ከፊሉ … ‘እነዚህ በሙስሊም ሃገራት ውስጥ ዛሬ የሚቋቋሙ ሸሪዐዊ ተቋማት ፖለቲካዊ ዝንባሌ አላቸው’… መሰል ነገሮችን ይላል”* የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ይሄውና መልሳቸው፡-

**الأعمال بالنيات فإذا اجتمع ناس وأسسوا مؤسسة لتعليم القرآن الكريم أو تعليم أحكام العبادات ليحضوا الناس على الأعمال وكانت نيتهم أن ينفعوا الناس بهذا العمل فهذا لاشك أنه من الجهد المبارك، وعن النبي ﷺ ذكر أن ابن آدم اذا مات انقطع عمله إلا من ثلاثة ..."أو علم ينتفع به" فهذه المؤسسات العلميه إذا دخلتها النية وأنشأت لا للأرباح وإنما للمصالح: كتثقيف المجتمع ثقافة إسلاميه شرعية فإنه يكون داخلا في هذا العمل الذي يستمر المؤسسون له بعد موتهم يعود إليهم عائد كبير ... ينبغي للانسان أن لا يلتمس أمورا يدعيها بدعا وهي ليس لها مجال في الابتداع والله أعلم.**

***“ስራዎች የሚለኩት በእሳቤዎቹ (በኒያዎቹ) ነው። የሆኑ ሰዎች ተሰባስበው የተከበረውን ቁርኣን ለማስተማር ወይም የዒባዳዎችን ህግጋት ለማስተማር ወይም ሰዎችን ለመልካም ስራዎች ለማነሳሳት***

***ተቋም ቢመሰርቱ ኒያቸው በዚህ ተግባር ሰዎችን መጥቀም ከሆነ ይሄ ያለጥርጥር ከተባረኩ ጥረቶች ውስጥ ነው።*** *ከነብዩ ﷺ እንደተገኘው የሰው ልጅ ሲሞት ጊዜ ከሶስት አይነት ሰዎች ሲቀር ስራው ይቋረጣል። ከነዚህም የጠቀሱት "ወይም የሚጣቀሙበት የሆነ እውቀትን ጥሎ ያለፈ ነው።" እናም* ***<u>እነዚህ የእውቀት ተቋማት ጥሩ ኒያ ከታከለባቸውና ለትርፍ ሳይሆን ልክ ህብረተሰብን ኢስላማዊ ሸሪዐዊ በሆነ እውቀት ማስታጠቅ አይነት ለመልካም ስራዎች ከተመሰረቱ ይሄ መስራቾቹ ከሞቱ በኋላ ምንዳው ከሚቀጥልላቸው ስራ ውስጥ የሚካተት ነው። ትልቅ የሆነም ተከታይ (ምንዳ) ይከተላቸዋል።… ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው ምንም አይነት የቢድዐነት ቦታው በሌለበት ነገሮችን 'ቢድዐ ናቸው' እያለ ከመሞገት ሊታቀብ ይገባል።</u>*** *አላህ ነው አዋቂው።"* [ሸርሑ ኪታቢ አተውሒድ፡ 15ኛ መጅሊስ]

**ጥቂት ነጥቦች**

- ጥሩ ኒያ እስከታሰበበት ድረስ ማህበር መመስረት እንደሚፈቀድ፣
- እንዲያውም ከሶደቀቱን ጃሪያ (ቀጣይነት ካለው ሶደቃ) እንደሚቆጠር፣
- ጉዳዩ ከቢድዐ ጋር እንደማይገናኝ፣
- ይህንን ጉዳይ በቢድዐ የሚገልፅ ሰው ሊታቀብ እንደሚገባው ከንግግራቸው እንረዳለን።

## 21. ሸይኽ ዑበይድ አልጃቢሪ [9]

[9] እዚህ ላይ በተለይ ሸይኽ ዑበይድን ማጣቀሴ ለአንዳንድ ወንድሞች ዋጋ እንደሌለው አውቃለሁ፡፡ ሆኖም ግን እንደነ ሸይኽ አሕመድ አነጅሚ፣ ረቢዕ አልመድኸሊ፣ ሱለይማን

**من المغرب يقول السائل :**

**نحتاج في بلدنا يا شيخ إلى تأسيس جمعية هدفها الدعوة إلى الكتاب والسنة على فهم سلف الأمة مع الارتباط في كل صغيرةٍ وكبيرةٍ مع مشايخنا السلفيين الكرام مع البعد عن التحزب المذموم، ذلك أن في بلدِنا لا يسمح لنا بالاجتماعات وعقد الدروس والمحاضرات وتدريس أبنائنا في معاهد بعيدة عن الاختلاط إلا تحت مظلة تأسيس جمعية، فنرجو من فضيلتكم بيان جواز ذلك وهل من شروطٍ في ذلك؟ ولكم جزيل الشكر بعد الله .**

**فأجاب حفظه الله:**

---

አኑሐይሊ፣ ሷሊሕ አሱሐይሚ፣ ሙሐመድ ዑመር ባዝሙል፣ ሌሎች ዑለማዎች ዘንድ ሸይኽ ዑበይድ የተከበሩ ዓሊም እንደሆኑ ይታወስ፡፡ ሸይኽ ረቢዕም *“ስለ ሸይኽ ዑበይድ አልጃቢሪ ምን አስተያየት አለዎት? እውን እሳቸው ተማሪ እንጂ ዐሊም አይደሉምን?”* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡

> ***“ወላሂ! እሱን በነገር የሚወጋና ‘ጃሂል ነው’ የሚል ሰው ይሄ የሸይጧኖችን መንገድ ነው እየተከተለ ያለው!! በሰለፍያ መንገድ ላይ ያሉ ዑለማዎችን በመንቆርም የቡድንተኝነት መንገዶችን ነው እየተከተለ ያለው፡፡*** *ሸይኽ ዑበይድ በጥንቃቄ፣ በዙህድና ሐቅን በመናገር የታወቁ ከሆኑ የተከበሩ የሰለፍያ ዑለማዎች ውስጥ ነው፡፡ ባረከላሁ ፊኩም!!* ***የአላህን ተባረከ ወተዓላ ፊት የሚሻ ሰው እሱን አያንቋሽሽም፡፡ እንዲህ አይነት (የሰለፍያ ዑለማን የማንቋሸሽ) ዘዴዎችን ከሒዝቢዮች (ቡድንተኞች) ነው የምናውቃቸው፡፡”***

በማህበራት ላይ የሰነዘሩትን ትችት ለመጠቀም ሲፈልጉ የሚያጣቅሷቸው ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ሃዲም ልክ እንዲሁ ከሸይኽ ዑበይድ አጥብቀው ይከላከላሉ፡፡

**أولاً: يجب على من يسعى في تأسيس هذه الجمعية _ جمعية الدعوة _ أن يكون على سنة وإن لم يكن عالماً لكن يكون على سنة ويستطيع التمييز بين البدعة والسنة .**
**ثانياً: يجب عليه أن يكون على اتصالٍ بعلماء السنة في القُطر وخارجه حتى يستشيرهم في المنهج الذي تسيروا عليه .**
**ثالثا: إذن ولي الأمر بها والله أعلم.**

**ጠያቂ ከሞሮኮ እንዲህ ይላል፡-**

*"ሸይኽ ሆይ! በሀገራችን በመልካም ቀደምቶች ግንዛቤ ቁርኣንና ሱናን የማስተማር አላማ ያነገበ ማህበር መመስረት እንፈልጋለን። በትንሽ በትልቁ ከተከበሩ የሰለፊያህ ዑለማዎች ጋር ትስስር ከማድረግ ጋርና ከተወገዘ ቡድንተኝነት ከመራቅ ጋር ነው። __ይህን የፈለግንበትም ምክንያት በሀገራችን በማህበር ጥላ ስር ካልሆነ በስተቀር ዲናዊ ስብሰባዎችን፣ ትምህርቶችን፣ ሙሓዶራዎችን እንዲሁም ከቅልቅል በራቀ መልኩ ልጆቻችንን ማስተማር ስለማይፈቀድ ነው።__ እናም ከክቡርነትዎ ይህ ነገር የሚፈቀድ መሆኑን እንዲገልፁልን እንከጅላለን። መስፈርቶችስ ይኖሩታልን? ከአላህ በመቀጠል የላቀ ምስጋናችንን እንገልፃለን።"*

**መልስ፡-**

*"**በቅድሚያ፡** ይህን ማህበር፣ የደዕዋ ማህበር- ለመመስረት የሚጥረው አካል ሱና ላይ ሊሆን የግድ ይላል። **ዐሊም እንኳን ባይሆን ቢድዐንና ሱናን መለየት የሚችል፣ ሱና ላይ መሆን አለበት።***

***ሁለተኛ፡-*** *በምትጓዙበት መንገድ ላይ ያማከራቸው ዘንድ በሀገሩም ይሁን በውጭ ካሉ ዑለማዎች ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይገባል።*

***ሶስተኛ፡-*** *የሀገሪቱ መሪ ፈቃድ መኖር አለበት። ይበልጥ የሚያውቀው አላህ ነው።"*

**ሌላ ጥያቄ፡-**

**يقول السائل من المغرب :**

**يقول: بارك الله فيكم شيخنا عندنا في بلادنا المغرب المسئولون ولله الحمد يُعطون للسلفيين تصاريح إنشاء جمعيات هدفها تدريس طلاب العلم ونشر الدعوة السلفية ويُسميها الإخوة عندنا غالباً دور القرآن أو دور قرآن وعدد هذه الجمعيات شيخنا بدأ يزداد فما نصيحتكم لنا بخصوصها خاصةً أن الإخوة في كل مدينة تقريباً يفكرون في إنشاء جمعيةٍ خاصةٍ بهم؟**

**فأجاب: إذا كانت هذه الجمعيات تعنى بتدريس الكتاب والسنة وعلى فهم السلف الصالح فلا مانع منها إن شاء الله فهي بمثابة مدارس أو مراكز دعوة للسنة ولكن يشترط ألا ينعقد عليها لذاتها ولاء ولا براء، فلا يقال هذا من جمعية كذا فلا يأتي إلينا وهذا من جمعية البلدة الفلانية فلا يأتينا، وكذلك لا يعاقب من يتخلف عن الدروس نعم الموظفون الذين وكِل إليهم تنظيم أعمال هذه الجماعة أو هذه الجمعية هؤلاء يربطون بدوام يحدده رئيس الجمعية**

አሁንም ከሞሮኮ ጠያቂው እንዲህ ይላል፡-

*"አላህ ይባርክዎትና እኛ ዘንድ በሃገረ ሞሮኮ ምስጋና ለአላህ ይሁንና ባለስልጣኖች ለሰለፊዮች ተማሪዎችን የማስተማር፣ የሰለፍያ ደዕዋን የማሰራጨት አላማ ያነገቡ ማህበራትን ለመመስረት ፍቃድ ይሰጣሉ። እኛጋ ያሉ ወንድሞች "የቁርኣን ግቢዎች" ሲሉ ይጠሯቸዋል። ሸይኻችን ሆይ! የነዚህ ማህበራት ቁጥር እየጨመረ ነው። እነሱን በተመለከተ ምን ይመክሩናል? በተለይ ደግሞ በሁሉም ከተሞች በሚያስብል መልኩ ሁሉም ለየከተማው ማህበር የመመስረት ሀሳብ ላይ ነው ያሉት።"*

**መልስ፡-**

***"እነዚህ ማህበራት ቁርአንና ሱናን በመልካም ቀደምቶች ግንዛቤ መሰረት በማስተማር ላይ የሚያተኩሩ ከሆነ ኢን ሻአላህ ከነሱ የሚከለክል ነገር የለም። ምክንያቱም በመድረሳዎች ወይም በሱና መርከዞች ደረጃ ናቸውና።*** *ባይሆን እነሱን (ማህበራቱን) ያማከለ መወዳጀትና መጣላላት ሊኖር አይገባም። ስለሆነም 'ይሄ ከእከሌ ማህበር ስለሆነ ወደኛ እንዳይመጣ። ይሄ ደግሞ ከእከሌ መንደር ማህበር ስለሆነ እንዳይመጣብን' እንዳይባል። ልክ እንዲሁ ከትምህርቶች ስለቀረ መቅጣት እንዳይኖር። አዎ የዚህ ስብስብ ወይም ማህበር ስራዎችን በማደራጀት ላይ የተወከሉት ሰራተኞች የማህበሩ ሀላፊ በሚያስቀምጠው ደንብ ሊገደቡ ይገባል።"*

http://www.sahab.net/forums/?showtopic=130343

**ንግግራቸው ሲጨመቅ**

- ማህበርን በመስፈርት እንደፈቀዱ፣
- መስፈርቶቹ አንዳንዶች እንደሚያስቡት የማይደረስባቸውና ጭራሽ የማይሟሉ አይነት እንዳልሆኑ፣

- ማህበራት በሱና መርከዞች ደረጃ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል።

**22. ሸይኽ ሱለይማን አሩሐይሊ**

*"ጥፋቶችን መከላከል ጥቅሞችን ከማምጣት ይቀደማል"* የሚለውን የፊቅህ መርህ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ፡-

*"ልክ እንዲሁ ለኔ እንደሚገባኝ ወላሁ አዕለም ከዚህ መርህ ምሳሌዎች አንዱ <u>ደዕዋዊ የእውቀት ማህበራትን</u> መመስረት ነው። ስራን ከማቀናጀት አንፃር ጥቅም አላቸው። **<u>በዚህም ሳቢያ ብዙዎቹ ምሁራን እንደሚፈቀዱ ገልፀዋል።</u>** ይሁን እንጂ የሚከተሏቸው ብዙ ጥፋቶች አሉ። እናም መጨረሻቸው በጣም መሪር ነው። ስለዚህ (ትክክለኛው) '**<u>አስገዳጅ ሁኔታ ካልኖረ በስተቀር</u>** ማህበራትን መመስረት አይፈቀድም' የሚለው አቋም ነው። ምክንያቱም ጥፋቶችን መከላከል ጥቅሞችን ከማምጣት ተቀዳሚ ነውና።*

***<u>ሰዎችን በመርዳት ላይ የሚሰማሩ የበጎ አድራጎት ማህበራትን፣ ግብረ-ሰናይ ተቋማትን በተመለከተ ግን እነዚህ ያለጥርጥር የተፈቀዱ ናቸው። ምክንያቱም ጥቅሞቻቸው ከጉዳቶቻቸው (ምናልባት ከኖራቸው) የላቁ ስለሆኑ ነው።</u>"*** [ሸርሑ ሪሳለቲ አሰዕዲ ፊ ኡሱሊ አልፊቅህ 5ኛ ካሴት 35ኛ ደቂቃ]

**ከሸይኹ ንግግር፡-**

- **<u>ለደዕዋ አላማ</u>** የሚቋቋሙ ማህበራት ጥቅምም ጉዳትም እንዳላቸው፣
- **<u>ብዙሃኑ</u>** ዑለማእ ዘንድ የተፈቀዱ እንደሆኑ፣

- እሳቸው ዘንድ ግን ጉዳታቸው ስለሚያደላ እንደማይፈቀዱ፣
- <u>**አስገዳጅ ሁኔታ ካለ ግን**</u> እሳቸውም ዘንድ እንደሚፈቀዱ፣
- <u>**በእርዳታ ላይ የሚሰማሩ ማህበሮች**</u> ግን <u>**ያለጥርጥር**</u> እንደሚፈቀዱ እንረዳለን።

**23. ሸይኽ ሙሐመድ ዐሊ ፈርኩስ**

**ጥያቄ፡-**

*"በሰለፎች ግንዛቤ መሰረት ወደ ቁርኣንና ሱና ለመጣራት እንዲሁም ትክክለኛውን ዐቂዳ ለመጠበቅ ያለመ ማህበር መመስረት ብይኑ ምንድን ነው? <u>**ከግንዛቤ እንዲገባ የምንፈልገው ለርሶ ሀገር ጎረቤት በሆነችዋ ሃገራችን ለደዕዋ ወይም ለእውቀት ፍለጋ መሰባሰብ አይፈቀድም።**</u> ብይኑን ይስጡን አላህ ይባርክዎትና።"*

**መልስ፡-**

የቡድንተኝነት በሽታ ያለበትን መሰባሰብ ኢስላማዊ ስያሜን ቢላበስ እንኳን የማይፈቀድ እንደሆነ ከገለፁ በኋላ እንዲህ ይላሉ፡-

**وإذا كان التجمُّع الحزبيُّ لا يجوز فإنّه لا يمنع من التعاون الشرعي الأخوي المبني على البرِّ والتقوى والمنضبط بالكتاب والسُّنَّة، لقوله تعالى: ﴿وَتَعَاوَنُواْ عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى وَلاَ تَعَاوَنُواْ عَلَى الإِثْمِ وَالعُدْوَانِ﴾، كما يدخل ضمن عموم الأمر بالتعاون الشرعي ما يقوم به الحاكم من تنظيم المسلمين في شكل هيئاتٍ رسميةٍ كالوزارات والمؤسَّسات التي لا تحمل الطابعَ الحزبيَّ ليوزِّع عليهم مهامًّا وأعمالاً،**

**تخصُّ الحياةَ الدينيةَ والدنيويةَ، فلا تتناوله النصوصُ التي تَذُمُّ الخروجَ عن وحدة الأُمَّة التي أمر بها أن تكون واحدة، فقال تعالى: ﴿وَإِنَّ هَذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَأَنَا رَبُّكُمْ فَاتَّقُونِ﴾. وعليه، فإنّ مجالَ التعاونِ الأخويِّ المنضبطِ بالشرعِ المبني على البرِّ والتقوى مشروعٌ ومطلوبٌ. والعلمُ عند اللهِ تعالى،**

*"ቡድናዊ የሆነው መሰባሰብ የማይፈቀድ እንደሆነ ካየን መልካም ስራንና አላህን መፍራት ላይ የተገነባው በቁርኣንና በሱና የተገደበው ሸሪዐዊ የሆነው የወንድማማችነት ትብብር ግን አይከለከልም። ምክንያቱም የላቀው ጌታ 'በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ። ግን በወንጀልና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ' ብሏልና። በዚህ በሸሪዐዊ ትብብር በሚያዘው ጥቅል መልእክት ውስጥ መሪው ሙስሊሞችን የሚያደራጅበት ቡድናዊ ገፅታ የማይሸከሙ የተለያዩ ሃላፊነቶችንና ተግባራትን የሚያከፋፍልበት እምነታዊም ይሁን ዱንያዊ ህይወትን የሚመለከቱ እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት ያሉ ኦፊሴላዊ ድርጅቶች ይካተታሉ። እንዲህ አይነቱን አካሄድ የሙስሊሙ ህዝብ አንድ እንዲሆን የታዘዘበትን አንድነት የሚሰነጥቁ ድርጊቶችን የሚያወግዙት ማስረጃዎች አይመለከተውም። የላቀው ጌታ እንዲህ ይላል፡- 'ይህችም አንድ መንገድ ስትሆን ሃይማኖታችሁ ናት። እኔም ጌታችሁ ነኝና ፍሩኝ።' ስለሆነም **<u>በመልካም ነገርና አላህን በመፍራት ላይ የተገነባውና በሸሪዐ ልጓም የተያዘው ወንድማዊ የትብብር ዘርፍ የተፈቀደና የሚፈለግ ነው።</u>** እውቀቱ ያለው የላቀው አላህ ዘንድ ነው። …"* http://www.ferkous.com/rep/Bb24.php

**24. ሸይኽ ሷሊሕ ኢብኑ ዐብዲል ዐዚዝ ኣሊ ሸይኽ**

(የሰዑዲያህ የኢስላማዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር)

- በቁርኣን ተሕፊዝ ላይ የተሰማሩ ማህበራት ከፍተኛ ምክር ቤት ሊቀመንበር፣
- የመልካም ጥሪ ተቋም (ሙአሰሰቱ አደዕወቱል ኸይሪያ) ሊቀመንበር፣
- የአለም ሙስሊም ወጣቶች ሊግ ሊቀመንበር፣
- አለም አቀፍ ኢስላማዊ ደዕዋና እርዳታ ቢሮ አባል፣
- የአካል ጉዳተኛ ህፃናት እርዳታ ኮሚቴ ሊቀመንበር ናቸው። http://www.saleh.af.org.sa/node/14

## 25. ሸይኽ ሷሊሕ ኢብኑ ሰዕድ አሱሐይሚ

*"አልጀምዒየቱል ኸይሪያህ ሊተሕፊዚ አልቁርኣኒል ከሪም ቢመንጢቀቲል መዲነቲል ሙነወራ"* የተሰኘ ማህበር ውስጥ አባል ናቸው። http://www.quranm.org.sa/index_ar.php?op=emp

*"አልጀምዒየቱል ዒልሚያ አሰዑዲያ ሊ ዑሉሚል ዐቂዳ ወልአድያን ወልፊረቅ ወልመዛሂብ"* በተሰኘ ማህበር ውስጥ ደግሞ የአስተዳደር ምክር ቤት አባል ናቸው። http://aqeeda.org/container.php?fun=manager

በተጨማሪም ማህበር ውስጥ እየተገኙ ደዕዋ ሲያደርጉ ነበር። በ 8/6/1434 ዓ.ሂ. ሞሮኮ ውስጥ በተደረገ ደዕዋ ላይ ማህበር ስለመመስረት ተጠይቀው የተወሰኑ መስፈርቶችን አስቀምጠው ዲናዊ ማህበር መመስረትን

ፈቅደዋል። **በቅድሚያ በጀማዐዎች መብዛትና ማህበርን በመመስረት መካከል እንደሚለዩ ተናግረዋል።** [10] የጠቀሷቸው መስፈርቶችም የሚከተሉት ናቸው፡-

- የምስረታው አላማ ከሙስሊሞች ህብረት የተገነጠለ ቡድን መመስረት ላይሆን፣ ማለትም የቡድናዊነት ገፅታ ላይኖረው፣
- ከአህሉ ሱና ወልጀማዐ ውጭ ወዳለ መንገድ ላይጣራ፣
- *"በእከሌ ማህበር ስር ያልታቀፈ ከኛ አይደለም"* በሚል ለሙስሊሞች መለያየት መንሰኤ ላይሆን፣
- ህብረተሰቡ ማህበሩን መመስረቱ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፣
- ምስጢራዊ ገፅታ ላይኖረው፣
- መሪዎቹ ድንበር ማለፍ የሌለባቸው የሱና ሰዎች ሊሆኑ፣
- ማንም ቢሆን በማህበሩ ውስጥ መሪነትን ላያስብ፣

እነዚህን መስፈርቶች አስቀምጠው ማህበር መመስረትን ፈቅደዋል። https://www.youtube.com/watch?v=lsh1pjFZz4Q

መስፈርቶቹን በእርጋታ ያስተውሏቸው!! አንዳንዶች ጉዳዩን በጠንካራ ቁልፍ ለመከርቸም ካላቸው ጥማት በመነሳት ብቻ መስፈርቶቹን ፈፅሞ የማይደፈሩና መቼም የማይሟሉ አድርጎ ለመሳል የሚጥሩት ልፋት ውሃ የሚያነሳ እንዳልሆነ ማስተዋል ይቻላል። ትምህርቱ የተሰጠው የሸሪዐ ህግ በሌለበት ሀገር ውስጥ በሚገኝ ማህበር ውስጥ እንደሆነ ይስተዋል።

---

[10] ምናልባት ካስተዋሉ "ጀምዒይ" እያሉ ልክ "ማህበር" የሚባል ቡድን እንዳለ እያስመሰሉ ለሚዘልፉ ሰዎች ጥሩ ጥቆማ ነው፡፡

አሁንም ሞሮኮ ላይ ስለ ማህበር ሲጠየቁ ዘለግ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል። የሚከተሉትን መስፈርቶችም ገልፀዋል፡-

- ከምስጢራዊ ቡድናዊ ቃል ኪዳን ነፃ ሊሆን፣
- ከቡድናዊ ወዳጅነት ነፃ ሊሆን፣
- ሰዎችን ለማካተት በማለም ልክ ብዙ የሂዝቢያ ማህበራት እንደሚያደርጉት አይነት ሽሪዐን ከሚፃረር ነገር ነፃ መሆን፣
- አላማው ነገሮችን በስርኣት ለማስኬድ ብቻ ሊሆን፣
- መርዳት ከሚፈልጉ አካላት በተለይም ቡድናዊ ዝንባሌ ካላቸው አካላት ገደቦች ላይቀመጡ፣

እነዚህ ገደቦች ከተከበሩ በፍፁም ማህበርን እንደማይከለክሉ ተናግረዋል። ለዚህም የራሳቸውን መዲና ውስጥ በሚገኘው የቁርኣን ተሕፊዝ ማህበር አባል መሆን፣ እንዲሁም በሌሎችም ማህበር በሚመስሉ ኮሚቴዎች ውስጥ አባል መሆናቸውን እንደማጠናከሪያ አውስተዋል። በአንዳንድ በተለይም ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት ውስጥ ከማህበር ጥላ ስር ካልሆነ በስተቀር የደዕዋ እንቅስቃሴ እንደማይፈቀድም ገልፀዋል። በቡድንተኞችና በሰለፍዮች በሚከፈቱ ማህበራት መካከል የሚኖረው ልዩነትም በነዚህ መስፈርቶች ሰበብ እንደሆነ የጠቆሙ ሲሆን የማህበርን ጉዳይ ምክንያት አድርገው እንዳይለያዩም መክረዋል። አንዳንድ ወንድሞች “ማህበር” የሚለውን ቃል እንዲፈሩ ያደረጋቸው በአንዳንድ ሙስሊም ሃገራት ቡድናዊነትን ወይም ገንዘብ-ተኮር የሆነን አነሳስ የተነሱ ማህበራት በመኖራቸው ሰበብ እንደሆነ ከገለፁ በኋላ መስፈርት እስከተጠበቀ ድረስ ምንም መጨናነቅ እንደማይገባ አስረግጠው ተናግረዋል። ገደቦች እስከተጠበቁ ድረስ በሁሉም ከተሞች እንዲኖር የሚፈልጉት እንደሆነ ገልፀዋል። በመጨረሻም **<u>እሳቸው አባል</u>**

<u>በሆኑበት ማህበር ውስጥ ከ 25 አመታት በፊት ጀምሮ አባል ሆነው እንደተመረጡና ከአንዳንድ ሃብታሞችና በጎ አድራጊዎች ዘንድ በመዞር ገንዘብ ያሰባስቡ እንደነበር ገልፀዋል።</u> ኋላ ላይ ግን ወቅፍ ስለተገኘ በአሁኑ ሰዓት ማህበሩ ሌሎች በቁርኣን ተሕፊዝ ላይ የተሰማሩ ማህበራትን እየረዳ እንደሆነ በመግለፅ <u>ገደቦች እስከተጠበቁ ድረስ አንዳንዶች ስለሚያናፍሱት ነገር ቦታ መስጠት እንደማይገባ ገልፀዋል።</u>

https://www.youtube.com/watch?v=u3YHmFXMJn4

### 26. ሸይኽ ዐብዱረሕማን ሙሕዩዲን

ካይሮ ውስጥ የሚገኘውን የአህሉል ሐዲሥ ወልአሥር ማህበር እያደነቁ ተናግረዋል። ምናልባት አንዳንዶቻችን ማህበርን ማድነቅና የማህበር ዝግጅት ላይ ተገኝቶ ደዕዋ ማድረግ ተራ ነገር ሊመስለን ይችላል። እነዚህ በማህበር ምክንያት አቧራ እያስነሱ ያሉ ወንድሞቻችን ዘንድ ግን ጉዳዩ ቀላል ነገር አይደለም። በዚህ ሳቢያ ዑለማዎችን እስከመወረፍ እንደደረሱ ይታወቅ።

### 27. ሸይኽ ሙሐመድ ሰዒድ ረስላን

ሸይኹ በታሪክ "ሒልፈል ፉዱል" ወይም "ሒለፈል ሙጠይዪቢን" የሚባሉትን ቁረይሾች ከተበዳይ ወገን ለመሆን ቃል ኪዳን የተጋቡበትን ትብብር ዛሬ ላይ ያሉ ኢስላም-ዘመም የፖለቲካ ፓርቲዎች መረጃ ሊያደርጉ መሞከራቸው ልክ እንዳልሆነ ሲያወሱ እንዲህ ይላሉ፡-

*"ይሄን የሚተካው በአንዳንድ ኢስላማዊ ህዝቦች ዘንድ የሚገኙ የበጎ አድራጎት ማህበራት ናቸው። እነሱ ከስር አመሰራረታቸው ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት የለውም። ፖለቲካን አያካትቱም። ፖለቲካ ላይ*

*እንዲሳተፉም አይፈቀድላቸውም። የኢኸዋን አልሙስሊሚን ማህበር ከመነሻው ሲመሰረት የበጎ አድራጎት ማህበር ነበር፣ ልክ እንደማንኛውም የበጎ አድራጎት ማህበር። ፖለቲካ ውስጥ በመግባታቸው ምክንያት በነሱ ብዙ የተሳሳቱ ነገሮች ተፈፀሙ። ይገድላሉ፣ ሽብርና ፍንዳታ ላይ ይሳተፋሉ። የበጎ አድራጎት ማህበርን በመጠቀም ለስልጣን የቋመጡ ነበሩ። በዚህም ሳቢያ ማህበሩ ተበተነ።*

*ልክ እንዲሁ ሁሉም የበጎ አድራጎት ማህበርም ከሱ ጋር ለስራ ስምምነት የሚደረገው ለህዝባዊ ግልጋሎት ሲባል ብቻ ነው። እነዚያን ግልጋሎቶች ወደ ህብረተሰቡ ለማድረስ ሲባል። እንጂ ፖለቲካ ላይ ለመሳተፍ አይደለም። ይሄ በበጎ አድራጎት ማህበራት መቋቋም፣ ምስረታና አወቃቀር ህጉ የተከለከለ ነው። ይሄ ከዚያኛው (ከፖለቲካ ቡድኖች) ጋር አይነፃፀርም። የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከበጎ አድራጎት ማህበራት ጋር የሚያነፃፅር ከጭንቅላቱ የሚወጣውን አያውቅም። ‘ለምንድን ነው የበጎ አድራጎት ማህበራት ላይ ሳትናገሩ ፓርቲዎች ግን አይፈቀዱም የምትሉት?’ ይላል። ይሄኛው እንደዚያኛው አይደለም በፍፁም። ይሄ አንድ ነገር ነው።*

*ሁለተኛው ነጥብ ፓርቲዎች ህብረተሰቡን ልዩነት ነው የሚጨምሩት። ይበጫጭቁታል። ...*

*የበጎ አድራጎት ተቋማት ግን ከዚህ ውስጥ ጭራሽ አይገቡም። ወደዚህ አይደርሱም፣ ጣልቃም አይገቡም። እነዚህ ፓርቲዎች ግን የሚበላሉ እንጂ ለመልካም የሚሽቀዳደሙ አይደሉም። ይልቅ አገዛዝ ላይ ለመድረስ የሚሽቀዳደሙ ናቸው። እያንዳንዱ ፓርቲ ይህን ነው*

*የሚፈልገው። ጫፍ ላይ የሚገዛቸው ህግ የበጎ አድራጎት ማህበራትን የሚገዛው አይደለም። የበጎ አድራጎት ማህበራትን የሚገዛው ህግ የአላህን ተባረከ ወተዓላ ሸሪዐህ መቃረን የለውም። ይልቁንም እነዚህ ሰዎች በሚሰጣቸው ገደብ ወይም እራሳቸው በሚያስቀምጡት ገደብ የታወቀ አገልግሎት እንዲያገለግሉ ነው የሚፈቀድላቸው። ከተወሰነ አካል ቁጥጥር እየተደረገባቸው ማለት ነው። ፓርቲዎች ግን ለፓርቲዎች ህግ ይገዛሉ። የፓርቲዎች ህግ ደግሞ ሃይማኖትን ከፖለቲካ ንክኪ ጥብቅ የሆነ ክልከላን ይከለክላል። የትኛውም ሃይማኖትን እንደ መዳረሻ የተጠቀመ ወይም ደግሞ ሃይማኖታዊ መፈክር ይዞ የተነሳ ፓርቲ የፓርቲዎችን ጉዳይ በሚይዘው ኮሚቴ ከፓርቲዎች ይሰረዛል። የበጎ አድራጎት ማህበራት ግን እንደዚህ አይደሉም። ከተግባሮቻቸው ውስጥ በህግ አጥር ውስጥ ሆነው በሚሰማሩበት ዘርፍ ሃይማኖታዊ ንቃተ-ህሊናን ከፍ ያደርጋሉ። ሃይማኖትን መፈክር አድርገው አይዙም። ይልቁንም ሃይማኖታዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው ሃይማኖትን ሽፋን አድርገው የሚይዙት። በሃይማኖት ሽፋን ስር ሆነው በመንቀሳቀስ መሀይማንና ምስኪኖችን ይሸውዳሉ። የሚሰሩት ግን ከአለማቱ ጌታ አላህ ሸሪዐ ጋር ግንኙት በሌለው ህግ ነው። ምክንያቱም መጨረሻ ላይ እያንዳንዱ እነዚህ ፓርቲዎች የግድ ዴሞክራሲያዊ እንዲሆኑ ይገደዳሉ። ስለዚህ እነዚህ ፓርቲዎች ፍፃሜ ላይ ዴሞክራሲያዊ ናቸው።"*

https://www.youtube.com/watch?v=TdKvfNKvyYc

**28. ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ሃዲ አልመድኸሊ፡-**

ሸይኹ ማህበራትን በፅኑ የሚኮንኑባቸው ጠንካራ ፈትዋዎች አሏቸው። ማህበር መመስረትን የሚከለክሉ ሰዎችም በብዛት የሳቸውን ንግግሮች ሲያጣቅሱ ያጋጥማል። አንድ ምሳሌ እንመልከት፡-

*<u>“ይሄ ማህበር፣ እነዚህ ማህበራት ከሰዎች እምነቶቻቸውን በገንዘብ ይሰርቃሉ! የነዚህን ሰዎች ልቦና የገንዘብ ፍቅር ተቆጣጥሮት ሲያገኙት ጊዜ ዐቂዳዎቻቸውን ይሰርቋቸዋል</u>፣ አላህ ከዚህ ይጠብቀንና። ሆድህን ስትሞላ ፊትህ ይዋረዳል!! ሲጠባ እጅ ይነሳል!! ሆድ ሲሞላ ፊት ይሳሳል። ‘እንዴት እየሰጠንህ በኛ ላይ ትናገራለህ?’ እንዳይባል ያፍራል። ባይሆን የዲን ሰው ስለዲን ይናገራል። …*

*እንዴት ለቢድዐ ሰዎች ሰለፍዮች እንደሆኑ ትመሰክርላቸዋለህ? ይሄ ዛሬ በነዚህ ሰዎች ድምፅ ተቀድቶ ይገኛል። ትላንት ‘እከሌ ማህበር ሱናን ይዋጋል’ ሲሉ ነበር። ዛሬ ግን ‘የሰለፍያ ማህበር ነው፣ እንደዚህ ማህበር ተውሒድን ያሰራጨ የለም! እንደዚህ ማህበር ሱናን ያሰራጨ የለም!’ እያሉ ነው። ትላንት የተቀዳውንና ዛሬ የተቀዳውን ድምፃቸውን ብትሰበስበው ምን ትላለህ? ፈተና ነው!! ነብዩ ﷺ በርግጥም **‘ሁሉም ህዝብ ፈተና አለው። የህዝቦቼ ፈተና ገንዘብ ነው’** ብለዋል። እናም ገንዘብ - ወንድሞች ሆይ!- ፈተና ነው። **‘ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ ፈተና ናቸው።’** (አላህ) መልእክተኛውን ﷺ ወደዱንያ ከማንጋጠጥ ከልክሏቸዋል። …”* [ከኢንተርኔት የተወሰደ]

በርግጥ ይህ የሸይኹ ንግግር ጥፋት ያለባቸው ማህበራትን በፅኑ ቢኮንንም *“ማህበር መመስረት መሰረቱ አይፈቀድም፣ ቢድዐ ነው”* የሚል መልእክት የለውም። ምናልባት ሌላ እንዲህ አይነት መልእክት ያለው ንግግር ካለ አላውቅም። ብቻ እኔ ባገኘኋቸው ንግግሮቻቸው ማህበራትን አጥብቀው ቢያወግዙም በደፈናው እንደማይቃወሙ የሚጠቁም መልእክት አላቸው። እሱም ሸይኹ እራሳቸው ሞሮኮ ድረስ ሄደው በአንድ ማህበር የተዘጋጀ

ትምህርት ላይ በመካፈል ያስተማሩ ሲሆን **ፕሮግራሙን ያዘጋጀውን ማህበርም አወድሰዋል።** ቀደም ብለው በማህበር ላይ ሸይኹ የሰነዘሩትን የሰላ ትችት ተንተርሰው ይህን ማህበር የሚተቹ ሰዎች እንዳሉ ሲነገራቸውም እነዚህን ተቺዎች የነቀፉ ሲሆን የማህበሩን አስተዳዳሪዎችም እንዲታገሱ መክረዋል። https://www.youtube.com/watch?v=I1bzAmtTvt8

ይህም ማህበርን የሚነቅፉት ብዙዎቹ ላይ በሚታየው ቡድናዊ ዝንባሌ እንጂ አስገዳጅ ነገር ካለ በጥንቃቄ መስራት ይቻላል የሚል አቋም እንዳላቸው መረዳት ይቻላል። እንዲያውም **ወሳኝ መስፈርቶችን በመጥቀስ አስገዳጅ ሁኔታ ባለበት ሃገር ማህበር ማቋቋም እንደሚቻል በግልፅ የተናገሩበት አለ**። ይሄውና!

**السؤال: بارك الله فيكم يتحرج بعض الاخوة السلفيين من أي عمل مؤسسي بحجة أن أغلب الجمعيات والمؤسسات حزبية أو أنها بدأت سلفية ثم انحرفت فلذلك لا يرون هذا العمل وإنما يكتفون بالدعوة الفردية فهل رأيهم صحيح؟**

**الجواب: التعاون مطلوب سواء على مستوى الأفراد أو على مستوى الجماعات يعني هذه المجموعة في هذه البلدة وهذه المجموعة في هذه البلدة يتعاونون جميعا في ترتيب أمور الدعوة، وترتيب أمور الدورات و أمور الدراسة، والحلقات التي تنظم هذا مطلوب، وأنا أخاف والله من المؤسسات هذه التي تقوم فإنه كما ذكر السائل أو ذكرفي السؤال تبدأها بكذا وتنتهي بالتحزب، لكن إذا كان العقد في الولاء والبراء إنما هو على السنة فلا بأس إذا دعت الحاجة إلى قيام هذه المؤسسة بحيث إن الدعوة في بلد ما لا تقوم ولا تنتظم إلا بفتح هذه المراكز والمؤسسات**

فلا بأس، ولكن نحن نحذر إخواننا السلفيين من أن يكون عقد الولاء والبراء على هذه الجمعية أو على هذه المؤسسة أو على هذه الجماعة، وإنما يكون عقد هذا الولاء والبراء على دين الله – تبارك وتعالى –وعلى سنة رسول الله– صلى الله عليه وسلم– فمن قال الحق وجب قبول قوله ولو لم يكن مندرجا ضمن هؤلاء الأشخاص الذين أسسوا هذه الجمعية أو هذه المؤسسة فيجب عليهم أن يأخذوا بقوله لأنه ناصح لهم و أخ لهم، ومشفق عليهم ومسدد ومصوب لهم فلا يقدم قول من كان في الجمعية، أوفي هذه المؤسسة إذا كان خطأ على قوله لا لشيء إلا لأنه في هذه الجمعية، ولا يرد الحق إذا جاءهم من خارجها، أو ممن ليس معهم في تأسيسها باعتبار أنه أو بدعوى أنه، بدعوى وزعم أنه لا يعرف المصالح والمفاسد التي تراعيها هذه الجمعية، الحق واحد يجب أن يقبل ممن قاله، داخل هذه المؤسسة أو خارجها, فإذا قامت المؤسسة على هذا النحو فلا بأس. ولكني أخاف والله كل الخوف من هذا فكم قد رأينا من مؤسسات بدأت كما يقال وكما ذكر في السؤال سلفية وانتهت بعد ذلك حزبية

**ጥያቄ፡-** *"አላህ ይባርክዎትና አንዳንድ ሰለፊ ወንድሞች 'አብዛሀኞቹ ማህበራትና ተቋማት ቡድንተኞች ናቸው ወይም ደግሞ ሰለፊ ሆነው ጀምረው ከዚያ ግን ፈር ለቀዋል' በሚል መነሻ የትኛውንም ተቋማዊ የሆነ ስራ ለመስራት ይቸገራሉ። በዚህም ሳቢያ ይህን ተግባር አያምኑበትም። ይልቁንም በነፍስ-ወከፍ ደዕዋ ነው የሚብቃቁት። ይህ እይታቸው ትክክል ነውን?"*

**መልስ፡-**

*“በግለሰቦችም ይሁን በስብስቦች ደረጃ መረዳዳቱ የሚፈለግ ነው። ማለትም በእከሌ አካባቢ ያለው ስብስብ በሌላ አካባቢ ካለው ስብስብ ጋር የደዕዋ ጉዳዮችን፣ የስልጠናና የትምህርት ጉዳዮችንና ሐለቃዎችን ለማደራጀት ባንድ ላይ ቢተባበሩ ይህ የሚፈለግ ነው። ወላሂ እኔ እነዚህ የሚመሰረቱ ተቋማትን እፈራለሁ። ጠያቂው እንደጠየቀው ወይም በጥያቄው እንዳነሳው በዚህ መልኩ ይጀምሩና ቡድንተኝነት ላይ ይደርሳሉ። ነገር ግን* ***<u>መወዳጀትና መጥላታቸው ሱናን መሰረት ያደረገ ከሆነና ይህን ማህበር ለማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ችግር የለውም። በሆነ አገር ውስጥ ደዕዋው እነዚህን መርከዞችና ተቋማት በመክፈት ካልሆነ በስተቀር የማይቋቋምና የማይደራጅ ከሆነ (ማህበር መመስረቱ) ችግር የለውም።</u>*** *ባይሆን ሰለፊ ወንድሞቻችንን ይህን ማህበር ወይም ይህን ተቋም ወይም ይህን ስብስብ ባማከለ መልኩ ወላእና በራእ (መወዳጀትና መጠላላት) እንዳይኖር እናስጠነቅቃለን። ይህ ወላእና በራእ ሊኖር የሚገባው የአላህን ተባረከ ወተዓላ ዲንና የመልእክተኛውን ﷺ ሱና ባማከለ መልኩ ነው።*

*ስለሆነም ይህን ማህበር ወይም ተቋም ከመሰረቱ ሰዎች ውስጥ ባይካተት እንኳን ሐቅ የተናገረን ንግግሩን መቀበል ግድ ይላል። መካሪያቸው ወይም ወንድማቸው ወይም አዛኛቸው ወይም አስተካካያቸው ወይም አራሚያቸው ነውና ንግግሩን ሊቀበሉ የግድ ይላቸዋል። ንግግሩ ውስጥ ስህተት ካለበት ማንም ቢሆን ማህበሩ ወይም ተቋሙ ውስጥ ስለሆነ ብቻ ንግግሩ ሊቀደም አይገባም። ከውጭ ያለ ስለሆነ ወይም ከምስረታው ውስጥ ስላልሆነ “እሱ እንዲህ ስለሆነ፣ እንዲያ ስለሆነ” በሚል ሙግት ወይም ማህበሩ ታሳቢ የሚደርገውን*

*ጥቅሞችና ጥፋቶች 'ኢያውቅም' በሚል ሙግት ያመጣው ሐቅ አይመለስም። ሐቅ አንድ ነውና ከተናገረው አካል መቀበል ግድ ነው፣ ከዚህ ተቋም ውስጥም ይሁን ከውጭ። **<u>ተቋሙ በዚህ መልኩ ከተዳቋመ ችግር የለበትም።</u>** ነገር ግን እኔ ወላሂ እንዲህ መሆኑን እጅግ በጣም እሰጋለሁ። በጥያቄው ላይ እንደተባለውና እንደተወሳው ሰለፊያህ ሆነው የጀመሩ ሒዝቢያ (ቡድንተኛ) ሆነው የጨረሱ ስንት ተቋሞችን አይተናል። ደህንነትንና ሰላምን እንለምናለን።"*

http://www.sahab.net/forums/?showtopic=130859

**ንግግራቸው ሲጠቃለል፡-**

- ማህበራት ወላእና በራእን በማዳከም ዐቂዳን እንደሚሰርቁ፣
- በዚህም ሳቢያ በከፍተኛ ስጋት እንደሚመለከቷቸው፣
- አስገዳጅ ነገር ከኖረ ግን ማህበሩን ያማከለ ጠባብ ወላእና በራእ እንዳይኖር እንጂ እንደሚፈቀድ፣
- ለዚህም ማሳመኛ እራሳቸውም በማህበር የተዘጋጀ ትምህርት ላይ መካፈላቸውንና ለማህበሩ መከላከላቸውን እንረዳለን።

እስካሁን ንግግራቸውን ካሳለፍናቸው ዑለማዎች በተጨማሪ በተለያዩ ማህበራት ውስጥ በአባልነት የሚካፈሉ ወይም ለማህበራት ልገሳ ማድረግን ያበረታቱ ወይም ደግሞ በማህበራት የተዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይ እያስተማሩ ወይም ስራዎቻቸውን እያደነቁ የተነጋሩ ዑለማዎች እጅግ ብዙ ናቸው። በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ ከሚችሉት ውስጥ ከላይ ከተዘረዘሩት ከፊሎቹ ያሉ ሲሆን ስማቸው ያልተጠቀሱትን ለናሙና ያክል ልጥቀስ፡-

**29. ሸይኽ ዐብዱል ዐዚዝ ኣሊ ሸይኽ** (የአሁኑ የሰዑዲያ ሙፍቲ)፡-

*"እንዴት ነው ሐጅን በሰደቃ ስራዎች፣ በበጎ አድራጎት ተግባራትና ከሑጃጆች ጋር ለመተባበር መጠቀም የሚቻለው?"* ተብለው ሲጠየቁ፡- የበጎ አድራጎት ማህበራትን መጠቀም እንደሚገባና በዚህ ረገድ ሑጃጆችን የሚረዱ በርካታ ማህበራት እንዳሉ ነው የጠቆሙት፡፡ http://www.mufti.af.org.sa/node/3585

በሌላም ቦታ ለማህበራት ልገሳ ማድረግን አስፈላጊ እንደሆነ የተናገረቡት ሁኔታ አለ፡፡ http://www.mufti.af.org.sa/node/3757

ሙፍቲ ዐብዱል ዐዚዝ በተለያዩ ማህበራት ላይ እየተገኙ ያስተማሩበት ወይም ንግግር ያደረጉበት ሁኔታም አንድና ሁለት አይደለም፡፡

**30. ሸይኽ ሷሊሕ አልፈውዛን ኢብኑ ዐብዲላህ አልፈውዛን**

ፈውዛን ማህበርን የሚፈቅዱ በርካታ የኢብኑ ባዝን፣ የአልባኒንና የኢብኑል ዑሠይሚንን ፈትዋዎች የያዘውንና በዚህ ጉዳይ የተፃፈውን *"ሑክሙል ዐመሊል ጀማዒይ ፊል ኢስላም"* የተሰኘ ኪታብ መቅድም መፃፋቸው ለጉዳዩ ይሁንታ መስጠታቸውን ግልፅ ጠቋሚ ነው፡፡ በኪታቡም ሆነ በአዘጋጁ ላይ ሂስ የሚሰነዝሩ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ **<u>የኔ ትኩረት ግን ፈውዛን ለኪታቡ እውቅና መስጠታቸው የሚሰጠው መልእክት ላይ ብቻ ነው፡፡</u>**

በተጨማሪም ሸይኹ ጧኢፍ ውስጥ በሚገኝ *"አልጀምዒየቱል ኸይሪያ ሊ ተሕፊዚል ቁርኣኒል ከሪም"* የተሰኘ ማህበር ባዘጋጀው **<u>የሓፊዞች</u>**

**<u>የምረቃ ድግስ</u>** ላይ ተገኝተው ማህበሩንና ስራዎቹን እያደነቁ ተናግረዋል። "
https://www.youtube.com/watch?v=5qeVZFdltBs

### 31. ሸይኽ ዐሊይ ኢብኑ ናሲር አልፈቂሂ

"አልጀምዒየቱል ኸይሪያህ ሊተሕፊዚል ቁርኣኒል ከሪም ቢ መንጢቀቲል መዲነቲል ሙነወራህ" የተሰኘ ማህበር ውስጥ አባል ናቸው። http://www.quranm.org.sa/index_ar.php?op=emp

### 32. ሸይኽ ዐሊይ ኢብኑ ዐብዲረሕማን አልሑዘይፊ (ታዋቂው የመስጂድ ነበዊ ኢማም)

ከላይ በጠቀስኩት ማህበር ውስጥ አባል ናቸው። http://www.quranm.org.sa/index_ar.php?op=emp

---

[11] ዛሬ አንዳንዶች ዘንድ የሚንሃጅ ችግር ተደርገው እየቀረቡ ካሉ ነገሮች አንዱ የሓፊዞች ምረቃ ነው፡፡ በቅርቡ እንዲህ የሚል ፅሁፍ አይቻለሁ:- *"በተጨማሪም ሌላም ቢደዓዎች እነሱ ("ጀምዒዮች" የሚላቸውን ነው) ጋር አሉ ለምሳሌ የቁርአን ሃፊዞች ምረቃ (የኢኽዋኒያ ቢደዓ የሆነው)። ከኢኽዋን ጋር ልጅና አባት ናቸው የተባለው ዝምብሎ እንዳይመስልክ!!"* የቃላት እርምት ሳልሰጥ እንደወረደ ነው የገለበጥኩት፡፡

ይሄው ሸይኽ ፈውዛንም ከቁርኣን ሓፊዞች ምረቃ ላይ ተገኝተዋል፡፡ እሳቸውንስ ምን ይሏቸው ይሆን?! ጉዳዩ ይህን ያክል ሰዎች ከሱና የሚወጡበት ከባድ ጉዳይ ቢሆን ኖሮ ድርጊቱ ቢድዐ እንደሆነ የሚገልፁት እንደነ ኢብኑ ባዝ ያሉና ሌሎችም ዑለማዎች ባልተሳተፉበት ነበር፡፡ ኢብኑ ሑመይድም እንዲሁ ይካፈሉ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ይህን ጉዳይ የፈቀዱት ዐሊሞችም አሉ፡፡ ለምሳሌ:- ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን፡፡ [ፈታዋ ኑሩን ዐለደርብ: 14/95-96] ስለዚህ እሳቸውም የኢኽዋን ልጅ ናቸው ማለት ነው በዚህ አደገኛ ስሌት መሰረት፡፡

### 33. ሸይኽ ሷሊሕ ኢብኑ ዐብዲላህ ኢብኒ ሑመይድ

(የታላላቅ ዑለማዎች ምክር ቤት አባል፣ በመስጂደል ሐራም ኢማም እና አስተማሪ ናቸው።)

- በራቢጦተል ዓለመል ኢስላሚይ የአንድ ንኡስ መጅሊስ አባል፣
- የአለም አቀፉ ኢስላማዊ እርዳታ ድርጅት ኮሚቴ ውስጥ አባል፣
- በኢስላማዊ ትብብር ድርጅት ስር ላለው አለም አቀፉ የኢስላማዊ ፊቅህ ማዕከል ሊቀመንበር ናቸው።

### 34. ሸይኽ ዐብዱሰላም አሱሐይሚ

("ኩን ሰለፊየን ዐለጃዳህ" በምትባለው ኪታባቸው የምናውቃቸው)

"አልጀምዒየቱል ዒልሚያህ አሰዑዲያህ ሊዑሉሚል ዐቂዳህ ወልአድያን ወልፊረቅ ወልመዛሂብ" የተሰኘ ማህበር አባል ናቸው። http://www.ajurry.com/vb/showthread.php?t=27237

### 35. ሸይኽ ሷሊሕ ኢብኑ ዐብዲል ዐዚዝ ሲንዲ

*"አልጀምዒየቱል ዒልሚያህ አሰዑዲያህ ሊዑሉሚል ዐቂዳህ ወልአድያን ወልፊረቅ ወልመዛሂብ"* ለተሰኘው ማህበር ሀላፊ ናቸው። http://aqeeda.org/container.php?fun=manager

### 36. ሸይኽ ዐብዱረዛቅ አልበድር

በተደጋጋሚ በማህበር የተዘጋጀ የደዕዋ መድረክ ላይ እየተሳተፉ ደዕዋ ያደርጋሉ።

### 37. ሸይኽ ሙሐመድ ዑመር ባዝሙል

- በለጅነቱል ዒልሚያ አሰዑዲያ ሊልሐዲሥ ወዑሉሚሂ አባል
- የመጅሊሱ ኢዳረቱል ጀምዒየቱል ኸይሪያ ሊ ተሕፊዚል ቁርኣን ቢል ዓሲመቱል ሙቀደሳህ አባል ነበሩ።

http://www.bazmool.net/index.php/%D8%AA%D8%B1%D8%AC%D9%85%D8%A9-%D8%A7%D9%84%D8%B4%D9%8A%D8%AE

በማህበር የተዘጋጁ የደዕዋ መድረኮች ላይ በመገኘት በተደጋጋሚ አስተምረዋል።

## ለ/ ማህበርን የከለከሉ ዑለማዎች

ባለኝ መረጃ በዚህ ረገድ ከታላላቅ ዑለማዎች ውስጥ የሚጠቀሱት ሸይኽ ረቢዕ ኢብኑ ሃዲ ብቻ ናቸው። ሌሎች ማህበርን "ከልክለዋል" የሚባሉ ዐሊሞች በተጨባጭ የሚፈቅዱባቸው ንግግሮች ስላሏቸው በሆኑ ጥፋቶች ሳቢያ ማህበራትን ማውገዛቸውን ነጥሎ በማቅረብ አቋማቸው ይሄ ብቻ እንደሆነ ማስመሰል ጤናማ አይደለም። ሸይኹ ከሊቢያ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት መልስ በከፊል እንመልከት:

أنا والله أخاف عليهم أن يفسدوهم لانو ما قامت جمعية إلا وسقطت على أم رأسها حذرناهم من هذا الشي، يكفيكم المساجد كل واحد يمسك مسجد ويدرس فيه أحسن من الجمعيات ولا أموال ولا شي – بارك الله فيك – الحمد الله شعبكم شعب غني كل واحد يمول نفسه و بس ما يحتاج جمع أموال وحاجات و أشياء...

**الجمعية هذه ناس مكرة ضحكوا على السلفيين، أنا أرى السلفيين ينسحبون منها ويروحون كل واحد يمسك له مسجد إذا عندوه علم يدعوا إلي الله فيه هذه طريقة السلف وبقى الإسلام وحفظ وأنتشر من هذه الطرق ...الجمعيات فيها تقليد للنصارى واليهود الجمعيات فيها إتباع لليهود والنصارى (لتتبعن سنن من كان قبلكم حذو القذة بالقذة) بارك الله فيك...**

**أتقو الله قل لهم ألزموا السنة وإياكم والبدع الجمعيات هذه من البدع والضلالات والله ومن شر الفتن ومن أسباب الانحراف – بارك الله فيك – و الدول لا تقبل هذه الدول الديموقراطية لا توافق على إنشاء جمعيه إلا بشروط، شروط تخضعه وتذله للباطل، ومن شروطهم أنو لابد يكون لها رصيد في البنك، – أيوه بارك الله فيك – هذا من أشد ما أنكر الالباني على أهل الجمعيات**

**أحد الحاضرين: التصوير يا شيخ برضوا يلزموهم يأتوا بصور و يلزموهم يعملوا دستور**

**الشيخ: يعملوا أيه**

**أحد الحاضرين: يلزموهم بالتصوير يأتوا بصور لأعضاء الجمعية**
**الشيخ: لابد لهم من الصور**

*"እኔ ወላሂ እንዳያበላሿቸው እፈራለሁ። ምክንያቱም* ***አንድም ማህበር አልተመሰረተም፣ በአናቱ የተደፋ ቢሆን እንጂ።*** *ከዚህ ነገር አስጠንቅቀናቸዋል። መስጂዶች ይበቋቸኋል። እያንዳንዱ መስጂድ ይዞ በውስጡ ቢያስተምር ከማህበራት የተሻለ ነው። ገንዘብ የለ፣ ምን የለ። አላህ ይባርክህ። ምስጋና*

*ለአላህ ይሁንና ህዝባችሁ ሀብታም ህዝብ ነው። እያንዳንዱ እራሱን ይቻል። በቃ። ገንዘብ፣ ድጋፎች፣ የተለያዩ ነገሮችን መሰብሰብ አያስፈልግም። …*

***እኔ ሰለፍዮች ከነዚህ ማህበራት እራሳቸውን እንዲያገሉ፣*** *ከዚያም እያንዳንዱ እውቀት ካለው መስጂድ እንዲይዝና በሱ ውስጥ ወደ አላህ እንዲጣራ ነው የሚታየኝ። ይህ ነው የሰለፎቹ መንገድ። ኢስላም የቆየው፣ የተጠበቀውና የተሰራጨው በነዚህ መንገዶች ነው። … ማህበራት የሁድና ክርስቲያኖችን በጭፍን መከተል አለባቸው። ማህበራት የሁድና ክርስቲያኖችን መከተል አለባቸው።* ***(ከናንተ በፊት የነበሩትን ሰዎች ፈለጎች ልክ የቀስት ላባ ከቀስት ላባ እንደሚስተካከለው ሆናችሁ ትከተላላችሁ።)*** *አላህ ይባርክህ።…*

*አላህን ፍሩ። ሱናን አጥብቃችሁ ያዙ። ከቢድዐ ተጠንቀቁ። እነዚህ ማህበራት ከቢድዐዎችና ከጥመቶች ናቸው። ወላሂ ከባድ ከሆኑ ፈተናዎች፣ ከጥመት ሰበቦች ናቸው። ባረከላሁ ፊክ። ዲሞክራሲያዊ መንግስታት በቅድመ-ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር እነዚህ ማህበራትን መመስረት አይፈቅዱም። ቅድመ-ሁኔታዎቹ (መስራቹን) ለሐሰት እንዲያጎነብስ የሚያደርጉ ናቸው። ከቅድመ-ሁኔታዎቹ ውስጥ የግድ በባንክ ተቀማጭ ሊኖራቸው ነው። አዎ አላህ ይባርክህና። ይሄ አልባኒ በባለ ማህበራት ላይ በጥብቅ ከተቃወማቸው ነገሮች ውስጥ ነው።*

**አንዱ ታዳሚ፡-** ፎቶም መነሳትም አለበት ሸይኽ። ፎቶ እንዲያቀርቡ ያስገድዷቸዋል። መተዳደሪያ ደንብ እንዲያዘጋጁም ያስገድዷቸዋል።

ሸይኽ ረቢዕ፡- ምን እንዲሰሩ?

አንዱ ታዳሚ፡- በፎቶም ያስገድዷቸዋል። የማህበሩ አባላት ፎቶዎችን እንዲያቀርቡ።

ሸይኽ ረቢዕ፡- ፎቶዎች የግድ ናቸው …”[ከኢንተርኔት የተወሰደ ነው]

<u>**ሌሎችም ተቀራራቢ ይዘት ያላቸው ፈትዋዎች አሏቸው።**</u> ይህን የሸይኹን ፈትዋ ለመጠቀም የተጠየቁበትን ሃገር ሁኔታ ከሃገራችን ሁኔታ ጋር ያለውን ዝምድናና ልዩነት ማጤን አስፈላጊ ነው። ይህንን ስንመለከት፡-

- ጥያቄው የቀረበው ከሊቢያ ነው። በሃገሪቱ ሸሪዐዊ ህግ አለመኖሩ ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ነው።
- ማህበራት ገንዘባቸውን በባንክ ማስቀመጣቸው የጋራ ሐቅ ነው።
- ለምስረታ የአባላት ፎቶ መጠየቁ የሁሉም ሃገራት የጋራ ሐቅ ነው።
- የሊቢያ ህዝብ ሀብታም እንደሆነ ማውሳታቸው ከኛ ሃገር ነባራዊ ሐቅ ጋር በብዙው አይገናኝም።
- ማህበራቱ ፖለቲካዊ አላማ አንግበው መነሳታቸው ከኛ ሃገር ነባራዊ ሁኔታ ጋር አይገናኝም። ምክንያቱም ማህበራት ፖለቲካ ውስጥ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውምና። በብዙ ሃገራት ያለውም እውነታ ሸይኹ ከተናገሩት ይለያል።
- ማህበር ከመመስረት ይልቅ እያንዳንዱ መስጂድ ይዞ እንዲያስተምር ማሳሰባቸው በብዙ ምክንያቶች በሃገራችን ቀላል ነገር አይደለም።

ስለዚህ ድጋፍም ይሁን ተቃውሞ የሚያንፀባርቅ ሰው <u>**ይህንን**</u> የሸይኹን ፈትዋ በሚያወሳበት ጊዜ እነዚህን ነገሮች በአንክሮ ቢመለከትና ከሃገራችን ነባራዊ ሐቅ ጋር ቢያገናዝብ ጤናማ አቋም እንዲይዝ ያግዘዋል።

ከሌላኛው ወገን ለሚነሳበት ጥያቄም እራሱን እንዲያዘጋጅ ይረዳዋል። ምክንያቱም አንድ *“ሸሪዐዊ ብይን ከሆነ ሰበብ ጋር ከተንጠለጠለ ያ ሰበብ የተገኘበት ነገር ሸሪዐዊ ብይኑ ይፀናበታል። ሰበቡ ካልተገኘ ግን ብይኑ አይፀናበትም። አንድ ሙፍቲ ሰዎች አንድን አላህ የፈቀደውን ነገር ቢፈፅሙት የሚከተል ክልክል ነገር ከኖረ ሊከለክለው ይችላል። ልክ ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ በአንድ ጊዜ የሚፈፀም ሶስት ፍቺን አስመልክቶ እንዳደረጉት። ሰዎች ሲቻኮሉበት ሲያዩዋቸው ጊዜ በሱው አፀኑባቸው። በነብዩ ﷺ ዘመን፣ በአቡበክር ዘመንና በዑመርም ኺላፋ ሁለት አመት ያክል በአንዴ የተፈፀመ ሶስት ፍቺ እንደ አንድ ነበር የሚቆጠረው።”* [ኪታቡል ዒልም፡ 212]

በነገራችን ላይ የሸይኽ ረቢዕ የቀድሞ አቋም ይህ አልነበረም። ይልቁንም ማህበር ማቋቋምን የሚፈቅዱ ንግግሮች አሏቸው። ይሄውና፡-

> *“የሱና ሰዎች ሁላቸውም ሙሉ በሙሉ በአላህ ገመድ ላይ የተሳሰረ፣ የማይለያይ አንድ ጀማዐ መመስረት እንዳለባቸው ያምናሉ። ወይም ከወደቁበት መለያየት መገላገል ይሻሉ። ከዚህ ጥብቅ ግዴታ ከሆነው መሰባሰብ በኋላ ሁሉም ወደ አንድ ግብ የሚያልሙ **<u>የበጎ አድራጎት ማህበራትን</u>** ለነሱ የፈለጉትን መመስረት ይችላሉ። እሱም (ግባቸውም) የአላህን ቃል የበላይ ማድረግና ሙስሊሞችን ባጠቃላይ ክብራቸውን መመለስ ነው።”* [ጀማዐቱን ዋሒዳህ ላ ጀማዓት፡ 80]

ሌላ ቦታም *<u>“ሰለፍዮች የተቀናጀ ማህበራዊ ስራን የሚቃወም ፈትዋ አላቸው”</u>* የሚለውን **ክስ ሲመልሱ** እንዲህ ይላሉ፡-

*"እነዚህ ዐብዱረሕማን ዐብዱል ኻሊቅ እነዚህን ፈትዋዎች የሚለጥፍባቸው ትክክለኛ አህሉ ሱና የሆኑ ሰለፍዮች ማህበራቱ የአንድ ጤናማ የነብያት ዐቂዳ ባለቤቶች ከሆኑ፣ የአንድ መንገድ ማለትም የትክክለኛው የነብያት ጎዳና ባለቤቶች ከሆኑ፣ እንዲሁም የአንድ የትክክለኛው የኢስላም ጥሪ ባለቤቶች ከሆኑ **<u>ለበጎ አድራጎትና ለመልካም ስራ ማህበራትንና ተቋማትን ማቋቋምን እንደማይከለክሉ በተደጋጋሚ አልፏል።</u>** … እነዚህ የዛሬዎቹ ማህበራትና ተቋማት ከምዕራባውያን የተቀዱ ናቸው። **<u>ምንም እንኳን እኛ 'በመልካም ነገርና አላህን በመፍራት ከተመሰረቱ እነዚህ ማህበራት ይቀዳሉ' ከማለታችን ጋር</u>** ግና አንተም ሆንክ ሌላ ከነዚህ ጋር የሚመሳሰል ቅርፅ ያለው የመልካም ነገርና የተቅዋ ስራ አፈፃፀም ከኢስላም ታሪክ ማምጣት አትችሉም።"* [ጀማዐቱን ዋሒዳህ፡ 106-107፣ 110-109]

ከዚህም በተጨማሪ ከሸይኹል አልባኒ ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ በተደራጀ መልኩ አንዱ ሌላውን ሳይጠላ በአንድ መንገድ ላይ የሆኑ የተለያዩ ስብስቦች ቢኖሩ እንደማይቃወሙ አልባኒ ሲገልፁ ረቢዕም *"ይህን ነው የምንፈልገው ሸይኽ ሆይ!"* ይላሉ። አልባኒም *"አዎ ይህ ነው የምንፈልገው"* ሲሉ ረቢዕ፡ ***<u>"ነገር ግን ይሄ ነገር እኛም ዘንድ እርሶም ዘንድ እንደማይፈቀድ ያስጠጉብናል"</u>*** አሉ። ሸይኹል አልባኒም *"ይሄ ወደኛ ከሚለጠፍብን ውሸት ውስጥ ነው አላህ ይባርክህና"* ይላሉ። [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 371]

ስለዚህ ከነዚህ ማስረጃዎች በመነሳት የሸይኽ ረቢዕ አቋም ቀድሞ ምን እንደነበር በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ሌላም ጊዜውን በውል ያልለየሁት ማህበርን የሚፈቅዱበት እንዲህ የሚል ፈትዋ አግኝቻለሁ፡-

**ጥያቄ፡-** ወደ ቁርኣንና ሱና ለመጣራት ማህበር ማቋቋምና እራስንም ወደሱ ማስጠጋት ከቡድንተኝነትና ከመለያየት ነውን?

**የሸይኹ መልስ፡-**

*“በመጀመሪያ በዚህ ሃገር (ሰዑዲያ) ውስጥ ማህበር ማቋቋም አይፈቀድም። ማህበርም ሆነ ሌላ። በጭራሽ!! ምክንያቱም መንግስቱ በአላህ ኪታብና በመልእክተኛው (ሱና) ላይ የቆመ ሙስሊም ነውና። ይህንንም ጎዳና በማስተማርም፣ በየመስጂዱ፣ በየዩኒቨርሲቲው፣ በየትምህርት ቤቱና በየሁሉም ቦታ ያንፀባርቃል። …*

*እራሳቸውን በገንዘብም በእውቀትም በማደራጀት ኢስላምን ለማስፋፋት፣ ለማስተማርና ሰዎችን ወደ ሐቅ ለመጥራት የተሰባሰቡ ሰዎችን ካገኘ ከልካይ የለም።* ***በህንድ ያሉ ሙስሊሞች፣ የህንድ ሰለፍዮች ይህን ባያደርጉ ኖሮ ኢስላም መቶ በመቶ በጠፋ ነበር። መንግስቱ ኢስላምን የሚዋጋ ከሃዲ የሆነ አለማዊ (ሴኩላር) መንግስት ነው። ስለሆነም ተነስተው መንግስቱ እውቅና በሚሰጠው መልኩ በማህበር መልክ ተሰባሰቡ።*** *ከዚያም መድረሳዎችና መስጂዶችን ከፈቱ። አላህ ኢስላምን የጠበቀባቸው አእላፍ መድረሳዎች!! ይሄና መሰሉ የግድ ሙስሊሞች ሊጠቀሙት የሚገባ አስገዳጅ ሁኔታ ነው። የሙስሊሙ አለም በአንድ መሪ ስር ቢሰባሰብ ኖሮ የተነጣጠለ ስብስብ ሊኖር አይፈቀድም ነበር። አላህ ይባርካችሁና።*

*ነገር ግን የሙስሊሙ አለም ተበጣጥቋል። ከዚች በቁርኣንና ሱና ላይ ከፀናችው ሀገር በስተቀር እያንዳንዱ ሀገር የራሱ ብልሹ ስርአት አለው።*

***ስለዚህ በየትኛውም ትክክለኛውን የኢስላም ጎዳና በማያራምድ ሃገር ውስጥ ያሉ ሙስሊሞች የአላህን ጥሪ የሚያሰራጩበት፣ ያቅማቸውን ያክል የሙስሊም ልጆችን በዚህ ጎዳና ላይ የሚኮተኩቱበት ኢስላምን አንግበው ማህበርን ወይም ማህበራትን ሊመሰርቱ፣ ትክክለኛ አደረጃጀትን ሊደራጁ ይገባል።"*** [ነሲሐ ሶሪሐ ሊ ጡላቢል ጃሚዐቲል ኢስላሚያ፣ ካሴት]

እንዲያውም ከጥፋቶች ከተራቀና ያለ ማህበራት ዳዕዋን ማካሄድ እንቅፋት ባለበት ሃገር የሚንቀሳቀስን ማህበር የፈቀዱበት ፈትዋ አላቸው። ይሄውና በ 1431 ዓ.ሂ በሞሮኮ ለሚገኙ ወጣቶች ደዕዋ ካደረጉ በኋላ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡትን መልስ እንመልከት፡-

**ጠያቂ፡-** *"ይህቺ እኛ ያለንባት ማዕከል - የሐዲሥ ማዕከል- ትንሽዬ ቤት ነች። በውስጧ እውቀትን የሚፈልጉ ወንድሞች አሉ። ተከራይተዋት ነው። ኢስላማዊ ትምህርቶች ይሰራጩባታል፣ መትኖችም ይተሐፍዝባታል። ከሸይኽ ኡሳማ አልዑተይቢ ጋር ሳምንታዊ ትምህርት አላቸው። ነገር ግን አንዳንድ ወንድሞች "ይሄ ማህበር ነው" በማለት በነሱ ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ቅሬታ አላቸው። በዚህም ሰበብ ከነሱ ጋር አይካፈሉም። በዚህ ላይ ፈትዋ ስጡን አላህ ይባርካችሁና።"*

**ሸይኽ ረቢዕ፡-** *"በቁርኣን ማዕከል ስም ቤት ተከራይተው ነው ያለው?"* ሲሉ ከጎናቸው ያለን ወንድም ጠየቁ።

**ከጎናቸው ያለው ወንድም፡-** *"በሐዲስ ማዕከል ስም ነው፣ ከመንግስት ፈቃድ ወስደው። በባንክ ሂሳብ እንደሌላቸውና የባንክ ግንኙነት እንደሌላቸው ተናግሯል። ይሄ ማዕከል በውስጡ ቁርኣንን ይሐፍዞበታል። የዑለማዎችን*

*ሽርሖች ያዳምጡበታል። በሆነ ጊዜ የዐቂዳ መትኖችን ወይም ኪታቦችን ይሐፍዞበታል። ከሳምንቱ በሆነ ቀን የዚያን ሸይኽ ሽርሕ ይሰሙበታል። ከሸይኽ ዑተይቢ ጋር የኪታቡ ተውሒድ ትምህርት አላቸው። ታዲያ ከፊል ወንድሞች 'ከናንተ ጋር አንካፈልም። ይሄ ማህበር ነውና' ይላሉ። ሰዎቹ ግን ማንም እንዲገኝ አያስገድዱም። የሚካፈለውም የማይካፈለውም እነሱ ዘንድ ሰለፊ ነው።"*

**ሸይኽ ረቢዕ፡-** *"በመስጂድ ውስጥ ደዕዋ ማድረግ የሚቻል ነው ወይ?"* ሲሉ ከጎናቸው ያለውን ወንድም ጠየቁ።

**ተጠያቂው ወንድም፡-** *"አይቻልም። ሁኔታቸው እንደኛ ሁኔታ ነው። ኸረ እንዲያውም የከፉ ነው።"* (እሱ አልጀሪያዊ ነው።)

**ሸይኽ ረቢዕ፡-** *"እኔ የምለው ሁኔታው እንደገለፃችሁት ከሆነና ይህ ማዕከል ቁርኣንን ለመሐፈዝ፣ የዑለማዎችን ንግግር ለማዳመጥና እውቀትን ለመተዋወስ ከሆነ፤ እንጂ ገንዘብ ለመሰብሰብ ካልሆነ፣ ከዚህ ሰለፍዮችን እየቦጫጨቀ ካለ* ***ሸይጣናዊ ፖለቲካ*** *ጋር ግንኙነት ከሌለው በዚህ ላይ ችግር የለበትም። ገንዘብ ለመሰብሰብ የምትመሰረት ማዕከል ከሆነች ወይም ደግሞ ፖለቲካዊ ማህበር ከሆነች ይሄ የምንስማማበት አይደለም። አይፈቀድምም። እንዲያውም ይሄ ለሰለፎች አካሄድ የሚፃረር ነው። የጠቀሳችኋቸውን መገለጫዎች የተላበሰ ከሆነ ግን በዚህ ላይ ችግር የለበትም።* ***ሌሎቹንም ወንድሞች ከናንተው ጋር እንዲሆኑ እመክራቸዋለሁ።*** *ይሄ በአላህ ፈቃድ መልካም ነገር ያለበት ስራ ነው። በከፊል እንዳልኩት በዚህ ጥረት ውስጥ ብዙ ጥቅም አለው።* ***ከዚህ መንገድ ውጭ ከፊታችሁ ሌላ የደዕዋ መድረኮች ከሌሉ ይህንን መቃወም ትልቅ ስህተት ነው። ማለትም ከዚህ ጀርባ ደዕዋን***

***መግደል፣ ከአዘቅት ውስጥ መቅበር እንጂ ሌላ የለም። እናም በዚህ ጥሩ መልኩ የቆመን ይህን ስራ የሚቃወሙ ወንድሞችን ከወንድሞቻቸው ጋር እንዲቀናጁና ከልዩነት መንስኤዎች እንዲርቁ ነው የምመክራቸው።*** *አላህ ይባርካችሁና። የነገሮችን መጨረሻ እንዲመለከቱ፣ የዚህ ተግባራቸው (ተቃውሟቸው) ውጤቶች እንዲመለከቱ (እመክራቸዋለሁ።) ከዚህ ውጭ ምርጫ ከሌለን ምን እናድርግ?! ከዚህ በኋላ ደዕዋን መግደል እንጂ ሌላ የለም።"* http://www.sahab.net/forums/index.php?showtopic=130290

እዚህ ላይ ሸይኹ የክልከላ አቋማቸው እንዳለ ሆኖ ነገር ግን ለአስገዳጅ ሁኔታ ብቻ እንደፈቀዱ እንረዳለን። ይህንን ፈትዋቸውን ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ስናገናዝብ፡-

- ከባንክ ጋር አለመነካካታቸው ከሃገራችን ሁኔታ ጋር አይዛመድም።
- በጥቅሉ ሃገራቱ በሸሪዐ አለመተዳደራቸው የጋራ ባህሪ ነው።
- ከመንግስት ፈቃድ መውሰዳቸው ከኛም ጋር የጋራ መገለጫ ነው።
- ኢስላማዊ ትምህርት መስጠታቸው በሃገራችን ካሉ ጥቂት **<u>የሙስሊም</u>** ማህበራት ውስጥ እጅግ ጥቂቶቹ ጋር የሚመሳሰል ነው። [12]
- ፖለቲካ ውስጥ አለመግባት የጋራ ሁኔታ ነው።
- በመስጂድ ውስጥ ለማስተማር እንቅፋት መኖሩ የሚመሳሰል ሐቅ አለው። የሞሮኮ መስጂዶች በሀገሪቱ አውቃፍ አስተዳደር ስር ስለሆኑ

[12] የልማት ማህበራት ከዚህ ውስጥ አይካተቱም፡፡ ምክንያቱም በሃገራችን ያለው የማህበራት ህግ ልማታዊና ሃይማኖታዊ ስራዎችን በአንድ ላይ ማስኬድ አይፈቅድም፡፡ ስለዚህ የአይታም እርዳታ፣ የትምህርት፣ የህክምና፣ የአዛውንት ወዘተ እርዳታ፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ስልጠና … ላይ የተሰማሩ ማህበራት የደዕዋ ስራ ውስጥ መገባት አይችሉም፡፡

የአሽዐሪያ ወይም የሱፍያ ትምህርት ነው የሚሰጥባቸው። የሃገራችን ሁኔታም በብዙ መልኩ ተመሳሳይ ነው።

ልብ በሉ! እኔ እነዚህን ነጥቦች ለማጉላት ስሞክር ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በራሴ አወዳድሬ "ይፈቀዳል" ወይም "አይፈቀድም" ለማለት አይደለም። ይልቁንም አላማዬ ፈትዋዎችን እንደወረዱ ወስደን ለተቃውሞም ይሁን ለድጋፍ ከማዋላችን በፊት ፈትዋዎቹ የቀረቡበት ሁኔታ ከኛ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያለውን መመሳሰልና መለያየት ማገናዘብ እንደሚገባ ለማስታወስ ነው። ፈትዋው የተያያዘበት ሰበብ (ዒላ) ከኛ ሁኔታ የሚለይ ከሆነ ያንን ፈትዋ ያለቦታው ማጣቀስ አግባብ አይሆንም። ፈትዋው የቀረበበት ሰበብ ከኛ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ግን ይህን ፈትዋ ማጣቀሱ ጤናማ ነው። ባይሆን የዑለማእ ፈትዋ ያለቀለት መረጃ አይደለምና ስሜቱን እስካላስቀደመ ድረስ በቁርኣን፣ በሐዲሥ ወይም በሌሎች ዑለማዎች ፈትዋዎች የሚሞግት ቢመጣ በምንም መልኩ ሊነወር አይገባም። ብቻ በአንድ ቦታ ላይ ያሉ ችግሮችን መነሻ በማድረግ የሚሰጥ ፈትዋ በሌላ ሁኔታዎቹ በሚለይ ቦታ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ሙግት ቢያጋጥም የትኛውንም ክፍል የዑለማእ ፈትዋ "ተቀብሏል" ወይም "መልሷል" ከማለታችን በፊት ከልብ ማስተዋል ይገባል። ምክንያቱም ሁኔታዎች በመለያየታቸው ምክንያት በአንድ ጉዳይ ላይ ከአንድ ዐሊም የተለያዩ ይዘቶች ያሏቸው ፈትዋዎች የሚመነጩበት <u>ሁኔታ</u> አለና። ባይሆን ይሄ ሁሉንም ርእሶች የሚመለከት አይደለም።

## <u>ሌላ ዑለማስ?</u>

ከሸይኽ ረቢዕ በተጨማሪ በአንዳንድ ፈትዋቸው ላይ ሸይኹል አልባኒና ሸይኽ ሙቅቢል በማህበራት ላይ ተቃውሞ የሰነዘሩባቸውና

የከለከሉባቸው ንግግሮች አሏቸው፡፡ [13] ማህበር መመስረትን ከሚያወግዙ ዑለማዎች ዝርዝር ስር ያላሰፈርኩት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-

1. እነዚሁ ሸይኾች በግልፅ ቋንቋ ማህበር መመስረትን የሚፈቅዱባቸው ፈትዋዎች ስላሏቸው፣
2. ድፍን አድርገው ከነጭራሹ ማህበር መመስረትን እንደሚቃወሙ የሚወራባቸው ክስ ሐሰትነቱን መናገራቸው፣
3. ትችት በሰነዘሩባቸው ቦታዎች ላይ የተቃውሟቸው ምክንያት በማህበራቱ ላይ የሚያዩት ጥፋት መሆኑ ከጥፋቱ ከራቁ ከስር መሰረቱ እንደማይቃወሙ የሚጠቁም ስለሆነ
4. ማህበርን የሚቃወሙት ሸይኽ ረቢዕ እራሳቸው ይህን ከነጭራሹ ማህበራትን የሚቃወም አቋም አንድም ያንፀባረቀው ዓሊም እንደሌለ ስለተናገሩ ነው፡፡ ይሄውና፡-

*“እኔ እስከዚህ ቀኔ ድረስ [በቁርኣንና በሱና ላይ የተመሰረተ የሆነን ጥንትም ዛሬም ሙስሊሞች ባሉበት ላይ ከሆነ] ከሰለፍዮች* ***<u>አንድ እንኳን</u>*** *ሸሪዐዊ የሆነን ማህበራዊ ስራን የሚቃወም አላውቅም፡፡ …* ***<u>ለነሱ በህንድ፣ በፓኪስታን፣ በባንግላዴሽና በሌሎችም ሃገራት ማህበራት አሏቸው፡፡</u>*** ***… አንሷሩ ሱና በግብፅና በሱዳን በህብረት የሚሰሩ ትምህርት ቤቶች፣ መስጂዶችና ሌሎችም ስራዎች አሏቸው፡፡ …*** *የተፈቀደ የሆነን ማህበራዊ ስራን የሚዋጋ፣ የሚከለክልና* ***<u>ባለቤቶቹን</u>***

---

[13] ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ሃዲም እንዲሁ፡፡

***በቪድዮ የሚገለፅ አንድም ዐሊም ወይም ሰለፊ የሆነ የዒልም ተማሪ አልሰማንም።***” [ጀማዐቱን ዋሒዳህ፡ 60]

## ዑለማዎችም “ጀምዒዮች” ናቸው?!

ቀደም ብሎ ከሰላሳ በላይ ማህበር የሚፈቅዱ ታዋቂ የሆኑ ታላላቅ ዑለማዎችን አሳልፈናል። በእርግጠኝነት ቁጥሩ ከዚህም የሚያልፍ ነው። በተለያየ መልኩ የፈቀዱትን ትተን ቀጥታ በማህበር ስራ ውስጥ የተካፈሉትን ለይተን እንመልከት። ሁሉንም አልዘረዘርኩም።

| ተ.ቁ | ሸይኽ | ስለማህበር ላይ አቋማቸው |
|---|---|---|
| 1 | ዐብዱላህ ጋዚፉሪ | መስራችና ሀላፊ |
| 2 | ሙሐመድ ዳውድ አልገዝነዊ | መስራችና ሀላፊ |
| 3 | ሙሐመድ ኢስማዒል አሰለፊ | መስራች |
| 4 | ሙሐመድ ሓሚድ ፊቂ | መስራችና ሀላፊ |
| 5 | ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ | መስራችና ሀላፊ |
| 6 | ሙሐመድ ኸሊል ሀራስ | አባልና ም/ ሀላፊ |
| 7 | ዐብዱረሕማን አልወኪል | መስራችና ሀላፊ |
| 8 | ኢብኑል ዑሠይሚን | ሀላፊ |
| 9 | ሷሊሕ አሱሐይሚ | አባል |
| 10 | ዐብዱሰላም አሱሐይሚ | አባል |
| 11 | ዐሊይ ኢብኑ ናሲር አልፈቂሂ | አባል |
| 12 | ዐሊይ አልሑዘይፊ | አባል |
| 13 | ሷሊሕ ኣሊሸይኽ | ሀላፊ |
| 14 | ሷሊሕ ሲንዲ | ሀላፊ |
| 15 | ሙሐመድ ዑመር ባዝሙል | ሀላፊ |

ስለዚህ “ጀምዒይ” ማለት ማህበርን የሚፈቅድ ወይም የሚመሰርት ወይም አብሮ የሚሰራ ወይም የሚያወድስ ወይም ለነሱ እርዳታ እንዲደረግ

የሚያበረታታ ከሆነ እነዚህ ሁሉ ዐሊሞች “ጀምዒዮች” ናቸው ማለት ነው። ለማህበር ገንዘብ መሰብሰብ ስርቆትና በየቲም ስም መነገድ ከተባለ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እነዚህ ዑለማዎች “ሌቦች ናቸው” የሚል አንድምታ አለው፣ አላህ ይጠብቀንና። ለበጎ አድራጎት ማህበራት ገንዘብ መሰብሰብ ወንድሞቻችን እንደሚሉት “ዘመናዊ ልመና” ከተባለ እነዚህ ሁሉ ዐሊሞች ዘመናዊ ለማኞች ናቸው። ከአንደበታቸው ባይወጣም የንግግራቸው <u>**አንድምታ**</u> ይህን ነው የሚሰጠው። “ጀምዒይ” ማለት “ሒዝቢ”፣ “ስውር ኢኸዋኒ” ማለት ከሆነ ይሄውና ምድር ላይ የቀረ ሱኒ የለም።

ይህንን አቋም የምታራምድ ወንድሜ ሆይ! ከዚህ በኋላ የማንን ኪታብ ነው የምትማረው? ወይም የምታስተምረው? የማንን ፈትዋስ ነው የምታጣቅሰው? የማንን ትምህርትስ ነው የምትከታተለው?! እባክህን ውስጥህን ከስሜት ንፁህ አድርገህ ተመልከት።

## <u>የሚነቅፉም የሚፈቅዱም መኖራቸው ምን ያሳያል?</u>

ከዑለማዎች ውስጥ ማህበርን <u>ሙሉ ለሙሉ</u> በመቃወም ሊጠቀሱ የሚችሉት - ባለኝ መረጃ - ሸይኽ ረቢዕ ብቻ ናቸው። እሳቸውም ቢሆኑ አማራጭ በሌለበት አስገዳጅ ሁኔታ የፈቀዱበትን ንግግራቸውን አሳልፈናል። እነዚህ በማህበር ጉዳይ ሰዎችን ከሱና እያስወጡ ያሉ ወንድሞች ግን ቢያንስ ከፊሎቹ ሸይኽ ረቢዕንም መጎነታተል አልፎም ከሱና ማስወጣት ከጀመሩ ሰንበትበት ብለዋል። ስለዚህ በዚህ ረገድ በቀዳሚነት የሚጠቅሷቸውንም በራሳቸው ፈቃድ ሰርዘዋል። ከዚህ በኋላ ማን ቀራቸው? ከታላላቅ ዑለማዎች ውስጥ ማህበርን በመከልከል በኩል የሚጋራቸው አንድም የለም። አንድ

ሊጠቅሱት የሚችሉት ከበርካታ ዑለማዎች የትችት ዶፍ የዘነበበትን የሕያ አልሐጁሪን ብቻ ነው።

በሚያዩት ጥፋት እንጂ ማህበርን ከመሰረቱ የማይቃወሙትን አልባኒን፣ ሙሐመድ ኢብኑ ሃዲንና ሙቅቢልንም አንዳንዶች የሚሞግቱትን እንዲሁ ይሁን ብለን እንደወረደ እንቀበልና እነዚህን ተቃዋሚዎች ናቸው እነበል። የሚፈቅዱ ዑለማዎችን ብዛት ናሙና ስላሳለፍኩ አልመለስበትም። ስለዚህ በማህበር ጉዳይ የሚፈቅዱና የሚነቅፉ ሁለት የዑለማእ ጎራዎች አሉ እንበል። በአንድ በኩል ከጥቂትም የሚያንሱ ተቃዋሚዎች፣ በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ በርካታ ደጋፊዎች። አስተዋይ የሆነ ሰው ከዚህ ትልቅ ቁም-ነገር ይማራል። "ብልህ አሽትቱኝ እንጂ አጉርሱኝ አይልም።" አላማዬ ጉዳዩን በቀላል የሂሳብ ስሌት አወራርዶ መቋጨት አይደለም። [14] ይልቁንም ጉዳዩ ተመሳሳይ መስመር ላይ ባሉ በሚከባበሩና በሚዋደዱ ዑለማዎች የተለያየ ሀሳብ የተሰነዘረበት የኢጅቲሃድ ርእስ እንደሆነ ማሳየት ነው። ይሄ ደግሞ ጉዳዩ ቅፅል ስም የሚያስለጥፍና የሚያናቁር እንዳልሆነ ማንም በቀላሉ ይገነዘበዋል። በርግጥ ልክ በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንደሚደረገው በዚህም ላይ ነቀፈም ደገፈም የያዘውን አቋም ሐቅ እንደሆነ የሚያምን አካል አደቡን በጠበቀ መልኩ ከሱ ሊከላከል በሌላው ላይ መልስ ሊሰጥ ይችላል። ግና ወንድማማችነትን በሚያቆራርጥ፣ ህብረትን በሚያናጋ መልኩ መሆን አልነበረበትም። *"የለም በዚህ ሀሳብ ያልተጋራኝን ሁሉ በቢድዐ እፈርጃለሁ"* የምትል ከሆነ፡-

---

[14] በርግጥ በሱና ዑለማዎች መካከል በሚከሰት ልዩነት ላይ ሐቁ **<u>በአብዛሀኛው</u>** ከብዙሃኑ በኩል ነው የሚሆነው፡፡ ይህን የሚደግፉ በርካታ መረጃዎችና የምሁራን ንግግሮች አሉ፡፡

1. *"መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ።"* ግና ከፊትህ ያሉት እነማን እንደሆኑ ተመልከት። ከምታጣቅሳቸው ዑለማዎች እጅግ የላቁና የበዙ ምሁራንን እየተዳፈርክ እንደሆነ ይታይህ።
2. ይህን የምታደርግ ከሆነ ደግሞ የምታጣቅሳቸውንም ዐሊሞች እየተዳፈርክ ነው። ምክንያቱም እነሱ የተለየ ሀሳብ ያንፀባረቁትን በክፉ አላነሱምና።
3. *"ኧይ ዑለማዎቹን ቢፈቅዱም አልነካም"* ካልክ በአንድ ጉዳይ የተለያየ ሚዛን እየመዘንክ እርስ በርስ የሚጋጭ አቋም እያንፀባረቅክ ነው።
4. በርግጠኝነት ይህን አቋምህን በሌሎች የኢጅቲሃድ ርእሶች ላይ አታንፀባርቀውም። ይህም ፍርደ-ገምድልነትህን የሚያጋልጥ ነው።

## <u>አንድም ዐሊም የሌለበት አቋም ውስጥ ነህ!!</u>

ማህበርን ስለፈቀደም ይሁን ስለነቀፈ ማንም *"ከሱና ይወጣል"* የሚል አንድም ዐሊም የለም። አንድም!! ያስተውሉ! እያልኩ ያለሁት *"ማህበር መመስረት የሚፈቅድ ወይም የሚነቅፍ ዐሊም የለም"* አይደለም። እንዲህ የሚል እንዳለማ አሳለፍኩኝኮ። ስለሆነም በሩ ለሂስ ክፍት ከመሆኑም ጋር የትኛውንም አቋም የሚያንፀባርቅ ሰው ወላእና በራእ የሚቋጥርበት ጉዳይ እስካላደረገው ድረስ በዚህ ርእስ መነሻ ብቻ ከሱና ሊወጣ አይችልም።

ስለዚህ አንተ "ጀምዒይ" እያልክ በማህበር ሳቢያ ሰዎችን **<u>ከሱና የምታስወጣ</u>** ወንድሜ ሆይ! ይህን አቋምህን የሚጋራ ከታላላቅ የሱና ዑለማዎች ውስጥ ምድር ላይ አንድም የለም። "ፅኑ መሰረት ላይ ነኝ" ብለህ የምታስብበት ጉዳይ ከዑለማእ የፀዳ፣ ጎረምሶች የሚመሩት ስብስብ እንደሆነ ስታውቅ አያስደነግጥህም?!!! ቆሻሻ የበዛበት፣ የነፍሳት ሲርሲርታ የነገሰበት፣ ክፉ ሽታ የሚሰነፍጥበት፣ ጨለማ የወረረው ኦና ክፍል ውስጥ እራስህን ድንገት

ብታገኘው ምን ይሰማሀል?! የስሜት ቆሻሻ፣ የመሀይማን ጫጫታ፣ አጉል ስነ-ምግባር፣ ጭልጥ ያለ ድንቁርና የነገሰበት፣ የሱና ዑለማዎች የሚዘለፉበት ስብስብ ከዚህ የከፋ እንጂ የተሻለ አይደለም።

## ፈቃጅ ፈትዋዎችን ዋጋ ለማሳጣት የሚደረጉ ብልጠቶችና ብዥታዎች

### 1. መረጣ

ከቀዳሚ ስልቶቻቸው አንዱ "መረጣ" ነው። ማህበርን የሚፈቅዱ በርካታ የዑለማእ ፈትዋዎችን በመደበቅ የሚያወግዙ ንግግሮችን ብቻ አጉልቶ ማውጣት የተካኑበት ስልት ነው። በዚህ ከንቱ ዘዴ ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ማህበር በኢጅማዕ የተወገዘ እንዲመስል አድርገው ሊሆን ይችላል። ጥቂት ሚዛናዊ የሚመስሉት ብዙሃን ያወገዙት እንዲመስል እያደረጉ ያቀርባሉ። ከውስጣቸው ማህበርን <u>**የሚፈቅዱት**</u> ብዙሃን እንደሆኑ የሚናገሩ ግን ጭራሽ አላጋጠመኝም። ይሄ አሳዛኝ ሸፍጥ ነው። ዲናዊ የኺላፍ ጉዳዮችን በዚህ መልኩ የሚያወራርድ ሰው ጆሮ ሊሰጡት የማይገባ ኻኢን ነው። *"ይሄ ዒልም ዲን ነው። ዲናችሁን ከማን እንደምትወስዱ ተመልከቱ"* የሚለውን የኢብኑ ሲሪን ንግግር ልናስታውስ ይገባል። አንድ ሰው *"ሐቁ ከብዙሃኑ አይደለም"* ብሎ ቢያምን እንኳን ጉዳዩን ሲፈትሽ ግን እውነታን ሊደብቅ አይገባም።

### 2. ልጠጣ!

ሌላኛው ስልታቸው ልጠጣ ወይም ግነት ነው። ማህበርን የሚያወግዙ የአንዳንድ ዐሊሞችን ንግግሮች መልእክታቸውን በመለጠጥ ከሱና ለማስወጣት ማዋል። አንዳንድ ዓሊሞች ማህበር ላይ በተመለከቱት ጥፋት ሳቢያ ጠንካራ ትችት ከመሰንዘር ባለፈ ይህን መነሻ በማድረግ ሰዎችን ከሱና

አላስወጡም። ዛሬ በስማቸው የሚነግዱ ሰዎች ግን የዋሆችን በማሳሳት የዐሊሞቹን ትችት ለጠርዘኛ አቋማቸው ፍጆታ እያዋሉት ነው።

### 3. "በሸርጥ ነው"- በቅጡ የማይፈተሽ መከላከያ

እነዚህ ሰዎችን ያለ በቂ ማስረጃ ከሱና የሚያስወጡ ሰዎች "ጀምዒያ" "ጀምዒያ" እያሉ ሲያስተጋቡ እንደ ጀህሚያ ያሉ አደገኛ ዐቂዳ ስላለው አንጃ የሚያወሩ እንጂ እጅግ በርካታ ዑለማዎች ስለሚፈቅዱት ስለማህበር የሚያወሩ አይመስሉም። በጉዳዩ ላይ ድንበር አልፈው ጩኸት በማብዛታቸው ምክንያት ብዙ የዋሆች መደናገጥ ላይ ወደቁ። ይህን የተመለከቱ አንዳንድ ወንድሞች ከያቅጣጫው የዑለማዎችን ፈትዋ ሲያወጡባቸው ጊዜ በመደናገጥ ዜማ እየቀየሩ ነው። ምን የሚል? *"በርግጥ ዑለማዎች ማህበርን ይፈቅዳሉ። ግን የሚፈቅዱት በመስፈርት (በሸርጥ) ነው"* የሚል። መስፈርቱ ምንድን ነው? አድፈንፍነው ነው የሚያልፉት። "በሸርጥ ነው…" እያሉ ከሚያስተጋቡ ውስጥ ሸርጦቹ ምን እንደሆኑ እንኳን የማያውቁ አጋጥመውኛል። እንዲያውም ብዙዎቹ ለተቃውሞ የሚጓጉትን ያክል የመስፈርቶቹ መሟላት አለመሟላት የሚያስጨንቃቸው አይደሉም። ይልቁንም በኢጅማዕ ወይም በብዙሃን ዑለማዎች የተከለከለ ሲያስመስሉ የነበረው አካሄድ ከንቱነቱ ገሃድ ሲወጣ ጊዜ የሚጠጉበት መሸሻ ነው። እንጂ፡-

**ሀ/ ማህበር ከሚፈቅዱት ውስጥ መስፈርት የጠቀሱት የተወሰኑት ናቸው።**

ከተጠቀሱ መስፈርቶች ውስጥ ጎላ ጎላ ያሉትን ሰብሰብ አድርገን ብናይ፡-

- ከቡድንተኘነትና ከጠባብ ወላእና በራእ መራቅ አለባቸው፣
- በጥሩ ኒያ መቋቋም አለባቸው፣
- ከምስጢራዊ ገፅታ የራቁና ፈቃድ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፣
- የማህበሩ መሪዎች ዑለማእ መሆን አለባቸው፣

- አንቀሳቃሾቹ ዐሊሞችም ባይሆኑ ጤናማ ዐቂዳ ሊኖራቸው ይገባል፣
- ህብረተሰቡ ማህበሩን መመስረቱ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፣
- ማንም ቢሆን በማህበሩ ውስጥ መሪነትን ላያስብ፣
- አማራጭ ሲጠፉ ነው ሊከፍቱ የሚፈቀደው፣
- ገንዘባቸውን በባንክ ማስቀመጥ የለባቸውም፣
- በሸሪዐ አስተዳደር ስር መመስረት አይፈቀድም ያለ አለ።

**እነዚህ መስፈርቶች፡-**

- **ክብደታቸው አንዱ ከአንዱ ይለያል።**

- ከፊሎቹ ባይሟሉ ከማህበሩ ፍቁድነት ባለፈ የአንቀሳቃሻቹን ሚንሃጅም ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ ናቸው። ቡድንተኝነት፣ ማህበሩን ያማከለ ወላእና በራእ፣ የመሪዎቹ ዐቂዳ ጤናማ መሆን አለመሆን ለዚህ እንደ ምሳሌ መቅረብ ይችላሉ።
- ከፊሎቹ የስነ-ምግባር ክፍተት ቢሆኑም አደጋቸው እንደ መጀመሪያዎቹ የከፉ አይደሉም። ለምሳሌ በማህበሩ ውስጥ መሪነትን ማሰብ፣ ጥቅምን ማሰብ በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ ይችላሉ።
- ከፊሎቹ የኺላፍ ነጥቦች ናቸው። ለምሳሌ ገንዘብን በባንክ ማስቀመጥ፣
- ከፊሎቹ ወሳኝ ቢሆኑም በአብዛሀኛው የማይጠፉ መስፈርቶች ናቸው። ለምሳሌ "የመሪዎች ፈቃድ መኖር"፣ "ምስጢራዊ ላይሆኑ" የሚሉት በመንግስት እውቅና ስለሚመሰረቱ ያለመሟላት እድሉ ብዙም አይደለም።

➢ **<u>መስፈርቶቹ የሁሉም ዑለማዎች ስምምነት ያለባቸው አይደሉም።</u>**

እነዚህ መስፈርቶች ከፊሉ በአንዱ ከፊሉ ደግሞ በሌላው ዐሊም የተጠቀሱ ናቸው። **<u>አንዱ የጠቀሰውን ሌላው ያልፈዋል። አንዱ ያጠበቀውን ሌላው ያላላዋል። አንዱ የሚያነሳውን ሌላው አስገዳጅ ሁኔታን ከግምት በማስገባት እንደመስፈርትም አይቆጥረውም</u>። በአንድ ዐሊም ብቻ የተጠቀሱ አሉ። ግልፅ ሸሪዐዊ ማስረጃ የሚደግፋቸው ያሉ ሲሆን አሻሚ የሆኑም አሉበት።** ይህም ለሚያስተውል አካል ትልቅ መልእክት አለው። ከዐሊሞቹ አንዱ የጠቀሰው መስፈርት ቢጎድል በዚያ ላይ ተንጠላጥሎ በሰዎች አቋም ላይ ለመፍረድ ከመቻኮል ይልቅ ረጋ ብሎ ማስተዋል እንደሚገባ ወሳኝ ደወል አለው። ሆን ብሎ "አይሟሉም" ብሎ የሚያስባቸው ሸርጦች ላይ ብቻ በማነጣጠር ሸርጦቹን ያስቀመጣቸው ዐሊም ባልሄደበት መልኩ ከሱና ለማስወጣት የሚውተረተር ጠባብ የፊትና ሰው ነው።

ጉዳዩ የእውነት የሚያሳስበው አካል *"የሚፈቅዱት በመስፈርት ነው"* እያለ የዑለማዎቹን ፈትዋዎች ዋጋ ለማሳጣት ከማምራቱ በፊት እራሱን ሊጠይቅ የሚገባው ነገር አለ። ይህም፡-

- መስፈርቶቹ ምን ምን ናቸው? በቂ ግንዛቤ መያዝ አለበት። ለመታዘብ ያክል "በመስፈርት ነው የፈቀዱት" እያለ የሚያነሳን አካል መስፈርቶቹ ምን ምን እንደሆኑ ጠይቀው? ካቀረበልህ፡
- የትኛው ዐሊም በየት ቦታ እንደጠቀሰ እንዲያቀርብ አድርገው። ከራሳቸውም የሚያወሩ ስላሉ ነው። ተጨባጭ መረጃ ካቀረበልህ፡
- ጣቱን የሚቀስርባቸው ማህበራት ከነዚህ መስፈርቶች የቱን እንዳጎደሉ **<u>መረጃ</u>** እንዲያቀረብ ጠይቀው። ካቀረበልህ፡

- እነዚህ መስፈርቶች ቢጎድሉ በሙብተዲዕነት ለመፈረጅ ይቻል ከሆነ የራሱን ሳይሆን **<u>የዐሊሞችን ንግግር በማስረጃ ከነምንጩ</u>** ጠይቀው።
- የሚጠቅሳቸው መስፈርቶች በሌሎች ዐሊሞች በዶሩራ (አስገዳጅ ሁኔታ) ሰበብ የታለፉ ናቸው አይደሉም የሚለውንም ከስሜት ነፃ ሆኖ እንዲፈትሽ ጋብዘው።

ስለዚህ ከሚቃወማቸው አካላት ዘንድ መስፈርቶቹ አልተሟሉም ወይ? ከስሜት ነፃ ሆኖ መፈተሽ ያስፈልጋል። የጎደሉ መስፈርቶች ካሉም በነዚህ ሳቢያ ሰዎችን ከሱና ማስወጣት ይቻላል ወይ? አላዋቂዎችን እየተከተሉ ገደል ከመግባት በፊት ረጋ ብሎ መመልከት የግድ ይላል። በዚህ ረገድ **<u>እንደ ፀሀይ ፍንትው ያለ መረጃ ሳይያዝ ወይም ደግሞ ከዑለማዎች በቂ ጥቆማ ሳይገኝ አንድ እርምጃ መራመድ አደጋ አለው።</u>** ሰዎችን ከሱና ማስወጣት ቀላል ነገር አይደለም። አልኢማም አሕመድ ረሒመሁላህ ***<u>"ሰዎችን ከሱና ማስወጣት ከባድ ነው"</u>*** ይላሉ። [አሱና ሊል ኸላል፡ 1/373]

### ለ/ በዐሊሞቹ የተጠቀሱት ሸርጦች ማህበር ላይ የሚገደቡ አይደሉም።

ዩኒቨርሲቲም ይሁን፣ መርከዝም ይሁን፣ የሐዲሥ ተቋምም ይሁን፣ **<u>የትኛውም ስብስብ</u>** ይሁን ስብስቡን ያማከለ ማቅረብና ማራቅ ከኖረው ወይም ደግሞ ፖለቲካዊ ዝንባሌ ካለው ወይም ደግሞ ሰዎቹ የሱና ሰዎች ካልሆኑ፣ … ሁሉም የተወገዘ ነው። ብዙ አካባቢዎች አጥፊ ሰዎች ማህበራትን ለጥፋቶቻቸው መንጠላጠያ ስለተጠቀሟቸው ጉዳዩ ተያይዞ ገነነ እንጂ **<u>መስፈርቶቹ ጀምዒያ ላይ የተገደቡ አይደሉም።</u>** ይሄው ማህበርን እየተቃወሙ ነገር ግን የራሳቸውን ስብስብ ባማከለ መልኩ ሲያቀርቡና ሲያርቁ እያየን ነው። ይሄ እነሱ ቢያስተባሉትም በገሀድ የሚታይ ሐቅ ነው። ጠርዘኛ አካሄዳቸውን የሚተችን

ሁሉ “ሰለፍዮችን አንቋሿል” በማለት በቀላሉ ያስወጡታል። እራሳቸውን የሱና መለኪያ አድርገዋል። ይሄ አደገኛ አካሄድ ነው።

**ሐ/ <u>ስለመስፈርት ምንም ሳያወሱ ማህበርን የፈቀዱ ዐሊሞች ጥቂት አይደሉም</u>።** ይህም እነዚህ ወንድሞቻችን ሆን ብለው በመደበቅ አጎንብሰው እራሳቸውን የሚሸውዱበት ሐቅ ነው።

## 4. ለዑለማዎች ፈትዋ የራሳቸውን ትንታኔ መስጠት

ሌላኛው ዑለማዎች ማህበር እየፈቀዱ የሰጧቸውን ፈትዋዎች ዋጋ ለማሳጣት የሚጠቀሙበት ዘዴ *“የሚፈቅዱት በሸሪዐ ህግ ስር ሲሆን እንጂ በሰው ሰራሽ አስተዳደር ውስጥ አይደለም”* የሚል ማመሀኛ ነው።

**አንደኛ**፡- ለዚህ ንግግራቸው ማሳመኛ የሚሆን ከዑለማዎቹ ማብራሪያ አያቀርቡም። ካላቀረቡ ደግሞ በሚያነሱት ሙግት ላይ ምን እርግጠኛ አደረጋቸው?! ምናልባት በዚህ ረገድ ቀረብ የሚልላቸው *“ማህበራት፣ <u>በሙስሊም</u> ሀገር ውስጥ ለሃይማኖታዊም ለአለማዊም ጥቅሞች ሲባል መመስረት ይፈቀዳል”* የሚለው የሸይኽ ዘይድ አልመድኸሊ ንግግር ነው። በርግጥ አነጋገራቸው እንደ ቅድመ-ሁኔታ ነው ያሰቡት ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። በዚያ ላይ እሳቸው ከሳዑዲ ውጭ ከሚገኝ ማህበር ጋር በመተባበር ደዕዋ ያደረጉበት ሁኔታ አለ። ደግሞም ማህበር እንደሚፈቀድ በግልፅ በመናገራቸው ከቢድዐ ጋር ለሚያያይዙ ሰዎች ንግግራቸው ምርኩዝ አይሆንም። በተጨማሪም እሳቸው በሌሎች አለማት የሚገኙ ማህበር የመሰረቱ ሰዎችን በዚህ ሳቢያ ከሱና ሊያስወጡ ይቅርና በክፉም አላነሷቸውም።

**ሁለተኛ፡-** የሸሪዐ ህግ ባለበት ሃገርማ የዲኑን ጉዳይ መንግስት እራሱ ሃላፊነቱን ይወስዳል። ለምሳሌ ሳዑዲን ብንወስድ ከኢስላም ጋር የሚያያዙ በርካታ መስሪያ ቤቶች አሏት። የኢስላማዊ ጉዳዮች፣ የደዕዋና ኢርሻድ ሚኒስቴር፣ የሐጅና ዑምራ ሚኒስቴር፣ በመልካም ማዘዝ ከመጥፎ የመከልከል ባለስልጣን መስሪያ ቤት፣ ወዘተ። በርካታ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎችና ተቋማት በመንግስት በጀት ይንቀሳቀሳሉ። ከራሳቸው አልፈው በያመቱ በሺ ለሚቆጠሩ የውጭ ዜጎች ነፃ የኢስላማዊ ትምህርት እድል ይሰጣሉ። መደበኛ ትምህርቶቻቸው እንደተዋረዱ ከታች እስከ ላይ ዲናዊ ትምህርቶችን እንደ መደበኛ የትምህርት አይነት ያካተቱ ናቸው። ሌሎች ተቋሞቻቸውም በብዙ መልኩ ከዲን ጋር ይያያዛሉ። ከዚህ ነጥብ የፈለግኩት ሳዑዲን ማወደስ አይደለም። ይልቁንም ይሄ ሁሉ ሁኔታ ከተመቻቸባት ሃገርና ኢስላምና ሙስሊሞች ብዙ ጫና ከሚያስተናግዱባቸው፣ ባይተዋር ከሆኑባቸው ሃገራት የትኛው ነው ማህበር የሚያስፈልገው?! እንዲያውም ለዚህም ነው አንዳንድ ማህበርን ተቃዋሚ ዐሊሞች የሸሪዐ ህግ በሌለበት ሀገር ብቻ የፈቀዱት።

**ሶስተኛ፡-** ታላላቅ ዑለማዎች በተለያዩ አህጉራት ከሚገኙ ማህበራት ጋር በመተባበር ሲሰሩ እንደነበር መረጃዎች መኖራቸውም የነዚህን ሰዎች አጉል ሙግት የሚያፈርስ ነው። ከተለያዩ የደቡብ ምስራቅ ኤሺያ ሃገራት ለተገኙ ታዳሚዎች ሸይኽ ኢብኑ ባዝ ባደረጉት ንግግር ላይ በማሌዥያና በኢንዶኔዢያ ቢሮዎች እንዳሏቸው በማንሳት በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ ኢስላማዊ ማህበራት፣ ኢስላማዊ ማዕከሎች፣ መድረሳዎችንና ተቋማት ላይ ለሚሰሩ ሰዎች ዱዓእ ያደረጉበትንና ምክር የሰጡበትን መመልከት ይቻላል። [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኒ ባዝ፡ 5/97] ከታላላቅ ዑለማዎች ጋር - **<u>ማህበር መመስረትን ከሚከለክሉትም ጋር ጭምር</u>** - ግንኙነት ያላቸው በሰሜን አፍሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣

ወዘተ የሚገኙ በማህበራት የሚንቀሳቀሱ ሙስሊሞች ዛሬም አሉ። ለማንም እንደማይሰወረው እነዚህ ሃገራት በሸሪዐ አይደለም የሚተዳደሩት።

**አራተኛ፡-** በህንድና በፓኪስታን የተመሰረቱት የዳሩል ሐዲሥ ማህበራት፣ እንዲሁም በግብፅና በሱዳን የተመሰረቱት የአንሷሩ ሱና ማህበራት መስራቾቹ ታላላቅ የሱና ሰዎች ወይም ከታላላቆች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ያላቸው ስብእናዎች ነበሩ። መቼም በነዚህ ሃገራት ውስጥ የሸሪዐ ስርኣት እንደሌለ ይታወቃል። ሸይኽ ኢብኑ ባዝ እንዲህ ይላሉ፡-

> *"በዚህ ዘመናችን - ምስጋና ለአላህ ይሁንና - በርካታ ወደ ሐቅ የሚጣሩ ስብስቦች አሉ። በዐረቢያ ልሳነ-ምድር የሰዑዲያ መንግስት እንደሚያደርገው፣ በየመን፣ በባህረ ሰላጤው ሃገራት፣ በግብፅ፣ በሻም፣ በአፍሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በህንድ፣ በፓኪስታንና በሌሎችም የአለም አካባቢዎች በርካታ ኢስላማዊ ስብስቦች፣ ማዕከሎችና **<u>ኢስላማዊ ማህበራት</u>**፣ ወደ ሐቅ ይጣራሉ፣ ወደሱ ያበስራሉ፣ ከተፃራሪዎቹም ያስጠነቅቃሉ። **<u>የትም ቦታ የሚገኝ ሐቅ ፈላጊ ሙስሊም እነዚህን ስብስቦች ሊፈልግ ይገባል።</u>** ወደ አላህ ዐዘ ወጀል ኪታብና ወደ መልእክተኛው ﷺ ሱና የሚጣሩ የሆኑ **<u>ስብስብ ወይም ማዕከል ወይም ማህበር ካገኘ ይከተላቸው፣ አጥብቆም ይያዛቸው። ልክ በግብፅና በሱዳን እንዳሉት አንሷሩ ሱና፣ በፓኪስታንና በህንድ እንዳሉት አህሉል ሐዲሥ ማህበርና</u>** ሌሎችም ወደ አላህ ኪታብና ወደ መልእክተኛው ﷺ ሱና የሚጣራ፣ ለአላህ ብቻ አምልኮትን ከሚያጠራ፣ ከሱ ውጭ በመቃብር ያሉንም ይሁን ሌላን ከማይጣራ የሆኑት ማለት ነው።"* [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኑ ባዝ፡ 8/181]

## 5. “ችግሮቹ የጎሉት ዛሬ ነው” - ሌላ ማመካኛ

ሌላ የሚፈቅዱ ዑለማዎችን ፈትዋ ዋጋ ለማሳጣት የሚጠቀሙት ስልት *“በነ ኢብኑ ባዝ ዘመን የማህበራት ችግር የጎላ አልነበረም”* የሚል ነው።

**በመጀመሪያ፡-** *ሙግቱ ሙግት ብቻ ነው።* በዘመናቸው ከማህበራት ጋር የተያያዙ ችግሮችና ልዩነቶች እንደተከሰቱ የተለያዩ ፍንጮች አሉና። ለምሳሌ፡-

**አልባኒ፡-** ከማህበራት ጀርባ ቂምና ጥላቻ መከሰቱ ተጨባጭ እንደሆነ ገልፀዋል። [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 792] ሆኖም ግን ሸሪዐዊ ህግጋትን ጠብቀው እንዲጓዙ ቢያሳስቡም ደጋግመው ነው የፈቀዱት።

**ኢብኑ ባዝ፡-** በማህበራትና በጀማዓዎች መብዛት ሳቢያ ስለተፈጠሩ ችግሮች ሲጠየቁ ከልዩነቶች እንዲርቁ ከመምከር ባለፈ *“ልዩነቱ የተፈጠረው በማህበራት ሰበብ ነውና መዘጋት አለባቸው”* የሚል መልእክት አላስተላለፉም። እንዲያውም ጤናማ ዐቂዳ ባላቸው ሰዎች የሚከፈቱ ማህበራት መብዛት ኸይር እንደሆነ መናገራቸውን አሳልፈናል። በሌላም ጊዜ ከዚህ ጋር ተቀራራቢ ይዘት ያለው ጥያቄ ሲጠየቁ ችግሩ ይቀረፍ ዘንድ ማህበራትና ስብስቦች ሊተባበሩ እንደሚገባ ከማሳሰብ ውጭ ማህበራቱን ተጠያቂ አላደረጉም። [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኑ ባዝ፡ 3/284]

**ኢብኑል ዑሠይሚን፡-** በማህበር ምክንያት እስከመወጋገዝ የደረሰ ልዩነት እንደተከሰተ ሲጠየቁ እንደ መዳረሻ እስከተያዘ ድረስ ማህበር መመስረቱ ችግር እንደሌለበት ገልፀዋል። [መጅሙዑ ፈታዋ፡ 18/465-466]

**ሸይኽ ሙቅቢል፡-** ተደጋጋሚ ትችቶችን በማህበራት ላይ መሰንዘራቸው ችግሮቹ በወቅቱ እንደነበሩ የሚጠቁም ከመሆኑ ጋር ግና በጅምላ እንደማያወግዙ በግልፅ ነው የተናገሩት። [ቱሕፈቱል ሙጂብ፡ 190]

***ሁለተኛ፡-*** ማህበርን ከሚፈቅዱ ዐሊሞች ውስጥ ከፊሎቹ ዛሬም በህይወት ያሉ ናቸው። ለምሳሌ ዐብዱል ሙሕሲን አልዐባድ፣ ሷሊሕ አሉሐይዳን፣ ዐብዱል ዐዚዝ ኣሊ ሸይኽ፣ ሷሊሕ አስሐይሚ፣ ሷሊሕ ኣሊ ሸይኽ፣ ዑበይድ አልጃቢሪ፣ ሱለይማን አሩሐይሊ፣ ሙሐመድ ሰዒድ ረስላን፣ ሙሐመድ ዐሊ ፈርኩስ፣ ወዘተ። ይህም *"ዛሬ በማህበራት ሰበብ የመጣውን ችግር ቢያዩ ኖሮ ዐሊሞቹ ይከለክሉ ነበር"* የሚለው ሙግት ባዶ ጩኸት እንደሆነ ያሳያል።

### 6. "ማህበር ቢድዐ ነው" - ሌላው የተብዲዕ መንጠላጠያ

ማህበርን የሚፈቅዱና በማህበር ውስጥ የሚሰሩ ሰዎችን በቢድዐ የሚወርፉ ሰዎች አንዱ መነሻቸው ማህበር በሰለፎች ዘመን ያልነበረ ቢድዐ ነው የሚል ነው። ለዚህ ተቃውሞ የሚሰጠው መልስ ሁለት አይነት ነው። አንዱ "ማህበር እውን ቢድዐ ነው ወይ? በዚህ ላይ ዐሊሞች ምን ይላሉ?" የሚለውን ማየት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ "ቢድዐ ቢሆንስ ከዚህ ጋር የተነካኩ ሰዎች በሙብተዲዕነት ለመፈረጅ በቂ ምክንያት ነው ወይ?" የሚለውን መፈተሽ ነው። ሁለቱም ወሳኝ ነጥቦች ስለሆኑ በየተራ እንመልከታቸው።

**አንደኛ፡- እውን ማህበር ቢድዐ ነውን? ዐሊሞች ምን ይላሉ?**

*ሀ/* በቅድሚያ ሊሰመርበት የሚገባው ነገር ማህበራት መዳረሻ እንጂ በራሳቸው ወደ አላህ መቃረቢያ ዒባዳ አይደሉም። ሸሪዐዊ ግቦችን ለማሳካት

የሚውሉ መዳረሻዎችን በአምልኮት ውስጥ ከሚፈፀሙ ቢድዐዎች ለይቶ ማየት ያስፈልጋል። ሺሃቡዲን አልቀራፊ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*"እወቅ! መዳረሻዎች ሊዘጉ ግዴታ የሚሆንበት ቦታ እንዳለ ሁሉ ሊከፈቱ ግዴታ የሚሆንበትም አለ። የሚጠላበት፣ የሚወደድበትና የሚፈቀድበትም እንዲሁ። … ወደ ሐራም የሚያደርስ መዳረሻ ሐራም እንደሆነው ሁሉ ወደ ዋጂብ የሚያደርሰው ደግሞ ዋጂብ ነው። … የአሕካም መደቦች ለሁለት ይከፈላሉ። (አንዱ) ግቦች ናቸው። እነሱም በራሳቸው ጥቅሞችንና ጉዳቶችን ያካተቱ ናቸው። (ሌላኛው) መዳረሻዎች ናቸው። እነሱ ወደ ግቦች የሚያደርሱ ናቸው። ብይናቸውም (ሜፍ ላይ) የሚያደርሱት ነገር የክልከላ ወይም የፍቁድነት ብይን ነው። ምንም እንኳን ደረጃቸው ከግቦች ብይን ዝቅ ያለ ቢሆንም። ወደ ላቁ ግቦች የሚያደርሱ መዳረሻዎች የላቁ መዳረሻዎች ናቸው። ወደ መጥፎ ግቦች የሚያደርሱ መዳረሻዎች መጥፎ መዳረሻዎች ናቸው። ወደ መካከለኛ ግቦች የሚያደርሱ ደግሞ መካከለኛ ናቸው።"* [ሸርሑ ተንቂሒል ፉሱል፡ 449]

## ለ/ የዑለማዎች አካሄድ

ሁሉም ለማለት **<u>በሚቀርብ</u>** ታላላቅና ታዋቂ ዑለማዎች ማህበር መመስረትን ፈቅደዋል። በዚህ መፅሐፍ ላይ ማህበር የመሰረቱ፣ የፈቀዱ፣ ሀላፊ ወይም አባል ሆነው የሰሩ፣ እንደሚቻል በግልፅ የተናገሩ፣ ያወደሱ፣ …. ከ 30 በላይ ዑለማዎችን ተመልክተናል። እንዲያውም ኋላ አቋማቸውን ከመቀየራቸው በፊት ሸይኽ ረቢዕ ይህንን ነገር የሚቃወም ከዑለማእ አንድም እንደማያወቁ የገለፁበትን አሳልፈናል። ይህም እነዚህ ዑለማዎች ዘንድ ጉዳዩ

ቢድዐ እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል። ከፊሎቹ ደግሞ ማህበር መመስረት ጭራሽ ቢድዐ እንዳልሆነ በግልፅ ተናግረዋል። ለምሳሌ፡-

**ሸይኹል አልባኒ፡-** *"መተባበር ከሸሪዐ አንፃር የሚፈለግ ነው። **<u>መዳረሻዎቹ ደግሞ ከዘመን ዘመን፣ ከቦታ ቦታ፣ ከሀገር ሀገር ሊለያዩ ይችላሉ።</u>** ስለዚህም <u>በዚህ መሰረት የሚቋቋምን ማህበር በሒዝቢያና በቢድዐ መወንጀል ይሄ ይጓዙበት ዘንድ ቦታ የሚሰጠው አቋም አይደለም</u>።"* [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ ካሴት ቁ. 590]

**ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን፡-** ማህበር "ቢድዐ ነው" "አይ አይደለም" በሚሉ ወጣቶች መካከል በተነሳው ልዩነት ሳቢያ የከረረ መሰዳደብ ውስጥ እንደተደረሰ ለቀረበላቸው ጥያቄ ***<u>"ለሸሪዐዊ ግብ መዳረሻ የሆነ በራሱ በመዳረሻው አምልኮት ካልታሰበበት በስተቀር ችግር የለበትም"</u>*** ሲሉ መልሰዋል። [መጅሙዑ ፈታዋ፡ 18/465-466]

**ሸይኽ ሷሊሕ አሉሐይዳን፡-** ***"እያንዳንዱ ሰው ምንም አይነት የቢድዐነት ቦታው በሌለበት ነገሮችን 'ቢድዐ ናቸው' እያለ ከመሞገት ሊታቀብ ይገባል"*** ብለዋል። [ሸርሑ ኪታቢ ተውሒድ፡ 15ኛ መጅሊስ]

### ሐ/ "መዳረሻም ቢሆን ቢድዐ ነው" ቢባልስ?

*"አይ መዳረሻነቱ አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ በነብዩ ﷺ ዘመን መፈፀም የሚችል ስለነበር ከቢድዐነት አይወጣም"* ሊሉ ይችላሉ። ይሄም ልክ አይደለም። ምክንያቱም በአሁኑ ሰዐት ሸሪዐ በሌለበት ሃገር ይቅርና በሳዑዲ እንኳን ሰፋ ባለ መልኩ ገንዘብ እየሰበሰቡ ለችግረኞች ለመላክ ፈቃድ ያስፈልጋል። በህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ከርቸሌ የወረዱ ዱዓቶች እንዳሉ አይዘንጋ።

ይህም የሆነበት ምክንያቱ ለኸዋሪጆችና ጠርዘኛ ቡድኖች ገንዘብ እሰረገ እንደሆነ ስለተደረሰበት ነው። በሌሎች ሃገራት ደግሞ ይበልጥ ህጉ የጠበቀ ነው። ተራ የደዕዋ እንቅስቃሴዎች ሳይቀሩ በህግ ጥላ ስር እንዲሆኑ የሚገደዱበት ሁኔታ ቀላል አይደለም። **ስለዚህ ማህበራቱ ዛሬ ላይ እየተከፈቱ ያለበት ቀዳሚው ምክንያት ድሮ ያልነበረ ነው።**

## መ/ በአስገዳጅ ምክንያት የሚፈፀሙ ሰበቦች በቢድዐ አይገለፁም።

የሆነ ሰው፡ *"እነ ኢማሙ አሕመድ በዚያ ፈተና ዘመን እንኳን ማህበርን አልተጠቀሙትም"* የሚል *"ለአስገዳጅ ነገር እንኳን መጠቀም አይቻልም"* አይነት አንድምታ ያለው ብዥታ ሲያነሳ ሰምቻለሁ። ይሄ አቋም ከተቃዋሚ ዑለማእ እራሱ አንድም የሚጋራው አይገኝም። ምክንያቱም **አስገዳጅ ችግር ካጋጠመና ምርጫ ከጠፋ የማይፈቅድ ዐሊም የለምና።** "ተቃዋሚ" የሚባሉት እራሱ አስገዳጅ ሁኔታ እያለ ማህበርን መቃወም ደዕዋውን መግደል እንደሆነ የገለፁበትን አሳልፈናል። በዚያ ላይ፡-

- *"ችግሮች ያልተፈቀዱ ነገሮችን ያስፈቅዳሉ"* الضرورات تبيح المحظورات
- *"ያለሱ ግዴታ ነገር የማይፈፀምበት ነገር እሱ እራሱ ግዴታ ነው።"*

  **ما لا يتم الواجب إلا به فهو واجب**
- *"ሁለት ጎጂ ነገሮች ባንድ ላይ ከመጡ ጉዳቱ የቀለለውን መፈፀም ይገባል።"* إرتكاب اخف المفسدتين عند التزاحم

የሚሉትን መርሆዎች የጣሰ ነው ይሄ ትንታኔ።

ደግሞ የማህበር አላማ በመንግስት እውቅና ስር ሆኖ አላማን ማሳካት ነው። ይህን አሰራር የዘመናችን መንግስታት እንዲቀበሉ ጫና ያሳደረባቸው እራሱን የቻለ ምክንያት አለ። እንዲህ አይነቱ አካሄድ በቀደሙት ዘመናት የተለመደ ካለመሆኑም ባሻገር እምብዛም የሚሞከር አልነበረም። እነ ኢማሙ አሕመድ "ቁርኣን ፍጡር ነው" የሚለውን ኩፍር እንዲቀበሉ ሲያስገድዷቸው የነበሩት መሪዎች አልነበሩምን?! ታዲያ "ካልተቀበላችሁ" እያሉ የሚያሰቃዩበትን ኩፍር እንዲቃወሙ ነው እንዴ ፈቃድ የሚሰጧቸው?! ሙግታችንን ምክንያታዊም ህሊናዊም ብናደርገው መልካም ነው።

ስለዚህ ለአስገዳጅ ጉዳይ የሚፈፀሙ ነገሮች ከቢድዐ ፅንሰ-ሀሳብ ጋር ተጨፍልቀው አይታዩም። ምናልባት ለአንዳንዶች ዶሩራው አይታያቸው ይሆናል። እልፍ አእላፍ የቲሞችን መርዳት፣ ሙስሊሞች ደካማ በሆኑባቸውና ሰለምቴዎች በሚበዙባቸው አካባቢዎች መስጂዶችን መገንባት፣ መሰናክል በሚበዙባቸው በተለይም በካፊር ሃገራት በፈቃድ ስር ሆኖ ማስተማር፣ በግለሰቦች ጥረት ለማቋቋም የሚከብዱ በድርቅ፣ በጎርፍ፣ በጦርነት የተጎዱ ወገኖችን መደጎም፣ ... በግለሰብ ደረጃ የሚሞከሩ ስራዎች አይደሉም። እነዚህ ሃላፊነቶች የነፍስ-ወከፍ ግዴታ ባይሆኑም ችላ ቢባሉ ሙስሊሞች እንዳለ ተጠያቂ የሚሆኑባቸው ፈርዶል ኪፋያ ናቸው። ከፊሎች በህግ ጥላ ስር ሆነው ካልሰሯቸው በምን መልኩ ሊፈፀሙ ይችላሉ?! ጉዳዩን ከሰፈር አጀንዳ አውጥቶ አርቆ መመልከት ይበጃል።

በርግጥ ማህበር መመስረት ቢድዐ እንደሆነ የአንድ ዐሊም ንግግር ያጣቅሳሉ፣ የሸይኽ ረቢዕን። [15] ነገር ግን የሸይኹን ንግግር በመመርኮዝ ፅንፍ ለሚረግጡ አካላት የሚሰጣቸው መልስ ቢኖር፡-

- ከዚህ የተለየ አቋም ያንፀባረቁ በርካታ ዑለማዎች ማህበር መመስረት ከቢድዐ ጋር እንደማይያያዝ በግልፅ እንደተናገሩ አሳልፈናል።
- ከሸይኽ ረቢዕ ቃላቸውን እንደወሰዳችሁ አፈፃፀማቸውንም ውሰዱ። ሸይኹ ማህበርን በቢድዐ ቢገልፁም የሚፈቅዱ ዑለማዎችን ግን ከሱና ሊያስወጡ ቀርቶ አልኮነኑም።
- ደግሞም ከቁርኣን፣ ከሐዲሥ፣ ከዑለማእ ኢጅማዕ ውጭ የአንድን ዐሊም ንግግር በሌሎች ላይ መጫን ፈፅሞ አያዋጣም። ሸይኽ ረቢዕ እራሳቸው እንዲህ ይላሉ፡-

*“ዛሬ ካለንባቸው ፈተናዎች ውስጥ - ከፊል ሰለፍዮች ዘንድ ጭምር ያለው- የሚፃረራቸው አካል ዘንድ ግልፅ ማስረጃ ቢኖር እንኳን ‘እከሌ እንዲህ ብሏል’ ‘እከሌ እንዲህ ብሏል’ በሚል ሙጭጭ ማለታቸው ነው። ይሄ ከጥመት ሰዎች መንገዶች ውስጥ ነው። ሰውየው የፈለገውን ደረጃ ቢደርስ የሰለፍያ መንገድ እንዲህ አይነት አካሄዶችን እውቅና አይሰጥም። ሰውየው ማስረጃ የማይደግፈው ፈትዋ ከሰጠ ወይም ንግግርን ከተናገረ ንግግሩን ሊቀበሉት አይፈቀድም። **<u>እናከብረዋለን፣ እናልፈዋለን፣ መሰል ነገሮችንም እናደርጋለን።</u>** ነገር ግን ከአላህ*

---

[15] ሰዎች ግን ለምንድን ነው የሚያብጠለጥሉትን ሸይኽ እየመረጡ የሚያጣቅሱት?! ሸይኽ ረቢዕ፣ ሙሐመድ ኢብኑ ሃዲና ዑበይድ አልጃቢሪ ቢያንስ ከፊሎቹ ዘንድ ቦታ የላቸውም፡፡ ግና እየመረጡ ከሚፈልጉት ቦታ ያጣቅሷቸዋል፡፡ ይሄ ስሜትን መከተል አይደለምን?!

*መልእክተኛ ﷺ በስተቀር ማንም ቢሆን ንግግሩ ሊወሰድ ወይም ሊመለስ ይችላል። ስለሆነም ከአላህና ከመልእክተኛው ﷺ ማስረጃ ያለው ንግግሩን መመለስ አይፈቀድም።"* [አልመጅሙዑ አራኢቅ፡ 419]

**ሁለተኛ፡-** *"ቢድዐ ቢሆንስ ከዚህ ጋር የተነካኩ ሰዎች በሙብተዲዕነት ለመፈረጅ በቂ ምክንያት ነው ወይ?"* የሚለው ሌላው ወሳኝ ጥያቄ ነው። ይህንንም ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመልከት ይበጃል፡-

**ሀ/** ቢድዐ ላይ የወደቀ ሁሉ ሙብተዲዕ ይባላል ወይ? በጭራሽ!! ምናልባት <u>**አንዳንዱ**</u> ሰው *"ማህበር ቢድዐ ነው"* የሚለው ድምዳሜ ካደላበት *"ከማህበር ጋር የተነካኩ ሰዎች ሙብተዲዖች ይሆናሉ"* የሚል ውሳኔ ላይ መድረስ እንዳለበት ሊያስብ ይችላል። ይሄ ግን የተሳሳተ እሳቤ ነው። ሙብተዲዕንና ቢድዐ ላይ የወደቀን ያለ ልዩነት የሚያቀላቅለው "ሐዳዲያ" የተሰኘው ተስፈንጣሪ ስብስብ ነው።

**ለ/** ከታላላቅ አኢማዎች ውስጥ ቢድዐ የሆነን ነገር በተጨባጭ የፈፀሙ ወይም የተናገሩ እጅግ ብዙ ናቸው። ቢድዐ ላይ የወደቀን ሁሉ "ሙብተዲዕ ነው" የምንል ከሆነ ከአኢማዎቻችን ብዙዎቹን እንጥላለን!!

**ሐ/** የአንድ እጅ ጣቶችን እንኳን ከማይሞሉት ውጭ ዑለማዎች በሙሉ ማህበራትን ፈቅደዋል። ስለዚህ *"ማህበር ቢድዐ ነው። ቢድዐ ላይ የወደቀ ደግሞ ሙብተዲዕ ነው"* አይነት የምንጓዝ ከሆነ ማህበርን የፈቀዱ ዑለማዎች በሙሉ "ሙብተዲዖች ናቸው" እያልን ነው። ይሄ የለየለት ጥመት ነው።

***መ/*** አንዳንዶች፡ *“ዑለማዎቹ ማህበር ቢፈቅዱም፣ ቢመሰርቱም፣ በውስጡ ቢሰሩም፣ ቢያወድሱም እነሱን አንነካም። ‘ጃምዒዮች’ ብለንም አንወርፍም። ምክንያቱም እነሱ ሙጅተሂዶች ስለሆኑ በስህተታቸው ተጠያቂ አይሆኑም”* እያሉ ነው።

በመጀመሪያ “ማህበር ይፈቀዳል” የሚለውን አቋም ለመጣል የሚያስችል ቆራጭና ቀጥተኛ (ሶሪሕ) የሆነ መረጃ ማንም ማቅረብ አይቻለውም። ሶሪሕ መረጃ ቢኖርማ ከአንድ ወይም ከሁለት በስተቀር ይህ ሁሉ ዑለማእ ባልፈቀደው ነበር።

ስለዚህ ጉዳዩ ሁሉም ለማለት በሚቀርብ የብዙሃኑን ፍቃድ ማግኘቱ በጉዳዩ ላይ ሚዛን የሚደፋው አቋም “ይፈቀዳል” የሚለው እንደሆነ፣ ምናልባት ወረድ ከተባለ ደግሞ የኢጅቲሃድ ስህተት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በኢጅቲሃድ ርእስ ደግሞ ማንም ማንንም ከሱና ሊያስወጣ አይፈቀድለትም። ምክንያቱም አንድ ሙጅተሂድ ሐቅን ቢገጥም ሁለት ምንዳ ካልገጠመ ደግሞ አንድ ምንዳ አለውና።

ታዲያ አንድ ሙጅተሂድ በሆነ ነጥብ ላይ ቢሳሳት እንደማይጠየቀው ሁሉ ሙጅተሂድን የሚከተልም ተጠያቂ አይሆንም። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- ***“በኢጅቲሃድ ርእሶች ላይ የከፊል ዑለማዎችን ንግግሮች ተከትሎ የሰራ ሰው አይወገዝም፣ አይኮረፍም።*** *ከሁለቱ አቋሞች በአንዱ የሰራ ሰው አይወገዝም። በጉዳዩ ላይ ሁለት አቋሞች ካሉና ሰውየው ከሁለቱ አንዱ ሚዛን ከደፋለት በሱ ይሰራበታል። ያለበለዚያ ግን ሚዛን የሚደፋውን በመግለፅ በኩል እምነት የሚጥልባቸውን ከፊል ዑለማዎች ይከተል።”* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 20/207]

የአንድ ወይም የሁለት ዐሊሞችን ፈትዋ ተከትለው “ማህበር ክልክል ነው” የሚሉ ሰዎች ቢሳሳቱ በቢድዐ ካልተፈረጁ፣ የሰላሳ የአርባ ዑለማዎችን ብይን የተከተሉስ ምናልባት አቋማቸው ስህተት ከሆነ እንዴት በቢድዐ ይፈረጃሉ?! ቁም-ነገሩ የሚነቅፍንም ይሁን የሚደግፍን ፈትዋ የሚከተል ሰው መለኪያው ስሜቱ ሊሆን አይገባም። መለኪያው ስሜቱ የሆነ ሰው ሐቅን ቢገጥምም ከተጠያቂነት አያመልጥም። የዐሊሞቹን አቋም *“የኢጅቲሃድ ስህተት ነው”* እያለ እያለፈ እነሱን የተከተሉ ሰዎችን ግን ድንበር አልፎ በቢድዐ የሚፈርጅ ሰው የራሱን ስሜት ተከታይ መሆን በገሃድ እያጋለጠ ነው። ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*“ከሰዎች ውስጥ ኢጅቲሃድ የሚፈቀድበትን ርእስ ለልዩነትና ለመበታተን መንሰኤ የሚያደርግ አለ። ምናልባትም እራሱ ጠማማ በሆነበት ጉዳይ ወንድሙን በጥመት የሚገልፅ ሁሉ አለ። ይሄ በዚህ ዘመን ከተስፋፉ መከራዎች ውስጥ ነው። በዘመናችን በተለይም ወጣቱ ዘንድ ባለው መነቃቃት ጥሩ ተስፋ ከመኖሩ ጋር። ምናልባትም በዚህ ልዩነት ምክንያት ይሄ መነቃቃት ተበላሽቶ ጥልቅ እንቅልፍ ሊከተል ይችላል። እያንዳንዱ ቁራጭ ማስረጃ በሌለበት የኢጅቲሃድ ጉዳይ ላይ ወንድሙ በተለየው ጊዜ ከሱ ወደ ማስበርገግ ያመራል። ይሰድበዋል፣ በክፉ ያነሳዋል። ይሄ ፈተና ከማንም በላይ የሚደሰቱበት የዚህ መነቃቃት ጠላት የሆኑ ሰዎች ናቸው። ‘በሌሎች ስብከት እፎይ አልን። ችግራቸውን በመካከላቸው አደረገው’ ይላሉና። አላህ ይጠብቀንና አንዳንዱ ሰው አመፀኞችን ከሚጠላው በላይ የዲን ወንድሙን እስከሚጠላ ደርሷል። ይሄ ያለጥርጥር ጉዳት ነው። ተማሪዎች ይሄ በኛ በሁላችንም ላይ የሚያሳድረውን ጉዳት ሊያስተውሉ ይገባል። ያንተ ንግግር ልክ ለመሆኑ ከአላህ ወሕይ መጥቶልሃልን? ንግግሩ ልክ*

*ለመሆኑ ወሕይ ካልመጣለት ምን አሳወቀው? ምናልባትም የዚያኛው አቋም ልክ ሆኖ እሱ ጥመት ላይ ሊሆን ይችላል። ይሄ ነው ተጨባጩ። ዛሬ ከሰዎች ማንም ወሕይ አይመጣለትም። ቁርኣንና ሱና ከፊት ለፊታችን ነው። ጉዳዩ ኢጅቲሃድ የሚያስተናግድ ከሆነ አንዳችን ወንድሙን ኢጅቲሃድ ባደረገበት ነገር ሊያልፈው ይገባል።"* [አሸርሑል ሙምቲዕ፡ 5/137-138]

## 7. "ለሰው ሰራሽ ህግ እውቅና ይሰጣሉ"- ሌላኛው ምክንያት ነው

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ እየተራገበ ያለው ማህበራቱ በደንባቸው ላይ የሃይማኖት እኩልነትን ተቀብለው፣ ለሀገራት ህጎች ስለሚፈርሙ በነሱ ላይ የሚሰሩ ሰዎችን "ሙብተዲዖች" ለማለት በቂ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱ አሉ።

***በመጀመሪያ፡-*** በማህበራትና ተቋማት ደንብ ላይ ይሄ ሀሳብ እንዲካተት የሚያስገድድ ህግ ስለመኖሩ ተጨባጭ መረጃ መያዝ ያስፈልጋል። እኔ ባደረገኳት ደካማ ጥረት አስገዳጅ ህግ መኖሩን ማረጋገጥ አልቻልም። ብቻ በቂ መረጃ ሳይዙ በዚህ ጉዳይ ሰዎችን መወንጀል ያለ እውቀት ማውራት ነው። እንዲያውም ይህን ሀሳብ የሚያፈርሱ ናሙናዎች በተጨባጭ አሉ። ይሄ ቀዳሚው መልስ ነው። ይስተዋል! ክፍተት ያለባቸው ደንቦችን እየመዘዙ ሁሉንም በዚያ መልኩ መፈረጅ፣ አልፎም አሳሪ ህግ እንዳለ ማውራት ያለበቂ መረጃ መደምደም ነው።

***ሁለተኛ፡-*** "የእምነት እኩልነት" ማለት ከሀገራቱ ህግ ፊት ያለውን እንጂ የሚገልፀው "ሃይማኖቶቹ እኩል ናቸው" የሚል ኢማን እንዲኖርህ አይደለም። ማንም ቢሆን የሌላው ሃይማኖት "ልክ አይደለም" ብሎ ስለሚያምን ነው

አንድን እምነት የሚከተለው። አላማው ሰዎች በእምነታቸው ሳቢያ አድሎና ጭቆና እንዳይደርስባቸው ማድረግ እንጂ ሁሉም ሃይማኖቶች "እኩል ልክ ናቸው" የሚል እምነት እንዲኖርህ አይደለም። ሃገራቱ በሚያወጡት ህግ ፊት እምነቶች እኩል እንደሚታዩ የሚሞግቱትን በተግባር ቢያስገኙት ኖሮ ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን ለማንፀባረቅ መሰናክል ባልበዛባቸው ነበር። ሙግታቸው እውነታ ቢኖረው ኖሮ መስጂድ ለመስራት ደም ባልፈሰሰ፣ ፀረ ሒጃብ ህጎች እዚህም እዚያም ባልወጡ ነበር።

**ሶስተኛ፡-** በመርህ ደረጃ ማህበራት ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ነዋሪዎችና ተቋማት የአገሪቱን ህግና ደንብ እንዲያከብሩ ይገደዳሉ። በቅጡ አለማስተዋል እንጂ ይሄ የተለያዩ ሰነዶችና ውሎች ሲፈረሙ፣ የተለያዩ ግልጋሎቶች ሲጠየቁ የሚያጋጥም ነው።

**አራተኛ፡-** አንድ አካል የሆነን ወሳኝ ጉዳይ ለማስፈፀም ስላስፈለገው ይህን የሚባለውን ህግ ቢፈርም በውስጡ ያሉ ይዘቶችን በሙሉ እንደ እምነት ተቀብሏል ማለት አይደለም። *"መፈረሙ በውስጡ ያሉ ህጎችን መቀበሉን ያሳያል"* ብሎ የሚያምን ካለ ሊያከፍር ግድ ይለዋል።

**አምስተኛ፡-** በተለያዩ አለማት የነበሩ ማህበራት ከፊሎቹ በታላላቅ ዑለማዎች የተከፈቱ ሲሆን ከፊሎቹ ደግሞ ዑለማዎች ጋር አብረው ሲሰሩ የነበሩ ናቸው። በነዚህ ሃገራት ያለው ስርኣት ምድራዊ ህግ መሆኑ ይታወቃል።

**ስድስተኛ፡-** በዚህ ጉዳይ ሰዎችን ከሱና ከሚያስወጡ ሰዎች ውስጥ በተለያየ መልኩ ለነዚህ ህጎች የሚፈርሙበት ሁኔታም አለ። ምሳሌ ብንወስድ አንድ ሰው የካናዳን ዜግነት መቀበል ቢፈልግ የሀገሪቱን ህገ-መንግስት ሊያከብር

ይፈርማል። ስለዚህ በተለይም በምዕራቡ አለም የሚኖሩ ከማህበራት ቢርቁም ከሱና የሚያስወጡበትን ጉዳይ ግን ይፈፅሙታል። በሌሎች አለማትም በሌሎች የስራ ዘርፎችም የተቀመጡ ህጎችን ለማክበር የሚፈርሙበት ሁኔታ ቀላል አይደለም። የተለያዩ ማህበራዊ ድረ-ገፆች፣ ሶፍት ዌሮችና አፕሊኬሽኖች ለተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፣ ደንቦችና ህጎች አሏቸው። **ክብደታቸው ቢለያይም** ከነዚህ ውስጥ **ከፊሎቹ ከሸሪዐ ጋር የሚስማሙ አይደሉም**። አነሰም በዛ ሰው ሰራሽ ህግ ከመሆን አያልፉም። ማንኛውም እነዚህን የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚጠቀም ሰው ባለቤቶቹ የሚያቀርቧቸውን ህግና ደንቦች "እቀበላለሁ" ወይም "እስማማለሁ" ብሎ ነው የሚጠቀመው።

ግን ግን በሰነዶች ማረጋገጫ ፅህፈት ቤት በኩል የሚፈፀሙ የተለያዩ ውሎችን፣ ውክልናዎችን፣ የአክሲዮን መተዳደሪያ ደንቦችን፣ ስምምነቶችን፣ ወዘተ የሚያደርጉና የሚያስፀድቁ ሰዎችም በዚህ ድርጊታቸው "ከሱና ይወጣሉ" ይሉ ይሆን? እነዚህ ህጎችና ስምምነቶች በሙሉ የሃገሪቱ ህጎችና አዋጆች አካል መሆናቸው የታወቀ ነው። ለምሳሌ ያክል **የንግድ አክሲዮን የሚከፍቱ ሰዎች በአክሲዮኑ ውስጥ በሚፈጠሩ አለመግባባቶችና አጠቃላይ ሂደት ላይ በሃገሪቱ ህግ እንደሚዳኙ የሚያስገድድ ህግ አለው።**

**ሰባተኛ፡-** የባሰን ችግር ለመጋፈጥ በሚል እሳቤ ማህበር ቀርቶ የፖለቲካ ምርጫ ውስጥ መግባትን ሳይቀር የፈቀዱ ዐሊሞች እንዳሉም ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል። *"ኩዌት ውስጥ ያለው ምርጫ ብይኑ ምንድን ነው? አብዛሀኞቹ በዚህ ጉዳይ ላይ የገቡት ኢስላማውያንና የደዕዋ ሰዎች እንደተፈተኑ ከመታወቁ ጋር። እንዲሁም ዛሬ ያሉት አካባቢያዊ ንኡስ ምርጫዎችስ ብይናቸው ምንድን ነው ያሸይኽ?"* ተብለው ሲጠየቁ ኢብኑል ዑሠይሚን ረሒመሁላህ እንዲህ ሲሉ ነበር የመለሱት፡-

*"እኔ እነዚህ ምርጫዎች **<u>ግዴታ እንደሆኑ ነው የሚታየኝ።</u>** ኸይር አለው ብለን የምናምነውን ልንመድብ የግድ ይላል። ምክንያቱም የኸይር ሰዎች ችላ ካሉ በነሱ ቦታ የሚተካው ማነው?! የሸር ሰዎች ወይም ደግሞ ለእንያንዳንዱ ጪሂ ተከታይ የሆኑ ኸይርም ሸርም የሌላቸው ከንቱ ሰዎች ናቸው!! ስለሆነም ደግ ነው የምንለውን ልንመርጥ **<u>የግድ</u>** ይለናል።"* [ሊቃኡል ባቢል መፍቱሕ፡ 211/13]

የቻለ ፈትዋውን ሙሉውን ቢያየው ጥሩ ነው። ልብ በሉ! ሸይኹ ከ"ይቻላል"ም አልፈው "ዋጂብ ነው" እያሉ ነው። በዚህ ፈትዋቸው ምክንያት እሳቸውን ከሱና ለማስወጣት የሚዳፈር ይኖር ይሆን?!

የሳዑዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴም ፖለቲካዊ ምርጫ ውስጥ መሳተፍን የፈቀዱበት ሁኔታ አለ። [ፈታዋ ለጅነቲ ዳኢማህ፡ 1/373፣ 23/406-407] አልባኒም ምንም እንኳን ምርጫ የሚታለምለትን ግብ እንደማያሳካ ቢናገሩም **<u>በጠበበ ሁኔታ</u>** የፈቀዱበት፣ ሴቶች ሳይቀሩ ወጥተው መምረጥ እንደሚችሉ የተናገሩበት አጋጣሚ አለ። [አልመጀለቱ አሰለፊያ፡ 03/1418] [መጀለቱል አሷላህ] እንዲያውም በዚህ ዘመን ፖለቲካ ውስጥ መግባትን በፅኑ የሚቃወሙት ሸይኹል አልባኒ *"የፖለቲካ ስራ ውስጥ የሚገቡ ሰዎች በቢድዐ ይወነጀላሉን?"* ተብለው ሲጠየቁ በግልፅ በዚህ መልኩ ለመፈረጅ እንደማያስኬድ ነው የገለፁት። [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 347]

ይበልጥ የሚደንቀውን ደግሞ እንመልከት፡- *"በአለማዊ (ሴኩላር) ሃገር ውስጥ ኢስላማዊ ፓርቲዎችን ማቋቋም ይቻላልን? ፓርቲዎቹ በህግ የታቀፉ አፊሻል ቢሆንም አላማቸው ግን ሌላ ነው። ስራቸው ምስጢራዊ የሆነ ማስተማር ነው"* የሚል ጥያቄ የቀረበለት የሳዑዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ የሰጠው

መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡ *“በካፊር ሃገር ውስጥ በመኖር የተፈተኑ ለሆኑ ሙስሊሞች ቢሻው **<u>በኢስላማዊ ፓርቲዎች ስም፤ ቢሻው በኢስላማዊ ማህበራት</u>** ስም ሊሰባሰቡ፣ ሊቀናጁና በመካከላቸው ሊተባበሩ ይፈቀድላቸዋል። በዚህ ውስጥ በበጎ ስራና በተቅዋ ላይ መረዳዳት አለና።”* [ፈታዋ ለጅነቲ ዳኢማህ፡ 23/ቁ. 5651] ፈትዋዉን የሰጡት ኢብኑ ባዝ፣ ዐብዱላህ ኢብኒ ቀዑድ፣ ዐብዱላህ ኢብኒ ጉደያንና ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ ናቸው። ከዚህም ይበልጥ የሚያስደንቁ ፈትዋዎችን መመልከት ይቻላል። [ፈታዋ ለጅነቲ ዳኢማህ፡ 12/ቁ. 6290]

እነዚህን ዑለማዎች በዚህና መሰል ፈትዋዎቻቸው ሳቢያ ከሱና ለማስወጣት የሚዳፈር ይኖር ይሆን?!

ሸይኽ ዐብዱል ሙሕሲን አልዐባድም እንዲሁ፡ *“ምርጫ ላይ ድምፅ ስለመስጠት ምን ይላሉ? በምርጫዎቹ ውስጥ የክርስቲያን ፓርቲ የሚሳተፍ ሲሆን ካሸነፈ በሙስሊሞች ላይ ትልቅ ተፅእኖና ጉዳት እንዳለው ከግንዛቤ ይግባ”* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ ነው የመለሱት፡- ***<u>“የሙስሊሞቹ መግባት የኸይር ሚዛኑ እንዲደፋ የሚያደርግ ከሆነ ይግቡ።</u>*** *መግባታቸው ልዩነት የማያመጣ ከሆነ እንዳይገቡ። መግባታቸው ሸርን ለማራቅ ወይም ሸሩ የቀለለውን፣ ጉዳቱ ያነሰውን ለማምጣት አስተዋፅኦ የሚያበረክት ከሆነ፣ ሙስሊሞች ዝቅተኛ በሚሆኑባቸው ሀገራት እንደሚያጋጥመው* ***<u>(እጩዎቹ) ከራሳቸው ከካፊዎቹ ቢሆን እንኳን (ይፈቀዳል።)”</u>***
http://www.youtube.com/watch?v=EJSonkGzGRc&feature=share

**ይስተዋል፡-**

- ከነዚህ ፈትዋዎች በተቃራኒ የተጓዘ ዐሊም አለ። እነዚህን ፈትዋዎች ያሰፈርኩት በምርጫና በፓርቲ ጉዳይ **ሚዛን የሚደፋው ይሄኛው አቋም እንደሆነ ለማሳየት አላማ አይደለም።** ይህን የምለው *"እነዚህ ፈትዋዎች ስህተት ናቸው"* የሚል ሙግት ቀስቅሶ አጀንዳ ለሚያስቀይስ አካል ቀዳዳ ላለመስጠት ነው።
- ከሰው ሰራሽ ህግ ጋር በተያያዘ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ወይም ምርጫ ላይ የሚነሳው ነጥብ ማህበራት ላይ ከሚነሳው እጅግ የገዘፈ ቢሆንም ለዶሩራ (አስገዳጅ ምክንያት) ሲሆን ከነዚህ ዑለማዎች ድጋፍ ማግኘቱን አስቡት።
- አንድ ነገር ጥፋት ከሆነ እሱን ከመተግበር ይልቅ "ይፈቀዳል" ማለቱ የከፋ ነው። ይህም ከመሆኑ ጋር እነዚህን ዑለማዎች ከማህበርም ባለፈ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ፈቃድ ቢሰጡም ከሱና ሊያስወጣቸው የሚዳፈር አይኖርም። ግፋ ቢል "ተሳስተዋል" ነው የሚባለው ። ታዲያ የጀምዒያ (ማህበር) ጉዳይ ሲሆን የተለየ አቋም የሚንፀባረቀው ለምንድን ነው?

እነዚህን ነጥቦች እንያዝና የሆኑ ሰዎች ይበልጥ አንገብጋቢ የሆኑ ስራዎችን ለመስራት በማለም ፈቃድ ለመውሰድ ያክል ጤናማ ያልሆኑ ህጎችን ያካተተ ወረቀት ላይ ቢፈርሙ *"ጉዳዩ የማይታለፍ ጥፋት ነው ወይ? ጥፋት ከሆነስ ከሱና የሚያስወጣ ነው ወይ?"* የሚለውን ረጋ ብሎ ከላይ የተጠቀሱትን ዑለማዎች አካሄድ እያገናዘቡ መፈተሽ ያስፈልጋል። ውሳኔያችንም መረጣና አድልዎ የገባበት አለመሆኑን ከስሜት ነፃ ሆነን ውስጣችንን ልናዳምጥ ይገባል። ይህ እንግዲህ በመተዳደሪያ ደንቦቹ ውስጥ ለሚነሱት ጥፋቶች እውቅና መስጠትን የሚያስገድድ ህግ እንዳለ ስንቆጥር ነው። እንጂ በተጨባጭ የሚባለው አስገዳጅ ህግ አለ ወይ የሚለውን ማጣራት ያስፈልጋል።

በነገራችን ላይ እነዚህ *“ማህበር ውስጥ ለምድራዊ ህግ እውቅና መስጠት አለበት”* በሚል ምክንያት ሰዎችን ከሱና የሚያስወጡ ሰዎች ደጋግመው የሚያጣቅሷቸውን ፈትዋዎች እንኳን በቅጡ እያገናዘቡ አይደለም። ሸይኽ ሙቅቢል ማህበራትን በተቹባቸው ፈትዋዎቻቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ለሰው ሰራሽ ህጎች እውቅና መስጠት እንዳለባቸው ጠቅሰዋል፡-

***“እነዚህ ማህበራት በማህበራዊ ጉዳዮች (መስሪያ ቤት) ቁጥጥር ስር ሆነው በተወሰኑ መስፈርቶች (ለምሳሌ)፡- ምርጫዎች ሊኖራቸው፣ ገንዘቦቻቸው ወለድ ባለባቸው ባንኮች ሊያስቀምጡ ሆነው እንጂ ፈቃድ የማይሰጥባቸው ናቸው።” “እነዚህ ማህበራት የግድ ለማህበራዊ ጉዳዮች (መስሪያ ቤት) ተገዥ ይሆናሉ። <u>ለሃገሪቱ ህጎች ተገዥ ናቸው።</u>”*** [ዘምሙል መስአላህ፡ 218] [አልጋረቱ ሽዲዳህ ዐላ ጀምዒየቲል ጀዲዳ፡ ካሴት]

ዛሬ በማህበር ጉዳይ አቧራ የሚያስነሱ ወገኖች ከሸይኽ ሙቅቢል ንግግሮች ውስጥ እነዚህን ትችቶች ሀሳባቸውን ለማጠናከር ብቻ ደጋግመው ያወሳሉ። ከሸይኹ ፈትዋዎች ውስጥ ትችቱ ላይ ብቻ እያነጣጠሩ እንጂ አጠቃላይ የፈትዋዎቻቸው ጭብጥ ተጨማሪ ቁም-ነገር አለው። እሱም በጀምዒያ አመሰራረትና አሰራር ውስጥ ለሰው ሰራሽ ህግ እውቅና መስጠት እንዳለ ቢናገሩም **<u>በማህበር ሳቢያ ከሱና ሊያስወጡ ቀርቶ ማህበራትን እራሱ ዝግት አድርገው አለመከልከላቸው ነው።</u>** ይሄውና በድጋሜ፡-

> *<u>“እኛ ማህበራቱን እራሳቸውን እንደምንቃወም ያወራሉ። እውን ማህበራትን እራሳቸውን እንቃወማለን? ምን ማለት ነው ወንድሞቻችን?! አዎ ምን ማለት ነው?!</u> ወንድሞች ሆይ! <u>እኛ</u>*

***<u>ማህበራትን አንቃወምም!! ይሄ በአህሉ ሱና ላይ የሚፈፀም ቅጥፈት ነው።</u>"*** [ሐዚሂ ሱሩሪያ ፈሕዘሩሃ፣ ካሴት]

*"እነዚያን ቡድንተኝነት፣ (ማህበሩን ያማከለ) ጠባብ መወዳጀት፣ ሌብነትና ገንዘብ መሞጭለፍን የያዙትን **<u>አንዳንድ</u>** ማህበራትን እንተቻለን። **<u>እነዚህ ናቸው የምንተቻቸውና ሰዎችን ከነሱ የምናስጠነቅቃቸው የሆኑት።</u>**"* [ቱሕፈቱል ሙጂብ፡ 190]

አንተ ሐቅ ፈላጊ ሆነህ የተሸወድክ ወንድሜ ሆይ! በግልፅ እንዳየኸው ሸይኽ ሙቅቢል በማህበር አሰራር ውስጥ፡- **<u>ለሀገሪቱ ህግ እውቅና መስጠት፣ ምርጫ፣ በባንክ ገንዘብ ማስቀመጥና መሰል መስፈርቶች እንዳሉ እየተናገሩም እንኳን በማህበር ሳቢያ ከሱና ሊያስወጡ ይቅርና በጅምላም አልከለከሉም</u>።** "ይቃወማሉ" ብሎ የሚያወራባቸውንም በአህሉ ሱና ላይ የሚዋሽ **<u>ቀጣፊ</u>** እንደሆነ ይሄው በግልፅ እየተናገሩ ነው። እሳቸው ይህን እያሉ በስማቸው ስትዋሽ አይሰቀጥጥህም? "በጅምላ ይቃወማሉ" ከማለትም አልፈህ በዚህ ምክንያት ከሱና እንደሚያስወጡ ከሞገትክስ ቅጥፈትህ አይከፋምን?!! በል ንገረኝ ይህን ከሱና የማስወጣቱን አቋም ከማን አገኘኸው?!

ጉዳዩ ብዙም ባይገናኝም አንድ ነገር ነክቼ ከዚህ ርእስ ልውጣ። በሰው ሰራሽ ህግ መዳኘት *"ህጉ ከሸሪዐ ይበልጣል ወይም እኩል ነው"* የሚል እምነት ካልተቆራኘው ወይም በሸሪዐ ህግ መካድ ካልተከተለው በስተቀር እንደ ትንሹ ኩፍር ነው የሚቆጠረው። ይሄ በበርካታ ማስረጃዎች የፀና ሐቅ ነው። መረጃ ያልጠቀስኩት ርእሴ ካሰብኩት በላይ ስለረዘመብኝ ነው። ከህገ-ደንብ ጋር አያይዘው በማህበር ጉዳይ ፊትና እየፈጠሩ ካሉ ወንድሞች ውስጥ የአንዳንዶቹ ዳርዳርታ ይህን ከግምት እንዳልተረዱ የሚያሳብቅ ነው።

## 8. "በከሃዲዎች መመሳሰል አለበት"- ሌላኛው መሰላል

ሌላኛው ደጋግመው የሚያነሱት ነገር የማህበር አሰራር ስር መሰረቱ ከካፊሮች ነው። ስለሆነም ማህበር መመስረት ከካፊሮች ጋር መመሳሰል አለበት የሚል ነው። ግን፡-

- የብዙሃኑ ዐሊሞች መፍቀድ <u>**ከነሱ ዘንድ**</u> ጉዳዩ ከመመሳሰል ጋር እንደማይገናኝ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።
- ማህበር መዳረሻ እንጂ በራሱ ዒባዳ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። *"በመዳረሻው መመሳሰልም የተወገዘ ነው"* ከተባለ እነዚህ ተቃዋሚዎች እራሳቸው ምንጫቸው ከካፊሮች የሆኑ ብዙ ነገሮችን ይጠቀማሉ። ማህበራዊ ሚዲያዎችን ለማስተማሪያነት መጠቀም እንደምሳሌ መቅረብ ይችላል። "አይ ይሄ እኮ በሰለፎች ዘመን ስላልነበረ ነው" የሚል ሙግት ዋጋ የለውም። አዋጣም አላዋጣም ለማንም ይህን ማንሳት የሚያስኬደው *"ቢድዐ ነው ወይስ አይደለም?"* ለሚለው ሙግት ነው። አሁን እየተወራ ያለው ስለመመሳሰል ነው። ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ መነሻው ከካፊሮች ስለሆነ ብቻ "መመሳሰል አለበት" እያልን የምናወግዝ ከሆነ እጅግ በርካታ ነገሮችን ለመጣል እንገደዳለን።
- *"አንድ ነገር ከካፊሮች ጋር መመሳሰል የሚሆነው መቼ ነው? ዑለማዎች በዚህ ረገድ ምን ይላሉ?"* የሚለውን በተመለከተ ስለሱሪ ባሰፈርኳት መጠነኛ ዳሰሳ ውስጥ ጥቂት የዑለማእ ንግግሮችን ምዕራፍ ሁለት ላይ አካትቻለሁ።
- በማያወላዳ መልኩ "መመሳሰል ነው" ቢባል እንኳን ሰዎችን ከሱና ለማስወጣት በቂ ምክንያት አይደለም። አንዱ ዐሊም "መመሳሰል አለበት" የሚለውን ጉዳይ ሌላው "በጭራሽ!" እያሉ የተለያዩ ሀሳቦችን

የሚሰነዝሩባቸው ጉዳዮች ሰዎችን ከሱና እስከ ማስወጣት የሚያደርስ ክብደት እንደሌላቸው መረዳት አይከብድም።

## 9. “ማህበራት የፖለቲካ ማስፈፀሚያ ናቸው!”- ሌላ ሙግት

በሚደንቅ ሁኔታ “ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር ይሰራሉ” እያሉ ሲያራግቡ ሁሉ አጋጥሞኛል። ይሄ ነጭ ውሸት ነው። በዚህ መልኩ የሚቃወም ሰው ሲሉ ሰምቶ ከማስተጋባት ውጭ ስለ ማህበር አሰራር ግንዛቤው እንኳን እንደሌለው የሚያጋልጥ ነው። ቀድሞ ነገር የትኛውም ማህበር ፍቃድ ከወሰደበት ዘርፍ ውጭ መስራት አይፈቀድለትም። ይሄ በህግ የተቀመጠ ነው። በተለይ ሃይማኖታዊ ማህበራት በምንም መልኩ ከፖለቲካ ጋር ንክኪ ሊኖራቸው አይችልም። ሆኖ ከተገኘም እርምጃ ነው የሚወሰድባቸው።

በርግጥ ስውር በሆነ መልኩ ማህበራትን ለፖለቲካ ፍጆታ የሚያውሉ አካላት አይጠፉም። ግና ከፖለቲካ ጋር ምንም አይነት ንክኪ የሌላቸው እንዳሉ እየታወቀ ሁሉንም በአንድ መጨፍለቅ፣ አልፎም ምንም መረጃ ማቅረብ በማይችሉበት ሁኔታ ወደሆነ አካል ለውንጀላ ጣትን መቀሰር ብልግናም ጭምር ነው። ምናልባት በውጪው አለም ማህራትን ለፖለቲካዊ አላማ እንደ ድልድይ የተጠቀሙ አካላት ስለነበሩ ወይም ስላሉ ብቻ በሁሉም ሃገራት የሚገኙ ማህበራትን በዚህ መልኩ መፈረጅ ከማንም ቢንፀባረቅ ውሃ የማያነሳ ድምዳሜ ነው።

## 10. “ልመና አለበት”- ሌላኛው ክስ ነው።

በመጀመሪያ የማህበራት የገቢ አሰባሰብ አንድ አይነት አይደለም። እራሱ ረጂው ማለትም መፅዋቹ ማህበራቱን ፈልጎ የሚመጣበት አጋጣሚ ብዙ

ነው። ይህም በዘርፉ ላይ የተሰማሩ ተቋማት እንደመሆናቸው ችግረኞቹን በተመለከተ የተሻለ መረጃ ይኖራቸዋል ከሚል እሳቤ ነው። በዚህ ጊዜ ገንዘቡ የሚመጣው በባለ ማህበራቱ “ልመና” አይደለም። የፕሮፖዛል ጥሪ ተደርጎ ለተሻለ አካል ፕሮጀክት የሚሰጥበት አለ። ይህም ልመና አይደለም። የአባላት መዋጮ ሊኖር ይችላል። ማህበራት አቅም ያላቸውን ሰዎች በአባልነት የሚያቅፉበት ሁኔታ ብዙ ነው። አላማቸውን በሚደግፉ ሌሎች ማህበራት የሚረዱም ብዙ ናቸው። የወቅፍ ንብረት ኖሯቸው እሱን የሚጠቀሙም አሉ። አትራፊ ድርጅት ከፍተው በሱ አማካኝነት እራሳቸውን የሚደጉሙም ይኖራሉ። እነዚህ የገቢ ምንጮች “ልመና” ተብለው የሚገለፁ አይደሉም።

ከዚህ በተጨማሪ በጋዜጣ ጥሪ፣ በአዳራሽ፣ በመስጂድ፣ በአካል፣ ወዘተ ጥያቄ እየቀረበ የሚሰበሰብበት አለ። ይሄኛው ነው “ልመና” እየተባለ ያለው እንግዲህ። ለዚህ ሁለት መልስ መስጠት ይቻላል።

**አንዱ፡-** በዚህ መልኩ ገንዘብ የሚሰበስቡት ባለ ማህበራት ብቻ አይደሉም። የተቸገረ፣ የተጎዳ ወገን ሲኖር፣ መሳጂድ ለመገንባት፣… በየመሳጂዱ፣ በየድግሱ፣ በየገበያ ቦታው፣… ሰዎች ከሰዎች ይሰበስባሉ። ስለዚህ በዚህ ረገድ ማህበራት ብቸኛ አይደሉምና ለተቃውሞ ከመቻኮል ይልቅ መረጋጋት ይበጃል። [16]

---

[16] ***“መስጂድ ውስጥ የልመና ሳጥን ማስቀመጥ የሂዝቢያ አካሄድ እንደሆነ ኡለማዎች ጠቅሰዋል አስሃቡል ጀምዕያት ደግሞ የዳዕዋቸው ነዳጅ ልመና ነው!!”*** ሲል አንዱ በቅርቡ ጠቅሷል፡፡ “ጀምዒዮች” የሚላቸው ሰዎች ያለባቸውን ከሱና የሚያስወጣ ችግር ሲዘረዝር ነው ይህን ያለው፡፡ በዚህ መልኩ ከሚከሳቸው ሰዎች ዘንድ ጉዳዩ አለ ወይስ የለም የሚለውን አጣርቷል ወይ የሚለውን እሱ ከጌታው ጋር የሚተሳሰበው ነው፡፡ ይሁን ብለን እንዳለ እንቁጠርለትና ይሄ እንግዲህ የፊቅህ ሳይሆን የሚንሃጅ ጉዳይ ነው ማለት ነው ከነሱ ዘንድ፡፡ ግን እኮ ይሄን መስጂድ ውስጥ የመዋጮ ሳጥን ማስቀመጥን የከለከሉት እንዳሉ ሁሉ የፈቀዱትም አሉ፡፡ ለምሳሌ ሸይኽ ኢብኑ ባዝ ፈቅደውታል፡፡ http://www.binbaz.org.sa/mat/16368

**ሁለተኛ፡-** በማህበርም ስም ይሁን በሌላ በአግባቡ እስከተወጡት ድረስ ችግረኛን ለመርዳት ሳንቲም መሰብሰብ **የሚያስወድስ እንጂ** የሚያስወቅስ ምግባር አይደለም። የሆነ አካባቢ ላይ ከባድ የጎርፍ መጥለቅለቅ ተከስቶ ብዙ ህዝብ ባዶ እጁን ቀርቶ ተፈናቀለ። እነዚህን ለመርዳት ሰው በየሀብታሙ፣ በየመስጂዱ፣ በየማህበሩ እየሄደ ገንዘብ ቢሰበስብ ምንድን ነው ነውሩ?! ሱብሓነላህ!! ጦርነት ባለባቸው አካባቢዎች እጅግ በርካታ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ይኖራሉ። አንድ ሰው እነሱን ለመታደግ እርዳታ ቢያስተባብር እንዴት እንደወንጀል ይቆጠርበታል?! አንድ ሰው ገንዘብ ሰብስቦ ደካማ የገጠር ሰዎች ዘንድ ገብቶ መስጂድ ቢገነባላቸው በምን ስሌት ነው እንደ ጥፋት የሚቆጠርበት?! የሆነ አካል በጼንጤዎች በርካሽ ጥቅማጥቅም እየተጠለፈ ያለ ወገን እንዳለ ተረድቶ ሰዎችን ለመታደግ የአካባቢው ተወላጆች በሚችሉት እንዲረባረቡ ቢያደርግ ምንድን ነው ጥፋቱ?! ሊወደስ ሲገባው ጭራሽ ይወቀስ?!! ወላሂ ይሄ ልጓም አልባ ተቃውሞ በርካታ ለኸይር ስራ ገንዘብ የሚያሰባስቡ ሰዎችን የሚያሸማቅቅ ወይም ስማቸውን የሚያጎድፍ ውንጀላ ነው። ጴንጤ በየዘርፉ ተሰማርቶ ህዝባችንን በሰበብ አስባብ በሚነጥቅበት ሁኔታ እዚህ ግባ የማይባሉ ደካማ ጥረቶች ላይ ቆሻሻ ስሞችን እየለጠፉ ማሰናከል አደጋው ከባድ ነው። አርቀው ያስተውሉት።

ቀድሞ ነገር የተከለከለው ልመና ምን አይነት ነው? አንድ ግለሰብ ለራሱ እየዞረ መለመኑ ነው። ይሄ ለራስ የሚፈፀም ልመና ለሶስት አይነት ሰዎች ብቻ ነው የሚፈቀደው። እነሱም፡- ሰዎችን ለማስታረቅ ወይም በመሰል

---

እስኪ ማነው በዚህ ፈትዋቸው መነሻ የኢብኑ ባዝን ሚንሃጅ ጥያቄ ውስጥ የሚከት ደፋር?!! ስለዚህ ስሜቱን እስካላስቀደመ ድረስ አንድ ሰው ይህን የኢብኑ ባዝን ፈትዋ ተከትሎ ቢሰራ ከሱና ማስወጣቱ ይቅርና ወንጀለኛስ ለማድረግ ይቻላል ወይ?! ኧረ እየተስተዋለ!

ምክንያት እዳ ላይ ለወደቀ፣ ንብረቱ ለወደመበት እንዲሁም ከወገኖቹ ሶስት አስተዋዮች የሚመሰክሩለት ከባድ ችግር ላይ የወደቀ ሰው ናቸው። እነዚህ ከችግራቸው የሚወጡበት እስከሚያገኙ ድረስ ሊለምኑ ተፈቅዶላቸዋል። [ሙስሊም፡ 1044] ከነዚህ ውጭ ያለ ግን በምንም መልኩ አልተፈቀደለትም።

ነገር ግን ለሶደቃ፣ ችግረኞችን እንዲረዱ ወይም ለመሰል ስራ ሰዎችን መቀስቀስ የሚበረታታ እንጂ የሚወገዝ አይደለም። ነብዩ ﷺ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመስጂድ፣ በዒድ ቦታ ለሰደቃ ሰዎችን ያነሳሱ፣ ሶደቃን ይሰበስቡ ነበር። አንድ ሁለት መረጃ እንመልከት፡-

ከሙዶር ጎሳ የሆኑ በጣም የተቸገሩ፣ የታረዙ ሰዎች መጥተው ነብዩ ﷺ ጉዳታቸውን ሲመለከቱ ፊታቸው ተለዋወጠ። ገቡ፣ ወጡ። ከዚያም ቢላልን አዛን እንዲያደርግ አዘዙት። ኢቃማም ተደረገ። ሰገዱና ኹጥባ አደረጉ። (ሰዎችን ለሶደቃ ቀሰቀሱ።) … አንዱ ሰው በዲናሩ፣ ሌላው ከዲርሃሙ፣ ሌላው ከልብሱ፣ ቁና ስንዴ፣ ቁና ተምር ተሰደቀ። (ነብዩ ﷺ) ***"በተምር ከፋይም ቢሆን (ሰድቁ)"*** አሉ። አንድ ከአንሷር የሆነ ሰው እጆቹ ለመያዝ ሊያቅታቸው የተቃረበ በከረጢት ብር ይዞ መጣ። ኧረ እንዲያውም አቅቷቸዋል። ከዚያም ሁለት የምግብና የልብስ ክምር እስከሚታዩ ድረስ ሰዎች በልገሳው ላይ ተከታተሉ። ነብዩ ﷺ ፊታቸው ወርቅ ቅብ መስሎ እስከሚያበራ ድረስ። ከዚያም የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ፡-

> ***"በኢስላም ውስጥ መልካም የሆነን ሱና የጀመረና ከሱም በኋላ ከተሰራባት የሰራባት ሰው አምሳያ ምንዳ (ለጀማሪው) ይፃፍለታል። ከምንዳዎቻቸው ምንም አይቀንስባቸውም። በኢስላም ውስጥ መጥፎ***

*የሆነን ሱና የጀመረና ከሱም በኋላ ከተሰራባት በሱ (በጀማሪው) ላይ የሚሰራባት ሰው አምሳያ ወንጀል አለበት። ከወንጀሎቻቸው ምንም* ***አይቀንስላቸውም"*** አሉ። [ሙስሊም፡ 1017]

ሌላ ደግሞ ጃቢር ረዲየላሁ ዐንሁ ባስተላለፉት ሐዲሥ ነብዩ ﷺ በዒድ ኹጥባ ላይ ወንዶችን ከመከሩና ከገሰፁ በኋላ ሴቶች ዘንድ በማምራት *"መፅውቱ። ብዞዎቻችሁ በርግጥም የጀሀነም ማገዶዎች ናችሁ"* አሉ። አንዲት ጎንጮቿ ላይ ማዲያት ያለባት ሴት ከሴቶች መሀል በመነሳት *"ለምን የአላህ መልእክተኛ ሆይ?"* አለች። እሳቸውም *"አቤቱታን ስለምታበዙና መልካም ውለታን ስለምትክዱ ነው"* አሉ። ከዚያ ሴቶች ከቢላል ልብስ ላይ እየጣሉ በጌጦቻቸው ሰደቁ። [ሙስሊም፡ 885]

ስለዚህ ለመልካም ስራ ሰዎችን እንዲመፀውቱ ማነሳሳት በማንም አስተያየት የማይናወጥ ጠንካራ መሰረት ያለው ሱና ነው። በነገራችን ላይ ለማህበር ስራ በየሀብታሙ ዘንድ እየዞሩ ገንዘብ ሲሰበስቡ የነበሩ ዑለማዎች ነበሩ። የሸይኽ ሷሊሕ አሱሐይሚን ንግግር አሳልፈናል። ሀብታሞች ለማህበራት እንዲሰጡ ያበረታቱ ወይም የፈቀዱ ዐሊሞችም ቀላል አይደሉም። ለምሳሌ ሸይኹል አልባኒ ረሒመሁላህ ሸሪዐውን የሚጠብቁ ከሆነ ለማህበራት ዘካተል ፊጥር መስጠት እንደሚቻል ተናግረዋል። [ዱሩሱን ሊሸይኺል አልባኒ፡ 26/10] ሸይኽ ኢብኑ ባዝም ዘካ መስጠት እንደሚቻል ተናግረዋል። [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኒ ባዝ፡ 14/254] ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚንም እንዲሁ ገንዘቧን መናዘዝ የምትፈልግ አሮጊት ጠይቃቸው *"የሰው ልጅ ከገንዘቡ የሆነውን ያክል ለመስጂዶች፣* ***<u>ለበጎ አድራጎት ማህበራት፣</u>*** *ለምሳሌ የቁርኣን ተሕፊዝ ማህበራት፣ የተራድኦ ማህበራትና ለመሳሰሉት ሊያደርግ እንደሚገባው እናስባለን"* ይላሉ። [አሊቃኡ ሸህሪይ፡ 40/14]

ከማህበር ጋር የተያያዙ በርካታ ጥያቄዎች ከአውሮፓ፣ ከአፍሪካ፣ ከባህረ-ሰላጤው ሃገራት፣… ለተለያዩ ዑለማዎች ይቀርባሉ። ግና *“ነቅተንባችኋል! የግል ኪሳችሁን ልታደልቡ፣ ባቋራጭ ሀብት ልታጋብሱ ነው”* አላሉም። *“ማህበር የተወገዘ ልመና ስላለበት መስራታችሁን አቁሙ። ማህበርቻሁንም አፍርሱ”* ብለው የሰጡት ፈትዋም የለም። እንዲያውም የሰዑዲያ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ ለማህበራት መስጂዶች ውስጥ ሳይቀር ገንዘብ መሰብሰብ እንደሚፈቀድላቸው ብይን ሰጥቷል። ይሄውና፡- ***“ለበጎ አድራጎት ማህበራት የሚውሉ ልገሳዎችን ከመስጂዶች ውስጥ መሰብሰብ ይቻላል። በዚህ ውስጥ በበጎና በመልካም ነገር ላይ መተጋገዝ አለውና።”*** [ፈትዋ ቁጥር 3664፣ ተራ ቁ. 4] (ፈትዋውን የሰጡት፡ **ኢብኑ ባዝ**፣ **ዐብዱላህ ኢብኑ ቀዑድ**፣ **ዐብዱላህ ኢብኑ ጉደያን**፣ **ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ** ናቸው።)

ሱብሓነላህ! ዐሊሞቹና እነ እንቶኔ ያሉበትን ርቀት ተመልከቱ። **ዐሊሞቹ ከ“ይቻላል”ም አልፈው እያበረታቱ ነው፣ ያውም በመስጂድ ውስጥ!!! እነዚህ ደግሞ ከ“አይቻልም”ም አልፈው እያንቋሸሹ ነው!!! ያውም ከሱና እስከማስወጣት በደረሰ ዘለፋ።**

ሸይኽ ሙቅቢልም እንዲሁ ባለ ማህበራቱና ሰብሳቢዎቹ ታማኞች ከሆኑ ገንዘብ ለነሱ መሰብሰብ እንደሚቻል በግልፅ ተናግረዋል። http://www.muqbel.net/fatwa.php?fatwa_id=2577

ደግሞም በሃገራችን ይሄ ነው የሚባል ብዙ የሙስሊም ማህበር የለም። ያሉት ጥቂቶችም በአብዛሀኛው ሙስሊሞች የሚበዙባቸው አካባቢዎችን እያሰሱ ነው የሚሰሩት። ሙስሊም አካባቢ ላይ ማተኮራቸውም የራሱ ትልቅ መልእክት አለው። እሱም “የኛ” የሚሉትን ህዝብ ችግር

እንዳቅማቸው ለመቅረፍ ማሰባቸው ነው። ሙስሊም አካባቢን በመምረጣቸውና ሙስሊሞች በመሆናቸው ብቻ ስራቸው ላይ ብዙ መሰናከል የሚደርስባቸው ብዙ ናቸው። ሰበብ እየተፈለገ የሚዘጉትም ጥቂት አይደሉም። ወገን በጴንጤ ርካሽ ጥቅማጥቅም በሚጠለፍበት እውነታ ክፍተቶችን ለማረም ከመሞከር ይልቅ እያንዳንዷን የእርዳታ ስራ በሰበብ አስባብ ለማኮላሸት መሮጥ ሃላፊነት የጎደለው አስተሳሰብ ነው።

ስለዚህ ሰብሳቢዎቹ ለግል ኪሳቸው ካላደረጉ ቢለመንስ ምንድን ነው ችግሩ?! አደጋ የደረሰባቸውን፣ ችግረኛ አይታምን፣ አካል ስንኩላንን፣… ለመርዳት፣ መስጂድ ለመስራት በጥሩ ኒያ ቢሰበሰብ ይህን ከተከለከለው ልመና ጋር ምን አገናኘው?! ለሰጪስ ለተቀባይስ ምንድን ነው ችገሩ?!

የሚደንቀው እነዚሁ ተቃዋሚ "ኡስታዞች" እራሳቸው ወይም መርከዞቻቸው የገቢ ምንጭ ስለሌላቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እርዳታ ላይ ጥገኛ የሚሆኑበት አጋጣሚ መኖሩ ነው። በተለይም ካስተማሪዎቹ ውስጥ ይሄ ነው የሚባል ስራ የሌላቸው በተጨባጭ ኑሯቸውን ድጎማ ላይ የመሰረቱ አሉ። *"ጀምዒዮች ዘመናዊ ለማኞች ናቸው"* የሚለው ጩኸታቸው ሳያሳፍራቸው በየጊዜው የማህበር እርዳታ የሚቀበሉም ከውስጣቸው አውቃለሁ። ይህን የምለው መቀበላቸው "ክልክል ነው" ለማለት ሳይሆን ጩኸታቸውና ተግባራቸው የማይገናኝላቸው እንዳሉ ለመጠቆም ያክል ነው። እንጂ ከባለ ማህበራቱ ምንም አይነት ቅድመ-ሁኔታ ካልቀረበ እርዳታን እንደሚቀበሉ ሸይኽ ሙቅቢል እራሳቸው የተናገሩበት አለ።

ሲጠቃለል <u>**ለሐራም አላማ ከተሰበሰበ በየትኛውም መንገድ ቢሰበሰብ ሐራም ነው።**</u> ያለበለዚያ በአግባቡ እስከተፈፀመ ድረስ ለኸይር ስራ ገንዘብ

ከሀብታሞች መጠየቅ ወይም እንዲለግሱ ማነሳሳት በምንም መልኩ የሚያስወቅስ ምግባር አይደለም። ይህን የፈለገ ትልቅ ሸይኽ ቢናገረው እንኳን ልክ አይሆንም። ጌታችን እኮ ***“ምስኪንን በማብላት ላይ ኢታነሳሱም”*** እያለ ነው የሚወቅሰው። [አልፈጅር፡ 18] የራሳችን ወደ ኋላ መቅረት አልበቃ ብሎ እንዴት የሚሰሩትን ስለስራቸው እንተቻለን?!

### 11. *“ገንዘባቸውን በወለድ ባንኮች ያስቀምጣሉ”- ሌላው ተቃውሞ*

በርግጥ ለዚህ ሙግታቸው ማህበራት ገንዘባቸውን በባንክ የሚያስቀምጡ ከሆነ እንደማይፈቀዱ የሚገልፀውን የሸይኽ አልባኒን ፈትዋ መነሻ ያደርጋሉ። ነገር ግን፡-

**አንደኛ፡-** ማህበራት ገንዘባቸውን በባንክ እንዲያስቀምጡ የሚያስገድዳቸው ሁለት ምክንያት አለ። አንዱና ዋናው ምክንያት መንግስት የገቢያቸውን ምንጭ፣ መጠንና አወጣጥ ማወቅና መቆጣጠር ስለሚፈልግ የግድ ባንክ እንዲጠቀሙ ያስገድዳቸዋል። ሁለተኛው ምክንያት በእጃቸው የሚገባን አደራ ለስርቆት ወይም ሌላ አደጋ እንዳይጋለጥ ይሰጋሉ። ለአስገዳጅ ችግሮች ገንዘብ በባንክ ማስቀመጥን ብዙ ዑለማዎች ፈቅደውታልና። ለምሳሌ፡-

### ሀ/ ሸይኽ ዐብዱል ዐዚዝ ኢብኑ ባዝ፡-

*“የሆነ መጠን ገንዘብ ያለው ሰው ከባንኮች ውስጥ ባንዱ በአማና ይቀመጥለት ዘንድ አስቀመጠው። አመት ሲዞረው ዘካውን ያወጣል። ይሄ ነገር ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀድም?”* ተብለው ተጠይቀው ነበር። መልሳቸው ይሄውና፡-

**"لا يجوز التأمين في البنوك الربوية ولو لم يأخذ فائدة؛ لما في ذلك من إعانتها على الإثم والعدوان، والله سبحانه قد نهى عن ذلك، لكن إن اضطر إلى ذلك ولم يجد ما يحفظ ماله فيه سوى البنوك الربوية، فلا حرج إن شاء الله؛ للضرورة، والله سبحانه يقول: (وَقَدْ فَصَّلَ لَكُمْ مَا حَرَّمَ عَلَيْكُمْ إِلَّا مَا اضْطُرِرْتُمْ إِلَيْهِ) ومتى وجد بنكا إسلاميا أو محلا أمينا ليس فيه تعاون على الإثم والعدوان يودع ماله فيه، لم يجز له الإيداع في البنك الربوي"**

> *"ወለድ ባይወስድም በወለድ ባንኮች ውስጥ በአማና ማስቀመጥ አይቻልም። በዚህ ውስጥ በወንጀልና ወሰን በማለፍ ማገዝ አለውና። የጠራው አላህ ከዚህ ከልክሏል። __ነገር ግን ለዚህ ከተገደደና ገንዘቡን የሚጠብቅበት ከወለድ ባንኮች ውጭ ካላገኘ ለአስገዳጅ ምክንያት ሲባል ኢን ሻአላህ ችግር የለውም። የጠራው አላህ እንዲህ ይላል፡- 'በእርግጥም በናንተ ላይ ክልክል ያደረገውን ዘርዝሮላችኋል፤ ወደሱ የተገደዳችሁበት ሲቀር።'__ ገንዘቡን የሚያስቀምጥበት በወንጀልና ወሰን በማለፍ ላይ መርዳት የሌለበት ኢስላማዊ ባንክ ወይም አስተማማኝ ቦታ ሲያገኝ ግን በወለድ ባንክ ውስጥ ማስቀመጥ አይፈቀድለትም።"*
> [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኑ ባዝ፡ 19/414]

አሁንም ኢብኑ ባዝ፡-

ጥያቄ፡- *"የተከበሩ ሸይኽ! ከቤት ውስጥ እንዳይሰረቅ በመስጋት ገንዘብን ያለ ወለድ በባንክ ውስጥ ስለማስቀመጥ የተለያዩ ብይኖች ወጥተዋል። በጉዳዩ ላይ ሚዛን የሚደፋውን አቋም ግልፅ እንዲያደርጉልኝ እከጅላለሁ። የበዛ ምስጋና ለርሰዎ ይሁን።"*

**መልስ፡-** ***<u>"በአስገዳጅ ምክንያት ገንዘቦችን በባንክ ማስቀመጥ የሚፈቀድ ነገር ነው። ከኛ በቋሚ የጥናትና ፈትዋ ኮሚቴው በኩል ፈትዋዎች ወጥተዋል። ይሄ ደግሞ ለአስገዳጅ ምክንያት ነው።</u>*** *ምክንያቱም አንዳንዱ ሰው በቤተሰቡ ላይ እምነት አይጥልም።* ***<u>ስለዚህ ለዚህ የሚጋብዝ ጉዳይ ካለ ወለድ ሳይወስድ በባንኮች ቢያስቀምጥ ችግር የለውም።</u>*** *ከባንኮች ውጭ በሌላ አስተማማኝ የሆነ ቦታ ማስቀመጥ ከቻለ ይሄ ነው ለሱ የሚገባውና በላጩ። ይሄ ካልተመቻቸ ግን (በባንክ) ማስቀመጡ ችግር የለውም። ይሄ በአራጣ ማባዛትም አይሆንም።* ***<u>በሱ ላይ ወንጀልም አይኖርበትም። ምክንያቱም እሱ በዚያ ያስቀመጠው ከአደጋ ተጠንቅቆ ለመጠበቅ ነው።</u>*** *በነሱ (በገንዘቦቹ) አራጣ የሚፈፅም ግን ወንጀሉ በሱ ላይ ነው።"* [ዱሩሱን ሊሸይኽ ዐብዲል ዐዚዝ ኢብኒ ባዝ፡ 6/12]

በሌላም ፈትዋቸው ላይ ገንዘብ በባንክ መላላኩንም ማስቀመጡንም አስገዳጅ ምክንያት ከኖረ እንደሚቻል ተናግረዋል። [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኑ ባዝ፡ 19/194-195]

## ለ/ ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን

*"አንድ ሰው ገንዘቡ እንዳይሰረቅ ወይም እንዳይዘረፍ ወይም ደግሞ ገንዘቡን ሊወስድ በሚፈልግ አካል እንዳይገደል የሚሰጋ ከሆነ በነዚህ ባንኮች ውስጥ ለአስገዳጅ ምክንያት ቢያስቀምጥ ችግር የለውም"* ይላሉ። [ፈታዋ ዑለማኡል በለዲል ሐራም፡ 801]

## ሐ/ ሸይኽ ሙቅቢል

ለገንዘቡ የሚሰጋ ሰው በባንክ ማስቀመጥ እንደሚችል ፈትዋ ሰጥተዋል። https://www.youtube.com/watch?v=tv-nAAwCzgo

## መ/ ሸይኽ ፈውዛን

እሳቸውንም እንዲሁ ለአስገዳጅ ምክንያት ማስቀመጥን የሚፈቅድ ፈትዋ አላቸው። https://www.youtube.com/watch?v=iXOFFt_Tulw

## ሠ/ የሳዑዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ

**ጥያቄ፡-** *"እኔ ከባንኮች በአንዱ ከወለድ ነፃ የሆነ ሂሳብ አለኝ። ባንኮቹ በወለድ የሚሰሩ መሆናቸው ከመታወቁ ጋር። ገንዘቤ ከወለድ ብይን ውስጥ ይገባልን? ወንጀል አለብኝን? ተቀማጭ ገንዘቤን ከባንኮቹ ላውጣ? እንዳይጠፉብኝ መስጋቴ ከግንዛቤ ይግባ።"*

**ج : لا حرج عليك في ذلك، أن تودع أموالك في البنوك خوفًا عليها، وهذه مسألة ضرورة، إذا احتجت إلى ذلك، فلا حرج إذا كان بدون فائدة،**

መልስ፡- *"ስለፈራህ ገንዘብህን በባንኮች ማስቀመጥህ በዚህ ላይ ምንም ችግር የለብህም። ለዚህ የሚጋብዝህ ከሆነ ይሄ አስገዳጅ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ያለወለድ ከሆነ ችግር የለውም።"* [ፈታዋ ለጅነቲ ዳኢማ፡ 19/307]

ቋሚ ኮሚቴው ሌላም እንዲህ የሚል ፈትዋ ሰጥቷል፡- *"በወለድ ባንኮች ውስጥ ማስቀመጥ **<u>በአስገዳጅ ሁኔታና ያለ ወለድ ካልሆነ በስተቀር</u>***

*ይከለከላል።"* [ፈታዋ ለጅነቲ ዳኢማ፡ 13/384] ፈትዋውን የሰጡት ኢብኑ ባዝ፣ ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ፣ ዐብዱላህ ኢብኒ ቀዑድና ዐብዱላህ ኢብኒ ጉደይያን ናቸው።

ከዚህም በላይ ብዙ የሚፈቅዱ ዑለማዎችን መዘርዘር ይቻላል። አንባቢ ሆይ! ከዚህ ምን ተረዳህ? አንድ ሰው ስሜቱን እስካላስቀደመ ድረስ እነዚህን ፈትዋዎች ተንተርሶ ቢሰራ መወደሱ ቀርቶ ሊወቀስ ይገባዋልን?

**ሁለተኛ፡-** *"የለም የሚፈቅዱ ዑለማዎች ፈትዋዎቻቸው ልክ አይደሉም"* የሚል ካለም - ምናልባት ሀሳቡ ልክ ከሆነለት - ይሄ የኢጅቲሃድ ጉዳይ እንደሆነ ለማንም አይሰወርም። "አይ" የሚል ካለ ይሄው ከፊቱ ያሉት እነማን እንደሆኑ ይመልከት።

**ሶስተኛ፡-** *"ለአስገዳጅ ችግሮችም ጭምር በምንም መልኩ ገንዘብ በባንክ ማስቀመጥ አይቻልም"* የሚል አቋም የምንወስድ ከሆነ ሙስሊሞችን ሙሉ ለሙሉ ከዋና ዋና የንግድ ስርኣት ውጭ ነው የምናደርጋቸው። ዛሬ ሁሉም ለማለት በሚቀርብ መልኩ የአለም የንግድ ልውውጥና የገንዘብ ዝውውር ባንኮችን መሰረት ያደረገ ነው።

**አራተኛ፡-** ማህበርን የሚከለክሉ ሰዎች እራሳቸው በንግድ እንቅስቃሴያቸው የወለድ ስርኣት ባላቸው ባንኮች ይጠቀማሉ። ምናልባት እነሱ ንግድ ፍቃድ የሚጠይቅ ስራ ከሌላቸው በገንዘብ የሚደጉሟቸው ነጋዴዎች ሳይወዱ በግዳቸው የወለድ ባንኮችን ለንግድ ስርኣታቸው ይጠቀማሉ። ንግድ ፈቃድ ሲያወጡ፣ አክሲዮን ሲመሰርቱ በባንክ ተቀማጭ (ዲፖሲት) እንዲያስቀምጡ ይገደዳሉ። ስለዚህ *"ንግድ ፈቃድ ለማውጣት በባንክ ተቀማጭ ማስቀመጥ*

*የሚጠይቅ ከሆነ ንግድም ሐራም ነው”* ይላሉን?!! *ታዲያ* እራሳቸው የሚገቡበትን ዘርፍ *ዶሩራ* (አስገዳጅ ምክንያት) የሚያደርጉት ከሆነ ሌሎች የሚገቡበትን ተመሳሳይ ሰበብ ያለው ዘርፍ ለምን የማይታለፍ ጥፋት ያደርጉታል?! ይሄ ስሜትን የተከተለ ፍርደ-ገምድል አካሄድ አይደለምን?

መኪናዎቻቸውም ያለጥርጥር ኢንሹራንስ እንዲገቡ ይገደዳሉ። ስለዚህ ለምን መኪና ይገዛሉ? ለምንስ በመኪና ይሄዳሉ? ኢንሹራንስ ሁሉም ለማለት በሚቀርብ መልኩ ያፈጠጠ ያገጠጠ ቁማር አለበት። እያንዳንዱ ባለመኪና ደግሞ ቁማር ከሆነው ኢንሹራንስ ውስጥ እንዲገባ ይገደዳል። ስለዚህ ለምን *“መኪና መግዛት፣ መኪና መሸጥ፣ በመኪና መሳፈር፣ በመኪና መጫን፣ በመኪና የትኛውንም ነገር መጠቀም ሐራም ነው”* አይሉም?!!

በነገራችን ላይ ስጋት እንኳን ቢኖር በባንክ ገንዘብ ማስቀመጥን የሚከለክሉት ሸይኹል አልባኒ ኢንሹራንሶች በሙሉ ቁማር፣ በሙሉ ክልክል እንደሆኑ ከመግለፃቸውም ጋር በመኪና ላይ <u>መንግስታት የሚጥሏቸውን አስገዳጅ ኢንሹራንስ</u> ግን *“ተገዶ ስለሆነ ባለመኪናው ተጠያቂ አይሆንም”* ይላሉ። [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 420] በርግጠኝነት ጤናማ የሆኑ ሰፋፊ ስራዎችን የሚሰሩ ማህበራት ፋይዳ አንድ ሰው በመኪናው ከሚሰራው ፋይዳ በላይ ነው። በሶማሊያ፣ በሶሪያ፣ በየመን፣ በአፍጋኒስታን፣ በፍልስጤም የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞችን እየረዱ ያሉ ማህበራት አሉ። እዚሁ ሃገራችን ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያፈሰሱ ሙስሊም የቲሞችንና ደካሞችን የሚረዱ በሙስሊሞች የተቋቋሙ የልማት ማህበራት አሉ። በተለያዩ አለማት ሙስሊሞች በአክፍሮተ ሃይላት የስብከት ጎርፍ እንዳይወሰዱ፣ ከሺርክ ሰባኪዎች መንጋጋ ሊነጥቁ ትንቅንቅ ውስጥ ያሉ ማህበራት አሉ። እስኪ አሁን የነዚህ ጉዳይ ዶሩራ ካልሆነ እንዴት የግል መኪና ጉዳይ ዶሩራ ሊሆን

ይችላል?! የማህበርን ሚና ከግለሰብ ጉዳዮች፣ ከግል መኪና በሚያንሱ ትንንሽ ጉዳዮች ብቻ ገድበን ካላየነው በስተቀር ይሄ እንዴት ልክ ሊሆን ይችላል?!

## 12. የፎቶ ጉዳይ- ሌላው የተቃውሞ ምክንያት

በርግጥ ይሄ እጅግ ብዙዎቹ ማህበራት የተለከፉበት በሽታ ነው። ሁኔታውም - ወላሁ አዕለም - በአብዛሀኛው ለአስገዳጅ ሁኔታ ከሚያስፈልገው በላይ ነው። ፎቶ የሚፈቅዱት ዑለማዎች ፈትዋ እራሱ ማህበራት የሚጠቀሙትን ያክል ድረስ የሚፈቅድ አይመስለኝም። ለነገሩ ብዙዎቹ ለጉዳዩ ደንታ ያላቸውም አይደሉም። ነገር ግን እዚህ ላይ ጥቂት ነገሮችን ማጤን ያስፈልጋል።

**አንደኛ፡-** ከለጋሽ አካላት ስራው ያለበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ ፎቶ የሚጠየቅበት ሁኔታ አለ። ችግሮች ምን ያክል አሳሳቢ እንደሆኑ ለማሳየት የፎቶ ማስረጃ የሚያስደግፉበት ሁኔታም ብዙ ነው። ተቃዋሚዎቹ ምናልባት ለምስረታው የሚሰጠውንም ጭምር ፎቶ እንደ አስገዳጅ ሁኔታ ላይቆጥሩት ይችሉ ይሆናል። ምናልባትም “ፎቶ ካለበት ችግረኛ መርዳቱም፣ መሰረታዊ ስራዎችን መስራቱም አይፈቀድም” ሊሉ ይችላሉ። ይህን የሚሉ ከሆነ ያለጥርጥር ጭራሽ የማይሞከር ነገር እያወሩ ነው። የይዞታ ማረጋገጫው፣ የንግድ ፈቃዱ፣ የስልክ መስመሩ፣ መታወቂያው፣ ፓስፖርቱ፣ ወዘተ ፎቶ የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው። ፎቶ የሚከለክሉ ዐሊሞችም እነዚህን ሁሉ በመከልከል አልተኳዙም።

**ሁለተኛ፡-** ከዑለማእ ውስጥ ፎቶን የሚፈቅዱ አሉ። አስገዳጅ ነገር ሲኖር ብቻ ሳይሆን የከፋውን ችግር ለመከላከል ዝቅ ያለውን መፈፀም እንደሚቻል የሚጠቁመውን መርህ በመመርኮዝ በቴሌቪዥን ቀርቦ ማስተማር እንደሚቻል

ሸይኽ ኢብኑ ባዝ ይናገራሉ። [መጅሙዑ ፈታዋ፡ 5/292-295] እንዲያውም አስገዳጅ ነገር ሲኖር ብቻ ሳይሆን ጠቅላይ የሆኑ ጥቅሞች ካሉት እራሱ ይህንን የሚፈቅዱ **<u>ብዙ</u>** ዐሊሞች እንዳሉ ኢብኑ ባዝ ይገልፃሉ። [መጅሙዑ ፈታዋ ኢብኑ ባዝ፡ 5/375]

**ሶስተኛ፡-** በአንድ ማህበር ውስጥ ፎቶን ያለ ገደብ የሚጠቀሙ ሰዎች ቢኖሩ እንኳን ሁሉንም በጥፋቱ ተጠያቂ ማድረግ ከባድ ነው። ከነዚህ ማህበርን ከሚቃወሙ ሰዎች ውስጥ እኮ ብዙ ጥፋት ባለባቸው ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ አሉ። ዩኒቨርሲቲዎች፣ የጤና ተቋማት፣ ቢሮዎች፣ ወዘተ። እነዚህ ተቋማት ከፎቶም ያለፈ ብዙ ነገር አለባቸው። ምናልባት ተራውንም ህዝብ በቡድንተኝነት ካልፈረጁት በስተቀር "ጀምዒዮች" ከሚሏቸው ሰዎች በላይ መርካቶ ውስጥ ሱሪ የሚያከፋፍሉት እነሱ ይመስሉኛል። ስለዚህ ለሌሎች ውንጀላ ሲሰፍሩ እራሳቸውንም ባይረሱ ጥሩ ነው።

**አራተኛ፡-** "ክልክል ነው" የሚለውን ይዘን ብንጓዝም የፎቶ ጉዳይ ሰዎችን ከሱና የሚያስወጣ ጉዳይ እንዳልሆነ ለማንም ግልፅ ነው፣ ለተቃዋሚዎችም ጭምር። ልብ በሉ! ጉዳዩን እያቀለልኩ አይደለም። ግና በተለያዩ የተሳሳቱ ተእዊሎች አንድ ሰው ፎቶ መጠቀምን እንደሚቻል ቢያምን ወንጀለኛ ልናደርገው አይቻለንም። ተጠያቂ በሚያደርገው መልኩ እየተጠቀመ ከሆነም ድርጊቱን መቃወም ይቻላል እንጂ ምናልባት በዚህ መነሻ ከሱና  ለማስወጣት የሚዳዳው ከኖረ የአንድም ዐሊም ድጋፍ አያገኝም።

**አምስተኛ፡-** ማህበር ውስጥ ሆነው ፎቶን ክልክል እንደሆነ የሚያምኑና የሚጠነቀቁ  ሰዎችም በተጨባጭ አሉ። ቁጥራቸው እጅግ ቢቀልም ከዚህ አይነት ተግባር የሚርቁ ማህበራትም አሉ። ስለዚህ በፎቶ ጉዳይ ለተቃውሞ

ከማሰፍሰፋችን በፊት በቅድሚያ ከምንቃወመው አካል ዘንድ ችግሩ በተጨባጭ መኖሩን ማረጋገጥ የግድ ይላል። ጥፋቱ በተጨባጭ ቢኖር እንኳን ለአስገዳጅ ምክንያት እየተፈፀመ ላለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። ለነገሩ ጫፍ ይዞ ለተቃውሞ ከመሮጥ በፊት ጤናማ የደዕዋ ስልት እየተጠቀምን መሆኑን እንፈትሽ። የደዕዋ አላማ ማጋለጥ ሳይሆን ማስተማር ነውና። ደግሞም ብንቃወም እንኳን ጩኸታችን በጥፋቱ ልክ ሊሆን ይገባል። ከተቃውሟችን ጀርባ ምን ሊከተል ይችላል የሚለውን ከግምት ማስገባትም ከአስተማሪዎች የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

### 13. "ስርቆት አለበት!"- ሌላው ክስ

*"ማህበራት በአይታም ስም እየሰበሰቡ የሰው ገንዘብ ያለ አግባብ ይበላሉ። አንድም ወደ ተጠቃሚው አይደርስም"* እያሉ የሚከሱም አሉ። በርግጥ ይሄ ልክ የሚሆንበትም የማይሆንበትም ሁኔታ ስለሚኖር በጅምላ መከላከልም በጅምላ ማውገዝም ልክ አይሆንም። ከጥፋቱ ወይም ከተረጋገጡ አጥፊዎች አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከማስጠንቀቅ ባለፈ ሁሉንም በዚህ መልኩ መግለፅ ግን በኢስላምና በሱና ስም ቀርቶ ማንም በሰውነቱ ብቻ ሊፀየፈው የሚገባ ቆሻሻ ጅምላ ፍረጃ ነው። ጅምላ ውንጀላ የመሀይማን ቋንቋ ነው። እሱን እንደ መሳሪያ የሚጠቀሙት በብዛት ተቅዋ የሚቀላቸው፣ ማገናዘብ የሚያንሳቸው አስተሳሰባቸው ጮርቃ የሆኑ ችኩሎች ናቸው። አላህን የሚፈራ አካል አንዱ ላይ ባየው ወንጀል ሌሎችን በጅምላ አያጭድም። ጥፋቱን በተጨባጭ ያላየንባቸውን አካላት በጅምላ መወረፍ የራስን ቀላልነት ነው የሚያሳየው። ስለዚህ ማህበር ውስጥ ስለሚሰሩ ብቻ ባላየነው ሰዎችን በስርቆት መወንጀልም ብልግና ነው። የሰው ክብር መዳፈርም ነው። ነብዩ ﷺ ***"በአንድ አማኝ ላይ የሌለበትን የተናገረ ከንግግሩ ጣጣ እስኪወጣ***

***ድረስ አላህ የጥፋት ማጥ ውስጥ ያኖረዋል!"*** ብለዋል። "የጥፋት ማጥ" ማለት የእሳት ነዋሪዎች መግል እንደሆነም ገልፀዋል። [አስሶሒሓህ፡ 37] ምናልባት በጅምላ በመተቸት በዚህ መልኩ የተናገረ ዐሊም ከኖረም ንግግሩ ማስረጃ ሆኖ መቅረብ አይችልም። ስህተት እንዴት ማስረጃ ይሆናል?!

በማህበር ሰዎች የሚፈፀሙ ጥፋቶች ስላሉ ማህበር መመስረት ከነጭራሹ አይፈቀድም የሚለው አመክንዮም ደካማ ነው። ይሄ መሰረታቸው ሐላል የሆኑ ምግባሮችን አንስቶ ለከፋት የሚያውሏቸው ሰዎች ስላሉ ሙሉ ለሙሉ ሐራም ናቸው ከማለት አይለይም።

### 14. "ማህበር ከዒልም ፍለጋ ያዘናጋል"- ሌላው የተቃውሞ ሰበብ

በርግጥ ኢስላማዊ እውቀትን <u>በጥልቅ</u> መማር ለሚፈልግ አካል ሐላልም ቢሆኑ ጊዜውን ከሚወስዱ ከብዙ ነገሮች እራሱን ነፃ ማድረግ አለበት። ስለሆነም በዒልም ላይ መሰማራት ለሚጓጓ ሰው ሰፊ ጊዜን ከሚሻማ የበጎ አድራጎት ስራ ውስጥ መግባቱ <u>የማይመከር</u> እንደሆነ ሸይኹል አልባኒም ይገልፃሉ። ነገር ግን ይሄ ምክንያት ከምክር አልፎ "ሐራም ነው" ለማለት መቅረቡ የሚደንቅ ነው። "ሐላል" ወይም "ሐራም" ማለት እኮ እንዲህ በውሽልሽል ሰበብ የሚደፈር ርእስ አይደለም። ጌታ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَا تَقُولُوا۟ لِمَا تَصِفُ أَلْسِنَتُكُمُ ٱلْكَذِبَ هَٰذَا حَلَٰلٌ وَهَٰذَا حَرَامٌ لِّتَفْتَرُوا۟ عَلَى
ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَفْتَرُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ لَا يُفْلِحُونَ ﴿١١٦﴾ ﴾

*"በአላህም ላይ ውሸትን ልትቀጣጥፉ ምላሶቻችሁ በሚመጥኑት ውሸት 'ይህ የተፈቀደ ነው'፤ 'ይህም እርም ነው' አትበሉ። እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ አይድኑም።"* [አነሕል፡ 116]

እንዲያውም ቁርአናዊ ወይም ሐዲሣዊ መረጃ ሳይቀርብ ኢጅቲሃድ ላይ ብቻ ተመርኩዞ “ሐራም” ወይም “ሐላል” ማለት ከባድ ነገር ነው። አልኢማም ኢብኑል ቀይዪም ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *“ነገር ግን ከአላህ ወይም ከመልእክተኛው ግልፅ መረጃ ሳያገኝ ኢጅቲሃዱ ያደረሰውን ነገር ‘አላህ ይህንን ሐራም አድርጓል’፣ ‘ይህንን ዋጂብ አድርጓል’፣ ‘ይሄንን ሐላል አድርጓል’፣ ‘ይሄ የአላህ ብይን ነው’ ሊል አይፈቀድለትም።”* [ኢዕላሙል ሙወቂዒን፡ 1/44] ስለዚህ የዑለማዎችን የኢጅቲሃድ ብይኖች እንደ ቁርኣንና ሐዲሥ ማስረጃ እያደረጉ ማቅረብ ጥንቃቄ የሚሻ አደገኛ ነገር ነው። ወደ ነገራችን ስንመለስ፡-

**በጀመሪያ፡-** አንድን ማህበር **<u>በማስተዳደር</u>** የሚሳተፉ ሰዎች እጅግ ጥቂቶች ናቸው። እነሱም ቢሆኑ 24 ሰዓት አይሰሩምና መሰረታዊ ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚያስችል ጊዜ ያጣሉ ማለት የማይመስል ነገር ነው።

**ሁለተኛ፡-** መሰረታዊ ነገሮችን ከጨበጡ ደግሞ ሸሪዐዊ እውቀትን በጥልቀት ማጥናት የነፍስ ወከፍ ግዴታ (ፈርዶል ዐይን) አይደለም። [ኪታቡል ዒልም ሊብኒል ዑሠይሚን፡ 120-121]

**ሶስተኛ፡-** ህዝባዊ ግልጋሎቶች ባሏቸው ማህበራት ከሚዘናጉት ይልቅ እንደ ንግድና ግብርና ባሉ ራስንና ቤተሰብን ብቻ በሚመለከቱ የዱንያ ስራዎች ከዲናዊ እውቀት የሚዘናጉት ይበዛሉ። ስለዚህ ይህን ምክንያት በማድረግ “ንግድና ግብርናም ሐራም ነው” የሚል ይኖር ይሆን?

**አራተኛ፡-** እንዲያውም ይሄ *“ማህበር ከዒልም ያዘናጋል”* የሚለው ክስ ዲናዊ ትምህርት በመስጠት ላይ የተሰማሩ ማህበራትን በጭራሽ አይመለከትም። ብዙዎቹ ዲናዊ ማህበራት የሚከፈቱበት አላማ የደዕዋ እንቅስቃሴዎች

መሰናክል በሚበዛባቸው አካባቢዎች ወይም ደግሞ ክፍተትና ሹቡሃት በሚበዛባቸው ዘርፎች ላይ ኢስላምን ለማስተማር፣ ብዥታዎችን ለመግለጥ አማራጭ ፍለጋ ነውና። የደዕዋ መድረኮችን ማመቻቸት፣ ዱዓቶች ጊዜያቸውን በእለት ጉርስ ፍለጋ እንዳያጨናንቁና ለማስተማር ሰፊ ጊዜ እንዲሰጡ መደጎም፣ ኢስላማዊ መፃሕፍትና ካሴቶችን ማሰራጨት፣ ዱሩሶችንና የደዕዋ ጉዞዎችን ማመቻቸት፣… ላይ ነው የሚሰማሩት። ታዲያ እነዚህ ተግባሮች ጊዜ ይሻማሉ በሚል ሰበብ የሚተቹ ናቸውን? በህንድና በፓኪስታን ኢስላማዊ እውቀቶችን ለማሰራጨት የተከፈቱ በርካታ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎችን መግቢያችን አካባቢ ተመልክተናል። እነዚህ እውቀትን የሚያሰራጩ ተቋማት የተከፈቱት በማህበራት ነው። እንደ ሸይኽ ሙሐመድ ሓሚድ ፈቂ፣ ዐብዱረሕማን አልወኪል፣ ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ፣ ሙሐመድ ኸሊል ሀራስ፣ አሕመድ ሻኪርና መሰል ታላላቅ ዑለማዎች በማህበር ስር ሆነው ዒልም ሲያሰራጩ የነበሩ ጀግኖች ናቸው።

### 15. “ማህበራት የልዩነት መንስኤ ናቸው”- ሌላው መቃወሚያ

**በመጀመሪያ፡-** የማይካደው ሐቅ ቡድናዊ አላማን ወይም ዱንያዊ ጥቅምን በሚያነግቡ ማህበራት ሳቢያ ቀላል የማይባሉ ልዩነቶች ይከሰታሉ። መሰረታዊ የሆነው የልዩነቱ መንስኤ ግን ማህበራቱን የሚመሰርቷቸው ሰዎች ዐቂዳ ወይም አካሄድ መለያየት ወይም መቀየር እንጂ በማህበራቱ ሳቢያ እንደ አዲስ የሚመጣ አይደለም። ስለዚህ ቁርኣንና ሐዲስን የምንረዳበት መንገድና ለሚያጋጥሙ ችግሮች የምንመርጠው የመፍትሄ አቅጣጫ ሲለያይ ነው ልዩነቱ የሚነሳው። አፈንጋጭ አንጃዎች አስተሳሰባቸውን ለመርጨት፣ ስውር ፖለቲካቸውን ለማራመድ ማህበራትን እንደ ድልድይ የሚጠቀሙበት አጋጣሚ

ብዙ ነው። ይሄ ግን በሚይዙት አቋም መለያየት ሳቢያ የሚመጣ መዘዝ እንጂ በማህበሩ ሳቢያ አዲስ የሚመጣ የዐቂዳ ልዩነት አይደለም።

***ሁለተኛ፡-*** ማህበራት በራሳቸው የልዩነት መንስኤ ቢሆኑ ኖሮ እጅግ በጣም ጥቂት ከሆኑት ውጭ ያሳለፍናቸው ዑለማዎች እንዳለ ባልፈቀዱት ነበር። ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ያክል የአንድ ታላቅ ዐሊም ንግግር ልጠቀም። ሸይኹል አልባኒ ማህበራት ውስጥ ቂምና ጥላቻ የሚከሰትበት ሁኔታ በተጨባጭ እንዳለ እያወሱም መሰረታዊ የልዩነቱ መንስኤ ግን ሌላ እንደሆነ ነው የገለፁት። እንዲህ በማለት፡- ***<u>"እ‌ይ (ማህበራትን) መመስረቱ ከዚህ ጉዳይ (ከልዩነት) ጋር ግንኙነት የለውም። ልዩነቱ ስር የሰደደ የዐቂዳ ልዩነት ነው። ከዚያም ይሄ ልዩነት ተግባራዊ ልዩነት ይከተለዋል</u>።"***

***ሶስተኛ፡-*** ማህበራት የአሰራር መዋቅር እንጂ የራሳቸው ዐቂዳ ወይም እምነት የላቸውም። መዳረሻ እንጂ በራሳቸው እምነትም አምልኮትም አይደሉም። ታዲያ ምናቸው ነው የሚለያየው? አንድን መዳረሻ አጥፊዎች በስፋት ስለተጠቀሙት ብቻ የጥፋት መንስኤ እንደሆነ መግለፅ ጤናማ ስሌት አይደለም። **<u>በርግጥ በማህበራቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች በዱንያ ጥቅም ወይም በሌላ ምክንያት ልዩነት ሊፈጥሩ ይችላሉ።</u>** ይሄ ደግሞ በመርከዞችም፣ በሐዲሥ ማዕከላትም፣ በዩኒቨርሲቲዎችም፣ በንግድ ኩባንያዎችም፣ **<u>በትኛውም ስብስብ በየትኛውም የጋራ ስራ</u>** ውስጥ ሊከሰት የሚችል ነው። በነዚህ ነገሮች ላይ ልዩነት ስለሚያጋጥም ለመሰባሰባቸው ሰበብ የሆኑትን ተቋማት "ሐራም ናቸው" ማለት ይቻላልን?! የተለያዩ የሐዲሥ ማዕከላትን ከከፈቱት የሸይኽ ሙቅቢል ተማሪዎች ውስጥ ከፊሎቹ ስለተለያዩ ከዚህ በመነሳት *"የሐዲሥ ማዕከላት የልዩነት ምንጭ ናቸው"* ማለት ያስኬዳልን?!

የሚደንቀው “ማህበር ይለያያል” የሚሉ ሰዎች እራሳቸው መስጂድ ውስጥ ለጆሮ የሚሰቀጥጡ ፀያፍ ዘለፋዎችን እስከሚዘላለፉ ያደረሳቸው ልዩነት በመሀላቸው የተከሰተ መሆኑ ነው። እንዲያውም በአሁኑ ሰዓት በሃገራችን ቢያንስ ለሁለት እንደተሰነጠቁ የሚታወቅ ነው። የመን ውስጥ ያለውን የሓጁሪ ተከታዮችን ሁኔታ ካየን ደግሞ በብዙ መልኩ ተለያይተው እየተባጬቁ ነው። ለመሆኑ እነሱ ስውር ማህበር ስለመሰረቱ ነው የተለያዩት? ወይስ አካሄዳቸው በራሱ ለተሐዙብ (ቡድንተኝነት) ስለሚጋብዝ ነው?

ስለዚህ ማህበራትንና ቡድንተኝነትን ፍፁም የማይፋቱ ነገሮች አድርጎ ማሰብ ልክ አይደለም። ማህበራት የቡድንተኝነት ችግር ያለባቸው ሰዎች ከመሰረቷቸው ያለጥርጥር ቡድንተኝነት ይኖራቸዋል። ካልሆነ ግን አይሆንም። *“ማህበር መመስረት በራሱ ቡድንተኝነት ነው”* የሚል ካለ ግን ከነ ጭራሹ የቡድንተኝነት ምንነትም አልገባውም። አልባኒ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

> *“ወደ አላህ በመጣራት ላይ ያለ የተደራጀ ማህበራዊ ስራ ቡድናዊ ሊሆን ይችላል፣ ቡድናዊ **ላይሆንም** ይችላል። … እነዚህ ስብስቦች በውስጣቸው ያሉ አባላት በመካከላቸው እስከመቡዳደን የሚያደርስ መቃያየም፣ ጀርባ መሰጣጠትና መጠላላት ከሌለ እነዚህ ስብስቦች የግድ ሊኖሩ ይገባል። ባይሆን የግድ ወጥ በሆነ መስመርና መርህ ላይ የተሳሰሩ ሊሆኑ ይገባል። ይሄ የግድ ሊሟላ ይገባል።”* [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 792]

ደግሞም ማህበር ኖረም አልኖረም በአንድ መስመር ላይ ባሉ ሰዎች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ልዩነት ሊከሰት ይችላል። ሸይኽ ዘይድ ኢብኑ ሃዲ አልመድኸሊ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*"አዎ! የቀደምቶችን መንገድ በሚከተሉ በሐቅ ጎዳና ላይ በሚጓዙ ወንድሞች መካከል የሆነ ልዩነትና ሙግት ሊከሰት ይችላል። ምክንያቱም ፍፁሞች ስላልሆኑ ነው። ነገር ግን ይሄ ወንድማማችነታቸው ላይ ተፅእኖ አያሳድርም። ልዩነታቸውም በሱኒና በሙብተዲዕ መካከል እንዳለው ከጥንት ጀምሮ እስከዚህ ጊዜያችን ድረስ እንደቀጠለው (ልዩነት) አይቀጥልም።"* [አውዶሑል መዓኒ፡ 156]

አንዳንዶች "ማህበር ይለያያል" የሚለውን ሽቀጣቸውን ለማሻሻጥ ሲሉ ብቻ በሆኑ አካላት መካከል የተከሰቱ ልዩነቶችን ከማህበር ጋር የግድ ሊያስተሳስሩ ይታገላሉ። ሙግታቸው እውነት ይሁን ሐሰት ለመለየት ቀላል ነው፡-

- የተከሰተው ምን አይነት ልዩነት ነው? መሰረታዊ ነውን?
- መንስኤውስ ማህበር ነውን?
- በልዩነቱ ላይ የማህበር (የጀምዒያ) ሚና አለበትን?
- በሁለቱም በኩል ያሉ ተወዛጋቢዎቹስ የማህበር አባል ናቸውን?
- ልዩነቱስ ሰሞንኛ ወይስ እስከወዲያኛው የሚያቆራርጥ ነው?

የሚሉትን ነጥቦች ተረጋግቶ <u>በተጨባጭ</u> <u>መረጃ</u> መመለስ ይጠይቃል። ከነሱ ስብስብ ውስጥ ያልገባን ሁሉ "ጀምዒይ" እያሉ ምንም ንክኪ የሌለውን ሁሉ ከሚጠሉት ማህበር ጋር የመቀላቀል አመል ያለባቸው ሰዎች ስላስተጋቡት ብቻ ውጫዊ ገፅታቸውን አይተህ፣ በሱና ስም የሚሰጡትን ድስኩር ሰምተህ ያለ መረጃ በየዋህነት አትቀበል። ***" 'እውነተኞች ከሆናችሁ መረጃችሁን አምጡ' በል"*** ይላል ጌታችን። [አልበቀራ፡ 111]

ይህን ነጥብ ስናጠቃልል ማህበራት በተለይም በኛ ሃገር የሚፈቀድላቸውና የሚሰማሩበት ዘርፍ እጅግ የተገደበ እንደሆነ ማስተዋል ይገባል። ይህን መለየቱ በተለይም ለሚቃወም አካል ተቃውሞው ውል እንዲይዝ ይበጀዋል። ይህን ነጥብ በሚገባ የተረዳ ሰው፡-

- በአይታም ድጋፍ፣ በጤና ዘርፍ፣ በተለያዩ የእርዳታ ስራዎች ላይ የተሰማሩ የልማት ማህበራትን በጠባብ ወላእና በራእ፣ በፖለቲካ እንቅስቃሴ፣... አይወነጅልም። ስራቸው ከዚህ ጋር ጭራሽ አይገናኝማ!!
- በደዕዋ ስራ ላይ የተሰማሩ ማህበራትን ደግሞ በአይታም ስም ገንዘብ በመዝረፍ ወይም በፖለቲካ እንቅስቃሴ አይወነጅልም። ምክንያቱም የልማትም ሆነ የፖለቲካ ንክኪ የላቸውማ!!

በእርግጥ ከወሰዱት ፈቃድ ውጭ በስውር የሚንቀሳቀሱ ሊኖሩ ይችላሉ። እርዳታን ሽፋን አድርገው የሰበካ ስራ የሚሰሩ ብዙ የጴንጤ ማህበራት እንዳሉ ይታወቃል። በሰበብ አስባብ የመዘጋት አድል የሚያንዣብባቸው የሙስሊም ማህበራት ግን ከተሰጣቸው ፈቃድ ውጭ የመስራት እድላቸው ዜሮ ነው ባይባልም **<u>በንፅፅር</u>** እጅግ የቀለለ ነው። ብቻ ስንቃወም ተቃውሟችን ውል እንዳይስት በቅድሚያ ተጨባጭ ነገሮችን መያዛችንን እርግጠኛ ልንሆን ይገባል። የተቃውሟችንን ፋይዳና አንድምታ ቀድሞ መገምገሙ እራሱ አርቆ ተመልካችነትን የሚያንፀባርቅ ነው።

የማይካደው ሐቅ ብዙዎቹ ማህበራት ከስራዎቻቸው ጋር የሚያያዙ መሰረታዊ አሕካሞችን እንኳን በማይለዩ አካላት ነው የሚንቀሳቀሱት። ይሄ አደጋ አለው። በዚህ ሳቢያ ወንጀል ላይ የመውደቃቸው እድል ሰፊ ነው። ለምሳሌ ለዘካተል ፊጥርና ለኡዱሒያ የተሰጣቸውን ገንዘብ የጊዜ ገደቡንና

ህግና ደንቡን ሳይጠብቁ የሚፈፅሙበት ሁኔታ ይኖራል። የዘካ ገንዘብ የሚገባቸው ውስን አይነት ሰዎች እንደሆኑ ይታወቃል። ሆኖም ግን እጃቸው የገባን የዘካ ገንዘብ ለማይመለከተው አካል ሊሰጡ ወይም ለፕሮጀክት ሊያውሉት ይችላሉ። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አውዳሚ ሰባኪዎችን በመርዳት አፍራሽ ሚናቸው ሊያመዝን የሚችልበት ሁኔታም ይኖራል። ተቅዋው የሚቀላቸው ደግሞ ለቁሳዊ ጥቅም የሚሽኮሩበት፣ በዚህም ሳቢያ እርስ በርስ የሚናቆሩበት ሁኔታ በተጨባጭ ያጋጥማል። በማህበራት አሰራር ውስጥ የሚዘረጉ ውስብስብ መንግስታዊ ህጎችና ቁጥጥሮች ለቀጥታ ዝርፊያ ባያፈናፍኗቸውም በተለያዩ ስልቶች የሌሎችን ሐቅ የሚሸራርፉበት አጋጣሚም አይጠፋም። በወሳኝ ጉዳዮች ላይ የሚይዟቸው አቋሞች ልክም ሆኑ ስህተት ቡድናዊ ገፅታ ሊያጠላባቸውና ከሌሎች ጋር ሊያቃቅራቸው ይችላል። ይህም በጊዜ ካልታከመ ጦሱ የከፋ ሊሆን ይችላል።

ግና እነዚህ ጥፋቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ ማለት የሁሉም ችግሮች ናቸው ማለት አይደለም። ይህን ለመረዳት ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው። በንግዱ አለም ብዙ የሚፈፀሙ ወንጀሎችና ማጭበርበሮች አሉ። ከመሆኑም ጋር ነጋዴ ሁሉ ወንጀለኛና አጭበርባሪ ነው የሚል ጅምላ ውንጀላ ውስጥ እንድንገባ ማለፊያ ምክንያት ሊሆነን አይችልም። *"ንግድ ሐራም ነው"* የሚል ድምዳሜ ላይ እንደማያደርሰንም ለማንም አይሰወርም።

ሲጠቃለል በውስጣቸው ጥፋቶች የሚፈፀሙባቸው ማህበራት ሊኖሩ እንደሚችሉ ሁሉ ብዙ ልማቶች የሚሰሩባቸውም እንዳሉ መካድ አይቻልም። ሁሉንም እንደ ሳሙና አንድ ቁርጥ ማድረግ ፍርደ-ገምድል ውሳኔ ነው። ብዙ ችግር ያለባቸው ስለሚያጋጥሙ ማህበር ከመሰረቱ ክልክል ነው ማለት ግን ብዙ ሐላል የሆኑ ስራዎች ውስጥ በርካታ ጥፋቶች ስለሚያጋጥሙ ስራዎቹ

በራሳቸው ክልክል ናቸው ወደማለት የቀረበ ነው። ልብ በሉ! ትኩረቴ ከምክንያቱ እንጂ ከብይኑ ላይ አይደለም። በተደጋጋሚ እንደተመለከትነው ከታላላቅ ዑለማዎች ውስጥ ማህበርን የከለከሉት የአንድ እጅ ጣቶችን እንኳን አይሞሉም። ይህም በሆነ ምክንያት *"ማህበር መመስረት ክልክል ነው"* ወደሚለው ሀሳብ ብናደላ እንኳን በየትኛውም መመዘኛ ጉዳዩ ሰዎችን ከሱና ማስወጫ ሆኖ የመቅረብ ክብደት እንደሌለው በቂ ጥቆማ ይሰጠናል። ይበልጥ አዋቂው አላህ ነው።

## ምዕራፍ ሁለት፡ ሱሪ

ሌላኛው ንትርክ የበዛበት ርእስ የወንዶች ሱሪ ጉዳይ ነው። ሱሪ ስለለበሱ ብቻ ሙስሊሞችን የሚያኮርፉ ሰዎች አሉ። ከፊሎቹ በዚሁ ሳቢያ ሰዎችን ከሱና እስከማስወጣት ደርሰውም ተመልክተናል። በርግጥ ከውስጣቸው *"እኛ በሱሪ ጉዳይ ከሱና አናስወጣም"* የሚሉ አሉ። ይሄ ይበል የሚያሰኝ ነው። ብቻ ይህን የሚሉት ስለሱሪ የሚጮኹትን ያክል፣ ስለማህበር የሚጮሁትን ያክል ከፊሎቹ ዘንድ ያለው ብልሹ እይታ ይታረም ዘንድ በሱሪ ጉዳይ እንደማያስወጡ በሚገባ ስለማይገልፁ ከነሱ ውጭ ያለ ቀርቶ ተከታዮቻቸውም ጭምር አቋማቸውን በውል አያውቁትም። ይህን የምለው ከፊሎቻቸው ለማስተባበል ቢሞክሩም ከውስጣቸው በሱሪ ሰበብ ሰዎችን ከሱና የሚያስወጡ፣ በተለይም ክፍላተ-ሃገራት ላይ ብዙ የሚበጠብጡ እንዳሉ በተጨባጭ ስለማውቅ ነው።

በጣም የሚደንቀው ግን በሱሪ ምክንያት ላንቃቸው እስከሚበጠስ የሚጮሁ ሰዎች ባደባባይ ሱሪ ሲያከፋፍሉ ማየት ነው። *"ቅልቅል ያለበት ትምህርት ሐራም ነው"* ብለው ተቀላቅለው የሚማሩም የሚያስተምሩም አሉ። በትራንስፖርትም ላይ ተቀላቅለው ይጓዛሉ። ማህበርን የሚያወግዙባቸውን ጥፋቶችም በተለያዩ ምክንያቶች ሲፈፅሟቸው ይታያሉ። ከማህበር እየተቀበሉ ሰደቃዎችን የሚበሉም በተጨባጭ አውቃለሁ። "ሐራም ነው" ከማለትም አልፈው ታፔላ በሚለጥፉበት ማህበር የቀረበን ምፅዋት መቀበል እጅጉን የሚደንቅ ነው። *"ምነው ሰዎችን የምትተቹበትን ግፋ ሲልም ከሱና የምታስወጡበትን ጉዳይ እራሳችሁ መፈፀማችሁ?"* ሲባሉ አንዳንዶቹ *"አንድ ሐራም ነገር ላይ የወደቀ ሰው ከዚያ ሐራም ማስጠንቀቅ አይችልም ወይ?"* እያሉ ይከላከላሉ።

በእርግጥ ጥፋት ላይ ያለ ሰው እራሱም ካለበት ጥፋት ማስጠንቀቁ ጥፋተኛ አያሰኘውም። እያጨሱ "አታጭሱ" እንደሚሉ ሲጋራ አጫሾች ይሆናል እንጂ!! ግና "አታጥፉ" እያሉ ማጥፋት፣ ያውም "ጥፋት" ማከፋፈል ለህሊና የሚጎረብጥ አካሄድ ነው። ጌታችን እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَتَأۡمُرُونَ ٱلنَّاسَ بِٱلۡبِرِّ وَتَنسَوۡنَ أَنفُسَكُمۡ وَأَنتُمۡ تَتۡلُونَ ٱلۡكِتَٰبَۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ﴾

*"እናንተ መፅሐፉን የምታነቡ ሆናችሁ ሳለ ሰዎችን በበጎ ስራ እያዘዛችሁ እራሳችሁን ትረሳላችሁን? አታገናዝቡምን?!"* [አልበቀራህ፡ 44]

በሸይኽ ሷሊሕ ኣሊ ሸይኽ የበላይ ተቆጣጣሪነት በምርጥ ዑለማዎች የተዘጋጀው ተፍሲር ላይ ይህቺን አንቀፅ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ፡- *"እራሳችሁን እየተዋችሁ ሰዎችን በመልካም የምታዙ መሆናችሁ የናንተም የዑለማዎቻችሁም ሁኔታ ምንኛ አስቀያሚ ነው?! ... ህሊናችሁን ትክክለኛ በሆነ መልኩ አትጠቀሙትምን?"* [ተፍሲሩል ሙየሰር፡ 7]

ስለዚህ ሰው በራሱ መጀመር ሲገባው ሌሎችን በሚያዝበት ነገር እራሱን መዘንጋቱ ማገናዘብ ለሚችል ሰው ሲበዛ አስተዛዛቢ የሆነ አካሄድ ነው። እንዲህ አይነት ባህሪ ያለውን ሰው አስመልክቶ ምን አይነት አስፈሪ ነብያዊ ዛቻ እንደመጣ እንመልከት።

> *"በቂያማ ቀን አንድ ሰው ይቀረብና እሳት ውስጥ ይጣላል። ከዚያም ሆድ እቃው ይዘረገፍና ልክ አህያ ወፍጮውን ይዞ እንደሚዞረው ይዞት ይዞራል። የእሳት ሰዎች ከሱ ዘንድ ይሰበሰቡና 'እከሌ ሆይ! ምን ነካህ? በመልካም ታዘን፣ ከመጥፎ ትከለክለን አልነበረምን?' ሲሉት 'እንዴታ!*

*ነገር ግን በመልካም እያዘዝኩ አልፈፅመውም ነበር። ከመጥፎ እየከለከልኩ እፈፅመው ነበር' ይላል።"* [ቡኻሪ፡ 3267፣ ሙስሊም፡ 2989]

ከሙስሊሙ ህዝብ ውስጥ እንዲህ አይነት ባህሪ የሚያንፀባርቅ ሰው በአይሁዶች መመሳሰል አለበት ይላሉ ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን ረሒመሁላህ። [ተፍሲር ኢብኑል ዑሠይሚን፣ አልፋቲሐ ወልበቀራህ፡ 129]

በመሰረቱ የማይሰሩትን ማውራት ምን ያክል ከባድ እንደሆነ ይህቺን አንቀፅ መመልከት ብቻ በቂ ነው፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لِمَ تَقُولُونَ مَا لَا تَفۡعَلُونَ ٢ كَبُرَ مَقۡتًا عِندَ ٱللَّهِ أَن تَقُولُواْ مَا لَا تَفۡعَلُونَ ٣ ﴾ الصف: ٢ - ٣

*"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለምን የማትሰሩትን ታወራላችሁ? የማተሰሩትን ማውራታችሁ አላህ ዘንድ መጠላቱ ገዘፈ።"* [አስሶፍ፡ 2-3]

የነዚህ ወንድሞቻችን ሁኔታ ግን ከዚህም የከፋ ነው። እስካሁን ባሳለፍነው የተወገዘው በሚያዙት መልካም አለመስራት፣ የሚከለክሉትን ጥፋት ደግሞ መፈፀም ነው። እነሱ ግን አልፈው ሌሎችን የሚያብጠለጥሉበትንና ባደባባይ የሚያወግዙበትን "ሐራም ነገር" ነው ለህዝብ እያከፋፈሉ ያሉት። ስራቸው ልክ "ቢራ ሐራም ነው" እያለ በቢራ እንደሚነግድ ሰው ምሳሌ ነው። ባደባባይ የሚወርፉበትን "ጥፋት" ወይም "ጥመት" ለህዝብ ማከፋፈል ሲበዛ የሚደንቅ ነው። ነብዩ ሹዐይብ ዐለይሂ ሰላም *"ከርሱ ወደከለከልኳችሁም ነገር ልለያችሁ አልሻም"* ይላሉ። [ሁድ፡ 88]

በዚህ ነገር ሁሉንም እየወቀስኩ እንዳልሆነ ከግንዛቤ ይግባ። ይህንን እንደመግቢያ ያክል እንያዝና ጥቂት ነጥቦችን እንመልከት።

## <u>ሲርዋል እና ሱሪ ይለያያልን?</u>

“ሲርዋል” የሚለውን ቃል በተመለከተ በተለያዩ ጠንካራ ሐዲሦች የመጡ መረጃዎች አሉ። እነዚህን መረጃዎች ለሱሪ እንዳንጠቀም ግን *“የዛሬው ሱሪና በሐዲሥ የተጠቀሰው ሲርዋል ይለያያሉ”* የሚል ተቃውሞ ይነሳል። ዛሬ “ሱሪ” እያልን የምንገልፀው ልብስ በዐረብኛው “ቢንጣል” ወይም “በንጠሉን” ይባላል። “ሲርዋል” የሚለው ዐረብኛ ምንም እንኳን “ሱሪ” እየተባለ በአማርኛው ቢተረጎምም ዘመናዊው ሱሪ እንደማይወክለው አንዳንድ ዐሊሞች ይገልፃሉ። ለምሳሌ ሸይኹል አልባኒ። “ሲርዋል” ዛሬ ካሉት ሱሪዎች በስፋቱ የሚልቅ ከላይ ሰፍቶ ከታች የሚጠብ ልብስ እንደሆነና አንዳንድ የሙስሊም አካባቢዎች እንደሚገኝ ይገልፃሉ። በሃገራችን “ተነፋነፍ” እየተባለ የሚጠራው ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም።

ሌሎች ዐሊሞች ደግሞ ሱሪ ወይም ቢንጣል በሐዲሥ የተገለፀው ሲርዋል እንደሆነ ወይም የሱው ዘር እንደሆነ ይገልፃሉ። ለምሳሌ ሸይኽ ኢብኑ ባዝ በአንድ ፈትዋቸው ላይ ስለሱሪ ሲጠየቁ በፈቀዱበት ፈትዋቸው ላይ በንጠሉን (ሱሪ) ማለት ሲርዋል ማለት እንደሆነ ገልፀዋል። [*መጅሙዑ ፈታዋ*: 10/413]

ሸይኽ ሱለይማን አሩሐይሊም እንዲሁ በንጠሉን (ሱሪ) *“ድሮ ዐረቦች ዘንድ ሰራዊል ይባል ነበር”* በማለት ሱሪና ሲርዋል አንድ እንደሆነ ይገልፃሉ። [ሸርሑ ኡሱሊ ሠላሣ]

## ሲርዋል "ሱሪ አይደለም" የሚሉ ሰዎች ምክንያቶች ሲፈተሹ

### 1. ርዝመት

*"የሲርዋል ቁመት ከእንብርት እስከ ጉልበት፣ ወረድ ካለም እስከ መሀል ባት ነው። ሱሪ (በንጠሉን) ግን በአብዛሀኛው እስከ ታችኛው እግር ነው። እስከ መሀል ባት የሚሆን ግን ጭራሽ የለም"* የሚል አለ። [አልቂስጧስ ፊ ሑክሚ ሉብሲል በንጦሉን ወተሽቡህ ቢልኩፋር ፊሊባስ፡ 137] ሱሪን ግን ፀሐፊው *"እስከ መሀል ባት ሊሆንም አይችልም። ለባሹ ሱሪው እስከ መሀል ባት ሊያደርገው ያፍራል"* ይላል። [አልቂስጧስ፡ 204]

በርግጥ ይሄ ውሃ የማያነሳ አመክንዮ ነው። እንዲያውም በዚህ ጉዳይ ላይ በተፃፈ ኪታብ ላይ ስለሰፈረ ብቻ ምናልባት የሚሸወድበት ሊኖር ይችላል በሚል እንጂ መልስ የሚሻም አይደለም።

ሀ/ ዛሬም ድረስ የሱሪ ርዝመት ወጥ አይደለም። ከመሀል ባት ከፍ ከሚል ጀምሮ እስከ መሬት የሚደርሱ መጠን ያላቸው ሞልተዋል። ስለዚህ *"እስከ መሀል ባት የሚሆን ጭራሽ የለም"* ማለት ከእውነት የራቀ ነው።

ለ/ ሲርዋል ማስረዘምን የሚከለክሉ የድሮ ፈትዋዎችና ንግግሮችም ረጃጅም ሲርዋል እንደነበር ጠቋሚ ናቸው። ለምሳሌ ኸሊፋው ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ *"ሲርዋላችሁን ቁረጡ"* ማለታቸው በጊዜው ረጃጅም ሲርዋሎዎች እንደነበሩ አንድ መረጃ ነው። [አተዕሊቃቱል ሒሳን ዐላ ሶሒሕ ኢብኒ ሒባን፡ 5430] ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ የሲርዋል ርዝመት ቁርጭምጭሚት ካለፈ ብይኑን ተጠይቀው እንዲህ ሲሉ ነው የመለሱት፡- *"የቀሚስ፣ ሰራዊልና ሌሎችም ልብሶች ቢያልፍ ከቁርጭምጭሚት በታች ሊሆን አይፈቀድም።*

*በዚህ ላይ ከነብዩ ﷺ የተረጋገጡ ሐዲሦች እንደመጡት እንዲህ ብለዋልና ‘(የተከለከለው) ማስረዘም በሰራዊል በሸርጥና በቀሚስ ነው።’ ይህም ከማስረዘም ከልክለዋል ማለት ነው።”* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 22/144] አልኢማም ዘሀቢም እንዲሁ ልብስን ማስረዘም ከታላላቅ ወንጀሎች እንደሆነ በጠቀሱበት ጊዜ ሲርዋልን አብረው ጠቅሰዋል። [አልከባኢር፡ 215] ከነዚህ መረጃዎች የድሮው ሱሪ እራሱ ረጃጅምም እንደነበረው እንረዳለን።

ሐ/ በዚያ ላይ የርዝመት ልዩነት ከኖረም ሁለቱ “የተለያዩ ናቸው” ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። መጤው ነገር ማስረዘሙ ከሆነ አጠቃላይ ልብሱ ላይ ሳይሆን ማስረዘሙ ላይ ማነጣጠር ነው።

ስለዚህ *“ሱሪ እስከ መሀል ባት ሊሆን አይችልም። የሚለብሰው ሰው መሀል ባት አድርጎ መሄድን ያፍራል”* ማለት ከእውነት የራቀ ነው። በሃገራችንም ሊያፍሩ ቀርቶ በልበ-ሙሉነት ሱሪያቸውን የሚያሳጥሩ ብዙ ሙስሊሞች መኖራቸው የዚህን ሙግት ባዶነት ለማሳየት በቂ ምሳሌ ነው።

የሚደንቀው ፀሐፊው *“እስከ መሀል ባት አድርጎ ምንም የሚሸፍነው ሳይኖር ቢወጣ አስነዋሪ መመሳሰል ላይ ይወድቃል። በክህደት በሺርክና ማፈንገጥ ሰዎች ሙሉ መነከር ነው። … [እስከ መሀል ባት ድረስ አሳጥሮ ቢለብሰው ይፈቀዳል ማለት አይደለም። እንዲያውም እስከ መሀል ባቱ አሳጥሮ ቢወጣ ይሄ በራሱ በከሃዲዎች መመሳሰል ላይ ይበልጥ መነከር ነው]”* ማለቱ ነው። [አልቂስጧስ፡ 204]

ሱብሓነላህ! ይሄ አነጋገር ሱሪ ከለበሱ አይቀር ማስረዘሙ ይሻላል ማለት ነው። ይሄ አደገኛ የሆነ ድምዳሜ ነው።

- ልብስ ማስረዘምን ከሚከለክሉ ሐዲሦች ጋርም መላተም ነው።
- *"ሱሪ ሐራም ነው"* ቢባል እንኳን ማሳጠሩ በራሱ ያለጥርጥር ወንጀልን መቀነስ ነው።
- ደግሞም *"ሱሪ ሁሉ ረጅም ነው። ካፊሮቹ አስረዝመው ነው የሚለብሱት"* የሚል ሰው እንዴት አሳጥሮ የሚለብስን ሰው ይበልጥ ተመሳስሏል ይላል? እንዲያውም *"ሲያሳጥር መመሳሰሉን ቀንሷል"* ሊል ይገባው ነበር።
- የፀሐፊው አነጋገር ሱሪን በስም ጠቅሰው ከማስረዘም ከሚከለክሉ የዘመናችን ዑለማዎች ፈትዋ ጋርም የሚቃረን ነው። *"ሱሪ ሐራም ነው"* የሚሉት ሸይኹል አልባኒ እራሱ ማስረዘሙን ይከለክላሉ። [አስሶሒሐህ፡ 2682] ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚንም ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ። [ሸርሑ ሪያዱ አሷሊሒን፡ ሐዲሥ ቁ. 801] ሸይኽ ፈውዛንም እንዲሁ ማስረዘም ላይ የመጣው ክልከላ ሱሪንም እንደሚመለከት ይናገራሉ። http://www.alfawzan.af.org.sa/node/3675

## 2. ማሰሪያ

ሌላው ሱሪና ሲርዋል ይለያያሉ የሚሉ ሰዎች የሚያነሱት "መለያ" መታጠቂያቸውን መሰረት ያደረገ ነው። *"ሲርዋል በውስጡ የሚሆን ማሰሪያ ገመድ አለው። ሱሪ ግን አንዳንድ ካልሆነ በስተቀር በብዛት ቀበቶ ነው ያለው"* ይላሉ። [አልቂስጧስ፡ 137]

እስኪ አሁን ይህን መለያ አድርጎ ማቅረብን ምን ይሉታል?! ሱብሓነላህ!! ዞሮ ዞሮ ሁለቱም አገልግሎታቸው አንድ ነው። ሁለቱም ማሰሪያ ናቸው። አለቀ። በቀበቶ ታሰረ፣ ውስጥ ባለ ገመድ ተሸምቅቆ ታሰረ ልብሱ ላይ

ምን የሚፈጥረው ልዩነት አለ? ሲርዋሉስ በቀበቶ ሲታሰር ሐራም ሊሆን ነው? አሁን ይሄ ቁም-ነገር ሆኖ እንደ መለያ መቅረብ ነበረበት? ደግሞም ቀበቶ የማይፈልጉ ብዙ ሱሪዎች ወይም ቁታዎች አሉ። እነዚህስ ማሰሪያቸው ስለተቀየረ ሲርዋል ይሆናሉ?!

ይሄ እንግዲህ “የድሮዎቹ ቀበቶ አይጠቀሙም” የሚለውን ለሙግት ያክል ብንቀበል ነው። እንጂ ሱሪና ሲርዋል “ይለያያሉ” የሚሉት ሸይኽ አልባኒ እራሳቸው ዛሬም በአንዳንድ ሃገራት ይገኛል የሚሉት ሲርዋል ሰዎች በቀበቶ ይታጠቁታል። ይህም *“የድሮው ቀበቶ የለውም”* የሚለውን አጉል ሙግት መሰረተ-ቢስነት የሚያሳይ ነው።

### 3. የሚሰራበት የጨርቅ አይነት

*“የሲርዋል ጨርቁ ቀላል ልብስ ነው። ሱሪ ግን በአብዛሀኛው የተለያዩ ቀለማት ያሉት ወፍራም ጨርቅ ነው።”* [አልቂስጧስ፡ 138]

ወላሂ እያንዳንዱ የሚቀርቡ ምክንያቶች አስተዛዛቢ ቢሆኑም ይሄኛው ግን ይበልጥ የሚደንቅ ነው። ይህ ነገር እውነት ቢሆን ኖሮ ዘመናዊው ሱሪ ከድሮው የሚሻልበት ምክንያት ሆኖ ነው መቅረብ የነበረበት። ያለጥርጥር ከቀላሉ ይልቅ ከባዱ ተመራጭ ነውና። ነገር ግን የድሮውም ሱሪ ከሱፍ፣ ከቆዳ፣ ከሐርና ከጥጥ ይዘጋጅ እንደነበር የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች አሉ። ብዙ ጊዜ የልብሶች ክብደትና ቅለት ለባሾቹ ከሚኖሩበት አየር ንብረት ጋር የሚያያዝ ነው። ብርዳማ አካባቢዎች የሚኖሩ ወፍራም ልብሶችን ያዘወትራሉ። ሞቃት አካባቢዎች የሚኖሩት ደግሞ ለአየሩ ተስማሚ የሆነ

አለባበስን ይጠቀማሉ። ስለዚህ ጥንትም ዛሬም ስስም ወፍራምም ሱሪዎች በተጨባጭ አሉ።

የቀለሙ ጉዳይ መቼም ጭራሽ መልስ የሚገባውም አይደለም። የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ቀሚሶች፣ ጥምጣሞች፣ ጃኬቶች፣… ላይ ተቃውሞ ለማንሳት የሚዳፈር ይኖራል? በዚያ ላይ "የጥንቱ ነጭ ብቻ ነው" የሚል ካለ መቼም መረጃ ማቅረብ የማይችልበትን ሙግት እየከፈተ ነው።

## 4. ሌሎች መለያዎች

ሱሪን ሐራም ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ኪስና ዚፑን እያነሱ አቃቂር እስከመፈለግ ደርሷል። [አልቂስጧስ፡ 138] ለምሳሌ *"ሲርዋል በቀላሉ መውለቅ ስለሚችል ዚፕ አያስፈልገውም ነበር። ሱሪ ግን ላጠቃቀም ስለሚከብድ ዚፕ ተደረገለት"* የሚል ምክንያት ቀርቧል። ይሄ ግን በቀላሉ የማይወልቀው ሱሪ እንዲያውም ይበልጥ አስተማማኝ እንደሆነ የሚጠቁም ነው። በዚያ ላይ ሽንት እንዳይረጫጭ ካልተሰጋ ቆሞ መሽናት ስለሚፈቀድ ዚፑ በምንም መልኩ መለያ ሆኖ የሚቀርብ አልነበረም። ልክ ጀላቢያው፣ ሸሚዙ፣ ጃኬቱ ላይ ዚፕ ስለኖረ ተቃውሞ ማንሳት እንደማያዋጣው ይህም አያዋጣም። እስኪ አሁን ጀላብያዎች ላይ ዚፕ ስለተደረገ *"መጤ ናቸው። ከድሮው ይለያሉ"* የሚል ተቃውሞ የሚያነሳ ይኖራል?

የኪስ ጉዳይም መልስ የማይሻ ተራ ብዥታ ነው። በዚያ ላይ ዚፕም ኪስም የሌላቸው ቱታዎች ዛሬም አሉ። እነዚህንስ *"ኪስ አልባ ስለሆኑ መጤ አይደሉም"* ብለው ይቀበላሉን?

### 5. “ሲርዋል ከሱሪ በተለየ የውስጥ ልብስ ነው”- ሌላኛው “መለያ”

ሁለቱ ይለያያሉ የሚሉ ሰዎች ሌላኛው ምክንያት *“ሲርዋል ከሱሪ በተለየ የውስጥ ልብስ ነው”* የሚል ነው። ይሄም ንትርክ የሚቆርጥ የማያሻማ መረጃ የሚያቀርቡበት አይደለም። ግፋ ቢል የሚጠቅሱት *“እከሌ የሚባሉት ሶሐባ ሱሪ ከውስጥ ለብሰው ታይተዋል”* የሚል ነው። ይሄ ግን ሱሪ ከውጭ አይለበስም ነበር የሚል መልእክት የለውም። ድሮም ዛሬም ከቀሚስ ስር፣ ከኩታ ስር ሸርጥ የሚለብሱ ነበሩ፣ አሉም። ስለዚህ ከዚህ በመነሳት ሸርጥ የውስጥ ልብስ ነው ማለት ያስኬዳል?!

እንዲያውም የድሮውም ሱሪ ከውጭ ይለበስ እንደነበር የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ። ለምሳሌ፡-

<u>**መረጃ-1**</u>

**عن ابن عباس رضي الله عنهما قال خطبنا النبي ﷺ بعرفات، فقال: من لم يجد الإزار فليلبس السراويل، ومن لم يجد النعلين فليبس الخفين**

ከኢብኑ ዐባስ ረዲየላሁ ዐንሁማ ተይዞ ነብዩ ﷺ ዐረፋት ላይ እንዲህ ሲሉ ኹጥባ አደረጉልን፡- *“(ሐጅ ላይ) ሸርጥ ያላገኘ ሱሪ ይልበስ። ጫማዎችን ያላገኘ ኹፎችን ይልበስ።”* [ቡኻሪ፡ 1843]

በዚህ ሐዲስ ውስጥ ከሐጅ ስርአት ውጭ ላለ አካል ሱሪ መልበስ እንደሚቻል ጥቆማ አለው። ለዚህም ነው ኢማሙ አሕመድ ረሒመሁላህ

ከዚህ ሐዲሥ ስር *"ይሄ (ሐዲሥ) ሰዎቹ (ሶሐቦቹ) ሱሪ እንደለበሱ ማስረጃ ነው"* ማለታቸው። [ፈትሑል ባሪ ሊብኒ ረጀብ፡ 2/175]

የሐዲሡ መልእክት ሐጅ ላይ ያለ ሰው ሽርጥ ካጣ ሱሪ መልበስ ይቻላል የሚል ነው። ነገር ግን ይሄ ለአስገዳጅ ምክንያት ሲባል የተፈቀደው ሐጅ ውስጥ ላለ ብቻ ነው። ከሐጅ ውጭ ያለ ሰው ይሄ ገደብ አይመለከተውም። ረጋ ብሎ ላስተዋለ ሰው የሐዲሡ መልእክት ግልፅ ነው። *"አይ ከሐጅ ውጭ እራሱ ከልብስ ውስጥ ብቻ ነው የሚፈቀደው"* የሚል ሰው ግልፅና የማያሻማ ማስረጃ ሊያቀርብ ግድ ይለዋል።

***<u>መረጃ-2</u>***

**عَنْ أَبِي أُمَامَةَ قَالَ خَرَجَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَلَى مَشْيَخَةٍ مِنْ الْأَنْصَارِ بِيضٌ لِحَاهُمْ فَقَالَ يَا مَعْشَرَ الْأَنْصَارِ حَمِّرُوا وَصَفِّرُوا وَخَالِفُوا أَهْلَ الْكِتَابِ قَالَ فَقُلْتُ يَا رَسُولَ اللهِ إِنَّ أَهْلَ الْكِتَابِ يَتَسَرْوَلُونَ وَلَا يَأْتَزِرُونَ فَقَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ تَسَرْوَلُوا وَائْتَزِرُوا وَخَالِفُوا أَهْلَ الْكِتَابِ قَالَ فَقُلْتُ يَا رَسُولَ اللَّهِ إِنَّ أَهْلَ الْكِتَابِ يَتَخَفَّفُونَ وَلَا يَنْتَعِلُونَ قَالَ فَقَالَ النَّبِيُّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَتَخَفَّفُوا وَانْتَعِلُوا وَخَالِفُوا أَهْلَ الْكِتَابِ قَالَ فَقُلْنَا يَا رَسُولَ اللهِ إِنَّ أَهْلَ الْكِتَابِ يَقُصُّونَ عَثَانِينَهُمْ وَيُوَفِّرُونَ سِبَالَهُمْ قَالَ فَقَالَ النَّبِيُّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قُصُّوا سِبَالَكُمْ وَوَفِّرُوا عَثَانِينَكُمْ وَخَالِفُوا أَهْلَ الْكِتَابِ**

ከአቡ ኡማማ ተይዞ (እንዲህ ብለዋል፡-) *"በአንድ ወቅት የአላህ መልእክተኛ ﷺ ፂማቸው ነጫጭ በሆኑ የአንሳር ሽማግሌዎች ዘንድ ወጡና። 'እናንተ የአንሳር ጎሳዎች ሆይ! (ፂማችሁን) በቀይና በዳለቻ መንከሪያ ቀቡ። ከመፅሐፉ*

*ሰዎች ተለዩ' አሉ። እኔም 'የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የመፅሐፉ ሰዎች ሲርዋል (ሱሪ) ይለብሳሉ። ግና ሽርጥ አይታጠቁም' አልኩኝ። ይህኔ የአላህ መልእክተኛ 'ሲርዋል ልበሱ። ሺርጥም ታጠቁ። ከመፅሀፉ ሰዎች ተለዩ' አሉ።*

*'የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የመፅሐፉ ሰዎች ኹፍ ይለብሳሉ። ጫማ ግን አይጫሙም' አልኳቸው። ነብዩም ﷺ 'ኹፍ ልበሱ፤ ጫማም ተጫሙ። ከመፅሐፉ ሰዎች ተለዩ' አሉ። 'የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የመፅሐፉ ሰዎች ፂማቸውን ይቆርጣሉ። ቀድሞ ቀመሳቸውን ግን ያጎፍራሉ' አልናቸው። ነብዩም ﷺ 'ቀድሞ ቀመሳችሁን ቁረጡ። ፂማችሁን ግን አጎፍሩ። ከመፅሐፉ ሰዎች ተለዩ' አሉ።"* [አስሶሒሐህ፡ 1245]

ከዚህ ሐዲሥ ሲርዋል (ሱሪ) መልበስ እንደሚፈቀድ ብቻ ሳይሆን የውጭ ልብስ እንደሆም መረዳት ይቻላል። እንዲያውም ይህን መነሻ በማድረግ ከ"ይፈቀዳልም" በማለፍ "ሱና ነው" ያሉ አሉ። [ከሽፉል ቂናዕ፡ 1/286] ሐዲሡ አንዳንዴ ሲርዋል፣ ሌላ ጊዜ ሽርጥ በመልበስ ከአይሁዶች መለየት እንደሚገባ ያመላክታል።

አንዳንዶች የሐዲሡ መልእክት ሲርዋል ለብሶ በሱ ላይ ሽርጥ መደረብ ይገባል የሚል እንደሆነ ይሞግታሉ። ሀሳባቸውን ሲያጠናክሩም *"አንዳንዴ ሽርጡን አንዳንዴ፣ ሲርዋሉን የምንለብስ ከሆነ ሲርዋል በምንለብስበት ጊዜ ከአይሁድ ጋር እየተመሳሰልን ነው"* የሚል አመክንዮ ያቀርባሉ። ለዚህ የሚሰጠው መልስ፡-

1. ለዚህ ሙግታቸው የሚበጅ አንድም መረጃ ማቅረብ አይችሉም። ይሄ ብቻውን የሙግታቸውን ባዶነት ለማሳየት በቂ ነው። እንዴት ሰው ያለ

አንድ ማስረጃ አንድን ልብስ በዚህ መልኩ መልበስ ሐራም ነው ይላል?! ሱሪ ዒባዳ ሳይሆን ዐዳ ነው። ዐዳ ደግሞ ግልፅ መረጃ የከለከለው ሲቀር መሰረቱ ሐላል ነው። *"ከልብስ ስር ካልሆነ አይፈቀድም"* የሚል የቁርኣን አንቀፅ ወይም ሐዲሥ ወይም የሰለፎች ኢጅማዕ የለም። ታዲያ ምን ላይ ተመርኩዘን ነው የምንከለክለው?! በብዙ ሐዲሦች ላይ ከመጠቀሱም ጋር አንድም ቦታ ሱሪ ከውስጥ ካልሆነ በስተቀር ለብሶ መውጣት "ሐራም ነው" የሚል የለም።

2. በርካታ ሰለፎች ሱሪ ለብሰው ታይተዋል። የዛሬ ተቃዋሚዎች ግን በአንድ ወይም በሁለት ላይ የተጠቀሱትን በመለጠጥ የሁሉም አለባበስ ከልብስ ስር እንደነበር ይሞግታሉ። "መረጃቸው" ግን *"ኣይ እሳቸው ታላቅ ሰው ናቸው። ሱሪ ለብሰው መቀመጫቸው እየተባለጠ ይወጣሉ ብሎ ማሰብ ይከብዳል"* የሚል ደፋር ግምት ብቻ ነው።

3. ደግሞም "የድሮው ሱሪ ቁመት እስከ ጉልበት ነው" የሚል ሰው እንዴት "ላለመመሳሰል ከላዩ ላይ ሸርጥ ይደረብበት" ይላል?! የት ይታያልና ነው በዚህ መልኩ ለሚለበስ ልብስ ስለመመሳሰል የሚወራው? ለዚህ ባዶ ሙግት ዋጋ የሚሰጥ ሰው ከጀላብያ ስር ሱሪ መልበስም መመሳሰል ስለሆነ ክልክል ነው ሊል ይገባዋል። (በተለይም የድሮውና የአሁኑ ሱሪ ይለያያሉ የሚሉ ሰዎች በምንም መልኩ አሁን ያለውን ሱሪ ከቀሚስ ስር እንኳን ሊለብሱ አይገባም።) ጥቂት ሸርጥ ከሚለብሱት ውጭ ዛሬ ብዙዎቹ ከቀሚሳቸው ስር የሚለብሱት ሱሪ መሆኑ ይታወቃል።

4. በሐዲሡ ውስጥ *"(ፂማችሁን) በቀይ ወይም በዳለቻ ቀቡ"* የሚለው ከሁለት በአንዱ ቀቡ ማለት እንጂ ሁለቱንም ተጠቅማችሁ ፂማችሁን ዝንጉርጉር አድርጉት ማለት አይደለም። ልክ እንዲሁ *"ሲርዋል ልበሱ። ሺርጥም ታጠቁ"* የሚለውም አንዳንዴ ያንን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ይሄንን

እየለበሳችሁ ከነሱ ተለዩ ማለት ነው። ፂም ላይ አንዱን ቀለም በመቀባት ከአይሁዶቹ መለየት እንደሚኖረው እዚህም እያፈራረቁ በመልበስ መለየቱ ይኖራል።

5. በሐዲሡ እንደተገለፀው አይሁዶች ኹፍ እንጂ ጫማ አያደርጉም ነበር። ከነሱ ለመለየት የተሰጠው ነብያዊ ትምህርት *"ኹፍ ልበሱ፤ ጫማም ተጫሙ"* የሚል ነው። መልእክቱ አንዳንዴ ኹፉን፣ ሌላ ጊዜ ጫማውን ልበሱ ማለት እንጂ በርግጠኝነት ደርባችሁ ልበሱ ማለት አይደለም። በነዚህ ሰዎች ግንዛቤ ከተጓዝን ኹፍ በጫማ ላይ ካልተደረበ በስተቀር በአይሁድ መመሳሰል ስለሆነ ብቻውን መልበስ ክልክል ነው ማለት ነው። በነሱ አመክንዮ (ሎጂክ) መሰረት ጫማ ስንለብስ ጊዜ በአይሁዶቹ ተመሳስለናል ማለት ነው። ይሄ ስሜት ሽብቦ ላልያዘው ሁሉ የማይሰወር ሐቅ ነው።

6. *"ሱሪውን በምንለብስ ጊዜ በአይሁድ መመሳሰል ይኖራል"* የሚለው አመክንዮም ብልሹ ግላዊ እይታ (ረእይ) ነው። ካለፈው ነጥብ ይህን መረዳት ቢቻልም ይበልጥ ግልፅ የሚያደርግልን አንድ መረጃ ነብዩ ﷺ *"ከአይሁዶች ተለዩ። እነሱ በጫማዎቻቸውና በኹፎቻቸው አይሰግዱም"* ማለታቸው ነው። [ሶሒሕ አቢ ዳውድ፡ 659] በተጨማሪም *"በጫማዎቻችሁ ስገዱ። በአይሁድ አትመሳሰሉ"* ይላሉ። [ሶሒሑል ጃሚዕ፡ 3790] መቼም የነዚህ ሐዲሦች መልእክት በጫማቸው ከማይሰግዱት አይሁዶች እንለይ ዘንድ አንዳንዴ በጫማችን እንድንሰግድ እንጂ በባዶ እግር መስገድ ክልክል ነው ማለት አይደለም። ይሄ ሲበዛ ግልፅ ነው። በነዚህ ወንድሞቻችን ግንዛቤ መሰረት ግን በባዶ እግራችን ስንሰግድ ጊዜ በአይሁድ እተመሳሰል ነው ማለት ነው።

ከአፋቸው በቀጥታ ባይወጣም ስሌታቸው የሚሰጠው ይህንን ነው። አሳዛኝ ግንዛቤ!!

ስለዚህ አንዳንዴ ሌላ ልብስ መልበሱ በቋሚነት ሱሪ ከሚለብሱት አይሁዶች ለመለየት በቂ ነው። አልኢማም ሸውካኒ ረሒመሁላህ ከላይ ባሳለፍነው ሐዲሥ ስር *"በዚህ ውስጥ ሲርዋሎችን በመልበስ ላይ ፍቃድ አለ።* ***<u>ከመፅሐፉ ሰዎች መለየቱ አንዳንድ ወቅት ላይ በመልበስ ብቻ ይገኛል። እንጂ ሁልጊዜም ሲርዋልን በመተው አይደለም"</u>*** ይላሉ። [ነይሉል አውጣር፡ 2/123]

ግና ሙግታቸው አያልቅም። ቀደም ብሎ የቀረበው ሐዲሥ መልእክት *"አንዳንዴ ሸርጥ ሳይደረብበት ሱሪ መልበስ እንደሚቻል የሚጠቁም ቢሆን ኖሮ ሶሐቦች በዚህ መልኩ ይለብሱ እንደነበር መረጃ ይደርሰን ነበር"* ይላሉ። ነገር ግን ይለብሱ እንዳልነበርስ ምን ማስረጃ አለ? አለማወቅ አለመኖርን አያሳይም። ደግሞም በዚህ መልኩ ባይለብሱስ ግልፅ ከልካይ ማስረጃ ባልቀረበበት ይሄ ብቻውን ለመከልከል በቂ ነው ወይ? ይሄ እኮ ዐዳ እንጂ በራሱ ዒባዳ አይደለም። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

> *"የሒጃዝ ነዋሪዎች ሃገራቸው ብርዳማ አይደለም። ስለሆነም ሸርጦችንና ኩታዎችን ነበር የሚያዘወትሩት።* ***<u>ሱሪ ከነሱ ዘንድ ቀላል ነበር።</u>*** *እንዲያውም ከነሱ ውስጥ ሱሪ ጭራሽ የማይለብስም ነበር። ከነዚህም ውስጥ ዑሥማን ኢብኑ ዐፋንና ሌሎች ይጠቀሳሉ።* ***<u>ይሄ እንግዲህ ከብርዳማ ሃገራት በተለየ ነው።</u>*** *እነዚህኞቹ ሸርጥና ኩታዎች ላይ ቢገደቡ አይበቃቸውም። ይልቁንም ቀሚስ፣ ኹፎች፣ ለምድና ሱሪዎች ያስፈልጓቸዋል።"* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 21/202]

**መረጃ-3**

ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- *“(ሐጅ ወይም ዑምራ ላይ ያለ ሰው) ቀሚስ፣ ጥምጣም፣ **ሱሪ** እና በርኖስ አይለብስም።... ጫማዎችን ካላገኘ ኹፎችን ይልበስ።...”* [ቡኻሪ፡ 134] በሌላም ሐዲሥ አንድ ሰው ተነስቶ *“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ኢሕራም ስናደርግ ጊዜ ምን እንድንለብስ ታዘናለህ?”* ሲላቸው *“ቀሚስን፣ **ሱሪዎችን፣** ጥምጣሞችንና በርኖሶችን አትልበሱ። ኹፎችንም እንዲሁ። ጫማዎች የሌለው ሰው ካልሆነ በስተቀር። ...”* ብለዋል። [ቡኻሪ፡ 5805]

ከነዚህ ሐዲሦች ሐጅ ወይም ዑምራ ላይ ያልሆነ ሰው ልክ የተዘረዘሩትን ሌሎቹን አልባሳት መልበስ እንደሚችለው ሱሪ መልበስም ይችላል። ከተዘረዘሩት አልባሳት ውስጥ ነጥሎ *“ሱሪ ለውስጥ ነው የተፈቀደው”* የሚል አካል የግል አስተያየት ሳይሆን ትክክለኛና ቀጥተኛ (ሶሒሕና ሶሪሕ) ማስረጃ ሊያቀርብ የግድ ይለዋል። መረጃዎች ያሉት ደግሞ በተቃራኒው ነው።

**መረጃ-4**

አቡ ኸልዳህ ረሒመሁላህ *“አቡል ዓሊያን ሱሪ ለብሶ አየሁት። ‘ምነው ከቤት ውስጥ ሱሪ?’ ስለው **‘ይሄ ከወንዶች ልብስ ነው’** አለኝ”* ይላሉ። [ሙሶነፍ ኢብኑ አቢ ሸይባ፡ 24876]

ይህን ትውፊት ዋጋ ለማሳጣት *“እሳቸው ከቤት ውስጥ ነው የለበሱት። ለብሶ ወደ ውጭ መውጣት መቻሉን አያሳይም”* ይላሉ። ግና፡-

- ከቤት ውስጥ ቢሆንስ ሰው እያያቸው አይደል? ተመልካች ከኖረ ውስጥና ውጭ መሆኑ ምን ልዩነት አለው?! የአካልን ቅርፅ የሚያሳይና ከግብረ-ገብነት ጋር የሚጋጭ ከሆነ ምነው ከሰው ፊት ይለብሱታል?!
- *"ምነው ከቤት ውስጥ?"* የሚለው አነጋገር እንዲያውም ከቤት ውጭ እንደሚለበስ ጥቆማ አለው። ምናልባት *"አይ ሱሪ ሃፍረተ-ገላን ለመጠበቅ ነው የሚጠቅመው። ከቤታቸው ደግሞ አጅነቢ ስለሌለ መልበስ አይጠበቅባቸውም። ለዚያ ነው 'ምነው ከቤት ውስጥ?' ብለው የጠየቋቸው"* የሚል ካለ ለዚህ ሙግቱ መረጃ ማቅረብ አለበት። በተረፈ ዘጋቢው *"እኔ ስገባ ልብስ ደረቡ"* አላለም። ይህም *"ሱሪ የሃፍረተ-ገላን ቅርፅ ስለሚያሳይ ክልክል ነው" "ከሳሊሖች አንድም የለበሰው የለም"* የሚሉ ሰዎች ጩኸት ልክ እንዳልሆነ ያሳያል።
- *"ይሄ የወንዶች ልብስ ነው"* የሚለው የአቡል ዓሊያ አነጋገርም ብቻውን እንደሚለበስ ይጠቁማል። ከልብስ ውስጥማ ሴቶችም ይለብሱት እንደነበር መረጃዎች አሉ። ስለዚህ እራሱን ችሎ መለበሱን ነው *"የወንዶች ልብስ ነው"* ማለታቸው። መረጃ ማድረግ የፈለግኩትም እዚህ ላይ ነው። በዘመኑ የነበረውን ግንዛቤ ያሳያልና።

<u>**መረጃ-5**</u>

ኢማሙ አሕመድ ረሒመሁላህ ከሱሪና ከሸርጥ የትኛውን እንደሚወዱ ሲጠየቁ፡ *"ሱሪ መጤ ነው። ቢሆንም ግን (ከሸርጡ) ይበልጥ ሸፋኝ ነው"* ብለዋል። [መሳኢሉ ኢብኒ ሃኒ፡ 2/147] ከዚህ የምንረዳው፡-

1. ሱሪ ቢኖርም በስፋት የሚታወቅ እንዳልነበር፣

2. በጊዜውም በተደራቢነት ሳይሆን እንደ አማራጭነት ይለበስ እንደነበር፣ (አጠያየቁንና አመላለሱን በጥንቃቄ ያጢኑት።) የኢማሙ አሕመድ መልስ የሚያመላክተው ሁለቱን በአንድ መልበስን አይደለም ሲሉ የገለፁ ዐሊሞች አሉ። [ጊዛኡል አልባብ፡ 2/239]
3. እንዲያውም ይበልጥ ሀፍረተ-ገላን የሚሸፍን እንደሆነ እንረዳለን።
4. ይህም *"ከጥንት እስከ ዛሬ ደጋጎች ሱሪ አልለበሱም"* የሚለው ሙግት ባዶ እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን።
5. *"ሸርጦች ናቸው አንተ ዘንድ ይበልጥ የተወደዱት ወይስ ሱሪዎች?"* የሚለው ጥያቄ እራሱ በጊዜው ሁለቱም ይለበሱ እንደነበር ጥቆማ አለው። ይህም ሰለፎች ዘንድ በጉዳዩ ላይ የነበረውን አረዳድ የሚያሳይ ነው።

***<u>መረጃ- 6</u>***

ኢብኑ ረጀብ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- ***<u>"በአንድ ልብስ (ብቻ) የሚሰግድን በተመለከተ</u>*** *ሻፊዒይና የእኛ ባልደረቦች (ሐንበልዮች) የሚሉት በላጩ ቀሚስ ነው። ቀጥሎ ኩታ። ቀጥሎ ሸርጥ።* ***<u>ቀጥሎ ደግሞ ሱሪ ነው።</u>*** *ከሻፊዒ ባልደረቦች ውስጥ ከሸርጥ ይልቅ* ***<u>ሱሪን ያስቀደመ አለ።</u>*** *ያለፈው የነቢዒ ንግግርም ይህን ነው የሚጠቁመው።"* [ፈትሑል ባሪ፡ 2/175]

ከዚህ የኢብኑ ረጀብ ንግግር ሱሪ ከሰለፎች ዘንድ በተደራቢነት ሳይሆን እራሱን ችሎ የሚለበስበት ሁኔታ እንደነበር ግልፅ መልእክት አለው። ከልቦና ሆነው ያጢኑት። ከዚህስ በኋላ *"ደጋጎች ከጥንት እስከ ዛሬ ሱሪ ለብሰው አያውቁም"* የሚል አጉል ሙግት ያዋጣ ይሆን? *"ከልብስ ውስጥ ነው"*

እንዳይባል "አንድ ልብስ" ተብሎ በማያፈናፍን መልኩ ተገልጿል። እንዲያውም ከሌሎቹ ከሸርጥ አስቀድመውታል።

## 6. የተደራቢ መለያ

ሌላው የአሁኑ ሱሪ ከድሮው ይለያል የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቡት *"ሲርዋል ከላይ ሲደረብበት ከሱሪ በተለየ ውበት ይጨምራል። ሱሪ ግን ሲደረብበት ለእይታ ይቀፋል፤ የለባሹንም ቅርፅ ያጠፋል"* የሚል ነው። [አልቂስጢስ፡ 138-139]

ሰዎቹ የአሁኑን ሱሪ ከድሮው ለመለየት እንደተቸገሩ የሚለቃቅሙት አቃቂር ይጠቁማል። በነገራችን ላይ "ሱሪ ሐራም ነው" የሚሉትን ጨምሮ ዛሬ ብዙዎቹ ቀሚስ የሚለብሱ ሰዎች ከስር የሚለብሱት ዘመናዊውን ሱሪ ነው። ይህም ተግባራቸውና ሙግታቸው እንዳልታረቀ ያሳያል። ደግሞም እውነት ለመናገር ውበት መለያ ከሆነ ከውስጥ ሽርጥ ከመልበስ ይልቅ የተሻለ ውበት ያለው ሱሪው ነው። በዚህ ላይ ብዙ ማለት አልፈልግም። እንዲሁ ለትዝብት ያክል ብቻ ነው ያቀረብኩት።

## 7. "ሱሪ ከሲርዋል በተለየ የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ ያሳያል"

ይህን ምክንያ ያነሱት ሸይኹል አልባኒ ናቸው። [17] ነገር ግን፡-

---

[17] ከላይ ያሉትን አስተዛዛቢ "መለያዎች" የዘረዘረው ፀሐፊ ግን የአልባኒን ከልካይ ንግግሮች በተደጋጋሚ ከመጥቀሱ ጋር ይሄኛውን በሳቸው የተጠቀሰውን መለያ አላካተተውም፡፡ ምናልባትም ይህን ያላደረገው የድሮው ሱሪ እራሱ የሰውነት ቅርፆችን የሚያሳይበት ሁኔታ እንዳለ በቀደምት ዑለማዎች መጠቀሱ ይመስለኛል፡፡ እራሱም ይህንን የነካካበት ሁኔታ

ሀ/ የድሮው ሱሪ ስፋት አሁን ካለው የሚለይ እንደሆነ የማያሻማ ማስረጃ የለም። አሁን በአንዳንድ አካባቢዎች ያለውን መነሻ በማድረግ የድሮው ይሄ ብቻ ነው ለማለትም አያስደፍርም። ብዛት የለውም እንጂ በምዕራቡም አለም ከላይ በጣም ሰፍተው ከጉልበት ጀምረው እየጠበቡ የሚሄዱ ሱሪዎች ነበሩም፣ አሉም። በሃገራችን እንዲህ አይነቱ ሱሪ በሰፊው ነበር። መጠኑ ቢሳሳም ዛሬም አለ። በሰርግ፣ በበአላት፣ በለቅሶ ላይ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚለበሱትን የሃገር ባህል ልብሶች ያስተውሉ።

ለ/ እንዲያውም የድሮው ሱሪ እራሱ የአካል ቅርፆችን በከፊልም ቢሆን የሚያጎላበት ሁኔታ እንደነበር ጥቆማዎች አሉ። ይህም መለያ ተደርጎ የሚነሳው ነገር ልክ እንዳልሆነ ይጠቁማል። የድሮው እራሱ ቅርፅ ሊያሳይ እንደሚችል ከተናገሩ ዐሊሞች ውስጥ የጥቂቱን ሀሳብ እንመልከት።

**ኢብኑ ተይሚያ፡-** *“ከቀሚስ ጋር ሱሪን መልበስም እንዲሁ* ***<u>የተወደደ</u>*** *ነው። ምክንያቱም ይበልጥ ሸፋኝ ነውና። ከቀሚስ ጋር ሲሆን <u>የሰውነት ቅርፆች ጎልተው አይወጡም።</u> ቀሚስ ከሱሪ በላይ መሆኑ ኩታ ከሱሪ በላይ ከሚሆነው በላይ ይሸፍናል። ምክንያቱም* ***<u>ይሄኛው የአካል ቅርፆችን አይሸፍንምና</u>****”* ይላሉ። [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 21/202]

**ሺራዚ፡-** *“ሱሪዎች* ***<u>የአካል ከፍሎችን ቅርፅ ያሳያሉ</u>****”* ይላሉ። [አልሙህዘብ፡ 221]

---

አለ፡፡ እንጂ መረጃ ቢደግፈው **<u>ኖሮ</u>** እሱ ከጠቀሳቸው ነጥቦች ይልቅ ይሄኛው ይበልጥ ዋጋ ነበረው፡፡

**መሕሙድ አሱብኪ፡-** *"ምናልባት ነብዩ ﷺ ያለ ኩታ በሱሪ ብቻ መሰገዱን የከለከሉት **<u>የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ ስለሚያሳይ</u>** የላይኛውን አካል ስለሚያጋልጥ ነው።"* [አልመንሀል፡ 5/27]

## 8. <u>"ዘመናዊው" ሱሪ መነሻው ምዕራቡ አለም ነው"</u>

ሌላው የአሁኑና የድሮው ሱሪ ይለያያሉ የሚሉ ሰዎች የሚያነሱት "መለያ" *"የአሁኑ ሱሪ ከምዕራቡ አለም የመጣ እንጂ መነሻው ከሙስሊሞች አይደለም"* የሚል ነው።

በርግጥ ጥንታዊው ሱሪ እራሱ መጤ እንደሆነ የሚጠቁሙ ብዙ መረጃዎች አሉ። ዐረቦች ያን ያክል አያውቁትም። ለምሳሌ ያክል፡-

1. ብዙሃኑ የቋንቋ ሊቃውንት "ሲርዋል" ቃሉ እራሱ ስር መሰረቱ ዐረብኛ እንዳልሆነ ገልፀዋል። [ዘኺረቱል ዑቅባ፡ 35/25]
2. ብቻውን የሚለብሱትም የሁዶች እንደነበሩ በሶሐቦች ተገልጿል።
3. ኢማሙ አሕመድም *"ሱሪ መጤ ነው"* ማለታቸውን አሳልፈና።

በነገራችን ላይ በሱሪ ላይ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት መነሻው ምስራቁ እንጂ ምዕራቡ አለም አይደለም። በምዕራቡ አለም ዘግየት ብሎ ከመታወቁ በፊት በስፋት የነበረው በምስራቁ የኤሺያ ክፍለ አለም ነው።

ግሪካውያን "ጆንያ" እያሉ የምስራቁ ልብስ እንደሆነ በማውሳት ያጣጥሉት ነበር። ሮማውያንም የኋላ-ቀሮች ልብስ እንደሆነ ይገልፁት ነበር። ኋላ ግን ከሜዲትራኒያን ባህር በመለስ ወዳለው አካባቢ ሲስፋፉ ነው ሱሪን ከምስራቁ የወሰዱት። ሮማውያኑ ዘንድ ሁለት አይነት ሱሪዎች ተስፋፍተው

ነበር። አንዱ እስከ ጉልበት ወይም መሀል ባት ድረስ ቁመት ያለው ሲሆን ሌላው ደግሞ እስከ ቁርጭምጭሚት ድረስ ነበር። ኋላ ላይ የነሱ ዲዛይን ወደ ፋርስና መካከለኛው ምስራቅ ተስፋፍቷል። ይሄ ሁሉም ጥንታዊ ታሪክ ነው። ወደ ህዝብ ከመውረዱ በፊት የወታደሮች ልብስ ሆኖ ለዘመናት ቆይቷል። የኋላ ኋላ መንግስታት ህዝባቸውን እያስገደዱ እስከሚያስለብሱት ደርሰዋል። ሲጠቃለል ምናልባት የዲዛይን ለውጥ ተደርጎበት ተስፋፍቶ ሊሆን ይችላል እንጂ የልብሱ መነሻ ምዕራቡ አይደለም። በሞቃት አየር ንብረቱ ሳቢያ ዐረቢያ ላይ በብዛት ባይታወቅም በሌሎች የመካከለኛው ምስራቅ አካባቢዎች እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ደግሞም ከካፊሮች መምጣቱ ብቻውን “ክልክል ነው” ለማለት በቂ መነሻ አይሆንም። ነብዩ ﷺ እራሳቸው በካፊሮች የተዘጋጁ ልብሶችን ሲለብሱ ነበር። ለምሳሌ የሻም ካፖርት ለብሰዋል። [ቡኻሪ፡ 363] ሻም በጊዜው በሮማውያውን እጅ ነበረች። *“ይሄ ካፖርት በኢጋሪዎች የተዘጋጀ ነው”* ይላሉ አልበይሀቂ ረሒመሁላህ። [አሱነኑል ኩብራ፡ 2/577] ኢብኑ ሐጀርም እንዲሁ ከዚህ ሐዲስ የሚወሰዱ ቁም-ነገሮችን ሲያትቱ *“ነጃሳነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ የከሃዲዎችን አልባሳት መጠቀም እንደሚፈቀድ እንረዳለን። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ዝርዝር ነገር ሳይጠይቁ ያቺን የሮማ ካፖርት ለብሰዋልና”* ይላሉ። [ፈትሑል ባሪ፡ 1/246]

ልክ እንዲሁ የመን የተዘጋጀ ልብስም ለብሰዋል። በወቅቱ ሙስሊሞች አልነበሩም። የተከፈኑትም የመን በተዘጋጀ ልብስ ነው። [ሙስሊም፡ 941]

ስለዚህ አሁን ያለውን ሱሪ ከድሮው ፍፁም የተለየ ለማድረግ የሚነሱት አቃቂሮች ውሃ የሚያነሱ አይደሉም። አንዳንዶች ይሄ

እንደማያዋጣቸው ስለተገነዘቡ “ይለያያሉ” የሚል ሙግት ውስጥ ከመግባት ይልቅ *“የድሮውም ብቻውን አይለበስም ነበር”* እያሉ ሙጭጭ ማለትን መርጠዋል። ይህም ጠንካራ መሰረት ላይ ያልቆመ ሙግት እንደሆነ አሳልፈናል።

## ብዥታ

ኸሊፋው ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ረዲየላሁ ዐንሁ ወደ አዘርባጃን ለዘመቱ ሙስሊሞች በፃፉት ደብዳቤ ላይ “ኹፍና ሱሪ” ከመልበስ እንዲቆጠቡ አሳስበዋል። [ሙስነድ አሕመድ፡ 301] ይህንን መነሻ በማድረግ የድሮውም ሱሪ ሐራም ነው ለማለት የሚዳዳቸው አሉ። አንዳንዶቹ ይህን የሚያቀርቡት የአሁኑ ሱሪ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ይበልጥ ለማጥበቅ በማለም ነው። የሆነ ሆኖ፡-

1. የዑመር መልእክት እነዚህ ነገሮች ሐራም ናቸው የሚል አይደለም። ሙሉ መልእክቱን የተመለከተ ይህን ሐቅ በቀላሉ ያገኘዋል። ደግሞስ ይህን የዑመርን ትውፊት መነሻ በማድረግ ኹፍ መልበስ፣ እርካብ መጠቀም፣ ጥሩ መመገብ፣ ጥሩ መልበስና ከፀሐይ መጠለል ክልክል ነው የሚል ይኖራልን? ታዲያ ለምን እየመረጥን እንወስዳለን?
2. በሌላ ዘገባ *“በባዶ እግር ሂዱ”* የሚልም አለ። [ጃሚዑ መዕመር ኢብኒ ራሺድ፡ 11/85] ስለዚህ በባዶ እግር መሄድ ግዴታ ነው ሊባል ነውን?!
3. የዑመርን ንግግር እንደ ክልከላ የምንወስድ ከሆነስ *“ከሸርጥ ስር መልበስ ይቻላል”* የሚሉት ሙግት ለምን አስፈለገ? ዘገባው ውስጥ “ሱሪዎችን ጣሉ” እንደሚል ከግምት ይግባ።

4. በነገራችን ላይ *“ሱሪያችሁን ቁረጡ”* የሚል ዘገባም አለ። <u>ምናልባት</u> የተፈለገው ይሄም ሊሆን ይችላል። [አተዕሊቃቱል ሒሳን፡ 5430]

ይህንን ነጥብ ስናጠቃልል ነብዩ ﷺ ሱሪ መልበስን በተለያዩ መልኩ እንደፈቀዱ እንረዳለን። በነገራችን ላይ እሳቸው እራሳቸው ሱሪ ገዝተዋል። [አተዕሊቃቱል ሒሳን፡ 7/400] ከዚህ ሐዲሥ አስከትለው ኢብኑ ሐጀር ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *“አብዛሀኛው ልብሳቸው ሽርጥ ቢሆንም ነገር ግን (ሱሪውን) እንዲሁ ለጨዋታ አልገዙትም።”* [ፈትሑል ባሪ፡ 5805] ኢብኑል ቀይዩምም *“(ነብዩ) ﷺ ሱሪ ገዝተዋል። ይህም የሚያሳየው የገዙት ሊለብሱት እንደሆነ ነው። በተለያዩ ሐዲሦች ሱሪ እንደለበሱ ተዘግቧል። (ሶሐቦችም) በሳቸው ፈቃድ ሱሪ ይለብሱ ነበር”* ይላሉ። [ዛዱል መዓድ፡ 1/34] ግና ነብዩ ﷺ ሱሪ “ለብሰዋልም” ይሁን “አልበሱም” የሚሉ ወገኖች አሳማኝ የሚመስሉ ትንታኔዎችን ቢሰጡም ከግላዊ ትንታኔ ያለፈ ቀጥተኛና ቁራጭ መረጃ ማቅረብ አይችሉም። በርግጥ ሱሪ ይለብሱ እንደነበር የሚጠቁም ሐዲሥ አለ። ነገር ግን ደካማ ስለሆነ መረጃ መሆን አይችልም።

በሚገርም ሁኔታ *“ከሶሐቦች፣ ከታቢዒዮች ጀምሮ እስከዚህ ዘመናችን ድረስ የተቅዋና የኢስቲቃማ ባለቤቶች ከሆኑ ደጋጎች ውስጥ በላዩ ላይ ደርቦበት ካልሆነ በስተቀር ሱሪ ለብሶ የወጣ አንድም እንደሌለ እርግጠኛ ሆነን እንናገራለን”* እያለ ኪታብ የፃፈ ሰው አለ። [አልቂስጧስ፡ 75] ሱብሓላህ! እስኪ በአስራ አራት ክፍል ዘመን ውስጥ ስላለፈ ታሪክ በዚህ መልኩ እንናገር ዘንድ ምን እርግጠኛ የሚያደርገን መረጃ አለ?! ፀሐፊው ሱሪ መልበስ እንደሚፈቀድ የሚጠቁሙ መረጃዎችን በሙሉ ከልብስ ስር ከውስጥ ብቻ በመልበስ ላይ ገድቧቸዋል። የሚደንቀው እንዲህ አይነት ድፍረት የሚያንፀባርቅ ሰው ከግላዊ

ትንታኔ ያለፈ አንድም ቆራጭ መረጃ መጥቀስ አለመቻሉ ነው። ያለ በቂ ማስረጃ ማንም ቢሆን የራሱን ግላዊ እሳቤ በሰዎች ላይ መጫንም ሆነ "ሐራም" የሚል ብይን መስጠትም ተገቢ አልነበረም። ከልካይ መረጃ በሌለበት እንዴት እንዲህ አይነት ብይን ይሰጣል? እንዲያውም መረጃው የሚያመላክተው በተቃራኒው ነው። *"ሱሪ ልበሱ። ሺርጥም ታጠቁ። ከመፅሐፉ ሰዎች ተለዩ"* የሚል ሐዲሥ አሳልፈናል። መልእክቱን በተመለከተም *"(ፂማችሁን) በቀይና በዳለቻ ቀቡ"* የሚለው አብሮ የመጣው መልእክት ሁለቱንም በአንድ ላይ ተጠቀሙ እያሉ እንዳልሆነ ግልፅ ያደርግልናል።

## በሱሪ ላይ የዑለማዎች አቋም

## [ሀ] ከልካዮች

### 1. ሸይኹል አልባኒ

*"ሱሪ በዚህ ዘመን ሙስሊሞችን ካገኙ መከራዎች ውስጥ ነው። ይህም ከሃዲዎች ሃገራቸውን በመውረራቸውና ባህላቸውንና እሴቶቻቸውን ይዘው በመምጣታቸው ነው። ከፊል ሙስሊሞች ይህን ተከተሉ። ይህም ረጅም ጥናት የሚሻ ነው። ባይሆን እኔ አሳጥሬ እንዲህ እላለሁ፡- ሱሪ መልበስ ሁለት ችግሮች አሉት። የመጀመሪያው የሃፍረተ-ገላን ቅርፅ ያሳያል። በተለይም ሱሪው ቀርፆ የሚያሳያቸውን ሀፍረተ-ገላና መቀመጫዎች የሚሸፍን ረጅም ልብስ የማይለብሱ ሰጋጆች። ሱጁድ ላይ ደግሞ በመካከል ያለውንም ጭምር። ይሄ በሚያሳዝን ሁኔታ የሚታይ ነው። በተለይም በጀማዐ ሶላት ላይ። አንድ ሰው ሱጁድ ሲያደርግ ከፊቱ ሱሪ የለበሰውን የተከፈሉ ታፋዎቹን ይመለከታል። እንዲያውም ከዚህም የከፋ ሊያገኝ ይችላል። ይሄ የመጀመሪያው ችግር*

*ነው። ሱሪ የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ ያሳያል። እንኳን ሴት ወንድም የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ የሚያሳይ ልብስ ሊለብስ አይፈቀድለትም።...*

*ሁለተኛው ችግሩ የከሃዲዎች ልብስ ነው። ሱሪ ካለፉት ረጃጅም ክፍለ-ዘመናት ውስጥ በየትኛውም ጊዜ ከሙስሊሞች ልብስ ውስጥ አልነበረም። ነብዩ ﷺ እንዲህ ማለታቸው ተረጋግጧል፦ '... በሰዎች የተመሳሰለ ከነሱው ነው።' በሶሒሕ ሙስሊም ላይም ነብዩ ﷺ የሆነ ሰው መጥቶ ሰላምታ ሲያቀርብላቸው 'እነዚህ ከከሃዲ ልብሶች ውስጥ ስለሆኑ አትልበሳቸው' ብለውታል። ስለሆነም በየትኛውም ምክንያት ሱሪ በመልበስ የተፈተነ እያንዳንዱ ሙስሊም ከላዩ ላይ ረጅም ጃኬት ሊደርብበት ይገባል። ልክ አንዳንድ ፓኪስታናውያን ወይም ህንዳውያን ወንድሞቻችን የሚለብሱትን እስከ ጉልበት የሚደርስ ረጅም ሸሚዝ የሚመስል።* [18] *ይሄ በተጨባጭ ሱሪ የአንድ ሙስሊም*

---

[18] ነገር ግን ይሄ እንደ አማራጭ የጠቀሱት የፓኪስታንና የህንድ ልብስ፦

**አንደኛ፦** በነዚህ ሃገራት ውስጥ ያሉ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ ሲኮቹም፣ ሂንዱዎቹም፣ ቡድሂስቶቹም የሚለብሱት የካፊሩም የሙስሊሙም የጋራ ልብስ ነው:: መመሳሰልን መከልከያ ምክንያት አድርገው ለሚያቀርቡ ሰዎች ያን ያክል አዋጭ መፍተሄ አይደለም::

**ሁለተኛ፦** በሌሎች የሙስሊም ሃገራት ብዙም የማይታወቅ እንግዳ የሆነ ልብስ ነው:: ይሄ ደግሞ ወደ ሌላ ነገር ይወስዳል:: እሱም *"የመታወቂያ (ሹህራ) ልብስ የለበሰ ሰው አላህ በቂያማ ቀን የውርደት ልብስ ያለብሰዋል"* ከሚለው ሐዲሥ ጋር የሚያላትም ነው:: የሹህራ ልብስ ማለት ምን ማለት ነው? ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፦ *"የሹህራ ልብስ ይጠላል:: እሱም ከተለምዶ የወጣ ከፍ ያለ ወይም ደግሞ ከተለምዶ የወጣ ዝቅ ያለ ነው:: ሰለፎች ሁለቱንም አይነት መታወቂያዎችን አይወዱም ነበር፣ ከፍ ያለውንም ዝቅ ያለውንም:: በሐዲሥም 'የመታወቂያ ልብስ የለበሰ ሰው አላህ በቂያማ ቀን የውርደት ልብስ ያለብሰዋል' የሚል አለ:: ከነገሮች ሁሉ ምርጡ መካከለኛ የሆነው ነው::"* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 22/138] ሑሰይን ኢብኑ ዐብዲርሕማን እንዲህ ይላሉ፦ *"ዘይድ አልያሚ በርኖስ ይለብስ ነበር:: ኢብራሂም እንዳነወረው ሰማሁና 'ሰዎች ይለብሱት ነበርኮ?' አልኩት:: እሱም 'ልክ ነው:: ነገር*

*ሃፍረተ-ገላ ተቀርፆ እንዳይታይ ከሚቀንሱት ውስጥ ነው።"* [ዱሩሱን ሊሸይኺል አልባኒ፡ 30/18]

ሌሎችም ተመሳሳይ ይዘት የያዙ ፈትዋዎች አሏቸው።

## 2. ሸይኽ ዐብዱል ሙሕሲን አልዐባድ

*"ከከሃዲዎች አልባሳት ውስጥ አንዱ ሱሪ እንደሆነ የታወቀ ነው። ስለሆነም ሊጠቀሙት አይገባም። ነገር ግን ሊጠቀመው አስፈላጊ ከሆነ ሰፊ፣ አካልን የሚቀርፅ ጠባብ ያልሆነ ሊድርጎ ከከሃዲዎች በሚለይ መልኩ ይጠቀመው።"* [ሸርሕ ሱነን አቢ ዳውድ፡ 1/2]

## 3. ሸይኽ ሙቅቢል፡-

---

*ግን ይለብሱት የነበሩት ሰዎች ጠፍተዋል፡፡ ዛሬ አንድ ሰው ቢለብሰው ያስተዋውቁታል፡፡ በጣት ይጠቋቆሙበታል' አለ፡፡"* [ሙሶነፍ ኢብኒ አቢ ሸይባ፡ 5/205]

ስለዚህ አንድ ሰው ከሚኖርበት ማህበረሰብ ወጣ ያለ ልብስ መልበሱ የሚደገፍ አይደለም፡፡ ኢማሙ አሕመድ የሆነ ሰው ነጭና ጥቁር መስመር ያለው ኩታ ለብሶ ያዩታል፡፡ *"ይህንን አስቀምጥና የሀገርህ ሰዎች የሚለብሱትን ልበስ፡፡ ሐራም ሆኖ አይደለም፡፡ መካ ወይም መዲና ብትሆን ኖሮ አላነውርህም ነበር"* አሉት፡፡ [ጊዛኡል አልባብ፡ 2/163]

ምናልባት በዚህ ወጣ ያለ አለባበስን በሚከለክለው ሐዲሥ መልእክት የሚጨናነቁ፣ መፈናፈኛ እንዳጡ የሚሰማቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ መልእክቱን ረጋ ብለው ቢያስተውሉት ግን የኢስላም ልዩ ውበትና ጥልቀት ነው የሚታይበት፡፡ አንድ ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ መጠቋቆሚያ የሚያደርገው ወይ ተጋንኖ ለአጉል ኩፈሳ የሚያግብዘው ወይም ደግሞ በጣም ወርዶ ዛሂድ ለመምሰል የሚለበስ ልብስ የልብ ብክለትን ሊያስከትል ይችላል- በኩራት ወይም በይሉኝታ፡፡ በአንድ ወይም በሆነ ምክንያት ሌሎችን ለጥፋት የሚጎትትበት ሁኔታም ይኖራል፡፡

እሳቸውም ሱሪ (በንጠሉን) *“ዝቅተኛ ሁኔታው የተጠላ መሆኑ ነው”* ሲሉ ተናግረዋል። ባይሆን እሳቸው እኔ ባገኘሁት መረጃ ቅርፅ ማውጣቱን አላወሱም። [ቀምዑል ሙዓኒድ፡ 318]

## [ለ] ፈቃጆች

### 1. ሸይኽ ኢብኑ ባዝ

ሱሪ የሚፈቅዱ የተለያዩ ፈትዋዎች ያሏቸው ሲሆን ምሳሌ ለመጠቀስ ያክል *“ሀፍረተ-ገላን በሚያጋልጥ መልኩ ካልሆነ የሚከለክል ነገር አላውቅበትም። እንዲያውም ሀፍረተ-ገላን ይሸፍናል። መመሳሰልም አይሆንም”* ይላሉ። http://www.binbaz.org.sa/noor/9596

### 2. ሸይኽ ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ

*“ሱሪ መልበስ ወይም ደግሞ ሰዓትን በግራ መልበስ በከሃዲዎች ከመመሳሰል ይታሰባልን?”* ተብለው ሲጠየቁ፡- *“በከሃዲዎች መመሳሰል እንደሆነ የሚቆጠረው የልብስ አይነት ሰው ለብሰኸው ቢያይህ ካፊር አድርጎ የሚያስብህ ከነሱ መለያዎች የሆነው ነው”* ብለው ነው መለሱት። [ፈታዋ ሸይኽ ዐብዱረዛቅ ዐፊፊ፡ 2188]

### 3. ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን

በተደጋጋሚ ሱሪን ፈቅደዋል። ለምሳሌ እንዲህ ብለዋል፡-

*“በከሃዲዎች መመሳሰል የሚባለው አንድ ሰው በአለባበስ፣ በአነጋገር ወይም መሰል ነገር ላይ ተመልካች ቢያው ይሄ ከከሃዲዎች ነው በሚለው መልኩ የነሱን ዘዬዎች ሲከተል ነው። እንጂ ሙስሊሞችም ከሃዲዎችም የሚጋሩት ነገር መመሳሰል አይባልም። ለምሳሌ አሁን የወንዶችን ሱሪ ብንወስድ መመሳሰል ነው አንልም። ምክንያቱም የሁሉም ባህል ሆኗልና።”* [ሊቃኡል ባቢል መፍቱሕ፡ 108/28]

### 4. ሸይኽ ፈውዛን

*“ሱሪ፣ ጂንስ፣ የእስፖርት ቱታዎችና ከራቫት መልበስ ብይኑ ምንድን ነው?”* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡- *“እኔ እነዚህን ነገሮች አላውቃቸውም። ጂንስ? ምንድን ነው ይሄ ጂንስ ማለት? ብቻ መልሱ በከሃዲዎች ብቻ የሚገደቡ ልብሶችን እንዳትለብሷቸው። ሙስሊሞችም የሚለብሷቸው* ***<u>የጋራ የሆኑ ልብሶችን</u>*** *ግን እነዚህ ከመመሳሰል አይደሉም።”* http://alfawzan.af.org.sa/node/14837

### 5. ሸይኽ ሙሐመድ ዐሊ ፈርኩስ

ሃይማኖታዊ ወይም ቡድናዊ መልእክት ያነገበ ወይም ደግሞ በጠባብነቱ ምክንያት የሰውነትን ቅርፅ አጉልቶ የሚያሳይ ካልሆነ በስተቀር ህዝባዊ የሆነ ልብስ ስለሆነ ችግር የለውም ይላሉ። [ፈታዋ ሸይኽ ሙሐመድ ዐሊ ፈርኩስ፡ 161/1]

### 6. ሸይኽ ሱለይማን አሩሐይሊ

የሚፈቅዱበትን ንግግራቸውን በቅርቡ የምናየው ይሆናል።

## 7. የሳዑዲ የፈትዋ ኮሚቴ

ጥያቄ፡- *“በብዙ የሙስሊም ሃገራት ሱፍ (ወይም ከኮትና ሱሪ የተቀናጀ የደንብ ልብስ) መልበስ ተስፋፍቷል። አንዳንዴ በበጋ ሙቀቱ ሲበረታ በሱሪና በሸሚዝ ወይ እጅጌ ሙሉ ወይም ጉርድ ከሆነ ሸሚዝ ጋር ሊገደብ ይችላል። ይህንን ልብስ መልበስ ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች ከመመሳሰል ይገባል ወይስ አይገባም?”*

**መልስ፡-**

*“የልብስ አይነቶችን በተመለከተ መሰረቱ ፍቁድነት ነው። ምክንያቱም ይሄ ከባህላዊ ነገሮች ነውና። የላቀው ጌታ እንዲህ ይላል፡-* ***‘የአላህን ጌጥ ያቺን ለባሮቹ የፈጠራትን ከሲሳይም ጥሩዎቹን ማነው ክልክል ያደረጋቸው?’*** *ከዚህ ተለይቶ የሚወጣው ሸሪዐዊ መረጃ ክልክልነቱን ወይም የሚጠላ መሆኑን ያመላከተበት ነው። ለምሳሌ ለወንድ ሐርን ይመስል፣ ቆዳን አሳልፎ የሚያሳይ ስስ በመሆኑ ወይም ደግሞ ቅርፅን የሚገድብ ጠባብ በመሆኑ ሀፍረተ-ገላን የሚያጎላን ይመስል። ምክንያቱም በዚህን ጊዜ የመገለጥን ብይን ነው የሚይዘው። መገለጡ ደግሞ አይፈቀድም። በከሃዲዎች ላይ የተገደቡ የነሱ መታወቂያ የሆኑ ልብሶችን ይመስል። ለወንድም ለሴትም እነዚህን መልበሱ አይፈቀድም። ነብዩ ﷺ በነሱ ከመመሳሰል ከልክለዋልና። ወንዶች የሴቶችን፣ ሴቶች ደግሞ የወንዶችን ልብስ መልበሳቸውን ይመስል። ነብዩ ﷺ ሴቶች በወንዶች ወንዶች ደግሞ በሴቶች ከመመሳሰል ከልክለዋልና።*

*ሱሪና ሸሚዝ የሚባለው ልብስ ከሃዲዎች በመልበስ የሚለዩበት አይደለም። ይልቁንም በብዙ ሃገራት የሙስሊሞችም የከሃዲዎችም የጋራ ልብስ ነው።* [19] *በአንዳንድ ሃገራት ነፍሶች የሚፀየፉት ስላልተለመደና ከነዋሪዎቹ ባህል ጋር ስለሚፃረር ነው። ምንም እንኳን ለሌሎች ሙስሊሞች ባህል የሚስማማ ቢሆንም። ነገር ግን አንድ ሙስሊም ነዋሪዎቹ ይህንን ልብስ ባልለመዱበት ሃገር ከሆነ በሶላት፣ በህዝብ መሰባሰቢያዎችና በመንገዶች ባይለብሰው በላጭ ነው። መታደል በአላህ ነው። አላህ በነብያችን በሙሐመድ፣ በቤተሰባቸውና በሶሐቦቻቸው ላይ ሶላትና ሰላም ያውርድ።"* [ፈታዋ ለጅነቲ ዳኢማ፡ ቁ. 1620]

ፈትዋውን የሰጡት ዐብዱላህ ኢብኑ ቀዑድ፣ ዐብዱላህ ኢብኒ ጉደይያን፣ ዐብዱረዛቅ ዐፊፊና ዐብዱል ዐዚዝ ኢብኑ ባዝ ናቸው።

የሚከለክሉትም ሆነ የሚፈቅዱት እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ ይስተዋል።

---

[19] ሸይኹል አልባኒ ረሒመሁላህ ሱሪን ለመከልከል ያነሷቸው ሁለቱ ምክንያቶች (መመሳሰልና ቅርፅን ማሳየት) በዚህ ፈትዋ ላይ መጠቀሳቸው ይሰመርበት፡፡ ፈትዋውን የሰጡት ዑለማዎች እነዚህ ነገሮች ያሉበት ልብስ እንደማይፈቀድ ከመግለፃቸው ጋር ነው ሱሪን የፈቀዱት፡፡ ይህም እነዚህ ሱሪን ለመከልከል የሚውሉት ምክንያቶች ከሱሪ ላይ አይገኙም- እነዚህ ዐሊሞች ዘንድ፡፡ በርግጥ ከስፋትና ጥበት አንፃር የሱሪዎች መጠን በጣም ስለሚራራቅ ሁሉንም አንድ ብይን መስጠት ይከብዳል፡፡ ሰፊነታቸው ለማንም የማይሰወሩ እንዳሉ ሁሉ ጠባብነታቸው እጅግ ከመግነኑ የተነሳ ለጤና አሳሳቢ እንደሆኑ ጥናት እስከሚወጣባቸው የደረሱም አሉ፡፡ **እነዚህ ክልክል በመሆናቸው ላይ ምንም ጥርጥር አይኖርም፡፡** በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እያወራን ያለነው ስለነሱ አይደለም፡፡

## ሱሪን ለመከልከል የሚነሱ ምክንያቶች ሲቃኙ

*“ሱሪ ሐራም ነው”* የሚሉ ሰዎች ሙግታቸው የሚሽከረከረው በሁለት ዛቢያዎች ላይ ነው። አንዱ *“ጠባብ ስለሆነ የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ ያሳያል”* የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ *“የከሃዲዎች ልብስ ስለሆነ መመሳሰል አለበት”* የሚል ነው። በየተራ ጠቅለል አድርገን እንመልከታቸው።

### [ሀ] የጥበት ጉዳይ

በርግጥ የስፋትና የጥበት ጉዳይ አንፃራዊ ስለሆነ አንዱ “ሰፊ ነው” ያለውን ሌላው “ጠባብ ነው” ሊለው ይችላል። በዚህ ምክንያትም ነው በአሁኑ ወቅት ያሉ ሱሪዎችን “ሐራም ነው” የሚሉ ዐሊሞች “ጠባብ ናቸው” ሲሉ ሌሎቹ መፍቀዳቸው። **የሚፈቅዱት በብዛት የሚታየው የሱሪ ስፋት “በቂ ነው” ከሚል እሳቤ እንጂ የሃፍረተ-ገላን ቅርፅ አጉልቶ የሚያሳይን ልብስ መፍቀዳቸው አይደለም።**

ብቻ የሱሪ ስፋትና ጥበት ብዙ አይነት ስለሆነ ሁሉንም አንድ ብይን መስጠት ከባድ ነው። ጥብቅብቅ ብለው ለጤና አስጊ፣ ለእንቅስቃሴ አስቸጋሪ የሆኑት ሱሪዎች ክልክል እንደሆኑ ሱሪን በጥቅሉ የሚፈቅዱት ዐሊሞችም ጭምር ይጠቅሳሉ።

ከዚህ ውጭ ግን ፋሺን የሚከተሉ ወጣቶች ካልሆኑ በስተቀር ብዙዎቹ ሱሪዎች ስፋታቸው ወይ መካከለኛ ወይ ደግሞ ሰፊ የሚባል ነው።

ጎንበስ ቀና ሲባል ወይም በእንቅስቃሴ ወቅት የአካል ቅርፆች መታየታቸውን የልብሶቹን ጠባብነት ማሳያ ማድረግ የሚዋጥ አይደለም።

ምክንያቱም በእንቅስቃሴ ወቅት ሸርጥ የለበሰም ሰው ሌላ ልብስ ካልደረበበት በስተቀር መቀመጫውና ዳሌዎቹ ይታያሉ። ቀሚስ ወይም ረጅም ካፖርት በመልበስ ካልሆነ በስተቀር ይህን ማስቀረት አይቻልም። መቼም *"ሸርጥም ከላይ ካልተደረበበት በስተቀር ሐራም ነው"* የሚል የሚኖር አይመስለኝም። እንዲያውም በቀሚስም የሚታይበት አጋጣሚ ይኖራል። አንዳንዴ ቀሚሱ የሚብስበትም ሁኔታ ይኖራል። የለበሱት ቀሚስና ከውስጥ ያለው ሱሪ <u>ስስ</u> በመሆኑ የተነሳ ሲንቀሳቀሱ የብልታቸው ቅርፅ ሁሉ የሚታይባቸው በተጨባጭ አሉ። በተለይም ነፋስ በሚነፍስበት ወቅት። ይሄ ሸርጥ፣ ከበድ ያለ ቀሚስና ሱሪ በሚለብሱ ላይ ያን ያክል አይስተዋልም።

የጀመርነውን ነጥብ ስናጠቃልል የሱሪዎች ስፋት ብዙ አይነት ነው። *"ሁሉም ጠባብ ነው፣ የአካልን ቅርፅ ያሳያል"* ማለት ሚዛናዊነት ያልሸተተው ፍርደ-ገምድል ውሳኔ ነው። ስለዚህ የፈለገ ቢሰፋ የማንቀበል ከሆንን "ሱሪ የአካልን ቅርፅ ያሳያል" የሚል ሙግት መከፈት ምንድን ነው ትርፉ? "አይ ስፋቱ የአካልን ቅርፅ ከማጉላት ቢተርፍ እንኳን መመሳሰል አለበት" የምንል ከሆነ ይሄው በቀጣይ አብረን እንመልከተው።

[ለ] <u>***የመመሳሰል ገደቡ ምንድን ነው?***</u>

ሱሪን ለመከልከል ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ *"መነሻው ከከሃዲዎች ዘንድ ስለሆነ በነሱ መመሳሰል አለበት"* የሚል ነው። አንድ ልብስ መነሻው ከሃዲዎች ዘንድ ቢሆን እንኳን የነሱ መለያ ከመሆን ወጥቶ የሙስሊሙም ጭምር የጋራ ልብስ ከሆነ ከመመሳሰል እንደሚወጣ የተናገሩ ብዙ ዐሊሞች አሉ። ለምሳሌ፡-

## 1) ኢብኑ ሐጀር፡-

*"'ግላስ (ከሐር የተሰራ የኮርቻ ልብስ) የተከለከለው ዐረብ ባልሆኑ ሰዎች መመሳሰል እንዳይኖር ነው' ከተባለ ለዲናዊ ጥቅም ሲባል ነው ማለት ነው (ሰበቡ)። <u>ነገር ግን ይሄ ያኔ ከሃዲዎች በነበሩበት ጊዜ የነበራቸው መታወቂያቸው ነው። ከዚያ አሁን የነሱ ልዩ መታወቂያ ስላልሆነ ይሄ (የተከለከለበት) ሰበብ ተወግዷል። ስሆነም መጠላቱ ይወገዳል ማለት ነው።</u> ወላሁ አዕለም።"* [ፈትሑል ባሪ፡ 10/307]

## 2) ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ኢብራሂም

*"ጃኬትና ሱሪን በተመለከተ ከከሃዲዎች ልብስና ልዩ መታወቂያ ከሆነ በመመሳሰሉ ምክንያት የተከለከለ ነው። ስለዚህ የተናገርነው በእርግጥም አልፏል። <u>ከነሱ ልዩ መታወቂያ ካልሆነ ግን በዚህ ላይ ችግር የለበትም። ልብሶችን በተመለከተ መሰረቱ ከልካይ ማስረጃ የመጣበት ሲቀር ፍቁድነት ነውና</u>።"* [ፈታዋ ወረሳኢል ሙሐመድ ኢብኑ ኢብራሂም፡ 4/68]

## 3) የሳዑዲ ዑለማእ ምክር ቤት፡-

*"የተከለከለው በከሃዲዎች መመሳሰል <u>እነሱ በሚለዩባቸው ባህሎች፣ እምነታዊም ሆኑ አምልኮታዊ ከሆኑ ሃይማኖታዊ ፈጠራዎች መመሳሰል ነው።</u> ፂምን እንደመላጩት፣... ያለ መመሳሰልም እንዲሁ። <u>ሱሪ፣ ቱታና የመሳሰሉ ልብሶች ግን የልብስ አይነቶችን በተመለከተ መሰረቱ ፍቁድነት ነው። ምክንያቱም ይሄ ከባህላዊ ነገሮች ነውና። ... ሱሪ የሚባለው ልብስ ከሃዲዎች ላይ ብቻ የሚገደብ አይደለም። ይልቁንም</u>*

*<u>በብዙ ሃገራት ሙስሊሞችም ከሃዲዎችም ዘንድ ጠቅላይ የሆነ ልብስ ነው።"</u>* [ፈታዋ ለጅነቲ ዳኢማ፡ 3/306-307]

**4) አልባኒ፡-**

ሶሐባው ዐብዱላህ ኢብኒ ዐምር ረዲየላሁ ዐንሁ እንዲህ ብለዋል፡- *"የአላህ መልእክተኛ ﷺ በኔ ላይ ሁለት ቢጫ ልብሶችን አዩና 'እነዚህ ልብሶች ከከሃዲዎች ልብሶች ውስጥ ናቸው' አሉ።"* [ሙስሊም፡ 2077]

ሸይኹል አልባኒ ረሒመሁላህ ሱሪን ለመከልከል ከሚያነሷቸው ምክንያቶች አንዱ *"ከካፊሮች ጋር መመሳሰል አለበት"* የሚል ሲሆን የተመረኮዙበት አንዱ መረጃም ይሄ ሐዲሥ ነው። [ዱሩሱን ሊሸይኺል አልባኒ፡ 30/18] ነገር ግን ነብዩ ﷺ እጅጌዎቹ ጠባብ የሆነ የሻም ካፖርት የለበሱበትን ሐዲሥ ሲያወሱ ጊዜ ሱሪን ለመከልከል የተጠቀሙትን ትንታኔ የሚያፈርስ መልእክት ነው ያሰፈሩት። ይሄውና ንግግራቸው፡-

*" 'ሙስሊም (6/144) እና ሌሎችም እንደዘገቡት ዐብዱላህ ኢብኒ ዐምር 'የአላህ መልእክተኛ ﷺ በኔ ላይ ሁለት ቢጫ ልብሶችን አዩና 'እነዚህ ልብሶች ከከሃዲዎች ልብሶች ውስጥ ናቸውና አትልበሳቸው' አሉኝ' እንዳለው በሸሪዐችን የከሃዲዎችን አልባሳት መልበስ እንደተከለከለ የተረጋገጠ ነው። ታዲያ እንዴት ነብዩ ﷺ የሮማውያንን ልብስ ለበሱ? እነሱ ከሃዲዎች ናቸው። ከነሱ ልብስ ደግሞ ከልክለዋል' ከተባለ መልሱ ልብሶች ሁለት አይነት ናቸው።*

*ከነዚህ ውስጥ አንዱ አይነት፦ **ሁሉም ህዝቦችና ሃይማኖቶች የሚጋሩት ነው። ከአንዱ ተለይቶ የአንዱ መታወቂያ አይደለም። ይሄ የፈለገ ቅርፅ ቢኖረው ምንጬ የትም ይሁን ሙስሊም ሊለብሰው ይፈቀድለታል። በዚህ ውስጥ በሙስሊም ላይ ችግር የለም።** አዱሩል ሙኽታር ላይ እንዲህ የሚል መጥቷል፦ በመፅሐፉ ሰዎች መመሳሰል በሁሉም ነገር አይደለም የሚጠላው። በዚህም ላይ ሂሻም እንዲህ እንዳለ አውስተዋል፦ 'በምስማር የተለጣጠፉ ጫማዎችን አቡ ዩሱፍ ላይ አየሁኝ። 'በዚህ ላይ ችግር ያለበት ይመስልሃል?' ስለው 'በጭራሽ!' አለኝ። 'ሱፍያንና ሠውር ኢብኑ የዚድ ግን በመነኮሳት መመሳሰል ስላለበት ይህን ጠልተውታል' አልኩት። ይህኔ እሱ 'የአላህ መልእክተኛ ﷺ ፀጉር ያለባቸው ጫማዎች ይለብሱ ነበር። እነዚህ የመነኮሳት ጫማዎች ነበሩ' አለኝ።' እንደሚታየን የነብዩ ﷺ የሮም ካፖርትም ከዚህ ምድብ ውስጥ ነበር።*

*ሌላኛው (የልብስ) አይነት፦ **የከፊል ከሃዲዎች ህዝቦች መታወቂያ የሆኑ ናቸው። ከሌሎች ህዝቦች የሚለዩበት ነው። በዚህ ላይ ሙስሊም ሊከተላቸውና ሊመሳሰልባቸው አይገባም።"*** [አስሉ ሲፈቲ ሶላቲ ነቢይ፡ 150-151]

ውድ አንባቢ ሆይ! እስኪ አላህን ፈርተህ፣ ህሊናህን አክብረህ ረጋ ብለህ አስተውል። ሱሪ ከሁለቱ የሸይኹል አልባኒ ምድቦች ውስጥ ከየትኛው ይገባል?! ከሁለተኛው ልታስገባ የምትችልበት ቀዳዳ ይኖርሀልን?!! በፍፁም!! እንዲያውም ***"ሁሉም ህዝቦችና ሃይማኖቶች የሚጋሩት ነው። ከአንዱ ተለይቶ***

***የአንዱ መታወቂያ አይደለም”*** የሚለው ንግግራቸው ያለጥርጥር ሱሪም ላይ ልክክ ብሎ የሚገጥም ነው።

## 5) ኢብኑል ዑሠይሚን፡-

*“የመመሳሰል መለኪያው የሚመሳሰለው አካል የሚመሳሰልበት አካል* ***የሚለይበትን*** *ነገር መስራቱ ነው።* ***ስለሆነም በከሃዲዎች መመሳሰል ማለት አንድ ሙስሊም እነሱ የሚለዩበትን ነገር መስራቱ ነው። እንጂ በሙስሊሞች መካከል ተሰፋፍቶ ከሃዲዎች የሚለዩበት ያልሆነ ነገር መመሳሰል አይሆንም። በሌላ አቅጣጫ ክልክል ካልሆነ በስተቀር በመመሳሰል ምክንያት ሐራምም አይሆንም።”*** [መጅሙዑ ፈታዋ፡ 12/290]

## 6) ዐብደላህ አልበሳም፡-

*“በከሃዲዎች መመሳሰል ሐራም እንደሆነ ዑለማዎች ተስማምተዋል። ስለሆነም ከነሱ መለየት ደንጋጊው ዘንድ የሚፈለግ ነው።* ***በነሱ ብቻ ላይ የማይገደብ የሆነና እነሱም ሙስሊሞችም የሚለብሱትን ልብስ መልበስ ከመመሳሰል አይደለም። ምክንያቱም ይሄ በነሱ ላይ የሚገደብ መለያ ተደርጎ የሚቆጠር አይደለምና።*** *የሚለብሰውም ባህላቸውን፣ ገፅታዎቻቸውንና ፋሺኖቻቸውን ተከታይ ተደርጎ አይታሰብም።”* [ተውዲሑል አሕካም፡ 3/124]

7) ፈውዛን፡-

*<u>“በከሃዲዎች ብቻ የሚገደቡ ልብሶችን እንዳትለብሱ። ሙስሊሞችም የሚለብሷቸው የጋራ የሆኑ ልብሶች ግን እነዚህ ከመመሳሰል አይደሉም”</u>* ማለታቸውን አሳልፈናል። በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፡- *<u>**“የከሃዲዎች አልባሳት ነጃሳ መሆናቸው ካልታወቀ በስተቀር የተፈቀዱ ናቸው።**</u> መሰረቱ ጦሀራነት ስለሆነ በጥርጣሬ አይወገድም። እነሱ ያዘጋጁትና ያቀለሙትም ይፈቀዳል። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ እና ሶሐቦቻቸው ከሃዲዎች የሸመኑትንና ያቀለሙትን ይለብሱ ነበርና።”* [አልሙለኸሱል ፊቅሂ፡ 1/20]

8) ሸይኽ ዐብዱል ዐዚዝ አራጂሒ፡-

*“ሰራዊልና በንጠሎኖች (ሱሪዎች) በአሁኑ ሰዓት ከሃዲዎች ላይ የተገደቡ አይደሉም። የወል ሆነዋል።”* [ሸርሑ ኪታቢ አሱና ሊልበርበሃሪ፡ 7/20]

9) ሸይኽ ሱለይማን አሩሐይሊ፡-

*“በከሃዲዎች መመሳሰል ገደቡ ምንድን ነው?”* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ ነው መለሱት፡-

> *“በከሃዲዎች መመሳሰል ገደቡ አንድ ሰው በከሃዲዎች <u>ብቻ</u> የሚሰራን ስራ መስራቱ ነው። እንጂ <u>በሰብአዊነታቸው የሚሰሩትን አይመለከትም።</u> እነዚህን ገደቦች ተገንዘቡ። **ከሃዲዎች እንጂ የማይሰሩት ሊሆን!! ከሃዲዎችም ሌሎችም የሚሰሩት ከዚህ ይወጣል። ይህን ተግባር ከሃዲዎችም ሌሎችም የሚሰሩት ከሆነ መመሳሰል አይሆንም። በዚህ ረገድ የሚታየኝ - ወላሁ አዕለም - ሰራዊል ወይም በዚህ ዘመን***

***አልበናጢል (ሱሪዎች) የሚባለውን መልበስ ነው። ሱሪው ጠባብና ስስ ካልሆነ እሱን መልበሱ መመሳሰል አይደለም።*** *ምክንያቱም ይሄ በከሃዲዎች ላይ የተገደበ አይደለምና። ይልቁንም* ***<u>ከድሮም ጀምሮ ከሃዲዎችም ያልሆኑትም ይለብሱታል።</u>*** *ድሮ ዐረቦች ዘንድ ሰራዊል ይባል ነበር።*

*ሌላኛው (የመመሳሰል) ገደብ በከሃዲዎች ብቻ ቢሰራም የሚሰሩት በሰብአዊነት መነሻ ላይሆን ነው። በሰብአዊነታቸው የሚሰሩት ከሆነ ግን ከነሱ ብንወስደው ችግር አይኖረውም። ለምሳሌ መኪናዎች። መኪናዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈበረኩት ከሃዲዎች ዘንድ ነው። ቢሆንም መኪናዎችን የሚሳፈሩት በሰብአዊነታቸው ብቻ ስለሚያስፈልጋቸው ነው። ስለሆነም መኪናዎችን ከነሱ እየወሰድን እንሳፈርባቸዋለን። ይሄ በሰብአዊነት (ሰው በመሆን ብቻ) የሚፈፀም ነው። ይሄ ከመመሳሰል ውስጥ አይደለም።"* [ሸርሑል ኡሱሊ ሠላሣ]

ብዙ ዑለማዎች ሱሪ በአሁኑ ጊዜ የሙስሊሙም የካፊሩም ልብስ መሆኑን በማውሳት መፍቀዳቸው ለአንዳንዶች አልተዋጠላቸውም። *"ቀድሞ ሐራም የነበረ ነገር እንዴት በመስፋፋቱ ብቻ ሐላል ይሆናል?"* ይላሉ። ግልፅ የሆኑ ወንጀሎችን እንደ ምሳሌ በማንሳትም *"በሰዎች ዘንድ ቢስፋፉ ሐላል ሊሆኑ ነው ወይ?"* ሲሉ ይሞግታሉ። ግና በመመሳሰል ሰበብ የተከለከሉ ነገሮችን በራሳቸው ሐራም ከተደረጉ ወንጀሎች ጋር ማቀላቀሉ ጤናማ ያልሆነ ስሌት ነው።

*"በሰፊው ተሰራጭቶ የጋራ ከሆነ መመሳሰል አይባልም"* የሚለውን አመክንዮ የሚቃወሙት ሸይኹል አልባኒ እራሳቸው ስለዚሁ ጉዳይ

በተጠየቁበት ጊዜ የመለሱት መልስ ዞሮ ማሳመኛ ሆኖ መቅረብ ይችላል። ስለ ቱርኮች ኮፍያ (ጦርቡሽ) ሲያወሱ መነሻው ኦስትሪያ እንደሆነና ቱርኮች ለጦርነት በሄዱበት ከነሱ እንደኮረጁት በሂደት ግን ኦስትሪያዎቹ ሙሉ ለሙሉ እንደተውት በማውሳት በዚህን አይነት ምሳሌ መነሻው ካፊሮች ዘንድ የሆነን ልብስ እነሱ ከተውት መልበስ እንደሚቻል ተናግረዋል። [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 813]

ልብ በሉ! ይሄ ትንታኔ አንድ እርምጃ ከመዘግየቱ ባለፈ እራሱ ኢብኑል ዑሠይሚንና ሌሎችም ስለ ሱሪ ያነሱት አመክንዮ ነው።

**ደረጃ አንድ፡-** ይሄ ኮፍያ (ጠርቡሽ) የካፊሮቹ ኦስትሪያውያን ልብስ ነበር።
**ደረጃ ሁለት፡-** ኋላ በቱርኮች ተኮረጀና ተስፋፍቶ የሙስሊምም የካፊርም ልብስ ሆነ።
**ደረጃ ሶስት፡-** ባለቤቶቹ ኦስትሪያውያን ካፊሮች ከነጭራሹ ተውትና ሙስሊሞቹ ቱርኮች ብቻ ሆኑ የሚለብሱት።

ደረጃ አንድ ላይ ሳለ በነ ኢብኑል ዑሠይሚንም በነ አልባኒም ትንታኔ በካፊር መመሳሰል ስለሆነ ሐራም ነው። ደረጃ ሁለት ላይ ሲሆን በስፋት ተሰራጭቶ የጋራ ልብስ ስለሆነ እነ ኢብኑል ዑሠይሚን ዘንድ ሐላል ነው። እነ አልባኒ ዘንድ ግን ካፊሮች ስላልተውት ሐራም ነው። ደረጃ ሶስት ላይ ካፊሮቹ ስለተውት እነ አልባኒም ዘንድ ሐላል ነው።

የአልባኒንም የነ ኢብኑል ዑሠይሚንንም ትንታኔ ስንመለከት፡- ደረጃው ቢለያይም መነሻው ከካፊር የሆነን፣ ድሮ መመሳሰል የሆነን፣ ቀድሞ ሐራም የሆነን ነገር ኋላ ላይ ፈቅደዋል። ስለሆነም *"ቀድሞ ሐራም የሆነ ነገር እንዴት ኋላ ላይ ሐላል ይሆናል"* የሚሉ ሰዎች የአልባኒን ሲሆን እየመረጡ

ሊወስዱ አይገባም። ሁለቱም ጋር ጫፍ ላይ የሚገናኝ ተቀራራቢ አመክንዮ አለና። በተጨማሪ አልባኒም ሱሪን ለመከልከል ያነሱትን ምክንያት የሚያፈርስ ትንታኔ እንደሰጡ በቅርቡ አልፏል።

ደግሞም ከሰበብ (ዒላ) ጋር ተቆራኝቶ የተከለከለ ነገር ያ ሰበብ ሲጠፋ የሚፈቀድበት ሁኔታ አለ። ይህም ከዚያ ነው። በመመሳሰል ሰበብ ተከለከለ እንጂ አልባሳት መሰረታቸው ሐላል ነው። ለምሳሌ የመታወቂያ (ሹህራ) ልብስን መውሰድ ይቻላል። በአንድ ሃገር ላይ ስለተለመደ ተፈቅዶ በሌላ ሃገር ላይ እንግዳ በመሆኑ የማይፈቀድበት ሁኔታ ይኖራል። በዚህ ረገድ ቀደም ብለው ያለፉትን መረጃዎች ያስታውሱ።

**<u>ሶላት በሱሪ</u>**

አንዳንዶች *"አማራጭ ካልጠፋ በስተቀር በሱሪ ሶላት መስገድ አይቻልም"* ይላሉ። ይሄ ግን ጠንካራ መረጃ ላይ ያልቆመ ልፍስፍስ ሙግት ነው። በርግጥ *"የአላህ መልእክተኛ ﷺ አንድ ሰው በላዩ ላይ ኩታ ሳያደርግ በሱሪ ብቻ እንዳይሰግድ ከልክለዋል።"* [ሶሒሕ አቢ ዳውድ፡ 646] ይሁን እንጂ፡-

**አንደኛ፡-** መልእክቱ ሌላ ምንም ልብስ ሳይኖር በሱሪ ብቻ እንዳይሰገድ ነው የተከለከለ ነው። *"የዚህ ሐዲሥ መልእክት ነብዩ ﷺ በሱሪ **<u>ብቻ</u>** ከመስገድ ከልክለዋል ማለት ነው"* የሚለው የአቡበክር አነይሳቡሪ ረሒመሁላህ ንግግር ይህን ይበልጥ ግልፅ ያደርግልናል። [ታሪኹ በግዳድ፡ 5/138] ሸይኹል አልባኒም ረሒመሁላህ የሐዲሡ መልእክት *"ለአንዳችሁ ሁለት ልብስ ከኖረው በነሱ ይስገድ። አንድ ብቻ እንጂ ካልኖረው በሱ ይታጠቅበት። እንጂ የአይሁድ መጠቅለልን አይጠቅለል"* ከሚለው ሐዲስ መልእክት ጋር ተመሳሳይ ነው

ይላሉ። [አስሶሒሐህ፡ 2905] ስለዚህ መልእክቱ ሱሪ ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም። ሸርጥም ቢሆን የተለየ ብይን የለውም። ነብዩ ﷺ *"አንዳችሁ በትከሻው ላይ ምንም ሳይኖር በአንድ ልብስ አይስገድ"* ብለዋል። [ቡኻሪ፡ 359፣ ሙስሊም፡ 516] **ስለዚህ የተከለከለው ትከሻ ላይ ምንም ልብስ ሳይኖር በአንድ ልብስ ብቻ መስገድ ነው።**

**ሁለተኛ፡-** ትከሻ ላይ ልብስ ጣል ማድረጉም ብዙሃኑ ዑለማእ ዘንድ ግዴታ አይደለም። ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *"ትከሻዎችን መሸፈን ሱና እንጂ ግዴታ አይደለም። ይህም በግዴታም ይሁን በትርፍ ሶላት ላይ ልዩነት የለውም። ይህም 'ጠባብ ከሆነ አሸርጥበት' የሚለውን ሐዲሥ መሰረት በማድረግ ነው። ይሄ ነው ሚዛን የሚደፋው አቋም። የብዙሃኑ መዝሀብም ይሄ ነው።"* [ሸርሑል ሙምቲዕ፡ 2/168]

ስለዚህ ከላይ ከተለበሰ ወይም የሆነ ነገር ጣል ከተደረገ ልክ እንደ ሸርጥ በሱሪ መስገዱ ችግር የለውም ማለት ነው። አንዳንድ ዐሊሞች ግን በሱሪ **ብቻ** መስገድ የተከለከለበት ምክንያት በጣም አጭር ከሆነ ሀፍረተ-ገላን (ጭንን) ስለሚያጋልጥ ወይም ደግሞ ብቻውን ከተለበሰ በሩኩዕና በሱጁድ ጊዜ ከኋላ በኩል ሀፍረተ-ገላ ሊጋለጥ ስለሚችል እንደሆነ ገልፀዋል። በየትኛውም ምክንያት ቢሆን ሃፍረተ-ገላ በማይጋለጥበት መልኩ ከላይ (ጋቢ፣ ሸሚዝ፣ ኮት፣...) ከተለበሰ በሱሪ መስገዱ ችግር እንደሌለው መረዳት ይቻላል። አንዳንድ ወጣ ያለ ቢያጋጥምም የአራቱም መዝሀብ አቋም ሰፊ ሱሪ ይቅርና አንድ የሃፍረተ-ገላን **ቅርፅ** የሚያሳይ ልብስ ለብሶ መስገድ እራሱ ሶላት እንደማያበላሽ ነው። ጥቂት ምሳሌ እንመልከት፡-

## 1. በሐነፍያ መዝሀብ

ዐላኡዲን አልካሳኒ አልሐነፊ *“የሚጠላው ልብስ በአንድ ሸርጥ ብቻ ወይም ደግሞ በአንድ ሱሪ ብቻ መስገዱ ነው”* ይላሉ። [በዳኢዑ ሰናኢዕ፡ 1/151] ሽርጥንም አብረው ማውሳታቸውን አስተውሉ። ኢብኑ ኑጀይም ደግሞ *“በአንድ ሽርጥ ቢሰግድ የሚጠላ ቢሆንም ይፈቀዳል። ያለ ችግር በሱሪ ብቻ መስገድም እንዲሁ ነው”* ይላሉ። [አልበሕሩ አርራኢቅ፡ 2/45] እዚህም ላይ ሱሪ ከሽርጥ የተለየ ብይን አልተሰጠውም።

ከዚህም ባለፈ ልብሱ ወፍራም ከሆነና የአካልን ቀለም ካላሳየ **ተለጥፎ ቅርፅ ቢያሳይም** ሶላቱ አይበላሽም የሚል አቋም አላቸው። [አዱርል ሙኽታር፡ 2/84]

## 2. በማሊኪያ መዝሀብ

ሌላ ልብስ ሳይኖር በሱሪ ብቻ መስገዱ እንደሚጠላ ኢማሙ ማሊክን ጨምሮ የተለያዩ የመዝሀቡ ምሁራን ይገልፃሉ። [አነዋዲር ወዚያዳት፡ 1/201] [አስሀሉል መዳሪክ፡ 1/182-183]

ከባዱን የሀፍረተ ገላ ክፍል ብቻ ከሸፈነ ወይም የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ ካሳየ በሱ መስገዱ ይጠላል። ወቅት ካለም ይመልሳል። [አልፈዋኪሁ ደዋኒ፡ 1/216] ልብ በሉ! መመለሱ የሚወደድ እንጂ ግዴታ እንዳልሆነና መጠላቱም ወደ ሐራምነት የቀረበ እንዳልሆነ (ከራሀተ አተንዚህ እንደሆነ) የጠቆሙ አሉ። [ሓሺየቱ ዱሱቂ] [በልገቱ ሳሊክ፡ 1/283]

## 3. በሻፍዕያ መዝሀብ፡-

አልኢማም ሻፊዒ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *“ወንድ በእብርቱና ጉልበቱ መሀል ያለውን ከሸፈነ **በሱሪ ይሰግዳል።** ሽርጥ ግን ይበልጥ ሸፋኝና*

*ከሱ የተወደደ ነው። እኔ ዘንድ ይበልጥ የሚወደደው ትከሻው ላይ እንደ ጥምጣም ወይም ሌላ ገመድ እንኳን ቢሆን አስቀምጦ እንጂ ላይሰግድ ነው።”* [አልኡም፡ 1/183]

አልኢማም አነወዊ ደግሞ *“(የሰውነት) ቀለምን ሸፍኖ እንደ ጉልበት፣ **__መቀመጫና__** የመሳሰሉ የአካል ክፍሎችን ቅርፅ ቢያጎላ መሸፈኑ ስለተገኘ ሶላቱ ልክ ነው። ዳሪሚና የበያን ባለቤት ቅርፅን ካጎላ እንደማይቻል ገልፀዋል። **__ይሄ ግን ግልፅ የሆነ ስህተት ነው__**”* ይላሉ። [አልመጅሙዕ፡ 3/176]

### 4. በሐንበሊያ መዝሀብ፡-

ብዙሃኑ የሐንበልያ መዝሀብ ምሁራን በሱሪ መስገድን ይፈቅዳሉ። የሀፍረተ-ገላ ቅርፆች ቢታዩም ችግር እንደሌለው ይገልፃሉ። [አልኢንሷፍ፡ 1/415]

ኢብኑ ቁዳማ እንዲህ ይላሉ፡- *“የአካልን ቀለም በሚሸፍን መልኩ መሸፈን ግዴታ ነው። ስስ ሆኖ ከጓላ ንጣቱ ወይም ቅላቱ በሚታወቅ መልኩ የአካልን ቀለም የሚያሳይ ከሆነ በሱ ሶላት መስገድ አይቻልም። ምክንያቱም በዚህ መሸፈኑ ስላልተገኘ። **__ቀለሙን የሚሸፍን ሆኖ ቅርፅ የሚያሳይ ከሆነ ግን ሶላቱ ይቻላል። ምክንያቱም ይሄ ሽፋኙ ሰፊ ቢሆን እንኳን ሊጠነቀቁት የሚቻል አይደለምና።__**”* [አልሙግኒ፡ 2/287] ኢብኑ ሙፍሊሕና በሁቲም ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ። [አረውዱል ሙረበዕ፡ 1/494] ኢብኑ ቃሲም ከበሁቲ ንግግር አስከትለው ይህ የሐንበልያ አቋም ከሶስቱም መዝሀቦች አቋም ጋር የገጠመ ነው ይላሉ። ከዚህም የአራቱም መዝሀቦች አቋም ተመሳሳይ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። አንዳንድ ወጣ ያለ መኖሩ ይህን እውነታ አያፈርስም።

ከዘመናችን ዑለማዎች ውስጥ ደግሞ ኢብኑል ዑሠይሚን በሱሪ መስገድ እንደሚቻል የገለፁበት አለ። [*መጅሙዑ ፈታዋ፡* 13/348] ኢብኑ ባዝም እንዲሁ [*መጅሙዑ ፈታዋ፡* 10/414] አልባኒም ጠባብ ካልሆነ ሶላቱ ትክክለኛ እንደሆነ ተናግረዋል። [*ፈታዋ አልኢማራት*] በሌላም ጊዜ ወንድ በሱሪ ስለመስገዱ ሲጠየቁ ከቁርጭምጭሚት በታች ማውረድ እንደማይፈቀድ ከማውሳታቸው ባለፈ ሶላቱ ውድቅ ነው አላሉም። [ሊባሱ ረጁል ወልመርአ] ሸይኽ ሙቅቢልም ሱሪን ከመቃወማቸው ጋር *"ሶላቱ ግን ትክክለኛ ነው። ያለቁርኣንና ያለ የመልእክተኛው ﷺ የሱና ማስረጃ የማንንም ዒባዳ ውድቅ ልናደርግ አይቻለንም"* ይላሉ። [አስኢለቱ ሸባቢ ቀርየቲ ሰዒድ] ፈውዛንም እንዲሁ የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ የሚያሳይ ጠባብ የሆነ ልብስ እንደማይፈቀድና ይህን ያደረገ ወንጀለኛ እንደሚሆን ቢገልፁም ሶላቱ ግን እንደማይበላሽ ገልፀዋል። [አልሙንተቃ፡ 3/308-309]

ዐብዱል ዐዚዝ አርራጂሒም *"በሱሪ፣ በተለያዩ አልባሳትና በሸርጦች መስገድ ችግር የለውም። ሱሪ ከወገብ በታች የሚለበሰው ነው፣ ከወገብ በታች ያለውን የሚሸፍነው። ሱሪ ወይም ኩታ ይለብስና ትከሻው ላይ ጣል ያደርጋል። ሸርጥ ወይም ሱሪ ይለብስና ትከሻው ላይ ኩታ ያደርጋል። በኩታና በሱሪ፣ በኩታና በሸርጥ ወይም ቀሚስ መስገድ ይቻላል"* ይላሉ።

**ማሳሰቢያ፡-**

የሀፍረተ-ገላን ቅርፅ በሚያሳዩ ልብሶች መስገድ *"ሶላቱን አያበላሽም"* የሚሉ የዑለማእ ብይኖችን የዘረዘርኩት ጥብቅብቅ ያሉ ልብሶች ይፈቀዳሉ ለማለት አይደለም። ይልቁንም በሱሪ መስገድ እንደሚቻል የሚጠቁሙ ከጥንት እስከ ዛሬ ያሉ የዑለማእ ንግግሮችን በአስገዳጅ ሁኔታ ላይ ብቻ የሚገድቡና አሁን ያለውን ሱሪም ከዚህ ምድብ ውስጥ የሚያሰፍሩ ሰዎች ልክ እንዳልሆኑ

ለማሳየት ነው። ለነገሩ ብዙዎቹ ሱሪዎች በአንዳንድ እንቅስቃሴ ጊዜ የሚከሰተውን መለኪያ ካላደረግን በስተቀር ቅርፅ እስከማሳየት የሚደርስ ጥበት አላቸው ለማለት ይከብዳል። ለዚህም ነው የሀፍረተ-ገላ ቅርፅ መታየት የለበትም የሚሉ ዐሊሞች ጭምር የፈቀዱቸው።

## <u>ለከት ይኑርህ!</u>

በአሁኑ ሰዓት ያለውን ሱሪ በተመለከተ የሚፈቅዱና የሚከለክሉ ሁለት የዑለማእ እይታዎች እንዳሉ ተመልክተናል። ከሁለቱ ሚዛን የሚደፋውን አንባቢ ከስሜት ነፃ ሆኖ መወሰን ይችላል። ነገር ግን “ሐራም ነው” የሚለው ቢያመዝንልን እንኳን ጉዳዩ ዛሬ አንዳንዶች የሚያራግቡትን ያክል የሚደርስ አይደለም። በፊቅሃዊ የኢጅቲሃድ ጉዳዮች አንድነትን መበጥበጥ፣ ማለቂያ የሌለው ጉንጭ አልፋ ሙግት መከፈት፣ ወንድማማችነትን ማደፍረስ በእርግጠኝነት “ሱሪ ሐራም ነው” የሚሉ ዐሊሞችም የተጓዙበት መንገድ አይደለም። አንድ ምሳሌ እንመልከት፡- ሸይኽ ዐብዱል ሙሕሲን አልዐባድ *“ሱሪ ሐራም ነው”* ከሚሉ ዐሊሞች አንዱ እንደሆኑ አሳልፌያለሁ። ከመሆኑም ጋር ግን *“አንዳንድ ልብሳቸውን የሚያስረዝሙ ወይም ደግሞ **<u>ሱሪ የሚለብሱ ዱዓቶችና የዲን እውቀት ተማሪዎች</u>** በተመለከተ **<u>መረጃው ከደረሳቸው በኋላ</u>** እንዴት ነው ከነሱ ጋር የሚኖረን መስተጋብር?”* ተብለው ተጠይቀው ነበር። አስተውል!! ሱሪ ለባሾቹ፡-

- መሀይሞች ሳይሆኑ ዱዓቶችና የዲን እውቀት ተማሪዎች ናቸው።
- “መረጃ” ደርሷቸዋል።

*“ሱሪ ሐራም ነው”* የምትለው ወንድሜ ሆይ! አንተ ብትሆን እንዲህ አይነት ሁኔታ ቢያጋጥምህ ምን ታደርጋለህ? ታኮርፈዋለህ? ባደባባይ ታነውረዋለህ? ከሱና ስ ታስወጣዋለህ? መልስህን በውስጥህ ያዝና የሸይኹን መልስ ተመልከት። ልክ የሚከለክል ፈትዋቸውን እንደምታጣቅሰው ይሄንንም አጣቅስላቸው። አካሄዳቸውንም ውሰድላቸው። መልሳቸውና ይሄውና፡-

*“የሰው ልጅ ሊመክርና ምክሩንም ሊደጋግም ይገባል። ከዚህ ተስፋ ሊቆርጥ አይገባም። ልክ እንዲሁ ከዚህ ሰውየ ዘንድ ቦታ ያለውን ሰው ፈልጎ ሊያስመክረው ይገባል። ምናልባት ይጠቀም ይሆናልና። **ይህን ነው ከሰዎች አንፃር ሊተገበረው የሚገባው።”*** [ሸርሕ ሱነን አቢ ዳውድ፡ 1/2]

አልባኒም ቢሆኑ በሱሪ ሰበብ ሰዎችን ማግለል፣ ማኩረፍ ወይም ከሱና ማስወጣትን አላስተማሩም። ይልቁንም ከዚህም በገዘፉ ከባባድ ጉዳዮች ላይ ጥንቃቄንና መረጋጋትን ነው ያስተማሩት። እንዲያውም ሚሊዮኖች በሽርክ በሚጨማለቁበት፣ ሶላት በማይሰግዱበት ሃገር ውስጥ “ክልክል ነው” ተብሎ ቢታመን እንኳን በአደብ ከማስተማር ባለፈ በሱሪ ምክንያት ማኩረፍ፣ መበጥበጥ፣ ህብረትን መሰንጠቅ፣ ሰዎችን ማስበርገግና ፈተና መፍጠር፣… የእውቀትን መቅለልን ብቻ ሳይሆን የማገናዘብ ችግር እንዳለም የሚያሳይ ነው።

## ምዕራፍ ሶስት፡ የተብዲዕ ቅድመ-ሁኔታ

አንድ ሰው መቼ ነው እንደ ከሃዲ ወይም ሙብተዲዕ አለያም ደግሞ እንደ አመፀኛ የሚቆጠረው የሚለውን ጠንቅቆ አለማወቅ ብዙዎችን እጅግ

አደገኛ ለሆነ ጥፋት ሲያጋልጥ ይታያል። አንድ በደዕዋ ዘርፍ ላይ የተሰማራ ሰው በዚህ ረገድ የሚያስፈልገውን መርህና ጥንቃቄ ካልለየ ጥፋቱ ከራሱም አልፎ ወደሌሎች ይሻገራል። ያለ አግባብ እየወነጀለ ክብራቸውን ከሚያጎድፋቸው ሰዎች በተጨማሪ ጥፋቱ ብዙዎችን ውዥንብር ላይ ይጥላል፣ ሰዎችን ያሳስታል፣ ለደዕዋም መሰናክል ይሆናል።

ይህን ምዕራፍ ማካተት የፈለግኩበት ምክንያት የሆነ ቢድዐ እንደሆነ የተረዳነው ነገር ከሆኑ ሰዎች ላይ በታየ ቁጥር ለፍረጃ የምንቸኩልበት ሁኔታ ስለበዛ እራሴን ጨምሮ ለሌሎችም ወንድም እህቶች ልጓም እንዲሆነን በማሰብ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የሚያስፈልጉ መርሆዎችን ለይቶ አለማወቅ በርካታ ፅንፍ የረገጡ አንጃዎች እንዲፈለፈሉ ሰበብ ሆኗል። በየጓዳው እየተፈለፈሉ ሙስሊሙን በጅምላ የሚያከፍሩ ወይም ያለ ጥንቃቄና ቅድመ-ሁኔታ ሰዎችን ከሱና የሚያስወጡ ሰዎች ተራውን ህዝብ ቀርቶ ታላላቅ የሱና ዑለማዎችንም ጭምር ክብራቸውን መቦጨቅ አለፍ ሲልም በቢድዐና በኩፍር መፈረጅ እንደ ቅዱስ ምግባር እየቆጠሩ ነው። ለእንዲህ አይነት የጥፋት ተጣሪዎች ሰለባ ከመሆናችን በፊት በዚህ ረገድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነጥቦችን ልንለይ ይገባል።

## ጠቃሚ መርሆዎችና ጥንቃቄዎች

ሁሌም የምትጓዝበት ቋሚ መርህ ይኑርህ። ሱኒ የሆነ ሰው ከሰው ሰው የማይቀያየር፣ እንደ ስሜቱ እንዳሻው የማይከረባበት ወጥ የሆኑ መርሆዎች ሊኖሩት ይገባል። ቋሚ መርህ ከሌለህ ዛሬ *“ማህበር ቢድዐ ነው”* ብሎ የበጠበጠህ ነገ *“ጃሚዐ (ዩኒቨርሲቲ) ቢድዐ ነው”* ብሎ ሊበጠብጥህ ይችላል። ዛሬ በሱሪ ጉዳይ ናላህን ያዞረህ ነገ ሌላ ልብስ አንስቶ *“ሰለፎች*

*ኢያውቁትም፣ ተሸቡህ ነው"* ብሎ ጩኸቱን እስክትጮኽለት ሊነዘንዝህ፣ ሰላምህን ሊነሳህ ይችላል። ነገሮች ሲደባለቁ ሁሉንም እያነሳህ በየመደባቸው የምታስቀምጥበት መመዘኛ ከሌለህ የሚለያየውን ታደበላልቃለህ። የሚመሳሰለውን ታራርቃለህ። ብታወራ ወሬህ ውል አይኖረውም። ብትፈርድ ፍትሕ አይታይብህም። አልኢማም ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*"ከእያንዳንዱ ሰው ጋር፡ በእውቀትና በፍትሕ ይናገር ዘንድ ቅርንጫፋዊ ጉዳዮች የሚመለሱበት ጥቅል መርሆዎች ሊኖሩት የግድ ይላል። ከዚያም ቅርንጫፋዊ ነጥቦች እንዴት እንደተከሰቱ ማወቅ ይችላል። ያለበለዚያ በቅርንጫፋዊ ነጥቦች ላይ ውሸትና መሀይምነት ውስጥ፣ በጥቅል መርሆዎች ላይ ደግሞ መሀይምነትና በደል ውስጥ ነው የሚቀረው። በዚህም ሳቢያ ትልቅ ጥፋት ይከተላል።"* [አልፈታዋ፡ 19/203]

ይህን ታሳቢ በማድረግ እያንዳንዱ ዒልም ፈላጊ ሊረዳቸው ከሚገቡ የአህሉ ሱና መርሆዎች ውስጥ ርእሳችንን ከሚመለከቱት ውስጥ ጥቂቶቹን እንመልከት፡- [20]

1. **የመረጃ ምንጩ ከቁርኣን፣ ከሱና እና ከሰለፎች ኢጅማዕ <u>ውጭ</u> የሆነ ሰው ሙብተዲዕ ነው።**

---

[20] ከዚህ በተጨማሪ ቢድዐ ላይ የወደቁ ሰዎች ላይ ብይን መስጠት የሚችለው እንዲሁ ማንም አይደለም፡፡ ይልቁንም በዚህ ረገድ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያሟላ ሰው መሆን እንዳለበት ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ [ዶዋቢጡ አተብዲዕ፣ ሸይኽ ረስላን፡ 59-76]

ምክንያቱም ከጥንትም ጀምሮ አህሉ ሱና ወልጀማዐህ ቁርኣንን፣ ሱናን እና የመልካም ቀደምቶችን ወጥ ስምምነት አይሻገሩም። ሙተሻቢሆችን እየመረጡም አይከተሉም። ይልቁንም ሶሐቦችና ታቢዒዮችን እንዲሁም በንግግርም በተግባርም ሙስሊሞች የተስማሙበትን ነው የሚከተሉት። [አልሑጃህ ፊ በያኒል መሐጃህ፡ 2/410]

ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*"እያንዳንዱ አማኝ በየትኛውም የዲን ጉዳይ መልእክተኛው ﷺ የመጡበትን ተከትሎ ካልሆነ በስተቀር ሊናገር አይገባውም። ከፊታቸው መቀዳደም የለበትም። ይልቁንም ወደተናገሩት ይመልከትና ንግግሩ ለንግግራቸው፣ እውቀቱ ለትእዛዛቸው ተከታይ ይሁን። ሶሐቦች፣ እነሱን በመልካም መንገዳቸውን የተከተሉ ታቢዒዮችና የሙስሊም ምሁራን እንዲህ ነበሩ። በዚህ ምክንያት ከነሱ አንድም ግልፅ ሸሪዐዊ መረጃዎችን በህሊናዊ ምዘናው አይመልስም፤ መልእክተኛው ﷺ ከመጡበት ውጭ የሆነን ዲን አይመሰርትም ነበር። የሆነን የዲን ወይም የንግግር ጉዳይ ማወቅ ከፈለገም አላህና መልእክተኛው ﷺ የተናገሩትን ይመለከታል። ከሱ ይማራል። በሱም ይናገራል። በሱ ላይ ይመለከታል። በሱ ላይ ያገናዝባል። እሱንም መረጃ ያደርጋል። ይህ ነው የሱና ባለቤቶች መሰረት።*

*የቢድዐ ሰዎች ግን በሰውርም ይሁን በቀጥታ በጉዳዩ ላይ ከነብዩ ﷺ በተቀበሉት ላይ አይመረኮዙም። ይልቁንም በሚመለከቱት ወይም በሚያጣጥሙት ላይ ነው የሚመረኮዙት። ለዚያም ነገር ሱና የሚገጥመው ሆኖ ካገኙ እሰየው። ካልሆነ ግን ከቁብም አይቆጥሩት። ሱናው እነሱ*

*ለያዙት ነገር ተፃራሪ ሆኖ ካገኙት አይበስብሰው ያልፉታል። ወይም ደግሞ መልእክቱን ይጠመዝዙታል። ይህ ነው በኢማንና በሱና ሰዎች እና በኒፋቅና በቢድዐ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት።”* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 13/62-63]

ከዚህ ነጥብ የሚፈለገው አንድ ሰው ላይ በምናየው ጥፋት ወደ ተብዲዕ ከማሰባችን በፊት *“የሚዳዝበት ጥቅል መርህ ማለትም የመረጃ አጠቃቀሙ በተጨባጭ ቁርኣን፣ ሐዲሥና የቀደምቶችን ኢጅማዕ መሰረት ያደረገ ነው ወይ?”* የሚለውን ማጤን እንደሚገባ ማስታወስ ነው። የመረጃ አጠቃቀሙ ቁርኣን፣ ሱና እና የሰለፎችን ኢጅማዕ መሰረት ያደረገ ካልሆነ እንደ ሱኒ የሚቆጠርበት አግባብ የለም። የመረጃ አጠቃቀሙ ቁርኣን፣ ሱና እና የሰለፎች ኢጅማዕን መሰረት ያደረገ ከሆነ ግን ይሄ ወደ ቀጣዩ ክፍል የምንወጣበት መሰላል ይሆነናል።

2. **ከቁርኣን፣ ከሱና እና ከኢጅማዕ የተቀዱ <u>መሰረታዊ መርሆዎችን</u> የሚጥስ ሰው የቢድዐ ሰው ነው።**

ኢብኑ ተይሚያ እንዲህ ይላሉ፡- ***<u>“ፍንትው ያለን ቁርኣናዊ መልእክት ወይም በሰፊው የተነሰራፋን ሱና ወይም ደግሞ ቀደምት ህዝቦች የተስማሙበትን ነገር</u> <u>በይቅርታ በማይታለፍ መልኩ</u>*** *የተፃረረ ሰው የቢድዐ ሰዎች በሚስተናገዱበት መልኩ ይስተናገዳል።”* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 24/172] በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፡- *“አንድ ሰው ከስሜት ተከታዮች እንደሆነ የሚቆጠርበት **<u>የቢድዐ አይነት</u>** የሱና አዋቂዎች ዘንድ ለቁርኣንና ለሱና ተፃራሪ መሆኑ **<u>በሰፋት የሚታወቀው</u>** ነው። እንደ የኸዋሪጅ፣ የረዋፊድ፣ የቀደሪያና የሙርጂአ ቢድዐን ይመስል።”* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 35/414]

ከዚህ ነጥብ የሚፈለገው አንድ ሰው እንደ ሙብተዲዕ የሚቆጠርበት የቢድዐ አይነት ከቁርኣን ከሱና ና ከቀደምቶች ኢጅማዕ ጋር መፃረሩ **<u>በማያሻማ መልኩ በግልፅ፣ በስፋት የሚታወቅ የሆነ የቢድዐ አይነት ነው</u>**። ስለዚህ ስውር ወይም አወዛጋቢ ወይም ቅርንጫፋዊ በሆነ ጉዳይ የተለየ ሀሳብ ስላንፀባረቀ ስህተት እንኳን ቢሆን ማንንም ከሱና ማስወጣት የዑለማዎች አካሄድ አይደለም። አቡል ቃሲም አተይሚ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- ***<u>“የኢጅቲሃዳዊ ጉዳዮችና ዲናዊ ቅርንጫፎች ሆነው ሰዎች የተወዛገቡባቸው ነገሮች አንድ ሰው በዚህ ሳቢያ ሙብተዲዕ ወይም የተዛተበት ውግዝም አይሆንም።”</u>*** [አልሑጃህ ፊ በያኒል መሐጃህ፡ 2/411]

ስለዚህ አንድ ሰው ከሙብተዲዕ የሚቆጠረው መሰረታዊ ወይም ጠቅላይ የሆኑ መርሆዎችን ሲጥስ እንጂ ቅርንጫፋዊ ጉዳይ ላይ የተለየ ሀሳብ ሲያንፀባርቅ አይደለም። ሻጢቢ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

> *“ይህም እነዚህ አንጃዎች እንደ ጠፊ አንጃዎች የሚቆጠሩት ለምትድነዋ ቡድን ዲን ውስጥ ባለ **<u>ጠቅላይ ጉዳይና ከሸሪዐ መርሆዎችም የሆነን መርህ በመፃረራቸው ሳቢያ ነው።</u>** **<u>እንጂ ከንኡስ ክፍሎች ውስጥ በሆነ ንኡስ ክፍል አይደለም።</u>** **<u>ምክንያቱም ወጣ ያለ ንኡስ ክፍልና ቅርንጫፋዊ ጉዳይ ላይ ያልለ እይታ የተለያየ አንጃ እስከሚያደርግ የሚያደርስ ልዩነትን አያስከትልም።</u>** **<u>መለያየት የሚከሰተው መፃረሩ ጠቅላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲሆን ነው።</u>** ምክንያቱም ጠቅላይ መርሆዎች ቀላል ያልሆኑ ንኡስ ክፍሎችን ያቅፋሉና። … **<u>ቅርንጫፋዊ የሆነ ጉዳይ ግን ብይኑ ከዚህ የተለየ ነው።”</u>*** [አልኢዕቲሷም፡ 2/177-178]

### 3. **የሰለፎችን መርሆች የሚፃረር ቢድዐ ላይ የወደቀን አካል እራሱ በተናጠል *“እከሌ ሙብተዲዕ ነው”* ከማለት በፊት ጥንቃቄ ያስፈልጋል።**

ጥቅል በሆነ መልኩ ከሰለፎች የተገኙ መሰረታዊ መርሆዎችን የሚጥስን ሰው *“ይህን የሰራ ሙብተዲዕ ነው”* በማለት መግለፅ ቢፈቀድም ግለሰቦች ላይ በተናጠል ስንመጣ ግን አንድ ሰው ግልፅ ቢድዐ ላይ ቢወድቅ እንኳን እንደ ሙብተዲዕ ከመቁጠራችን በፊት ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎችና ሊነሱ የሚገባቸው ከልካይ ነገሮች አሉ። ምክንያቱም ቢድዐ ላይ የወደቀ ሁሉ ሙብተዲዕ ሆኗል አይባልምና። ስለሆነም አንድ ሰው የመረጃ ምንጬ ሰለፎች ከነበሩበት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እንዲሁም ለመልካም ሰለፎች ወዳጅ ሆኖ ሳለ ባልተረዳው መልኩ የሰለፎችን መሰረት የሚፃረር ጥፋት ላይ ቢወድቅ **<u>በዚያ ጥፋቱ ውዴታንና ጥላቻን ካልቋጠረበት በስተቀር</u>** መስፈርቶች ሳይሟሉ በፊት እንደ ሙብተዲዕ አይቆጠርም። ይህን ሀሳብ ግልፅ ያደርግልን ዘንድ ጥቂት የቀደምት ዑለማዎችን አካሄድ እንመልከት፡-

**ምሳሌ አንድ፡-** ነብዩ ﷺ አስር ሶሐቦቻቸውን በአንድ ሐዲሥ ላይ በጀነት እንደመሰከሩላቸው ይታወቃል። [ሶሒሑል ጃሚዕ፡ 4010] ከዚህ ሐዲስ መልእክት በተቃራኒ *“ ‘አስሩ የጀነት ናቸው’ ብሎ የመሰከረ ሙብተዲዕ ነው”* በማለት የሐዲሡን መልእክት የሚመልስ ሰው ቢያጋጥማችሁ ምን ትላላችሁ? እስኪ እኛ ብንሆን በእንዲህ አይነት ሰው ላይ ምን ብይን እንወስድበታለን?! መልሳችንን በውስጣችን እንያዝና ኢማሙ አሕመድ ምን እንዳደረጉ እንመልከት፡-

*" 'አስሩ የጀነት ናቸው' ብሎ የመሰከረ ሙብተዲዕ ነው"* ስለሚል አንድ የሐዲሥ ሰው ሲጠየቁ ጥፋቱን ከባድ እንደሆነ አንፀባረቁ። ከዚያስ ምን አሉ? ***"ምናልባት* የማያውቅ መሀይም እንዳይሆን**" አሉ። *"ከአህሉ ሱና ይሆናል?"* ሲባሉ ***"ከሱና ላስወጣው አልዳፈርም።*** *ሲተነትን ተሳስቷል"* አሉ። [አሱና ሊልኸላል፡ 1/369]

አስተውሉ! ጥፋቱ ከባድ ነው። በዚያ ላይ ተራ መሀይም ሳይሆን የሐዲሥ ሰው ነው። ይህም ከመሆኑ ጋር ግን የኢማሙ አሕመድን ጥንቃቄ ተመልከቱ። በተረጋገጠው ግልፅ ጥፋት ከመወሰን ይልቅ በምናልባት መከላከልን ነው የመረጡት።

**ምሳሌ ሁለት፡-** *ቀደምቶቻችን "ቁርኣን ፍጡር ነው"* የሚለውን የኩፍር ዘመቻ በብርቱው ተጋፍጠውታል። በዚህም ሳቢያ ዘግናኝ የሆኑ ስቃዮችን አስተናግደዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተዘልዝለዋል፣ ተገድለዋል። ደግመው ደጋግመው *"ቁርኣን ፍጡር ነው"* የሚል ሰው ሙብተዲዕ ብቻ ሳይሆን ከሃዲ እንደሆነም ተናግረዋል። ይህም ከመሆኑ ጋር አሕመድ ኢብኑ መኒዕ አልበገዊ ረሒመሁላህ ምን እንደሚሉ እንመልከት፡- *" '(ቁርኣን) ፍጡር ነው' ብሎ የምገተ ሰው ጀህሚ ነው። **በዚህ ላይ ያመነታ እንደ አትክልት ሻጮች፣ ሴቶችና ህፃናት ያሉ የማያውቁ ከሆኑት ውስጥ ከሆነ ዝም ይባልና ትምህርት ይሰጠዋል።"***
[አልሑጃህ ፊ በያኒል መሐጃህ፡ 2/424]

እነዚህ ምሳሌ ብቻ ናቸው። እንጂ ብዙ መዘርዘር ይቻላል። የሚከተለው የኢብኑ ተይሚያ ንግግር ይህን ይበልጥ ግልፅ ያደርግልናል፡-

> ***"እንዲያውም ሐቅን አስቦ ከሐቅ የሚስት አለ። በፍለጋው ጥሮ ሳላልደረሰበት አይቀጣም። ምናልባት ከታዘዘበት ከፊሉን ይሰራና በጥረቱ ምንዳ ይኖረዋል። ከትክክለኛው ጉዳይ ፈር የለቀቀበት ስህተቱ***

*<u>ይማርለታል። ከቀደምቶቹም ይሁን ከኋለኞቹ ብዙ ሙጅተሂዶች ቢድዐ መሆኑን ሳያውቁ በእርግጥም ቢድዐ የሆነን ነገር ተናግረዋል፣ ፈፅመዋልም።</u> ይህም የሆነው ወይ ትክክለኛ መስለዋቸው ደካማ ሐዲሦችን ይዘው ነው። ወይ ደግሞ ትክክለኛ ያልሆነን መልእክት (በተሳሳተ መልኩ) ከ(ቁርኣን) አንቀፆች ተረድተው ነው። ወይ ደግሞ መረጃዎች ሳይደርሷቸው በጉዳዩ ላይ የራሳቸውን እይታ ተንተርሰው ነው።"* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 19/191]

አሁንም ኢብኑ ተይሚያ ስለ ሙብተዲዕ ማንነት ሲገልፁ እንዲህ ይላሉ፡-

*"የነዚህ አምሳያ የሆነው <u>የፈጠሩትን ነገር</u> በሱ ሳቢያ የሚወዳጁበትና የሚጠሉበት፣ ከሙስሊሞች ህብረት የሚገነጠሉበት ንግግር ካላደረጉት <u>**እንደ ስህተት ነው የሚቆጠረው።**</u> የጠራውና የላቀው አላህ በዚህ አመሳያ ላይ ያሉ ስህተቶችን ለአማኞች ይምራልና።*

*ለዚህም ነው <u>**ከመልካም ቀደምቶችና ምሁራን ውስጥ ብዙዎች ይህን በሚመስሉ ጥፋቶች ላይ የወደቁት።**</u> በኢጅቲሃድ የተናገሯቸው ከቁርኣንና ከሱና ጋር የሚፃረሩ ንግግሮች አሏቸው።"* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 3/349]

ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን ደግሞ እንዲህ ይላሉ፡- ***"የዐቂዳ ስህተትን በተመለከተ ለመልካም ቀደምቶች መንገድ ተፃራሪ የሆነ ስህተት ከሆነ እሱ ያለጥርጥር ጥመት ነው። ነገር ግን ባለዚህ ጥፋት መረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በጥመት አይፈረጅም። <u>መረጃ ቀርቦበት በስህተቱና በጥመቱ ላይ የሚፀና ከሆነ ግን</u>*** *ሐቅን በጣሰበት ጉዳይ ሙብተዲዕ ሆኗል። ከዚያ ውጭ ባለው ሰለፊ ቢሆንም።"* [ኪታቡል ዒልም፡ 135]

ልብ በሉ! ይሄ፡ ብዥታን የሚገልጥ መረጃ እስከሚቀርብ ድረስ እራስን ከውሳኔ መቆጠብ አንዳንዶች እንደሚሉት የተከፈር ውሳኔ ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም። የሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን ንግግርም ይህን ያስረዳል። ኢብኑ ተይሚያም ይህንኑ ጉዳይ አስረግጠው ተንትነዋል። [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 10/371-372]

ውድ የኢስላም ወንድሜ! ስሜታችንን ረግጠን ለሐቅ እጅ የምንሰጥ ያድርገንና እኛ በሰዎች ላይ በምንፈርድ ጊዜ ምን ያክል ይህንን ቅድመ-ሁኔታ ከግምት እናስገባለን?! ምን ያክልስ በራሳችን ከመቀዳደም ይልቅ ከዑለማእ ኋላ እንሰለፋለን?!

አሁንም እንቀጥልና እንመልከት። ሸይኹል አልባኒ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *"ከሰዎች ውስጥ የሆነ አካል* ***<u>መረጃ እንደቀረበበት ከታወቀ ወይም ከተረጋገጠ</u>*** *እሱን* ***<u>ከሃዲ ወይም አመፀኛ ወይም ሙብተዲዕ ብሎ መበየን ይቻላል። ካልሆነ ግን አይፈቀድም።</u>*** *ይህ ነው ትክክለኛው።"* [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 778]

አሁንም አልባኒ እንዲህ ይላሉ፡-

*"ይሄ ተፃራሪ፡ መረጃን የሚፃረር ከሆነ በቅድሚያ ሊከተሉት አይፈቀድም። ሁለተኛ ከመረጃ ተፃሮ የተናገረውን ንግግሩን* ***<u>'ቢድዐ ነው' ብንልም ተናጋሪውን ሙብተዲዕ አናደርግም።</u>*** *እኔ 'እከሌ ክህደት ላይ ወድቋል' በማለትና 'እከሌ ከፍሯል' በማለት መካከል እለያለሁ።* ***<u>'እከሌ ቢድዐ ላይ ወደቀ' በማለትና 'እከሌ ሙብተዲዕ ነው' በማለትም ላይ እንዲሁ ነው።"</u>*** [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 850]

ባጭሩ ከዚህ ነጥብ የተፈለገው ግለሰቦች ላይ በተናጠል ብይን ለመስጠት <u>የወደቁበት ጥፋት ከመሰረታዊ መርህ ጋር የሚፃረር መሆኑ ብቻውን በቂ አይደለም። ይልቁንም ብዥታቸውን የሚገልጥ መረጃ ሊደርሳቸው ይገባል። እንደ ሙብተዲዕ የሚቆጠሩት መረጃ ከቆመባቸው በኋላ ነው ለማለት ነው።</u> ይሄ መርህ የሚመለከተው ተራ መሀይማንን ብቻ አይደለም። ይልቁንም ታላላቅ ዑለማዎች ሳይቀሩ በተሳሳተ ኢጅቲሃድ ወይም በሆነ ብዥታ ምክንያት ዐቂዳዊ የሆኑትን ጨምሮ ቀላል የማይባሉ ስህተቶች ላይ ወድቀው አጋጥመዋል። በዚህ ላይ በርካታ የምንወዳቸውንና የምናከብራቸውን ዑለማዎች መጥቀስ ይቻላል።

ይሄ ማለት ግን ጥፋት ላይ ምላሽ አይሰጥም ማለት አይደለም። መረጃ ደረሰም አልደረሰም በጥፋቱ ሰዎች እንዳይሸወዱ እርምት መስጠት ያለ ነው።

**ብዥታ፡-**

ምናልባት የአጥፊውን ተጨባጭ ሁኔታ ሳይመለከቱ ማለትም *"መረጃ ደርሶታል ወይስ አልደረሰውም"* የሚለውን ሳይጠቁሙ አጥፊውን በቢድዐ የፈረጁበት ከአንዳንድ ሰለፎች ተገኝቷል። እነዚህ ነጠላ ክስተቶችን በመመርኮዝ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ሰዎችን በቢድዐ በፈረጅ የታወቁ መርሆዎችን የሚዳፈሩ አሉ። ይሁን እንጂ ከማንም ቢያጋጥሙ አንዳንድ ወጣ ያሉ ክስተቶችን ሁሌ የምንጓዝባቸው ቋሚ መርሆዎች ማድረግ ጤነኛ አካሄድ አይደለም። *"ለምን?"* ከተባለ መልሱን ከታላቁ ኢማም ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንመልከት፡-

*"ብዙዎቹ የኢማም አሕመድም ይሁን የሌሎች ምሁራን መልሶች* ***ተጠያቂው ሁኔታውን ከሚያውቀው የጠያቂ ጥያቄ መሰረት*** *ወይም ደግሞ* ***ለሆነ ሁኔታው በውል ስለሚታወቅ የሆነ ሰው አስመልክቶ*** *የተሰጠ ንግግር ነው። ስለሆነም ይሄ ከመልእክተኛው* ﷺ *እንደተላለፉ* ***አንዳንድ ልዩ ክስተቶች የሚታይ*** *ነው።* ***ብይናቸው የሚፀናው በባጤዎቻቸው ላይ ብቻ ነው።"*** [መጅሙዑል ፈታዋ: 28/213]

## 4. በኢጅቲሃድ ጉዳዮች ላይ መለያየት የሚያቆራርጥ አይደለም!!

ይሄ ነጥብ ለማጉላት ያክል እንጂ ካለፉት ነጥቦች ውስጥ የሚገኝ ነው። ከዑለማዎች ውስጥ አንዱ "ሱና ነው" ያለውን ሌላው "ቢድዐ ነው" ሲለው፣ አንዱ የፈቀደውን ሌላው ሲከለክለው ያጋጥማል። የአራቱ የፊቅህ መዝሀቦች መለያየት የዚህ ውጤት እንጂ ሌላ አይደለም። በመካከላቸው እጅግ በርካታ የሚለያዩባቸው ርእሰ-ጉዳዮች ከመኖራቸውም ጋር በተለይም ቀደምቶቹ በነዚህ የኢጅቲሃድ ልዩነቶች ሳቢያ አልተናቆሩም። አንዱ መዝሀብ *"ይህን ያደረገ ሶላቱ ውድቅ ነው"* ሲል ሌላው *"ችግር የለውም"* ይላል። አንዱ ከባድ ነጃሳ ያደረገውን ነገር ሌላው ከነጃሳም አይቆጥረውም። ከመሆኑም ጋር ግን አንዱ ሌላውን እየተከተለ ሰግዷል። በርግጠኝነት ከማህበርና ከሱሪ ርእስ የሚልቁ በርካታ ልዩነቶች በመዝሀቦች መካከል ይገኛሉ። ነገር ግን በተለያዩ ወቅቶች በጠባቦች ከተከሰቱ ልዩነቶች ውጭ በተለይም ታላላቆቹ በመካከል ያሉትን ልዩነቶች ለብጥብጥና ለፊትና አላዋሏቸውም። የአራቱ መዝሀቦች ተከታዮች በመካከላቸው ባሉ ልዩነቶች ሳቢያ ቢናቆሩ ኖሮ ምን እንደሚከሰት አስቡት። በሶሐቦችም መካከል ቀላል የማይባሉ የኢጅቲሃድ ልዩነቶች ተመዝግበዋል።

ከዘመናችን ዑለማዎችም ዘንድ በርካታ የኢጅቲሃድ ልዩነቶች ተከስተዋል። በርካቶች ኢጅማዕ ቢሞግቱም ሸይኹል አልባኒ ለሴቶች ክብ ወይም ቀለበታማ ቅርፅ ያላቸውን ወርቆች መጠቀም ሐራም እንደሆነ በጥብቅ ተከራክረዋል። ከዘመናችን ብዙዎቹ የሱና ዑለማዎች በተለየ ለሴት ፊትን መሸፈን ግዴታ እንዳልሆነ በፅኑ ተሟግተዋል። ግና አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙ ጠንካራ ቃላት ቢኖሩም የሀሳብ ልዩነታቸውን መነሻ በማድረግ አንዳቸው ሌላውን ከሱና  እስከ ማስወጣት ግን አልደረሱም።

ልክ እንዲሁ ከሩኩዕ መልስ ስንቆም እጅን ደረት ላይ ማድረግን አልባኒ *"ጥመት የሆነ ቢድዐ ነው"* ሲሉት እነ ኢብኑ ባዝና ኢብኑል ዑሠይሚን ደግሞ እንኳን ቢድዐ ሊሆን እንዲያውም *"ሱና ነው"* ይላሉ። ይሁን እንጂ *"ቢድዐ ነው"* ያሉት አልባኒ እነ ኢብኑ ባዝን *"ወደ ቢድዐ ተጣርታችኋል፣ ሙብተዲዖች ናችሁ"* አላሉም። እነ ኢብኑ ባዝ ደግሞ *"እንዴት ሱናውን ቢድዐ ትላለህ? አንተ እራስህ ሙብተዲዕ ነህ!!"* አላሉም። ይልቁንም አንዳቸው ሌላቸውን እያወደሱ ነው የሞቱት፣ ሁሉንም አላህ ይማራቸውና።

ተራዊሕ ላይ ከአስራ አንድ በላይ መጨመርን በተወሰኑ ዐሊሞች ቢድዐ እንደሆነ ሲገለፅ ሌሎች ደግሞ ለመፈቀዱ ኢጅማዕ እንዳለበት ሁሉ ጠቅሰዋል። እንዲህ አይነት በዑለማዎች ተቃራኒ ብይን የተሰጠባቸው ብዙ ምሳሌዎችን መዘርዘር ይቻላል። በእንዲህ አይነት ርእሰ-ጉዳዮች ማንንም ቢሆን የተለየ ሀሳብ ስላንፀባረቀ በሙብተዲዕነት መፈረጅ የራስን ጥራዝ-ነጠቅነት የሚያጋልጥ ውሳኔ ነው። እንጂማ ነብዩ ﷺ በኢጅቲሃዱ የተሳሳተን *"አንድ አጅር አለው"* እያሉ እንዴት በጥመት ልትገልፅ ድፍረቱ ይኖርሃል?!

በርግጥ እነዚህ ነጥቦች <u>እንደምናይበት አንግል</u> ከማህበር ወይም ከሱሪ ጉዳይ የከበዱ ወይም የቀለሉ ወይም ተቀራራቢ ሊሆኑ ይችላሉ። ዋናው የፈለግኩት ነጥብ ማወዳደር ሳይሆን አንድ ሙጅተሂድ አንድን ጉዳይ “ቢድዐ ነው” ማለቱ በዚያ ላይ ያልተጋሩትን ሁሉ በሙብተዲዕነት እንዲፈርጅ ወይም ሌሎች ተከትለውት እንዲፈርጁ በቂ ምክንያት እንደማይሆን ማሳየት ነው።

ዑለማዎች ከጥንት እስከ ዛሬ በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያዩ ቦታዎች፣ በተለያዩ የኢጅቲሃድ ርእሶች ላይ የተለያዩ ሀሳቦችን አንፀባርቀዋል። ማህበር ወይም ሱሪ በዚህ ረገድ የመጀመሪያም የተለዩም አይደሉምና እነሱን የሚመለከት ከሌሎች ርእሶች የተለየ ብይንም መርህም አይኖርም። ውዝግብ በሚንፀባረቅባቸው የኢጅቲሃድ ርእሶች ሳቢያ የመረረ መለያየት ቢኖር ኖሮ በሌሎች የኢጅቲሃድ ርእሶች ሳቢያም መለያየት በተከተለ ነበር። እናም በኢጅቲሃዳዊ ርእሶች ላይ መተላለፍ ከጥንት እስከዛሬ ዑለማዎች የተጓዙበት ጠንካራ መሰረት ነው። ዛሬ ለማህበርና ለሱሪ ሲባል መሰረቱ አይናድም። ሸይኽ ኢብኑል ዑሠይሚን ረሒመሁላህ *“በዑለማዎች መካከል በሚገኙ አወዛጋቢ ጉዳዮች ላይ ተፃራሪን መቃወም የሚቻለው መቼ ነው?”* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ ነበር የመለሱት፡-

*“አወዛጋቢ ነጥቦች ሁለት አይነት ናቸው።*

***የመጀመሪያው አይነት፡-*** *በጉዳዩ ላይ ያለው ማስረጃ ግልፅ በመሆኑ ኢጅቲሃድ የማይፈቀድበት አይነት ነው። ይሄኛው ተፃራሪው ግልፅ መረጃን ስለተፃረረ የሚተችበት ነው። ይህም ፂምን እንደመላጨት፣ ልብስን ከቁርጭምጭሚት በታች እንደማስረዘም፣ በአላህ ዲን ውስጥ እንደመለያየትና ሌሎችንም የሚመስል ነው።* ***<u>ነገር ግን ይሄም ቢሆን ለመሰዳደብ፣ ለመጠላላት መዳረሻ ሊደረግ አይገባም።</u>*** *በተለይም ደግሞ*

*ተፃራሪው መልካም እሳቤ እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን። **ይልቁንም ነገሮች ስምምነት እስከሚመጣ ድረስ በጥበብ ሊታከሙ ይገባል።***

***ሁለተኛው (የውዝግብ) አይነት፡-** መረጃው ግልፅ የማይሆንበት ነው። ይህም የሚሆነው ወይ የመረጃው መፅናት ወይ አመላካችነቱ ስውር በመሆኑ ወይ ከልካይ ብዥታ በመኖሩ ወይ ደግሞ በሌላ ምክንያት ነው። **ይሄ ተፃራሪው አይተችበትም። ምክንያቱም የተወዛጋቢዎቹ ንግግር የአንዱ በአንዱ ላይ መረጃ መሆን አይችልምና።** የዚህ ምሳሌዎች ብዙ ናቸው።"* [ኪታቡል ዒልም፡ 197-198]

አንተ የዲንህ ጉዳይ የሚያሳስብህ ወንድሜ ሆይ! አንቺ ለሱና ተቆርቋሪ የሆንሽ እህቴ ሆይ! በሌሎች ላይ የምንመለከታቸውን ስህተቶች በተመለከተ ለትችት ጣታችንን ከመሰንዘራችን በፊት አቅሙ ካለን "ጥፋቶቹ" የእውነት ጥፋት መሆናቸውን በመረጃ እናረጋግጥ። ጥፋቶች እንደሆኑ ካረጋገጥን ደግሞ ከላይ ኢብኑል ዑሠይሚን ከጠቀሷቸው ሁለቱ መደቦች ውስጥ ከየትኛው መደብ ውስጥ እንደሚያርፉ ከስሜት ነፃ ሆነን እንፈትሽ። እስኪ ወንድምና እህቶች ሆይ! ለንትርክ ያበቁንን እነዚህ የማህበርና የሱሪ ርእሶች በተመለከተ ሐቁ ከየትኛው ወገን ነው? የሌላኛውን ወገን አቋም እንደ ስህተት ካሰብነውስ "ስህተቱ" ከላይ ከቀረቡት ሁለት የኺላፍ መደቦች ውስጥ ከየትኛው ውስጥ ነው የሚያርፈው? እኛስ ጉዳዩን እያስተናገድነው ያለው ጤናማ በሆነ መልኩ ነው ወይ? ረጋ ብለን እናስተውል።

ወንድም እህቶች!! ማህበርን ከአንድ ወይም ከሁለት በስተቀር ሁሉም ታላላቅ ዐሊሞች ፈቅደውታል። ወንድሞቻችን *"ለምን እነዚህን የሚፈቅዱ ታላላቅ ዐሊሞች ጀምዒዮች፣ ሙብተዲዖች ናቸው አትሉም?"* ሲባሉ *"እነሱ*

*ሙጅተሂዶች ናቸው። ኢጅቲሃድ አድርገው ተሳስተዋል"* እያሉ ነው። የሰላሳና የአርባ ዐሊሞችን ኢጅቲሃድ የመንደር ጎረምሳ ሲሸረው ተመልከቱ። እሺ "ሁሉም ተሳስተዋል" የሚለውን ሙግታችሁን ለአፍታ እንቀበላችሁ። የኢጅቲሃድ ርእስ መሆኑን ማመናችሁ በራሱ ትልቅ ነገር ነው። ታዲያ ኢጅቲሃድ በሚያስተናግድ ብዙሃን ዑለማዎች በሚፈቅዱት ርእስ ምክንያት መበጥበጥ ለምን? ለምንስ የማይጋራችሁን ሁሉ "ጀምዒይ" እያላችሁ ታስበረግጋላችሁ? በኢጅቲሃድ ርእስ የተለየ ሀሳብ ያንፀባረቀ ሁሉ በዚያ ሊሰየም ይገባዋል ማለት ነው? ስለዚህ ሱሪ የሚፈቅደውን ዐሊም "ቢንጣሊይ"፣ ለአስገዳጅ ምክንያት ገንዘብ በሪባ ባንክ ማስቀመጥን የሚፈቅደውን "ሪበዊይ"፣ ማህበር የሚፈቅደውን "ጀምዒይ" ማለት ይቻላል ማለት ነውን?! ልክ እንዲሁ በኢጅቲሃድ ርእሶች "ተሳስቷል" ብለን የምናምነውን ሁሉ ከዚያ እየፈለቀቅን የምናብጠለጥልበት ስም መለጠፍ ይፈቀድልናልን?! እውን ይሄ የአህሉ ሱና አካሄድ ነውን?

ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *"በተለይም የመልእክተኛው ﷺ ተከታዮች የሆኑት የሱና ሰዎች ሐቅን ይከተላሉ። **<u>በኢጅቲሃድ ሳቢያ የተፃረራቸውን ደግሞ ያዝኑለታል። አላህና መልእክተኛው ዑዝር ሰጥተውታልና</u>**። የቢድዐ ሰዎች ግን ከንቱ የሆነ ቢድዐ ይፈጥሩና በዚያ ላይ የተፃረራቸውን ያከፍራሉ።"* [ሸርሑል አስፈሃኒያህ፡ 30]

ኢማሙ ዘሀቢን አላህ ይማራቸውና እንዲህ ይላሉ፡-

***<u>"አንድ ኢማም በነጠላ ጉዳዮች የሚማርበት የሆነን ስህተት በኢጅቲሃዱ በተሳሳተ ቁጥር ተነስተን በቢድዐ የምንፈርጀውና የምናኮርፈው ከሆነ ከኛ ጋር ኢብኑ ነስር አይተርፉም፣ ኢብኑ መንዳህም አይተርፉም። ኧረ</u>***

***<u>ከነሱ የበለጠም አይተርፍም።</u>*** *ፍጡርን ወደ ሐቅ የሚመራው አላህ ነው። እሱ ከአዛኞች ሁሉ አዛኝ ነው። <u>ከስሜትና ከክፉ አመል በአላህ እንጠበቃለን።</u>"* [አሲየር፡ 14/39-40]

አሁንም ዘሀቢ እንዲህ ይላሉ፡- *"ኢማሙ ተክክለኛ፣ ሐቅን ለመከተል የሚያልም የሆነን ሁሉ* ***<u>በኢጅቲሃዱ በተሳሳተ ቁጥር</u>*** *ጊደል የምንከተውና* ***<u>በቢድዐ የምንፈርጀው ከሆነ</u>*** *ከአኢማዎች ውስጥ የሚተርፍልን በቀለለ ነበር።"* [አሲየር፡ 14/376]

እንኳን እንደ ማህበር ያለ ብዙሃን ዑለማዎች የሚደግፉት ጉዳይ ይቅርና፣ እንኳን እንደ ሱሪ ያለ የፊቅህ ርእስ ይቅርና አንድ መሰረቱ ሱኒ የሆነና በሱና የሚታወቅ ሰው ተራ ጥፋት ሳይሆን **<u>የሚንሃጅ ክፍተት ወይም ጥፋት ብናገኝበት እንኳን በዚያ መነሻ ከሱና ልናስወጣው አይፈቀድልንም።</u>** ሸይኹል አልባኒ፡-

*"አንድ መሰረቱ የአህሉ ሱና መሰረት የሆነ፣ በዚያም ላይ የሚጓዝ የሆነ፣ ከሱና ሰዎች በመከላከልና መንገዳቸውን በማገልገልም የሚታወቅ የሆነ ሰው* ***<u>አልፎ አልፎ አንዳንድ የሚንሃጅ ስህተቶች ቢንፀባረቁበት፡ (1)</u>*** *ከሱ ማስጠንቀቅ ነው የሚገባው? ወይስ (2) ስህተቶቹን ግልፅ ማድረግ ነው የሚገባው?"* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ነበር የመለሱት፡- ***<u>"መልሱ ሁለተኛው ነው እንጂ የመጀመሪያው አይደለም።"</u>*** (ስህተቶቹ ግልፅ ይደረጋሉ እንጂ ከሱ ማስጠንቀቅ አይገባም።) [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር ካሴት ቁ. 751]

የቀረበውን ጥያቄና የሸይኹን መልስ በሚገባ እናስተውል። ከዚያም እኛ ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታ እናገናዝብ። ለሙግት ያክል *"ማህበር መመስረት ክልክል ነው"* የሚለው ከጥቂትም በሚያንሱ ዐሊሞች የተንፀባረቀው አቋም

ልክ ነው እንበል። ከዚህም አልፈን *“ማህበርን መፍቀድ የሚንሃጅ ችግር ነው”* የሚለውን ለሙግት ያክል ልክ እንደሆነ እናስብ። ከላይ የቀረበውን የሸይኽ አልባኒን ፈትዋ ብንወስድ የሚጠበቅብን ይህን “የሚንሃጅ ስህተት” ያየንበትን ሰው ስህተቱን ግልፅ ማድረግ እንጂ “ጀምዒይ” “ሒዝቢይ” እያሉ ከሰውየው ማስበርገግ አይደለም። ይሄ እንግዲህ ማህበርን የሚፈቅዱትን የብዙሃን ዑለማዎች ፈትዋ እንደ ስህተት ከቆጠርን፣ አልፈንም የሚንሃጅ ስህተት አድርገን ካሰብነው ነው።

የአንድ ጉዳይ ክልክልነት ለኔ ወይም ላንተ ፍንትው ብሎ መታየቱ በሌሎች ላይ ለመፍረድ በቂ ምክንያት አይሆነንም። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*“ከኣኢማዎች (ከሱና ምሁራን) ውስጥ* ***ሊከተሉት የማይገባ የሆነ ንግግር ወይም ድርጊት የሌለው አንድም የለም!! በዚህ ሳቢያ የማይወገዙ ከመሆኑም ጋር።*** *ከቁርኣንና ከሱና ጋር መፃረራቸው ቁርጥ ባለ መልኩ ያልታወቁ ይልቁንም የእውቀትና የኢማን ሰዎች የተጨቃጨቁባቸው* ***የኢጅቲሃድ ርእሶች*** *የሆኑ ንግግሮችና ተግባራት ይኖራሉ።* ***እነዚህ ነገሮች አንዳንድ አላህ ሐቁን የገለጠለት ሰው ዘንድ ቁርጥ ያሉ እውነታ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ለሱ ግልፅ በሆነለት ለሌሎች ግን ባልተገለፀ ነገር ሰዎችን ሊያስገድድ አይገባውም።”*** [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 10/383-384]

ሸይኹል አልባኒም ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*“ያለ ጥርጥር ከፊሎቹ ንፁህ በሆነና ባለቤቱ የሚመነዳበት በሆነ ኢጅቲሃድ ሳቢያ* ***ቢድዐ*** *ላይ ወድቀዋል። ግና ይሄ የዚያን ዐሊም ደረጃ*

*ምንም አይጎዳውም። ልክ እንዲሁ አላህ ሐራም ያደረገውን ሐላል በማድረግና በተቃራኒውም (ሐላሉን ሐራም በማድረግ) ላይ ሙሉ ለሙሉ የወደቁ አሉ። ይሄ የሆነው የተዳዘበትን አቋም የሚፃረር ሸሪዐዊ ማስረጃ ባለማግኘታቸው ወይም ደግሞ ቢያገኙትም አንድ አጅር በሚያገኙበት (የተሳሳተ ኢጅቲሃድ) በመረዳታቸው ነው። ስለዚህም* ***<u>ጉዳዩ በቢድዐዎቹ ብዛት አይደለም የሚለካው።</u>*** *ይልቁንም የተገለጠልን ይሄ ዐሊም ቢድዐ ላይ ሲወድቅ ጊዜ መረጃው ቀርቦለት ለራሱ እይታ ጭፍንነትና መረጃን አለመቀበል ከተንፀባረቀበት ይሄ ነው ቢድዐው የሚጎዳው።"* [ሱኣላቱል አልባኒ፡ 181]

## 5. "ሙብተዲዕን ሙብተዲዕ ያላለ ሙብተዲዕ ነው" የሚል ኢልዛም አደጋ ሊያስከትል ይችላል!!

በዚህ ዘመን በግልፅ ከሚታዩ ፈተናዎች ውስጥ አንዱ ልጓም አልባ የተብዲዕ ዘመቻ ነው። የሆነ አካል አንድን በሱና የሚታወቅ ሰው በቢድዐ ይፈርጃል። ፈራጁ አካል ዐሊም ሊሆን ይችላል። በብይኑም ልክ ሊሆን እንደሚችል ሁሉ ሰው ነውና ሊሳሳትም ይችላል። ነገር ግን ዛሬ እየታየ ያለው ሁለት ፅንፍ ነው። አንዱ ለዑለማዎች ብይን ፍፁም ቦታ የማይሰጥ በደካማ ጭንቅላቱ ላይ የሚንጠለጠል አጉል ኩፍስ ሲሆን ሌላው ደግሞ የዑለማዎችን ንግግር ልክ እንደ ፈጣሪ ቃል ወይም እንደ መልእክተኛው ﷺ ቃል መፈተኛ አድርጎ የሚያቀርብ ነው። ሐቁ ያለው ከሁለቱ ፅንፍ መሀል ነው። በርግጥ ሙብተዲዕን ሙብተዲዕ ያላለ ሰው እራሱም በቢድዐ እንደሚፈረጅ ከአንዳንድ አኢማዎች የተላለፈ መርህ ነው። ነገር ግን ይሄ መርህ ያለ ልጓም እንዲሁ የሚለቀቅ አይደለም።

ግና ከራሳቸው ጠባብ ስብስብ ውጭ ያለውን ማህበረሰብ በጅምላ እንደሚያከፍሩት ተክፊሮች፣ በጅምላ በቢድዐ የሚፈርጁ ደፋሮችም እዚህም እዚያም እያቆጠቆጡ ነው። ሸይኽ ዐብዱሰላም ቡርጂስ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*“በዚህ ዘመን እራሳቸውን ወደሰለፊያ ከሚያስጠጉት ውስጥ ሰዎችን በቢድዐ በመፈረጅ ላይ ድንበር በሚያልፉ ሰዎች ተፈትነናል። ነገሩ ማህበረሰቡን ባጠቃላይ በጅምላ በቢድዐ መፈረጅ እስከሚደርስ ድረስ። ከነሱ ውጭ ያለ መሰረቱ ቢድዐ ነው፣ ነገራቸውን እስከሚያረጋግጡ ድረስ። እነዚህ ሸሪዐን የማያውቁ መሀይማን ናቸው። በቢድዐዎችና በባለቤቶቻቸው ላይ ዑለማዎች የተናገሩትንም የማያውቁ ናቸው። ስለሆነም ንግግራቸው ቦታም አይሰጠውም። እንዲያውም ክብደት የሌለው ትቢያ ነው።”* [ቡሑሡ ነድወቲ አሡሪል ቁርኣኒል ከሪም ፊ ተሕቂቂል ወሰጢያ፡ 218]

ከራሱ ስብስብ ውጭ ያለውን ተራውን ህዝብ ጭምር በሙሉ ከሱና ውጭ እንደሆነ የሚያስብ ሰው ምን አይነት አደጋ ውስጥ እንዳለ አስቡት። ከዚህም ዝቅ ብለን አንድ ተግባራዊ ምሳሌ እንውሰድ። ለምሳሌ እያንዳንዱ የኢኽዋን አልሙስሊሚን ቡድን ውስጥ የሚገኝን ሰው ከሱና ማስወጣት ይቻላልን? እሱን “ሙብተዲዕ” ያላለስ ሙብተዲዕ ይሆናልን? አንተ ጋር ያለውን ግንዛቤ በውስጥህ ያዝና የሸይኽ ሙቅቢልን መልስ አብረን እንመልከት፡-

*“አልኢኽዋን አልሙስሊሙን አካሄዳቸው የአህሉ ሱና አካሄድ አይደለም። ከውስጣቸው ያሉ የተምታታባቸው ሰዎችን ግን*

*በእያንዳንዱ ላይ ሱኒ አይደለም ብለን ልንበይን አይቻለንም። ባይሆን ሱኒይነቱ የተናጋ ነው። … ተምታቶበት ይህን ጉዳይ በሚገባ የማያውቅን 'ሱኒ አይደለም' ልንል አንችልም።"* [ፈዷኢሕ ወነሷኢሕ፡ 123-127]

በሌላ ፈትዋቸውም ላይ እንዲህ ብለዋል፡-

*"የኢኽዋን አልሙስሊሚን፣ የተብሊግና የቁጥቢያ ቡድኖችን በተመለከተ በላጩ በሚጓዙበት መንገድ ላይ ብይን መስጠት ነው። መንገዳቸው የአህሉ ሱና ወልጀማዐ መንገድ አይደለም። በተናጠል ሰዎቻቸውን በተመለከተ ግን ከፊሉ ሰው ተምታቶበት እንጂ ሰለፊ ይሆናል። የአላህን ዲን በመርዳት በሚል በር ይመጡበትና አብሯቸው ይሄዳል። ያሉበትን አያውቅም። ስለሆነም ድብልቅ ስለሆኑ ጥቅል በሆነ መልኩ ሊበየንባቸው አይቻልም።"* [አስኢላ ሚን መዲነቲ ጣኢፍ]

ይህን እውነታ በጥንቃቄ እናስተውል። አካሄዳችን ሁሌም ልጓም ይኑረው። ከዚህም ባለፈ አንዳንዴ አንድ ዐሊም ሌላውን "ሙብተዲዕ ነው" ቢልና ሌሎች ዐሊሞች በዚህ ላይ የተለየ ሀሳብ ቢያንፀባርቁ ማንን እንከተል? መለየት ከቻልን ከሐቁ ልንሆን ይገባል። ሐቁ የት እንዳለ በማንለይበት ሁኔታስ? መርሁ የሚለው *"የተተነተነ ሂስ ከጥቅል ሊድናቆት ቅድሚያ ይሰጠዋል"* ነው። ስለዚህ አንድ ዐሊም ግልፅ በሆነ መልኩ፣ ለተብዲዕ በቂ የሆነ ጥፋት፣ አስተማማኝ በሆነ መልኩ በሆነ አካል ላይ ሂስ ቢያቀርብ የአድናቂዎች አድናቆት ሰውየውን ከመውደቅ አያተርፈውም። ግና የሚቀርበው ሂስ ሌሎች ዘንድ ግልፅ ካልሆነ፣ ወይም ደግሞ አስተማማኝ መረጃ ካልቀረበበት፣ ወይም ደግሞ ጥፋቱ ኖሮም ለተበዲዕ በቂ ካልሆነ ግን ሂሱን መቀበል አይገባም ወይም ግዴታ አይሆንም። በነዚህ ወይም ደግሞ በሌሎች

ምክንያቶች ሌላው ዐሊም ከተሀየሰው አካል ሊከላከል ይችላል። ያንኛውን ዐሊም የሚከተሉ ሊኖሩ እንደሚችሉት ሁሉ ይሄኛውንም የሚከተሉ ሊያጋጥሙ ይችላሉ።

እንዲህ አይነት የተለያዩ የዑለማእ ውሳኔዎች ቢያጋጠሙን የአንዱን ዐሊም አቋም እንዲከተሉ ሌሎችን ማስገደድ ይቻላል? በጭራሽ!! የሂስና የሙገሳ ዘርፍ በራሱ የኢጅቲሃድ ርእስ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። ለዚህም ነው ከሰለፎች ጀምሮ በተመሳሳይ ሰው ላይ የተለያዩ ብይኖች የሚያጋጥሙት። ሸይኽ ሙቅቢል ረሒመሁላህ *“በሂስና ሙገሳ (ጀርሕ ወተዕዲል) ዘርፍ ላይ በሸይኽ ረቢዕ የሂስ ፅሁፎች ላይ እንዲሁም በሚጓዙበት መንገድ ላይ ይስማማሉ ወይስ ይቃረናሉ? ሸይኽ ኢብኑ ባዝ፣ ኢብኑ ዑሠይሚንና አልባኒ እንደሚጋሯቸውስ ያውቃሉን?”* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡-

> *“የሱና ሰዎች የሚቀዱበት ምንጫቸው አንድ ነው። እሱም የአላህ ኪታብና የመልእክተኛው ﷺ ሱና ነው። በሁሉም ኢስላማዊ ሃገራት ዐቂዳቸውም አንድ፣ መንገዳቸውም አንድ ነው። አዎ እኛ የቢድዐ ሰዎችንና ቡድንተኞችን በመሀየስ ላይ እንስማማለን። በዚህ ላይ እንስማማለን። <u>**የሚቀረው፡ አንዱ ዘንድ የተተቹ ሌላኛው ዘንድ ግን ያልተተቹ የሆኑ ሰዎች ጉዳይ ነው። ይሄ በሰለፎችም ዘመን ተከስቷል። ምናልባትም አንዱን ዘጋቢ አሕመድ ኢብኑ ሐንበል ‘ታማኝ ነው’ ብሎት የሕያ ኢብኑ መዒን ግን ‘ውሸታም ነው’ ያለው ወይም በተቃራኒው የሆነ ስንት ዘጋቢ ያጋጥማል።**</u> ቡኻሪ፣ አቡ ዙርዐና አቡ ሓቲም ዘንድም ተመሳሳይ ነገር ያጋጥማል። ቁም ነገሩ <u>ከፊላቸው ከፊሉን በጭፍን አይከተሉም። በአንድ ሰው ታማኝነት ወይም</u>*

***<u>ብልሹነት ላይ ብንለያይ ይሄ ማለት ዐቂዳ ላይ ተለያይተናል ማለት አይደለም። በአካሄድ ላይ ተለያይተናል ማለት አይደለም።</u>***

*'ሸይኽ ኢብኑ ባዝና አልባኒ ይጋሩታል ወይስ ይቃረኑታል?' ስለተባለው ጉዳዩ እኔ የሸይኽ ረቢዕን ኪታቦች በብዛት አላነበብኩም። ይሄ አንድ ነገር ነው። እንደገና ሌላው ነገር እንዲልነው* ***<u>የሱና ሰዎች ከፊሉ ከፊሉን በጭፍን አይከተሉም። ምንም ይሁን ምን ሁላችንም እናገኛለን፣ እንሰታለን። እንዘነጋለን፣ እናውቃለን።</u>*** *ወላሁል ሙስተዓን።"* [አዱረር ፊ አጅዊበቲ ዐበስ ወሸፈር፣ ካሴት]

ዛሬ ሰዎችን ከአንድ ወይም ከሁለት ዐሊም ጀርባ ለማሰለፍ አጉል የሚለፉ ሰዎችን ድካም በነዚህ የዑለማዎች አካሄድ እያበራን እንመልከታቸው። እንታዘባቸውም። ሸይኽ ሙሐመድ ረሺድ ሪዷ ከህቡኡ የአይሁድ ድርጅት "ማሱኒያ" ውስጥ አባል በመሆናቸው ሳቢያ ሸይኽ ሙቅቢል በሙብተዲዕነት ፈርጀዋቸዋል። ሸይኽ አልባኒ ግን ይህንን የሙቅቢል ውሳኔ እንዲህ ሲሉ በብርቱው ነቅፈዋል፡-

*"እኛ ያለጥርጥር ወደየትኛውም ቡድን መታቀፍን አንደግፍም። በተለይም ደግሞ ከሸሪዐ በመስፈንጠር የሚታወቁ ከሆኑት ጋር።* ***<u>ነገር ግን እኛ ጉዳዩ ኢጅቲሃድ የሚቀበል እንደሆነ ነው የምንረዳው።</u>*** *እኔ ክቡር ረሺድ ሪዷ ኢስላምን የላቀ የሆነ ማገልገልን እንዳገለገለ አስባለሁ። ከማሱኒያ ውስጥ መታቀፉ በተሳሳተ ኢጅቲሃድ ምክንያት እንደሆነ እንጂ ኢድለ-ቢሶች እንደሚያደርጉት ለግላዊ ጥቅሙ እንዳልሆነ እናስባለን። ስለሆነም ከሱ ስህተትና ጥመት ስለተንፀባረቀ እሱን ወደ ጥመት ማስጠጋት ይሄ ሊሰነዘሩት የማይገባ የማይመሰገን እርምጃ ነው። (በተለይም) ይህን በመሰለ እንደኔ እምነት በዚህ ዘመን*

*በብዙ የሱና ሰዎች ላይ ውለታ ባለው ሰው ላይ። ... በዚህም ምክንያት **<u>ይሄ ከወንድማችን ከሙቅቢል አምሳያ ሊወጣ የማይገባው ድንበር ማለፍ ያለበት ንግግር እንደሆነ ይታየኛል።”</u>*** [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 42]

እዚህ ላይ በግልፅ እንደሚታየው ሸይኽ ረሺድ ሪዷ ላይ ተጨባጭ ጥፋት ተገኝቷል። በዚህም ሳቢያ ሸይኽ ሙቅቢል በጥመት ወርፈዋቸዋል። ሂሱ ግልፅና የተተነተነ ነው። አልባኒ ግን እንኳን የሙቅቢልን ብይን ሊቀበሉ ጭራሽ ውሳኔያቸው ድንበር ማለፍ እንዳለበት በመግለፅ ነው ጠንከር አድርገው የሀየሷቸው። አልባኒን *“ከሙብተዲዕ የተከላከለ ሙብተዲዕ ነው”* የሚል መርህ በመጠቀም ከሱና ሊያስወጣቸው የሚዳፈር ይኖራል? ምናልባት አልባኒ የረሺድ ሪዷን ችግር “ስላላወቁ ነው” እንዳይባል እራሳቸው ገልፀውታል። ከዚህ ምን እንማራለን?!

ስለዚህ የሱና ዑለማዎች አንዱ በሌላው ላይ ተብዲዕ የደረሰ ሂስ ቢሰነዝሩ አንድ ሰው *“ግራ ቀኝ ሳልመለከት፣ የሌሎችንም ሀሳብ ሳላይ አንዱን በጭፍን ተከትየ ሌላውን ከሱና አላስወጣም”* ቢል ይደነቃል እንጂ አይወቀስም። በሀሳብ ስላልተጋራው ብቻ አልፎ ተብዲዕ አደርጋለሁ የሚል ካለ ግን እራሱን እንጂ ማንንም አይጎዳም። ሸይኹል አልባኒ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

*“አንድ ሰው መረጃ አድርሶ አንድ ሰው ቢያከፍር ሰዎች ሁሉ ያንን ሰው በማክፈር ላይ አብረውት ሊሆኑ በምንም መልኩ ሸርጥ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም በተሳሳተ ድምዳሜ ሊሆን ይችላል እዚህ ላይ የደረሰው። ሌላኛው ዐሊም ሊያከፍሩት እንደማይገባ ሊያስብ ይችላል።*

*<u>'እከሌ አመፀኛ ነው' ወይም 'ሙብተዲዕ ነው' በማለት ላይም እንዲሁ ነው።</u> ይሄ እውነታ ከዘመናችን ፈተናዎችና ዲልምን በመሞገት ላይ አንዳንድ ወጣቶች ዘንድ ከሚታይ መቻኮልም ነው። የሚፈለገው እንዲህ አይነቱ ሰንሰለታማ ብይን፣ ይህ (የአንዱን ውሳኔ እንዲከተሉ ሰዎችን) ማስገደድ በጭራሽ አሳሪ አይደለም። ይሄ ሰፊ ርእስ ነው። አንድ ዐሊም ጉዳዩን ግዴታ እንደሆነ ሲያይ ሌላው በተለየ መልኩ ሊያየው ይችላል። ዑለማዎች ፊትም ኋላም የተወዛገቡት የኢጅቲሃድ ርእስ ስለሆነ ነው። ሌሎች የሱን ሀሳብ ሊይዙ አይገደዱም።"* [ሲልሲለቱል ሁዳ ወኑር፡ 778]

ብዙ ጊዜ እነዚህ ሰዎችን እንዳለ ከአንድ ዐሊም ኋላ ማሰለፍ የሚሹ ሰዎች የሌሎች ዑለማዎችን ንግግሮች በተልካሻ ምክንያቶች ዋጋ ያሳጣሉ። በዑለማዎች መካከል ውዝግብ ያለባቸው ርእሶች ቢያጋጥሙን የአንዱን ዐሊም ምርጫ *"ካልተከተላችሁ"* የሚል ሽብር በሰዎች ላይ መንዛት አደገኛ ነው። ዛሬ ግን በቀጥታ *"እከሌን ካልተከተላችሁ"* ባይሉም የሚያከብሩትን ሰው ያማከለ ወላእና በራእ የሚያደርጉ ሰዎች ግን ያጋጥማሉ። ያ ሸይኽ የተናገረውን እንደወረደ መውሰድ፣ ንግግሩን ያልተቀበለን ወይም እሱን የነካን ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ከሱና ጠራርጎ ማስወጣት ድረስ የሚቃጣቸው ሰዎች ያጋጥማሉ። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ ***"በተራ ሰዎች ላይ 'እከሌን ወይም እከሌን በጭፍን መከተል ግዴታ ነው' እያለ የሚናገረውን በተመለከተ ይሄ ሙስሊም የሆነ ሰው የሚናገረው አይደለም"*** ይላሉ። [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 22/249]

ስለዚህ ከትልልቅ የሱና ዐሊሞች ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ አንዳንዴ ወጣ ያለ ትችት ቢሰነዝር ያንን ተከትለን ማለቂያ የሌለው ፊትና ውስጥ

ከመግባት እንቆጠብ። ሺ ጊዜ ብንወደው ማንንም የሐቅ መለኪያ ልናደርግ አይፈቀድልንም። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *"ከአላህ መልእክተኛ ﷺ ውጭ ከሰዎች የትኛውንም ሰው መድቦ እሱን የወደደና ከሱ የተስማማ ከአህሉ ሱና ወልጀማዐ፣ እሱን የተፃረረ ደግሞ ከቢድዐና የልዩነት ሰዎች የሚያደርግ ካለ ... **ይሄ ከቢድዐ፣ ከጥመትና ከልዩነት ሰዎች ሆኗል።"*** [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 3/347] ይሄ የተወሰኑ ግለሰቦችን መለኪያ አድርጎ የመመደብ አካሄድን ሸይኽ ሷሊሕ አሱሐይሚ *"እውነት ለመናገር ይሄ በአንድ ጎዳና ላይ የሚገኙ ሰዎችን እስከሚለያዩ፣ እስከሚቦዳደኑና እስከሚወዛገቡ ያደረሰ ጠባብ የሆነ የቡድንተኛ መንገድ ነው"* ሲሉ ይገልፁታል። [ተንቢሁ ዘዊል አፍሃም፡ 17]

እንዲያውም ግልፅ ቁርኣናዊ ወይም ሐዲሣዊ መረጃዎች ባሉበት ሁኔታ የፈለገ ቢልቁ "እከሌ እንዲህ አሉ" "እከሌ እንዲህ አሉ" ውስጥ አትግባ። ይልቁንም የሚቀድመውን አስቀድም። የላቀው ጌታ እንዲህ ይላል፡- ***"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ታዘዙ። መልእክተኛውንና ከናንተ የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ። በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልእክተኛው መልሱት። ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው።"*** [አኒሳእ፡ 59] ሁሌም ሊዘነጋ የማይገባው ነገር *"የዑለማእ ንግግሮች ለላቀው አላህና ለመልእክተኛው ﷺ ንግግሮች ተከታዮች ናቸው እንጂ የአላህና የመልእክተኛው ንግግሮች ለነሱ ንግግሮች ተከታዮች አይደሉም።"* [መጅሙዑ ፈታዋ፡ 7/35]

ይህን ንኡስ ርእስ በሸይኽ ፈውዛን ንግግር ልቋጭ። *"አንዳንድ ዱዓቶችን ተብዲዕ በማድረግ ሰዎችን የሚያስገድዱና ይህን መሰረት አድርገው*

*የሚወዳጁና የሚጠሉ፣ ተብዲዕ ያላደረገን የሚያኮርፉ ሰዎች ብይናቸው ምንድን ነው?"* ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ብለው ነበር የመለሱት፡- *"ይህን እንዳትይዝ። በዚህ ላይ እንዳትታዘዛቸው። 'እኔ ከዚህ የጠራሁ ነኝ። አላህ ከዚህ ጠባቂዬ ነው። በዚህ ውስጥ አልገባም። ስለዚህ ምንም አላውቅም' በል። "*[ደርሱ አተፍሲር ቢል ሐረም፡ ረጀብ 14/1433]

### 6. ሱኒ የሆነ አካል ቢያጠፋም ከስሜት ተከታዮች ጋር ተመሳሳይ የሆነ አያያዝ አይያዝም

አካሄዱ የአህሉ ሱና አካሄድ የሆነ ሰው ጥፋት ላይ ቢወድቅ የቢድዐ ሰዎችን በምናስተናግድበት መልኩ ልናስተናግደው አይገባም። ሸይኽ ሷሊሕ ኣሊ ሸይኽ ለዚህ መርህ ኢብኑ ኹዘይማን፣ ሲዲቅ ሐሰን ኻንን፣ ሸውካኒንና ሙሐመድ ኢብኑ ኢስማዒል አስሶንዓኒን እንደ ምሳሌ ያነሳሉ። እነዚህ ታላላቆች በቀላሉ የማይታዩ ጥፋቶች ላይ ቢወድቁም ነገር ግን በነበራቸው ጠንካራ የሱናና የተውሒድ አቋም እንዲሁም ለኡማው ባበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ ምክንያት ታላላቅ ዑለማዎች የስሜት ተከታዮችን ከሚያስተናግዱበት በተለየ ነው የተመለከቷቸው። ለምሳሌ ኢማም ኢብኑ ኹዘይማ ረሒመሁላህ በመረጃ እንደተረጋገጠው ለአላህ ሱራን ባለማፅደቃቸው ምክንያት ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ ከሙቶ ገፅ የበለጠ መልስ ፅፈውባቸዋል። ይህም ከመሆኑ ጋር የሱና ዑለማዎች ኢብኑ ኹዘይማን *"የአኢማዎች ኢማም"* እያሉ የሚያሞካሿቸው ከመሆናቸውም በላይ ማንም በክፉ እንዲያነሳቸውም አይፈልጉም። በዚህ ላይ የሸይኽ ሷሊሕ አሊ ሸይኽን ወሳኝ ማብራሪያ ቢመለከቱ ጥሩ ነው። [ሙሓዶራ፡ አልፈትዋ በይነ ሙሳየረቲል አህዋእ ወ ሙጧበቀቲ ሸርዕ]

ሸይኽ ዐብዱል ሙሕሲን አልዐባድ እንዲህ ይላሉ፡- *“ከአህሉ ሱና የሆነ ሰው ስህተት ካለበት ይመከራል። መልካም በሆነ መልኩም ይከራከሩታል። እንዲቀና፣ እንዲቀርብ፣ እንዳይርቅ፣ እንዳይወረወር ይጣርለታል።”* [ሸርሕ ሱነን አቢ ዳውድ፡ 1/2]

ስለዚህ *“ወንድምህ ቢንሸራተት በክብደትህ አትውረድበት። ይልቁንም የሚመለስበትን መንገድ መክፈትህ የጨዋ ስነ-ምግባር ነው። እንጂ አጣብቂኝ ውስጥ አታስገባው። ለማዋረድ፣ ክብርን ለመግፈፍ መጓጓት የፈሪዎች መታወቂያ ነው።”* [ሸይኽ ኗሊሕ ሲንዲ]

### 7. ለማንም ያለን ጥላቻ ሚዛናዊነታችንን አያሳጣን

ሚዛናዊነት ከሱና ሰዎች አንኳር መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ነው። የፈለገ በዳይ ቢሆኑ፣ ካፊሮች እንኳን ቢሆኑ በማንም ላይ ወሰን እንድናልፍ አልተፈቀደልንም። አንድየው እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَقَٰتِلُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ ٱلَّذِينَ يُقَٰتِلُونَكُمۡ وَلَا تَعۡتَدُوٓاْۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلۡمُعۡتَدِينَ ١٩٠ ﴾ البقرة: ١٩٠

*“እነዚያንም የሚጋደሏችሁን (ከሃዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሏቸው። ወሰንንም አትለፉ። አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።”* [አልበቀራህ፡ 190]

በካፊሮች ያውም በሚዋጉን ላይ በህግ ከተቀመጠው ውጭ ወሰን እንዳንተላለፍ ከተነገረን በሙስሊሞች ላይማ እንዴት ሊሆን ነው?!! ወላሂ እንዲህ አይነቱን የኢስላም ፍትሕ የተመለከተ ሁሌ እንደተደመመ ነው የሚኖረው። እስኪ ይህን አዋጅ እናስተውል!

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُونُواْ قَوَّٰمِينَ لِلَّهِ شُهَدَآءَ بِٱلۡقِسۡطِۖ وَلَا يَجۡرِمَنَّكُمۡ شَنَـَٔانُ قَوۡمٍ عَلَىٰٓ أَلَّا تَعۡدِلُواْۚ ٱعۡدِلُواْ هُوَ أَقۡرَبُ لِلتَّقۡوَىٰۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ ﴿٨﴾ ﴾ المائدة: ٨

***"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለአላህ ቀጥተኞች ስትሆኑ በትክክል መስካሪዎች ሁኑ። ሰዎችንም መጥላት ሚዛናዊ እንዳትሆኑ አይገፋፋችሁ። ፍትሐውያን ሁኑ። እርሱ (ፍትሐዊነት) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው። አላህንም ፍሩ። አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ-አዋቂ ነው።"*** [አልማኢዳህ፡ 8]

ኢብኑል ቀይዩም ረሒመሁላህ ከዚች አንቀፅ ስር እንዲህ ይላሉ፡-

> *"ጠላትነታቸውና ተቃርኗቸው ግልፅ ከመሆኑ ጋር ባሮቹን ለጠላቶቻቸው ያላቸው ጥላቻ ሚዛናዊነታቸውን እንዳይጋፉ ከከለከለ፣ ኢማንን የሚሞግት የሆነ ሰው ወደ መልእክተኛው እራሷን በምታስጠጋ ልክ ልትሆንም ልትሳሳትም ለምትችል ክፍል ግን እንዴት ጥላቻው ሚዛናዊ እንዳይሆን ያደርገዋል?!! እንዴት ጥላቻንና ፈተናን ብቻ ይደቅንባቸዋል?!"* [በዳኢዑል ፈዋኢድ፡ 2/650]

ወንድሜ ሆይ! እህቴ ሆይ! ይሄ ተግሳፅ ለኛ ነው። እስኪ እኛ በመስመር ከሚለየን የዲን ወንድም ያለንን ሚዛናዊነት እንፈትሽ። ከዚያም ቀረብ እንበልና በኢጅቲሃዳዊ ርእሶች ከሚለየን ወንድማችን አንፃር ምን ያክል ፍትሐዊነት እንዳለን እንገምግም። እስኪ ነፍስያችንን ረግጠን ውስጣችንን እናዳምጥ። አዋጁ እንደቀጠለ ነው፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُونُواْ قَوَّٰمِينَ بِٱلۡقِسۡطِ شُهَدَآءَ لِلَّهِ وَلَوۡ عَلَىٰٓ أَنفُسِكُمۡ أَوِ ٱلۡوَٰلِدَيۡنِ وَٱلۡأَقۡرَبِينَۚ ﴾ النساء: ١٣٥

***"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በትክክል (በፍትሕ) ቋሚዎች፣ በነፍሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢሆን እንኳን ለአላህ መስካሪዎች ሁኑ።"*** [አኒሳእ፡ 135]

ስለዚህ እንዲህ አይነት ሰማያዊ አዋጆችን የሚያከብር ሰው የፈለገ ቢጠላ በማንም ላይ ኢ-ፍትሐዊ ውንጀላ አይወነጅልም። ተወንጃዩ የሌላ አንጃ ተከታይ ቢሆን እንኳን ሚዛኑን ሊጠብቅ ይገባል። ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

> *"ከዚህም ጋር የሱና ሰዎች ከነሱ (ከስሜት ተከታዮች) ጋር ፍትሕንና ሚዛናዊነትን ይጠቀማሉ እንጂ አይበድሏቸውም። እንዳሳለፍነው በደል ሁሌም ቢሆን ሐራም ነው። እንዲያውም የሱና ሰዎች ለሁሉም ከነዚህ (የስሜት ተከታዮች) ይልቅ የተሻሉ ናቸው፣ እነሱ ከፊላቸው ለከፊላቸው ከሚሆኑት በላይ! ኧረ እንዲያውም እነሱ (የሱና ሰዎች) አንዳንድ ራፊዷዎች (ሺዐዎች) ለሌሎቻቸው ከሚኖራቸው በላይ ለራፊዷዎቹ እንኳን የተሻሉና ፍትሐውያን ናቸው። ይሄ እራሳቸውም 'ከፊላችን ለከፊላችን በሚዛናዊነት የማያስተናግደንን እናንተ ግን በሚዛናዊነት ታስተናግዱናላችሁ' እያሉ የሚመሰክሩበት ነው።"* [ሚንሃጁ ሱና፡ 5/157-158]

ይህ ነው የሱና ሰዎች አንኳር መታወቂያ። ለማንም ያላቸው ውዴታ አይናቸውን አይጋርዳቸውም። ለማንም ያላቸው ጥላቻ ድንበር

አያሳልፋቸውም። የሚደግፋቸውን እየመረጡ የሚነቅፋቸውን አይተውም። ስለዚህ ወንድሜ ሆይ! እስከ ጥግ ድረስ ሚዛናዊ ሁን። ሚዛናዊ ካልሆነ ሰው ጋር አትጎዳኝ። ወይ ጀርሙን ያስተላልፍብሃል። ወይ ውስጥህን ያቆስልሃል። ሚዛናዊ ካልሆነ ሰው ዒልም አትውሰድ። እውቀቱ ከሚጠቅምህ በላይ (ያውም ምናልባት ከጠቀመህ) ውስጥህን በክሎ የተንሻፈፈ ፍርድ እንዲኖርህ ያደርግሃል። አልኢማሙ ሻፊዒ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- *"አላህ ልቡን እንዲከፍትለትና እውቀትን እንዲለግሰው የሚወድ ሰው በብቸኝነት፣ ምግብ በማቅለል እንዲሁም ከቂላቂሎችና አንዳንድ ሚዛናዊነትና አደብ ከሌላቸው የእውቀት ሰዎች ጋር ከመቀላቀል በመራቅ ላይ ያተኩር አደራውን።"* [ቡስታኑል ዓሪፊን፡ 1/53]

ሊዘነጋ የማይገባው ነገር ቢኖር ሙብተዲዖችን የምንተችበት ቀዳሚ ምክንያት ተላላፊ የቢድዐ ቫይረሳቸው ሌሎችን እንዳይበክል ለመከላከል እንጂ ስሜታችንን ለማርካት ወይም ቂማችንን ለመበቀል አይደለም። ዐባድ ኢብኑ አልኸዋስ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

> *"በነውራቸው ለማሸብረቅ በማለም ቢድዐዎችን ኢታነውሩ። የቢድዐ ሰዎች መበላሸት የናንተን በጎነት አይጨምርም። በባለቤቶቹ ላይ ድንበር በማለፍ ቢድዐዎችን ኢታነውሩ። ድንበር ማለፍ የራሳችሁ ብልሹነት ነው። ሃኪም የሆነ ሰው እራሱን በሚያሳምም፣ በሽተኞችን ግን በሚያድን መልኩ ሊያክም አይገባውም። ምክንያቱም እሱ ከታመመ በራሱ ህመም እነሱን ከማከም ይዘናጋል። ነገር ግን በሽተኞችን ለማከም ይበረታ ዘንድ ለራሱ ጤንነትን ሊፈልግ ይገባል። ስለዚህ በወንድሞቻችሁ ላይ ስትቃወሙ እራሳችሁን እየተመለከታችሁ ይሁን። እንዲሁም ጌታችሁን በማሰብ ለመምከርና ለወንድሞቻችሁ በመቆርቆር*

*ይሁን። ከዚህም ጋር ሌሎች ዘንድ ካሉ ነውሮች ይልቅ በራሳችሁ ነውሮች ላይ ይበልጥ የምታተኩሩ ሁኑ።”* [ሱነኑ ዳሪሚ፡ ቁ. 675]

## 8. መሰረት ከሌለው ክፉ ጥርጣሬ እንጠንቀቅ

በጥርጣሬ ከሚወረወር ውንጀላ እንጠንቀቅ! *“እነ እከሌ የሌሎችን ገንዘብ ያለአግባብ እየበሉ ነው”፣ “እነከሌ ከሙብተዲዖች ጋር ስውር ግንኙነት አላቸው”፣ “እነከሌ ስውር ኺዋኖች ናቸው”፣ “እከሌ ዐሊም ቅናት አለባቸው”፣* … የሚሉ የትችት ፍላፃዎች ዛሬ ዛሬ እንደ ቀላል ነገር በማንም እየተወረወሩ ነው። እነዚህ ከጥርጣሬ ያለፈ መሰረት የሌላቸው ውንጀላዎች መሪር ውጤት ያስከትላሉ። ጌታችን እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱجۡتَنِبُواْ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلظَّنِّ إِنَّ بَعۡضَ ٱلظَّنِّ إِثۡمٞۖ وَلَا تَجَسَّسُواْ وَلَا يَغۡتَب بَّعۡضُكُم بَعۡضًاۚ أَيُحِبُّ أَحَدُكُمۡ أَن يَأۡكُلَ لَحۡمَ أَخِيهِ مَيۡتٗا فَكَرِهۡتُمُوهُۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ تَوَّابٞ رَّحِيمٞ ١٢ ﴾ الحجرات: ١٢

***“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ። ከጥርጣሬ ከፊሉ ሃጢአት ነውና። ነውርንም አትከታተሉ። ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ። አንዳችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ሆኖ ሊበላው ይወዳልን?! (መብላቱን) ጠላችሁትም፤ (ሃሜቱንም ጥሉት።) አላህንም ፍሩ። አላህ ፀፀትን ተቀባይ አዛኝ ነውና።”*** [አልሑጁራት፡ 12]

ነብዩም ﷺ ***“ጥርጣሬን ተጠንቀቁ። እሱ ከወሬ ሁሉ ቅጥፈት ነውና”*** ይላሉ። [ቡኻሪ፡ 5143፣ ሙስሊም፡ 2563]

ሲፈፀም ባላየው ነገር በጥርጣሬ እየተመራ ሰዎችን ሲሻው በስርቆት፣ ሲሻው በማጭበርበር፣ ሲሻው ከሙብተዲዕ ጋር በመተሻሸት፣ ሲሻው

ከካሀዲያን ጋር በመተባበር የሚወነጅል ሰው ከባድ ጥንቃቄ በሚያስፈልገው የአላህ ዲን ላይ ቀርቶ እሩብ ኪሎ በማይሞላ ቲማቲም ላይ አማና የሚጣልበት አይደለም። እንዲህ አይነቱን ሸውራራ አካሄድ ያለምንም ጥንቃቄ የሚያራምድ ሰው የራሱን ሰንካላ ህሊና፣ የራሱን የአስተሳሰብ ቁንፅልነት ነው የሚያጋልጠው። ምናልባት ስሜት የሰበሰባቸው ጭፍን አጃቢዎች ቢያገኝ እንኳን ረጋ ብለው ያስተዋሉ እለት ምርቃና የሚጋልበው ጥራዝ-ነጠቅነቱን ተረድተው ይርቁታል።

ዛሬ ግን ያለ ምንም ጥንቃቄ በሀሳብ የተለያቻቸውን ሁሉ ጥርጣሬ ላይ ተመስርተው ከሱና የሚያስወጡ ሰዎች በዝተዋል። አንዳንዶቹ ግን ከጥርጣሬም አልፈው በሐሰት ብቻ በሰዎች ላይ እስከ መፍረድ ደርሰዋል። ባላዩት ባልሰሙት በሐሰት ይመሰክራሉ። የሐሰት ምስክርነት አደገኛ ወንጀል መሆኑም ተዘንግቷል። እስኪ ይህን አስፈሪ ሐዲሥ እንመልከት፡-

**عن عبد الرحمن بن أبي بكرة ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلى اللهُ عليهِ وسلمَ: (أَلاَ أُنَبِّئُكُمْ بِأَكْبَرِ الْكَبَائِرِ – ثَلاثًا – ؟ قُلْنَا: بَلَى يا رَسُولَ اللهِ. قَالَ: الإِشْرَاكُ بِاللهِ، وَعُقُوقُ الْوَالِدَيْنِ، وَكَانَ مُتَّكِئًا فَجَلَسَ، فقالَ: أَلاَ وَقَوْلُ الزُّورِ، وَشَهَادَةُ الزُّورِ) فَمَا زَالَ يُكَرِّرُهَا حتَّى قُلْنَا: لَيْتَهُ سَكَتَ**

ዐብዱረሕማን ኢብኒ አቢ በክራ ረዲየላሁ ዐንሁ እንዲህ ይላሉ፡-

*“የአላህ መልእክተኛ ﷺ ከትልልቆቹም ወንጀሎች የበለጡ የሆኑትን አልነግራችሁምን?” አሉ - ሶስት ጊዜ። ‘እንዴታ ይንገሩን የአላህ መልእክተኛ ሆይ!’ ስንል ‘በአላህ ማጋራት፣ የወላጆችን ሐቅ መቁረጥ’ አሉና ተደግፈው ከነበሩበት ተቀመጡ። ከዚያም ‘ኣዋጅ! **የሐሰት ንግግር! የሐሰት ምስክርነት!!**’ አሉ። **‘ምነው ዝም ባሉ’ ብለን***

***እስከምንመኝ ድረስ ከመደጋገም አልተወገዱም።"*** [ቡኻሪ፡ 5976፣ ሙስሊም፡ 87]

ስለዚህ እያንዳንዱ በሰዎች ላይ የምንለጥፈው ነገር ነገ ከአላህ ፊት ስለሚያስጠይቀን ተገቢ ጥንቃቄ እናድርግ። ካልሆነ ደግሞ ከወዲሁ መልስ እናዘጋጅ። ጌታችን እንዲህ ብሏል፡-

﴿ سَتُكْتَبُ شَهَٰدَتُهُمْ وَيُسْـَٔلُونَ ﴾ الزخرف: ١٩

*"ምስካሬያቸው ይፃፍና ይጠየቃሉ!"* [አዙኽሩፍ፡ 19]

ወንድሞች ሆይ! እህቶች ሆይ! እነዚህ በማህበር ሳቢያ ሰዎችን በክፉ የሚያነሱ ሰዎች ስንቱን በሌለበት የየቲም ሐቅ በመብላት፣ የሰው ገንዘብ በማጭበርበር ወንጅለዋል?! ስንቱን ምንም አይነት ንክኪ ሳይኖረው "ጀምዒይ" እያሉ አስከፍተዋል?! ስንቱን *"በሰለፊያ ስም የሚነግድ ስውር ኢኽዋኒ"* እያሉ በሐሰት ወንጅለዋል?! ከሰው ልቦና ውስጥ ስላለ ነገር ምን አሳወቃቸው?! ስንቱን ምንም በሌለበት ከሙብተዲዖች ጋር እንደሚያብር፣ ከነሱ ጋር ስውር ግንኙነት እንዳለው እያወሩ ስም አጥፍተዋል?! ምን ያክል በሙስሊም ክብር ላይ እንደሚረማመዱ ተመልከቱ። ነብዩ ﷺ ግን *"ወለድ ሰባ ሶስት እርከን አለው። ከሁሉም ቀላሉ ልክ አንድ ሰው ከእናቱ ጋር ግንኙነት የመፈፀም ያክል ነው።* ***ከወለድም እጅግ የከፋው ወለድ አንድ ሰው በሙስሊም ወንድሙ ክብር ላይ መረማመዱ ነው"*** ይላሉ። [ሶሒሑ አተርጊብ ወተርሂብ፡ 3/2830]

እንዲያውም የነዚህ ሰዎች በስፋት የሚታይ ነፀብራቅ የሌሎችን ስራዎች እየመዘዙ ከልባቸው ውስጥ ስላለና ከአላህ ውጭ ማንም ስለማያውቀው ነገር መናገር ሆኗል። የሚጠሉትን ሰው ንግግር እየመዘዙ *"ይሄ*

*እኮ ምን ማለት መሰለህ?"* እያሉ ከተናጋሪው አፍ ያልወጣን ከፉ ድምዳሜ ይሰራሉ፣ ይሳለቃሉ። *"ገንዘብ ሲፈልጉ ማህበር ይመሰርታሉ"* እያሉ ልባቸውን ሰንጥቀው ያዩ ይመስል የሙስሊም ክብር ይዳፈራሉ፤ ባደባባይ ክፋት ይዘራሉ። ወንድሜ ሆይ! በሰዎች ልቦና ውስጥ ስላለ ነገር በድፍረት አትናገር። ኋላ መዘዙን አትችለውም። ታላቁ ሰለፍ መክሑል ረሒመሁላህ ምን እንደሚሉ ተመልከት፡- *"አንድ ሰው በሶላቱ ውስጥ ሆኖ ሲያለቅስ አየሁትና ለመታየት እንዳደረገው በማሰብ ወነጀልኩት። በዚህ ሳቢያ ለአመት ያክል በሶላት ውስጥ ማልቀስን ተነፈግኩኝ።"* [አልዑቁባት ሊብኒ አቢ አዱንያ፡ 83]

## 9. ከውሸት እንጠንቀቅ!!

ሙስሊም በሙስሊምነቱ ብቻ ውሸትን ይፀየፋል። የፈለገ ብንጠላ በማንም ላይ ልንቀጥፍ አይፈቀድልንም። ሱና **<u>በቅጥፈት አይጠበቅምና።</u>** ለሱና መቆርቆር ከድንበሩ እየቆሙ ነው። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡- ***"ሱና የግድ በሐቅ፣ በእውነትና በፍትሕ ልትጠበቅ ይገባታል። እንጂ በቅጥፈትና በበደል አይደለም የምትጠበቀው። አንድ ሰው ሐሰትን በሐሰት ከመለሰ ቢድዐን በቢድዐ ከተጋፈጠ ይሄ ሰለፎችና አኢማዎች ያወገዙት ነገር ነው።"*** [ደርኡ ተዓሩዲል ዐቅል ወነቅል፡ 7/182]

ዛሬ ግን በሚለያቸው ሰው ላይ በአንድ እውነት አስር ውሸት እያቦኩ ውንጀላ የሚጋግሩ ብዙ ናቸው። ነብዩ ﷺ ጠላት እንኳን የመሰከረላቸው አንዱ ባህሪያቸው ሐቀኝነት ነበር። ከውሸት እጅግ ደጋግመው አስጠንቅቀዋል። ውሸት ብዙ መዘዝ አለው። *"ውሸት ወደ አመፅ ይመራል"* የሚለው ሐዲሥ በደማቁ ይሰመርበት። [ቡኻሪ፡ 6094፣ ሙስሊም፡ 2607] ውሸቱ ሌሎችን

በመወንጀል ላይ ሲሆን ደግሞ ምንኛ የከበደ ጥፋት ነው?!! ጌታችን እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ يُؤْذُونَ ٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتِ بِغَيْرِ مَا ٱكْتَسَبُوا۟ فَقَدِ ٱحْتَمَلُوا۟ بُهْتَٰنًا وَإِثْمًا مُّبِينًا ﴿٥٨﴾ ﴾ الأحزاب: ٥٨

***"እነዚያንም ምእመናንንና ምእመናትን ባልሰሩት ነገር (በመዝለፍ) የሚያስቸግሩ ሰዎች ቅጥፈትንና ግልፅ ወንጀልን በእርግጥ ተሸከሙ!!"*** [አልአሕዛብ፡ 58]

### 10. እያየን እንጓዝ!

ብዙዎቻችን የራሳችን ነውር አይታየንም። ስለሆነም ውስጣችንን ከመፈተሽ ይልቅ የሌሎች ጥፋት ላይ የምናነጣጥርበት አጋጣሚ በዝቷል። በእርግጥ ተሻጋሪ ጥፋት ያላቸው የጥፋት ሃይሎች አላዋቂዎችን ሲሸውዱ፣ እውነትን እያጠለሹ፣ ሐሰትን እያሸበረቁ በዲን ስም ሲነግዱ ዝም ማለት የሚመለከታቸውን ክፍሎች ያስጠይቃል። ይሁን እንጂ የሌሎች ጥፋት ለኛ ጥፋት ማለፊያ ምክንያት አይሆነንም። ስለሆነም ስናርምም ከልክ መሆናችንን ልናጤን ይገባል። ወንድሜ ሆይ! ይልቅ ወደ ሌሎች ስታንጋጥጥ እራስህ ገደል እንዳትገባ ከልብ ሁን። ብዙ ሰዎች ሌሎችን እየኮነኑ እራሳቸው አደጋ ላይ ወድቀዋል። ኢብኑ ተይሚያ ረሒመሁላህ ምን እንደሚሉ እንመልከት፡-

*"ይሄ ግን በተለያዩ አይታዎችና የኢጅቲሃድ ርእሰ-ጉዳዮች ላይ የሚገጥመውን ከሚወዳጅ፣ ከሱ የሚለየውን ግን ጠላት ከሚያደርግና የሙስሊሞችን ህበረት ከሚሰነጥቅ፣ የሚመስሉትን እየተወ የተለየውን ከሚያከፍርና አመፀኛ ከሚያደርግ፣ የሚገጥመውን እያለፈ የሚፃረረውን*

*መዋጋትን ሐላል ከሚያደርግ ይለያል። እንዲህ አይነቶቹ ከልዩነትና ከውዝግብ ሰዎች ናቸው።"* [መጅሙዑል ፈታዋ፡ 3/349]

## ማጠቃለያ

በመጨረሻም ሁላችንም እንደምናውቀው ብዙ ህዝባችን ሺርክና ቢድዐ ላይ እየዋለለ ነውና ከምንም በላይ ተውሒድና ሱና ያስፈልገዋል። ጨለማ ውስጥ ነውና የእውቀት ብርሃን ያስፈልገዋል። ወገናችን በተለያዩ ኮተቶች፣ ድንቁርናና አጉል እምነቶች ተማርኳልና በንፁሁ የኢስላም ግንዛቤ ነፃ ማውጣት ያስፈልገዋል። ህዝባችን የመፍተሄ ሰበብ የሆነ እንጂ ችግር የሚጨምርለት ዳዒያ አያስፈልገውም። ለችግርማ እግር ከወርች ጠፍሮ የያዘው ብዙ መልክ ያለው ችግር በቂው ነው። ትኩረት የምንሰጠው ትምህርት ለህዝባችን ይበልጥ አስፈላጊ የሆነው ይሁን። አካሄዳችን *"የቡድኔን ሰዎች ካስደሰተ ስለ ሰፊው ህዝብ ምን አገባኝ?"* አይነት እንዳይሆን እንጠንቀቅ። በሺርክ የሚጨማለቁ ወላጆችህን "ማህበር" "ማህበር" "ቢንጣል" "ቢንጣል" እያልክ ሰርክ እየጮህክ የተውሒድ ደዕዋ እንዳይሰሙ መንገድ አትዝጋባቸው። "አቋሜ ነው" ብለህ ማንሳት ካለብህም ቦታና ጊዜ እንዲሁም የሰዎችን የግንዛቤ ደረጃ እያገናዘብክ ይሁን። ዐብዱላህ ኢብኒ መስዑድ ረዲየላሁ ዐንሁ እንዲህ ይላሉ፡- *"አንተ ሰዎችን ህሊናቸው የማይደርስበትን ወሬ አታወራቸውም፣ ለከፊላቸው ፈተና የሚሆንባቸው ቢሆን እንጂ።"* [ሙስሊም፡ 1/11]

ወላሂ ሰለፎቻችን እንዲህ አይነት ግንዛቤዎችን በመመርኮዝ ትልልቅ ርእሰ-ጉዳዮችን ሳይቀር ቦታና ጊዜ እያገናዘቡ በመህይማን ፊት ከማስተጋባት ታቅበዋል። ከሱሪ ውጭ ሌላ ልብስ ብዙም በማይታወቅበት ሃገር ውስጥ ለብዙ ኢስላማዊ ግንዛቤ ባይተዋር የሆነን ህዝብ *"ሱሪ ሐራም ነው"* እያሉ

ላንቃ እስኪበጠስ መወትወት፣ ሱሪ ስለለበሰ ማብጠልጠል፣ ማኩረፍ፣ ሰላምታን አለመመለስ፣ የጎሪጥ መመልከት፣ ብዙዎች ከሱና እንዲበረግጉ፣ የሱና ዳዒያዎችንም ማገናዘብ የማይችሉ ጭራቅ አድርገው እንዲስሉ የሚያደርግ ምናልባትም አንዳንዶችን በሃይማኖታቸው እንዲሸማቀቁ አልፎም እንዲጠራጠሩ ጭምር የሚገፋ አደገኛ አካሄድ ነው። አላህ ማስተዋሉን ያድለን።

ተፈፀመ

ነሐሴ/ 2008